ኢትዮጲስ

ሁለተኛው

በግርማ ዘውዴ

1992 ዓ.ም.

ምስጋና

ይህ ኢትዮጲስ ሁለተኛው የተሰኘ መጽሐፍ ከተለያዩ የታሪክና የሃይማኖት መጻሕፍት ተቀስሞ በውስጡ የተቀመጠው እውነት በጽሑፍ ሰፍሮ እንባቢያን እውነትን ከተረት ለይተው መሠረታዊ ግንዛቤ እንዲያገኙ ልቤን በማነሳሳት አስጀምሮ ያስፈጸመኝን አምላኬን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ::

በተጨማሪም የባለቤቴ የወ/ሮ ማርታ መኩሪና የልጆቼ የዘወትር ጸሎት ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው አገልግሎቴ የጀርባ አጥንት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ታይፕ ራይተር በመፍቀድ ወ/ሮ ቀጸላ ሥዩምን፣ በታይፑ ጽሑፍ ዝግጅትና በኮምፒዩተር ቅንብር ልጄ ከአብነሽ ግርማ እንዲሁም በኮምፒዩተሩ ቀረጻ ፓስተር ጎሩይ ጽጌ ላደረጉት ትጋት ለተሞላበት ትብብር ጌታ እግዚአብሔር ይባርካቸው::

ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን

አሜን!

መጽሐፉን መልሶ የማሳተም መብት በአዘጋጁ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved!

ማውጫ

ክፍል

ርዕስ

ገጽ

መቅድም 7

ክፍል አንድ

1.1 ኢትዮጵያ የሚል ቃልና ትርጉሙ 11
1.2 ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥልጣኔና የአምልኮ ተመራራሽነት . . 13
1.3 የዘንዶ አምልኮት በኢትዮጵያ 16
1.4 በዘንዶ ጎይል ይሾሙ የነበሩ ነገሥታት በኢትዮጵያ 18
1.5 የደብረ ዳሞ ዘንዶና አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) 20
1.6 ስለ ዘንዶ የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ምን ይላል . 24

ክፍል ሁለት

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሰፋሪዎችና አምልኮታቸው 25

ክፍል ሦስት

3.1 ጥንታዊው የአክሱም ሥልጣኔና የሥነ-ጥበብ ዕድገት . . . 26
3.2 የአክሱም ጥንታውያን ነገሥታትና ያሰሩአቸው ገንዘቦች . . 27
3.3 በጥንታዊው የአክሱም ገንዘብ ላይ የተገኘ አርማና ጽሑፍ . . 30
3.4 ስለ ገንዘቡ የተደረገ ጥናትና ምርምር 32
3.5 የገንዘቡ አሠራር 35

ክፍል አራት

4.1 የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት 38
4.2 በእስልምናና በሌሎች የድንበር ግጭት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት 39

ክፍል አምስት

5.1 ቋንቋ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ 41
5.2 የግዕዝ ሳባዊ ፊደል መሠረት 41
5.3 በግዕዝ ፊደል ላይ የአናባቢ ቅጥያዎች ድርሻና ጠቃሚነት . . 43
5.4 የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ለሥነ ጽሑፍ ያበረከተው ድርሻ . . . 45

ክፍል ስድስት

የእንዝና የቁጥር ስልት በኢትዮጵያ 48

ክፍል ሰባት

የኢትዮጵያ የዓመታት አቆጣጠር የዕለታትና የአውራኅ (ካለንደር) 49

ክፍል ስምንት

8.1 ጎሳበ ዘመን በኢትዮጵያ 51

8.2 ስምንተኛው ሺህ የተባለው ዘመን 51

ክፍል ዘጠኝ

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታህሣሥ 29 ስለመከበሩ የተጠቀሰ ሀሳብ 53

ክፍል አሥር

10.1 የዘመን መለወጫ (ርዕሰ ዐውደ ዓመት) 57
10.2 የአራቱ ወቅቶች (ክፍለ ዘመናት) አቀማመር 58
10.3 መስከረም 1 ለምን ርዕሰ ዐውደ ዓመት ተባለ 59

ክፍል አሥራ አንድ

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን (ውል) ለዓለም ሁሉ

11.1 የቃል ኪዳን አስፈላጊነት 62
11.2 እግዚአብሔር ለአዳምና ለሄዋን የገባው ቃል ኪዳን 65
11.3 እግዚአብሔር ለናህ የገባው ቃል ኪዳን 66
11.4 እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን 67
11.5 ለሙሴ የተሰጠ የሲና ቃል ኪዳን 68
11.6 ለዳዊት የተሰጠ ቃል ኪዳን 69
11.7 ኪዳነ ምህረት (በክርስቶስ ኢየሱስ ለሰው ሁሉ የተሰጠ የፀጋ ቃል ኪዳን) 70

ክፍል አሥራ ሁለት

ታቦት

12.1 የታቦቱ አሠራር 73
12.2 የእስራኤል ታቦትና የማደሪያው ድንኳን አቀማመጥ 75
12.3 የእስራኤል የቃል ኪዳን ታቦት የት ደረሰ? 77
12.4 የቀኖና (ዲድስቅልያ) መጻሕፍት ስለታቦት ምን ይላሉ . . . 80
12.5 የእስራኤል ታቦት አቋም 81
12.6 ታቦቱ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተሠርቆ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶአልን? 83

ክፍል አሥራ ሦስት

13.1 ሰው ከሞተ በኋላ ለፈሳ የሚደረግ ልዩ ልዩ ሥርዓትና እገናዝ . 90
13.2 ሕያዋን ለሙታን ሙታንስ ለሕያዋን ይጸልያሉን? 92
13.3 ሰው ከሞተ በኋላ ፈሳን የማጠብና የሽቱ ማርከፍከፍ ሥርዓት . 94
13.4 ስለ እምነት ነፃነት የተሳለፈ መመሪያና ተግራሪዎቹ 95
13.5 በተቀበረ ፈሳ ላይ የተደረገ ኢሰብአዊ ድርጊት 102

ክፍል አሥራ አራት

በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈውን የሚያትቱ የማደናገሪያና የፈጠራ ጽሑፎች

14.1 የባሃኡላህ ጥሪ ፓምፍሌትና «ባሃኡላህና አዲሱ ዘመን» የሚል መጽሐፍ ይዘት 104

14.2 ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የሚል መጽሐፍ ይዘት . . . 108
14.2.1 ከሰው አእምሮ ውጪ የሆነ የመናፍስት አሠራር ሲጋለጥ . . 112
14.2.2 ሳጥናኤል ከተማ ሠራ ይላሉ አባ 114
14.2.3 ጸሐፊው በሰው ፈሳ ሽታ የሚታደሱ ናቸው የሚሉአቸው መናፍስት 115
14.2.4 ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩት ጳጳሳት አቋም እንደ ጸሐፊው አባባል 117
14.2.5 ከነቢያት ከሐዋርያትና ከግብፅ ፓትሪያርኮች አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው ይላሉ 118
14.3 «መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ ምን ይላል» የሚል መጽሐፍና ይዘቱ። 120
14.3.1 ከወንድሞቻቸው መካከል የሚለው ቃል ትክክለኛ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ 121
14.4 ሼህ አህመድ ዲዳት ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ክርስትና እምነት ምን እንዳሉ ያውቃሉ? 124
14.4.1 የይሆዋ ምስክር ነኝ ከሚል ሰው ጋር ያደረጉት ክርክር . . . 124
14.4.2 ኢየሱስ ፈጣሪም አምላክም አይደለም ይላሉ ፀሐፊው . . . 125
14.4.3 የመጽሐፍ ቅዱስን ሀሳብ በቁርዓን ጥቅስ ለማፍረስ ሲሞክሩ . 126
14.4.4 የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች የተሰኘ ቡድን ያሰራጨው ፓምፍሌት ይዘት 127
14.5 ክርስትናና እስልምና በኢትዮጵያ 128
14.5.1 ኤንጂል (ወንጌል) የሚያስተላልፈው መልዕክት በአጭሩ . . 131
14.6 ሃይማኖት አይለያየንም የሚል መጽሐፍ ይዘት 132
14.6.1 የሊቢያው የጋራ ጉባዔ ዋና ዓላማ 132
14.6.2 በመጽሐፉ ላይ የተገለጸ ጉባዔው የተስማማበት ሀሳብ . . . 133
14.6.3 ጉባዔው አንዳንድ መጻሕፍትን ለማስወገድና ሌሎችን ለመቀበል የደረሰበት ውሳኔ 135

ክፍል አሥራ አምስት

15.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የሌለባቸው መጻሕፍት 141
15.2 ወይራ ነጭ ሽንኩርትና ዕጣን ስለማጤስ 144

ክፍል አሥራ ስድስት

16.1 የቀኖና ዲድስቅልያ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን . . 146
16.1.1 ተረፈ ኤርምያስ 146
16.1.2 መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ 150
16.1.3 ተረፈ ዳንኤል 152
16.1.4 መጽሐፈ ባሮክ 155
16.1.5 መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 158
16.1.6 መጽሐፈ ጦቢት 160
16.2 የአዋልድ መጻሕፍት አውራ የተባለውና ተከታዮቹ 162
16.3 የአንዳንድ መጻሕፍት ይዘት ከቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ አንጻር . 166

ክፍል አሥራ ሰባት

17 ተበዳይ በዳይና አማላጅ (ጠበቃ) 169
17.1 ብቃት ያለው አማላጅ (ጠበቃ)ና የዘላለም ካህን 169

17.2 ምልጃ በመልክአ ሥላሴ 171
17.3 ሰው ከሞተ በኋላ በሕይወተ ሥጋ ላለው ዋስ (ጠበቃ) ይሆናል ስለሚባለው 176
17.4 ፍጡር የሆነ የፍጡራን የኃጢአት ዕዳ ሊከፍል አለመቻሉ . . 177
17.5 ማስታረቅና ማማለድ 180

ክፍል አሥራ ስምንት

18.1 ቅድስት ድንግል ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎች መጻሕፍት 185
18.2 ርግማንና ፍርድ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ የሥርዓት መጽሐፍ . . 187

ክፍል አሥራ ዘጠኝ

ጻድቃን ሰማዕታት

19.1 የሞቱ ጻድቃንና ጽድቃቸው 191
19.2 ፍጡራን ከሞቱ ወዲያ ሌሎችን ሊረዱ አይችሉም 193

ክፍል ሃያ

20.1 መላዕክትና አገልግሎታቸው 195
20.2 የመላዕክት ተልዕኮ 197
20.3 የመላዕክት ባህሪይ 199
20.4 መላዕክት ለተለያዩ ሰዎች ያስተላለፉት መልዕክት 201
20.5 መላእክት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሲቆሙ 202
20.6 የመላዕክት መመሪያ ለእግዚአብሔር ሕዝብ 203
20.7 «ገብርኤል» የምስራች ተናጋሪ መልዓክ 205
20.8 መልዓክ የደህንነትን መንገድ ሲገልጥ 208
20.9 መላዕክት ለጥበቃ ሲታዘዙ (ጠባቂ መላዕክት) 209
20.10 የመላዕክት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን 211
20.11 ለቅዱሳን መላዕክት ይሰገዳልን? 213
20.12 ጂን እንደመልዓክና «ጂንሆይ» እንደ ማዕረግ ስም 216

ክፍል ሃያ አንድ

ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች

21.1 ኢትዮጵያ የማንንም አጋዥነት አትሻም (ዳግማዊ ምኒልክ) . . 218
21.2 እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ (ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) 222
21.3 የርግ ብርሃን (ታህሣሥ 1932 ዓ.ም) 227
21.4 የቀ.ኃ.ሥ. ጅግሬና ፍጻሜ 231
21.5 ከሁሉም በላይ አብዮቱ (ደርግ - ኢሠፓ) 234

ክፍል ኻያ ሁለት

22 ስለ ኢትዮጵያ በተለያዩ ነቢያት የተተነበየ የተስፋ ቃል ኪዳን . 236
ዋቢ መጻሕፍት 239

መቅድም

ይህ ኢትዮጲስ 2ኛ የተባለው መጽሐፍ ትክክለኛውን የታሪክ ምንጭ ዋቢ በማድረግ በተለያዩ ደራሲያን በተዘጋጁ መጻሕፍትና እንዲሁም ሀሳባቸው ምን እንደሆነ በማይጨበጥ በአንዳንድ የጎትመት ውጤቶች መጽሔቶች ጋዜጦችና ፓምፍሌቶች ላይ በማተኮር እውነትን በእውነትነቱ ለአንባቢያን ለማስጨበጥ አቅጣጫ ያሳያል።

የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንድ መጻሕፍትና የተለያዩ ጽሑፎች እውነተኛውን ታሪክ ወደ ጐን በመተው የግለሰቦችን ሀሳብና እምነት ብቻ ማንጸባረቃቸውንም ያወሳል።

የኢትዮጵያ ታሪክ በጽሑፍ ሰፍሮ ቅደም ተከተል የያዘው ከአጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344) ጀምሮ ነው። ከዚያ በፊት የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔው የገነነ ቢሆንም እንኳን በጽሑፍ ሰፍሮ የተገኘው ሥልጣኔውና ኃይሉ በሙሉ ሳይሆን በጣም ጥቂቱ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በዘመኑ የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ስላልነበረ ትክክለኛውና እውነተኛው ታሪክ ተመዝግቦ ባለመቀመጡ ነው።

የኢትዮጵያ ታሪክ በአብዛኛው አፈ-ታሪክ (legend history) ወይም የትውፊታዊ ቅብብሎሽ ነው። ነገር ግን «በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል» ነውና በቁም ነገር ደረጃ በጽሑፍ ሰፍሮ ያልተገኘ የቃል ቅብብሎሽ አንዳንዱ ጸሐፊ ካለው ሲያጐድል ሌላው ደግሞ የሌለውን ሲጨማምር ታሪኩ ሙሉ ሳይሆን ጐደሎ ሆኖ ይቀራል ወይም የተለያየ ቡቱቶ ጨርቅ የተሰፋበት ድሪቶ ይመስላል።

መጽሐፉ ጥንታውያን የኢትዮጵያ ሰፋሪዎችንና አምልኮታቸውን በተመለከተ የተደረገውን ጥናት በማስመልከት ቀዳሚዎቹ የኢትዮጵያ ሰፋሪዎች የሆኑት የኩሽ ነገዶች ሥነ ጽሑፍ ፊደልና ቋንቋ ስላልነበራቸው ታሪካቸውና ማንነታቸውም በይፋ ሊታወቅ የሚገባውን ያህል አለመታወቁን ይገልጻል።

ነገር ግን ከእነዚህ ከኩሻውያን በኋላ ወደ አገሪቱ የመጡት የሴም ነገዶች (ሴሜቲክ ጐሳዎች) የራሳቸው የሆነ ቋንቋ ፊደልና የአምልኮ

ሥርዓት ስለነበራቸውና ይህም በተለያዩ ሐውልቶች ተመዝግቦ ለትውልድ ስለተላለፈ ከኩሻውያን ይልቅ ማንነታቸውን ሊያሳይ ችሎአል።

ከዚሁ ጋር የአክሱምን መንግሥት ጥንታዊ ሥልጣኔ ስንመለከት በዘመኑ የተሠሩት ልዩ ልዩ ቅርጽና መጠን ያላቸው ሐውልቶች የነገሥታቱና የመኳንንቱ የመቃብር ቤቶች አብያተ ክርስቲያናትና በተለያዩ ዘመናት የተሠሩ የወርቅ የብርና የመዳብ ገንዘቦች የነበረውን ሥልጣኔ ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። በገንዘቦቹና በአንዳንድ ሐውልቶች ላይ የተቀረጸው ጽሑፍ በንጉሥ እገሌ ዘመን ተሠራን በእገሌ ዘመን አገለገልን በማለት እነዚህ ግዑዛን የጥበብ ሥራዎች አፍ አውጥተው እንደመናገር ያህል የተሠሩበትን ዘመንና ያሠሩአቸውን ነገሥታት ስም ከተረሳበት ሊያስታውሱ ችለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ በርካታ የታሪክ ፀሐፊዎች የዓለምና የቤተ ሃይማኖት መጻሕፍት እውነተኛውን ምንጭ ዋቢ በማድረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ከፍተኛ ምርምርና ጥናት አድርገዋል እያደረጉም ነው። ስለሆነም ትላንት ምን ተደረገ ዛሬ ምን እየተደረገ ነው ነገስ ...? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከትላንቱ እውነተኛ ታሪክ በመነሳት በዛሬው እውነት ላይ በመቆም የነገን አሻግሮ ማየትና መተለም ይቻላል።

በተቃራኒው ግን አንዳንድ ራስ ወዳድ ፀሐፊዎች በሌሎች ተፅዕኖም ይሁን በግል ጥቅም ፍለጋ በውል ባይታወቅም እውነተኛውን የዓለምና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲያዛቡና ሲያደበዝዙ ማየት እየተለመደ መጥቶአል። አበው ሲተርቱ «ሁሉ ሰው ሌባ በሆነበት አካባቢ አንድ ንጹሕ ሰው ቢገኝ እርሱ ሌባ ነው ይባላል» ይላሉ። ውሸትንም ለማባዛት ችግር የለበትም ጊዜም አይፈጅም። በጽሑፍም ሆነ በንግግር የሚዋሽ ሰው ቀጥፎ ዋሽቶ አስቆ ወይም አስለቅሶ ያልፋል። እውነት ግን እንደዚህ አይደለም ብዙ ጊዜ አድማጭና ተቀባይ ያጣል። እውነት ነውና ዋጋ ያስከፍላል። ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አንዳንድ ጸሐፊዎች እውነት የሚያስከፍለውን ዋጋ በመፍራት ይሁን በቸልተኝነት ያዩትን የሰሙትንና የዳሰሱትን እውነት ለሌሎች የመግለጽ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ይዘነጉታል።

ይህ መጽሐፍ በአንዳንድ የዓለምና ከቤተ ሃይማኖት ታሪክ እንዲሁም ከእምነት መመሪያው ጋር የማይጣጣሙትን መጻሕፍት የጻፉአቸው ግለሰቦች ከምን ምንጭ እንዳገኙና እንዴትስ ሊጽፉ እንደቻሉ ማብራሪያ ይጠይቃል። በተጨማሪም በአንዳንድ መጻሕፍት ላይ በክርስትና ስም የተጻፉት ሀሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ስለሆኑ ጥያቄ ቀርቦባቸዋል።

ሌሎች የክርስትናን ሃይማኖት የሚቃወሙ ጣታቸውን ወደ ራሳቸው መልሰው በቅድሚያ የራሳቸውን እምነት እንዲመረምሩ ይጠቁማል።

እያንዳንዱ አንባቢ እንዲገነዘብ የሚያስፈልገው ሰው የሚሠራው ሥራ ሁልጊዜ ስህተት ነው ለማለት ባይቻልም ሰብዓዊ ፍጡር በሁሉም ነገር ሁልጊዜ እኔ ልክ ነኝ ማለት እንደማይችል ነው። ሁልጊዜ እኔ ልክ ነኝ የሚል ሰው ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑን የረሳ መለኮት ነኝ ለማለት የሚቃጣ እንደሆነ ያስገምተዋል። ምክንያቱም የማይሳሳት እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ከስህተቱ የሚማር ግን እጅግ አድርጉ ዕውቀትን ለመገብየት አእምሮውን ክፍት የሚያደርግ ብልህ ሰውን ይመስላል።

አግባብ ባለው መንገድ ስህተትን ጠቁሞ መቃወም ጤናማ ተቃውሞ ነው ይባላል። ጤናማ የሆነ ተቃውሞ ደግሞ ለመሻሻልና ራስን ለመመርመር የሚጠቅም ስለሆነ «እንዴት ቢደፍረኝ ነው!» በማለት ከመፎከር ይልቅ ነገሩ እውነት ነው? ወይስ ውሸት? ብሎ ቆም በማለት ራስን መጠየቅ ተገቢ ይሆናል።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ መጽሐፉ በብዙ ምሁራን የተጻፉ መጻሕፍትና መጽሔቶች ጭማቂ የሆነ የአእምሮአቸው ውጤት ጥርቅም ነው። በእርግጥ ሀሳቡን በአንድ ላይ ለማጠቃለልና ከብዙ አቅጣጫ ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት የሚናቅ አይደለም። ከእነዚሁ ጸሐፊዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ለታሪክም ሆነ ለእውነት የማይቆረቆሩ በመሆን የራሳቸውን የግል ስሜትና አመለካከት ጽፈው ያስቀመጡም አልታጡም። እንደነዚህ ዓይነት ጸሐፊዎች አንድ ጽሑፍ ለትውልድ የሚወረስ ሆኖ እነርሱ እንኳን ቢያልፉ የማያልፍ ቅርስ እንደሆነ ሳይገነዘቡ ቀርተው እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም ጽሑፋቸው ተመዝኖ ማንነታቸውን ሳይገልጽ አይቀርም። ምክንያቱም አንድ ጸሐፊ የተወሰነለትን የዕድሜ ዘመን ጨርሶ ቢያልፍም ጽሑፉ ግን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ነውና።

በኢትዮጵያም ውስጥ ከፍ ብሎ በተገለጸው መሠረት የተለያየ ጽሑፍ ያዘጋጁ ጸሐፊዎች በየዘመኑ ብቅ ሲሉ ተስተውለዋል። ያዘጋጁአቸው መጻሕፍትም ሆኑ ሌሎች በራሪ ጽሑፎች የጸሐፊዎቹን የአመለካከትና የእምነት አቅጣጫ የሚጠቁሙ ናቸው።

ስለዚህ እውነትንና ውሸትን ባለመለየት ቶሎ ሚዛናዊነት ወደሌለው ፍርድ ሄዶ ጽሑፉን ወይም ፀሐፊውን ከመኮነን ይልቅ በዚህ መጽሐፍ ላይ በአስረጅነት የተጠቀሱትም ሆነ ከመንፈሳዊና ከታሪካዊ እውነት አኳያ ትክክል መሆን አለመሆናቸው ይታወቅ ተብለው የተጠቀሱት መጻሕፍት ሩቅ ሳይሆኑ በየሰፍራው በቅርብ ሊገኙ የሚችሉ ስለሆነ ትክክለኛውን

ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚፈልግ ሰው መጻሕፍቱን ማንበብና መረዳት ይችላል።

ስለሆነም የዚህ ጽሑፍ የትኩረት አቅጣጫ ባለፉት ረዥም ዘመናት አገራችን ኢትዮጵያ በሥነ ጽሑፍ ዕድገትና በሥልጣኔ ጥበብ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የነበረች ስትሆን ከጊዜ በኋላ ግን የሥነ ጽሑፉ ይዘት የውሸት ድርሰት እየተቀላቀለበት ታሪካዊ መሆኑ ቀርቶ ተረታዊ ሲሆን በሥልጣኔ ረገድም ወደፊት ከማደግ ይልቅ አሽቆልቁላለች። በመሆኑም የችግራችንን ምንጭና መነሻ በማየት ለወደፊቱ የውሸት ወይም የፈጠራ ታሪክ ማውራት ፋይዳ ስለሌለው ከዚህ ይልቅ በተጨበጠ እውነት ላይ መመሥረት በሁሉም አቅጣጫ ለማደግ ተገቢ መሆኑን ለመጠቆም ነው።

በመጨረሻም የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን ታላቁንና ኃያሉን እግዚአብሔርን በማወቅና በመፍራት በቃሉ ላይ እንደተጻፈው ኢትዮጵያውያን በሙሉ በነፍስ በሥጋና በመንፈስ ሁለንተናዊ በረከት ለማግኘት አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ሳይሆን «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» (መዝ. 68÷31) ተብሎ እንደተጻፈ ከኃጢአት ከበደል ከአመጽና ከአለመታዘዝ መንገድ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር በመመለስና በመማረክ እጆቻችንን ፈጥነን ወደ ፈጣሪ እንድናነሳ ለማሳሰብ ነው።

«ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች»።

«ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» (መዝ. 68÷31)።

1.1 «ኢትዮጵያ» የሚል ቃልና ትርጉሙ

ኢትዮጵያ የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለአርባ አንድ ጊዜያት ተጽፎ እንደሚገኝ በተለያዩ መጻሕፍት ተመዝግቦአል። <u>ኢትዮጵያ</u> የሚባለው አካባቢ <u>ሳባ</u> ተብሎም ይታወቃል። በሌላ ታሪክ ደግሞ በሳባ ልጅ <u>በኢትዮጲስ</u> ስም የተሰየመ እንደሆነ ተገልጾአል።

ከክርስቶስ ልደት ከ260-222 ዓመት በፊት ባለው ጊዜ መካከል በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ከአብራይስጥ ወደ ጽርዕ ቋንቋ ከተተረጐመውና «ሰብተዋጀንት» በመባል ከሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ሲታይ በአብራይስጥ «ኩሽ» ተብሎ የተጻፈው በጽርዑ «ኢትዮጵያ» ተብሎ ተተርጉሞአል። (ዘፍ. 2÷13፤ ኢሳ. 18÷1፤ 45÷14፤ ኢዩ. 28÷19)

በጽርዕ (በግሪክ) «ኢትዮ» ማለት ትርጉሙ ጥቁር (ጠቋራ)፥ ከሰልማ ማለት ሲሆን «ጵያ» ማለት ደግሞ ፊት ማለት ነው። ስለሆነም <u>ኢትዮጵያ</u> ማለት ጠቋራ፥ ሻንቅላ እንደማለት ነው። ነገደ ኩሽ ከሠፈሩበት የመሬት አቀማመጥ እንዲሁም ሞቃት አየር ሁኔታ የተነሳ መልካቸው (ቆዳቸው) ስለጠቆረ ይህንኑ ለመግለጽ እንደ አብራይስጡ ኩሽ ከማለት ይልቅ ተርጓሚዎች ኢትዮጵያ ብለው ጽፈዋል የሚሉም ባለታሪኩች አሉ።

በጥንት ዘመን የግብፅ መንግሥት ግዛትም ሆነ የሱዳን (ኑቢያ) አካባቢ በሙሉ ኢትዮጵያ ተብሎ ይታወቅ ነበር ይባላል። እንግዲህ ኩሽ (ኢትዮጵያና ሱዳን) ከግብፅ ጋር ወሰንተኞች የነበሩበትና እርስ በርስም የተገዛዙበት ጊዜ እንደማይጠፋ በመጠቆም የዛሬዎቹ ኢትዮጵያ፥ ሱዳንና ግብፅ እንደ አንድ የተጠቃለለ የመንግሥት ሀገር ወይም በየራሳቸው በተለይ በዚህ ስም ተጠርተውበት እንደሆነ በሰብተዋጀንት ተርጓሚዎች አባባል እንደሚከተለው ተገልጾአል።

1ኛ) <u>ኩሽ (ኢትዮጵያ) በግብፅ ቦታ ሲነገር</u>

2 ነገ. 18፡19-25፡ 19፡5፡ 13 ኢሳ. 36፡4-10፡ 37፡8-13 ይገናዘብ።

2ኛ) <u>ኩሽ (ኢትዮጵያ) በዛሬዪቱ ሱዳን ቦታ ሲነገር</u>

ኤር. 36፡25 ናሆም 3፡8-9 ሐ.ሥ 8፡27-39 ሕዝ. 29፡10

3ኛ) <u>ኩሽ (ኢትዮጵያ) ምድረበዳ ቆላ ሆኖ ሲነገር</u>

ሀ) መዝ. 74፡14 የሌዋታንን (የዘንዶውን) ራስ ቀጠቀጥህ ለምድረ በዳ ሕዝቦች ምግብ አድርገህ ሰጠሃቸው ተብሎ በእብራይስጥ የተተረጐመውን «ለኢትዮጵያውያን» ማለታቸው

ለ) መዝ. 72፡9 «የምድረ በዳ ዘላኖች» በፊቱ ይሰግዳሉ የሚለው «በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ» ተብሎ ተተርጉሞአል።

ሐ) የሳባ (የሼባ) ንግሥት የእስራኤልን ንጉሥ የሰለሞንን ጥበብና ዝና ልትጐበኝ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷ ተተርኳል። 1 ነገ. 10፡12፤ ?ዜና 9፡1

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ታሪኳን ጠቅሶ ሲያስተምር «የአዜብ ንግሥት» ብሎአታል። ማር. 12፡42 «አዜብ በደቡብ ምዕራብ የሚገኝ አቅጣጫ ነው።» ይህች ንግሥት እስከ ግብፅ ወሰን ድረስ ያለውን በረሃማውን አገር በሙሉ ትገዛ እንደነበረ ብዙ ባለታሪኮች ይስማሙበታል።

4ኛ) <u>ኩሽ (ኢትዮጵያ) የሳባውያንን አገርና መንግሥት ያመለክታል</u> :- ምክንያቱም ከታሪክ ነገሥት አገላለጽና ከባለታሪኮች ትረካ እንደምንረዳው እስከ ዘመናችንም የደረሰውና የወረሰነውም ትውፊት (ቅብብሎሽ) እንደሚገልጸው በቀድሞ ዘመን ሳባውያን የያዙትና ከነገደ ኩሽ ጋር በመደባለቅ የኖሩበት ዋና ከተማቸው የነበረው አክሱም ስለሆነ ሳባ የተባለው ስም የአሁኗ ኢትዮጵያ የተጠራችበት እንደሆነ ግልጽ ነው።

እንግዲህ ከላይ ከተራ ቁጥር 1-4 በተጠቀሰው ዝርዝር ስንመለከት ኩሽ (ኢትዮጵያ) ተብሎ ይታወቅ የነበረው አካባቢ የአሁኗ ኢትዮጵያ፡ ሱዳንና ግብፅ ያሉበትን የሚያጠቃልል እንደሆነ ያሳየናል።

በሌላ ስፍራ ደግሞ ኩሻውያን (ኢትዮጵያውያን) ከሊቢያውያን ጋር ወታደራዊ አንድነት መሥርተው ሁለቱም ሕዝቦች አንድ ሠራዊት ሆነው ወደ ምድረ እስራኤል መዝመታቸው ተገልጾአል። (2 ዜና. 14፡9-13፡ 16፡8) ምናልባት ይህ ወታደራዊ ሠራዊት በአንድነት ሊዘምት የቻለው በግብፅ መሪነት ወይም የኢትዮጵያ ሠራዊት ግብፅን ድል አድርጐ ሠራዊቱን ከርሱ ጋር አዋህዶ እንደሆነ ይገመታል። ስለሆነም ሠራዊቱ የተጠራው በኢትዮጵያ ስም ነው።

በሌላው የታሪክ ገጽታ ግን በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ተጽፈው የተገኙት የታሪክ ቅርሶች ከነገደ ኩሽ ልዩ የሆነ ዘር ወደ ኢትዮጵያ ለመግባቱ ግልጽ የታሪክ ማስረጃ ሆነው የቆዩ ሐውልቶች አሉ። በሐውልቶቹ ላይ የተጻፉት ፊደሎች የሳባውያን ናቸው። ይህንንም ጽሕፈት የታሪክ ተመራማሪዎች በጠቃሚ ማስረጃነት እንደሚጠቀሙበት የተረጋገጠ ነው።

በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል የተገኙት እነዚህ ጽህፈቶች ከባህር ማዶ ከደቡብ ዐረቢያ በተመሳሳይ ሁኔታ በምርምር ከተገኙት ጋር ሲገናዘብ አንድ ዓይነት ሳባዊ ፊደል እንደሆነ ተረጋግጦአል። በሁለቱም አካባቢዎች የነበሩት ህዝቦች አንድ ዓይነት ሳባዊ ፊደል መጠቀማቸው ከሴም ነገድ የሆነው የዮቅጣን ልጅ የሳባ ዘር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሳባውያን እንደተባሉ በክብረ ነገሥት የተጻፈው ታሪክም ይስማማበታል። በርካታ የታሪክ ፀሐፊዎች የሚስማሙበት ነገደ ኩሽ በቅድሚያ በኢትዮጵያ ገብተው መኖራቸውን ሲሆን ከነገደ ሴምም ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን ብቻ ሳይሆኑ እስራኤላውያንም በተለያዩ ዘመናት ወደ ኢትዮጵያ እንደዘለቁ ተረጋግጦአል። ይህንንም ትረካ እውነተኛ የሚያደርጉት በርካታ የባህልና የሃይማኖት ተመሳሳይ ሁኔታዎች አሉ።

እንግዲህ ነገደ ሴም (ሳባውያን) ቀደም ሲል ቦታ ይዘው በኢትዮጵያ ምድር ይኖሩ ከነበሩት ከነገደ ካም (ኩሽ) ጋር ተዋግተው በማሸነፍ ራሳቸውን ነገደ አግአዝያን (ነፃ አውጪዎች) ብለው ከጠሩ በኋላ በዘመናት ቆይታ ሁለቱም ነገዶች በሃይማኖት፡ በማህበራዊ ኑሮ፡ በባህልና በፖለቲካ እየተዋሃዱ በመጣመር በመካለስና በመደባለቅ አንድ ህዝብ ሆነው በነፃነት የኖሩባትን የዛሬዪቱን ኢትዮጵያ አቆይተውናል።

1.2 ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥልጣኔና የአምልኮ ተወራራሽነት

የአንድ ትውልድ ዘመን በሚተላለፍበት በስድሳ ወይም በሰማኒያ ዓመት ዕድሜ ውስጥ አንዱ ደሃ፡ ሌላው ሀብታም፡ አንዱ ደካማ ሌላው ኃይለኛ፡ አንዱ ተገዥ ሌላው ገዥ፡ አንዱ ተጨቋኝ ሌላው ጨቋኝ ... ወዘተ. በመሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሥፍራ እየተለዋወጡ ደሃው

የሀብታሙ፡ ደካማው የኃይለኛው፡ ተገዥ የገዥው፡ ተጨቋኝ የጨቋኙ፡ የበላይ እየሆነ የምድር ዘመናት ይፈራረቃሉ።

ከክርስቶስ ልደት አምስት ሺህ ዓመት በፊት ጀምሮ እስከ ልደቱ በነበሩት ረዥም ዘመናት ምዕራብን ያስፈራሩ የነበሩ መንግሥታት ግብፅ፡ አሦር፡ ባቢሎን፡ እስራኤል፡ ሕንድ፡ ቻይና፡ ልዳ፡ ሜዶን፡ ፈንቄ፡ ፋርስና ግሪክ ሲሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ሮማውያን ኃያል መንግሥት ነበሩ። በእነዚህ አገሮች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በዘመኑ በኑሮ ድሎት የወርቅና የሐር ልብስ ሲለብሱና ሺምነሽሹ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ገና ከቆዳ ልብስ አልተለዩም ነበር።

ነገር ግን አንዱ አገር ሥልጣኔ ሊያገኝ የሚችለው ከሥልጡኑ መንግሥት ጋር የግንኙነት መስመር ሲኖረው ሲሆን ይልቁንም በሥልጡኑ መንግሥት ሥር በቅኝ ሲገዛ ነበር። ስለሆነም ግብፆች ወደ ታናሹ እስያ እየተሸጋገሩ ሲጓዙ ፈንቄዎች ደግሞ ወደ አውሮፓ ደቡብ ወደ ኢጣልያ ወደ ፈረንሳይና ወደ እስፓኝ እየሄዱ ሲጓዙ ግሪኮች ግን ወደ ፋርስና ወደ ሕንድ ሲዘልቁ ሁሉም ለሚገዙት አገር ሥልጣኔን በውድም ሆነ በግድ አትርፈዋል። እንደዚሁ እያለ ሥልጣኔ ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው መተላለፍ ጀመረ። ሥልጣኔን ከምሥራቅ ይልቁንም ከግሪክ የወሰዱት ሮማውያን የተነሱበት ሥፍራ ከምሥራቅ ክፍል ሳይሆን በአውሮፓ ደቡብ በመሆኑ ግራና ቀኝ ያለውን አገር እስከ እንግሊዝ ድረስ ስለገዙና በገዙት አገርም ከግሪክ አዋህደው የያዙትን ሥልጣኔያቸውን ስላስተማሩ በግሪክና በእነርሱ ትምህርት የአውሮፓ መንግሥታት እነ ፈረንሳይ (ጋልያ) እነ እንግሊዝ መሠልጠንና መታወቅ ጀመሩ። የተለየ ሥልጣኔ የነበራቸው (ፍራንኮች) ጀርመኖችና ሞስኮቦች ከእነዚሁ ተገዝተው ከነበሩት ከፈረንሳዮችና ከእንግሊዝ ከሮማ ውድቀት በኋላ በየፊናቸው ተነስተው የየራሳቸውን መንግሥት ማስፋፋት ጀመሩ። እንግዲህ እነዚህ ሲሰለጥኑና ኃይል ሲሰማቸው በተራቸው የጌቶቻቸውንና የገዥዎቻቸውን አገር ግብፅን፡ ባቢሎንን፡ ፋርስን፡ ግሪክን፡ ሕንድን፡ ቻይናንና ሮማንም ለመግዛት አስፈራሩ። ዘመን ሲለወጥ ጊዜም ሲያልፍ በፊት ተገዥዎችና ተጨቋኞች የነበሩት አገሮች የተገላቢጦሽ ገዥዎቻቸውን ወረሩአቸው።

በዚህ መካከል ኢትዮጵያን ስንመለከት ነገሩ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም ኢትዮጵያ ለተወሰኑ ጊዜያት የመንን የገዛች ቢሆንም በወሰንዋ ያለውን አካባቢ ከማስፋት በስተቀር ሌላውን አገር ከመግዛቱም ሆነ ከመገዛቱ እንደሌለችበት ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበዋል። ስለሆነም ከአክሱም ሥልጣኔ በስተቀር በሌላው እንደእነ ግብፅ፡

ባቢሎን፡ ሕንድ፡ ግሪክ ከራሷ በሆነ ከፍተኛ ሥልጣኔ የምትኮራ አይደለችም በግለት ታሪክ ጸሐፊዎቹ ስለ ኢትዮጵያ ሲጠቅሱ፤ የእርስዋን ተደራቢ አድርገው ወይም የምሥራቁ ሥልጣኔ በመጠኑ መግባቱን ከመጻፍ በቀር በራሷ ስም አልጻፉላትም። የዚህም ምክንያት ስውር ሳይሆን በጥንቱ ዘመን ሠለጠኑ በሚባሉት ሸሮማውያን በላቲኖች በጀርመኖች ወዘተ. ሳትገዛ በመቅረቷና ከባቢሎን ከሕንድና ከፋርስ ... ጋርም በወዳጅነት እንጂ በግዛት ስላልተገናኘች ሥልጣኔያቸውን ሙሉ በሙሉ ለመውረስ አልቻለችም። ግብጾች ግን ወደታች ወደ ኢትዮጵያ ሲወርዱ ኢትዮጵያውያንም ወደ ላይ ከፍ እያሉ ወደ ግብፅ ደቡብ በመዝለቅ በአንድ ወቅት ቴብ የተባለውን አካባቢ ይዘው እንደነበረ ተጽፎአል። ከክርስቶስ ልደት ወደ 600 ዓመት በፊት ግብፅን ይገዙ ከነበሩት የመጨረሻዎቹ ነገሥታት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ በአንዳንድ መጻሕፍት ተጠቅሶአል።

ስለሆነም የአክሱም ሥልጣኔና ኃይል ከግብፅ፥ ከፋርስ፥ ከዐረብ፥ ከእሥራኤላውያን፥ ከግሪክ ወዘተ. የተደባለቀ ነው ለማለት ፍንጭ ይሰጠናል። የአምልኮ ተወራራሽነትንም ስንመለከት በዘር፥ በአምልኮ፥ በልማድ፥ በቋንቋ፥ በሃሳብ ወዘተ. የሚገናኘውና የሚመሳሰለውም ከእነዚሁ ከታናሽ እስያ፥ ከእስያ አገሮች ከግብፆችና ከዐረቦች ጋር ነው። ቢሆንም የሥልጣኔ ተበዳሪም ብቻ ሳይሆን ለትልልቆቹ ለግብፅ፥ ለባቢሎን፥ ለፋርስ መንግሥት በመጀመሪያ በመርዌና በአክሱም ያለው ሳባዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ጓደኛ ነበር። ከእነዚህ መንግሥታት ጋር የወዳጅነት ደብዳቤም ይጻጻፍ ነበር። ይልቁንም ከንግሥተ ሳባና ከዚያም ወዲህ በኢትዮጵያ በነገሡ ነገሥታት ዘመን በመሬት (በየብስ) በባህርም ከታላላቆቹ የእስያ መንግስታት ጋር የገበያና የሸቀጥ ልውውጥ ያደርጉ ነበርና የኢትዮጵያ መንግሥት በልብስ፥ በጌጥ፥ ወዘተ. እየሰለጠነ ሄደ። እንደ ምሥራቅ መንግሥታት የከበረ ታላቅ መንግሥት ሆነ። መርከቦች እስከ ሰባ የሚሆኑ ነበሩት። በዚሁ ምክንያት ታምሪን የሚባለው ኢትዮጵያዊ ነጋዴ አስቀድሞ ኢየሩሳሌምን አይቶ ስለነበረ በንግድ ምክንያት ሄዶ ሳለ ያየውን የንጉሡን የሰለሞንን ጥበብና አስተዳደር ለንግሥቲ ሳባ በመንገሩ ይህንኑ በጆሮዋ የሰማችውን በዐይንዋ ለማየት እስከ ኢየሩሳሌም እንደሄደች ይነገራል።

ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ታላላቅ ከነበሩት ከእስያ መንግሥታት ጋር ትቆጠር እንደነበረ በተረትም በቁምነገርም በሥጋዊና በመንፈሳዊ መጻሕፍት ስምዋ አልፎ አልፎ ተጽፎ ይገኛል። የግሪኩ የሆሜር መጽሐፍ ደግሞ ተረትና እውነት በተደባለቀበት ሁኔታ ስለ ኢትዮጵያ

ያወሳል። እንግዲህ በዚህና በሌላም ታሪክ ስንመለከት ኢትዮጵያ ጥንታዊ አገር እንደሆነች እንገነዘባለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዘለቀው ጓደኝነት ከክርስቶስ ልደት በኋላ የተነሱት የአክሱም ነገሥታት እነ አልዓሜዳ እነ ካሌብ ከፋርስ ነገሥታት ጋር ጓደኛሞች ነበሩ። ፋርሶች በግዛትና በሃይማኖት ሲቀናቀኑአቸው ደግሞ ከክርስቲያኖቹ ከቁስጥንጥንያ ነገሥታት ይኸውም ከምዕራብ የሮም ግዛት ለብቻው ተለይቶ የምሥራቅ የሮም ግዛት እየተባለ እስከ 1400 ዓ.ም ድረስ በቆየው የሮም ግዛት ላይ የነገሡ ሲሆኑ ከእነዚህ ጋር ወዳጆች ነበሩ።

በዚሁ ግንኙነት ሳቢያ ስማቸው በኢትዮጵያ የሚታወቀው ፈጠኙ ቅዱሳን የተባሉት ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ እንደቻሉ ይታወቃል። በየመንም አይሁዶቹ ክርስቲያኖችን ባሳደዱና ባጠቁ ጊዜ አፄ ካሌብ በመርከብ ተሻገሮ የየመንን አረቦች አሸንፎ ለመቶ ዓመታት ገባር ያደረጋቸው አስቀድሞ በነገሩ ከቁስጥንጥንያ ንጉሥ ከዩስቲያኖስ (ጁስቲኖ) ጋር በመልዕክት ሁለቱም ተነጋግረውበት ነው። ከዚህም በቀር የኢትዮጵያን የጥንት ታላቅነት የሚመስክሩ ጸሐፊዎች ደጋግመው የሚጠቅሱአቸው ዋና ዋና ነገሮች የአክሱም ከተማና በውስጡም ያሉትን ሐውልቶች ሲሆን ከክርስትና ወዲህ ደግሞ የእነ አቡነ አረጋይ፥ የእነ አባ ጴንጤሌዎን ሕንፃ ፍራሾች እንዲሁም በአባይ ወንዝ ዳርቻ የተገኘው የድል አድራጊነቱን ምልክት የሚገልጽ የአንድ የአክሱም ንጉሥ የድንጋይ ዙፋን (ምናልባት የንጉሥ አብርሃ) እና በንጉሥ ላሊበላ ዘመን በላስታ የታነጹ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች ናቸው። በእርግጥም የተጠቀሱት ሐውልቶችና የታነጹ ሕንፃዎች የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ አሻራ እንደሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዴት እንደተሠሩ ለማወቅ ገና ምርምር የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።

1.3 የዘንዶ አምልኮት በኢትዮጵያ

ከኢትዮጵያ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ግንኙነት ያደርጉ የነበሩት የአሶር የባቢሎን የፋርስ የግሪክ ወዘተ. መንግሥታት የአምልኮም ተወራራሽነት እንደነበራቸው ተመልክተናል። በተጨማሪም በዘመኑ ለነበረው ሕዝብ እንደ ትልቅ ቁምነገር ይቆጠር የነበረና ለዛሬው ትውልድ ግን ተረትና የማይታመን የሚመስል የአምልኮ ሁኔታም እንደነበረ ይታወቃል። ስለሆነም የአንዱ አገር ባህልና ልማድ ከጐረቤት አገርና በንግድም ሆነ በሌላ የግንኙነት መስመር ከሚገናኙት አገሮች የሚዘመት ስለሚሆን ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሁኔታ ገጥሞአታል። ለምሳሌ ፋርሶች፥ ግሪኮች፥ ሮማውያን፥ ግብፆችና ባቢሎናውያን ታላላቅ ወንዞችን፥

ተራሮችን ጨረቃንና ፀሐይን እንዲሁም በጀግንነት የታወቁትን ሰዎች እንደ አማልክት ይሰግዱላቸው ነበር። በጦርነትም ሆነ በሰላም ጊዜ ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ እነዚህ አማልክት ወይም ከአማልክቱ ሥልጣን የወሰዱ ነገሥታት ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ገሚሱ እንደ ተረት ሌላው እንደ እውነት ሲቆጠር በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ ምልክቱና አሻራው ይታያል።

«ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና» በሚል ርዕስ በአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በ1941 ዓ.ም በተጻፈ መጽሐፍ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ንጉሥና አምላክ ዘንዶ እንደነበረ ይተርካል። ሲያትትም በዘመኑ የነበረች አንዲት ቆንጆ ልጃገረድ አንዲት ሴት ልጅና አጋቦስ የተባለ ዘንዶ ሴቷን ከሰው፥ ዘንዶውን ከዘንዶ ወለደች ይላል። ከዚያም እናቲቱ ከሞተች በኋላ ከእርሷ የተወለዱት መንትዮች ዘንዶውና ሴቷ ልጅ አብረው አደጉ። በኋላም ዘንዶው ቁመቱ ሰባ ክንድ ሲሆን ጥርሱም ሰባ ሆኖ ሰውን ሁሉ እያሳደደ ይበላ ጀመር። በዚህ ነገር ሕዝቡ በከፋ ችግር ውስጥ በመግባቱና ዘንዶውን ለመግደል ወይም ለማጥፋት ዘዴና ብልሃትም ሆነ አቅም እንዳጣ ይናገራል። በኋላ ግን በእህቲቱ አማካይነት ሕዝቡ ለዘንዶው ለአጋቦስ በቀን አስር በሬ፥ አስር ላም፥ ሃምሳ ፍየል፥ ሃምሳ በግ እንዲሁም ማርና ወተት ሊገብሩለትና አንዲት ልጃገረድ ሊሰውለት ውል ገቡና ዕርቅና ሰላም ሆነ። እርሱም አገሪቱን አርባ አመት ገዛ። ከእነዘሩ ለአራት መቶ ዓመታት ገዝቶአል የሚሉም አሉ። አጋቦስ የተባለው ዘንዶ አርባ ዓመት እንደገዛ ከወደ ሐማሴን ስሙ ገብገቦ የተባለ ሰው ወደዚያ አካባቢ መጥቶ ስለ ሁኔታው ሲሰማ ሕዝቡን ይህን ያህል ግብርና መስዋዕት ለዘንዶ ከምትገብሩ ለምን አትገድሉትም ቢላቸው አቅምና ጉልበት በማጣታቸውና ዘዴም ስለጠፋባቸው ነፃ መውጣት አቅቶአቸው ሊገብሩ መገደዳቸውን ገልጸው አንተ ችሎታ ኖሮህ ብትገድለው ንጉሣችን ትሆናለህ ይሉታል። ከዚያም ቃልኪዳን ከገቡለት በኋላ ገብገቦ ዘንዶው አጋቦስ በሚተኛበት ስፍራ ሰባት ጊዜ የሚዞር አጥር በቶሎ አሳጥሮ አጥሩ ከደረቅ እንጨትና ከቅጠል እንዲሆን በማድረግ በአራት ማእዘን በእሳት አያያዘ። ከዚያም በኋላ ዘንዶው ከተኛበት ተቀስቅሶ ለመውጣት ሲሞክር አጥሩ በሙሉ በእሳት ተያይዞ ስለነበረ በሚንቀለቀለው የእሳት ነበልባል ውስጥ እያለፈ ከአንደኛ እስከ ሰባተኛው አጥር ድረስ ተጉዞ ወላፈንና ጭሱ ገላውን ለብልቦት ሳለ ገብገቦ ጋሻ፥ ጦርና መጥረቢያ ይዞ በመጠበቅ በመጥረቢያው የዘንዶውን ጭንቅላት ፈለጠውና ገደለው። የዘንዶው ጭንቅላት ሲፈለጥ ከራሱ ላይ ደምና እሾ ወጥቶ እመሬት ላይ ፈሰሰ። ወዲያው በጊዜው ዝናብ ቢዘንብበት

በስፍራው ጤፍ በቀለ። ዘንዶውንም እህቱ አልቅሳ ቀበረችው። የተቀበረበት ስፍራ በትግራይ ከአክሱም በስተምዕራብ ተሞንዜውያ ተብሎ የሚጠራ ቦታ እንደሆነ ይነገራል። ገብገቦም ዘንዶውን በዚህ ዓይነት ከገደለ በኋላ ኩርፋ የተባለችውን የዘንዶውን እህት አግብቶ የአገሩ ገዥ ሆነ። ገብገቦ ከሚስቱ ከኩርፋ ሰርፌን፥ ሰርፈ አኪላን፥ አኪላ ጵርስቅላን፥ ጵርስቅላ አጋቦስን (በሚች ዘንዶ ስም የተሰየመ) አጋቦስም በወንጌል ንግሥተ አዜብ በመጽሐፈ ነገሥት ንግሥተ ሳባ በክብረ ነገሥት ማክዳ የተባለችውን ወለደ። እርሷም በነገሠች ጊዜ ሕዝቡ «ለሴት አንገዛም» ብሎ እምቢ አላት። ማክዳም በዚሁ ተናዳ የቀድሞው ዘንዶ ተገድሎ እተቀበረበት ቦታ ላይ ሄዳ እያለቀሰች ብትለምን ከዚያ ስፍራ ሌላ ዘንዶ ተወለደ። እርሱም በአምስት ቀን ውስጥ አምስት ቀንድ አበቀለ ሕዝቡም ይህን ባየ ጊዜ ደነገጠ። በልመና እርሷ እንዳስነሳችው አወቀ። ከዚያም በኋላ ከነገደ አርቄ ዙፋኑ ወጥቶ ለሌላ ባዕድ እንዳይተላለፍ ድንግል ሆነሽ ልትኖሪ እንጂ ባል ላታገቢ ቃል ኪዳን ግቢልንና እንገዛልሻለን ብለው ለመኑዋት። እርሷም ውለታቸውን ተቀብላ ከመሬት በልመናዋ ያስነሳችውን ዘንዶ በድንጋይ ገድላ በሕዝቡ ላይ ነገሠች። ከዚህም የተነሳ የአገራችንን ሰው ላለማግባት በገባችው ቃልኪዳን መሠረት እስራኤል አገር ሄዳ ጠቢቡን ሰለሞንን አግብታ ቀዳማዊ ምኒልክን ልትወልድ እንደቻለች ይተረካል።

1.4 በዘንዶ ኃይል ይሾሙ የነበሩ ነገሥታት በኢትዮጵያ

በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ የተለያዩ ነገሥታት ተብለው ይጠሩ የነበሩት ባላባቶችም ሲሾሙ በዘንዶ ኃይል ሥልጣን እንደሚይዙ ይተረካል። ለምሳሌ የአነሪያ ሕዝብ በዘንዶና በዛር ያመልኩ እንደነበረና ንጉሡም ለዘንዶ ይገብር እንደነበረ ይነገራል። ንጉሡ ከሁሉም ጐሣ ሚስት ስለሚያገባ ብዙ ልጆች ይኖሩታል። ንጉሡ ሲሞት ደግሞ ልጆቹን በሙሉ ይሰበስቧቸውና ዘንዶ ወዳለበት ስፍራ በሌሊት ይወስዱአቸዋል። መናገሻው ከዚያ ነውና ልጆች በአንድ ቦታ ይቀመጣሉ። ከዚያ በፊት ያልታወቁ ልጆችም በዚያን ሌሊት ይመጣሉ። ብዙ ድግስ ተደግሶ ሕዝቡ ከልጆቹ ሁለት ሺህ ከንድ ርቆ ይጨፍራል የዛር ዘፈንም ይዘፍናል። ጩኸትና ማጓራት በደሞቀ ጊዜ ዘንዶው ከጐሬው መዘገ ብሎ ይወጣና ከታረደው ከከብቱ ደም ይቀምሳል። ከዚያም ከልጆቹ በአንዱ ላይ ሄዶ ይጠመጠማል። ወዲያው የቀሩት የንጉሡ ልጆች ለዚያ ዘንዶው ለተጠመጠመበት ወንድማቸው ወድቀው በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ። ሕዝቡ ሁሉ ዘፋኞችና ጨፋሪዎችም እንዲሁ እየተደፉ

ይሰግዱለታል። ከዚያ በኋላ ቀቢው ዘንዶ ተላቆ ወደ ጐሬው ይገባል። የቀሩት ወንድሞቹ ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደ ሕዝቡ ናቸው እንጂ ከንጉሥ ዘር ቁጥር የላቸውም። ከዚያ በኋላ የታረደው ሥጋ እዚያው ይበላል እንጂ ቢተርፍም ወደቤት አይወስዱትም፥ ሥርዓታቸው ነውና እዚያው ጥለውት ይሄዳሉ። ከዚያም በኋላ ንጉሡ ሴሰኛ ይሆናል። በተጨማሪም በዙሪያው ያሉት ነገሥታት መልእክተኞችን ወደ እርሱ ይልካሉ። እነዚህም የከፋ፥ የኩሎ፥ የኮንታ፥ የከምባታ፥ የወላይታና የቀሩትም አካባቢዎች ነገሥታት ናቸው።

ንጉሡ በዘንዶው በተዳሰሰበት ቀን ከላይ እንደተገለጸው ትልቅ ግብዣ ይደረጋል፥ የዛር ዘፈን ይዘፈናል። ሕዝቡ ሁሉ ይጋበዛል ይበላል ይጠጣል። እነዚህ የጐሬቤት አካባቢና ግዛት ነገሥታት ከሚሾማቸው የዛር አለቃ (ቃልቻ) ጋር በሴትና በመሬት በግዛት እየተቀናኑ እምብዛም አይፋቀሩም።

በጃንጀሮ (የም) አካባቢ ሥርዓት ደግሞ ስንመለከት ዛርን የሰደበ ወይም ያንቋሸሸ የሚፈረድበት የሞት ፍርድ ለዘንዶ ተሰጥቶ መቀጥ ነው። የዛር አለቅነቱን ደርቦ የያዘው የጃንጀሮ ንጉሥ ነገሩን ካጣራ በኋላ እውነት ሆኖ ከተገኘ በንጉሡ ፍርድ አጥፊ ነው የተባለውን ሰው ዘንዶ እንዲውጠው በዘንዶ ጐሬ ይጣላል። (የዓለም ታሪክ ከዮሐንስ ወ.ማርያም)

በተመሳሳይ መንገድ ከባቢሎንና ከፋርስ በሠረጸው አምልኩ አብዛኛው የባላገርና እንዲሁም ጥቂት የከተማ ነዋሪ ሕዝብ እንደእነዚያ ድንጋይና እንጨት ቀርጸው መርቅና ብር አፍስሰውበት ምስል ሠርተው እደሰግዱም ነበር እንጂ በፀሐይ በጨረቃ በአራዊት በዛርና በመናፍስት ማምለካቸውና የአመላለኩም ዓይነትና ሥርዓት ከእነዚያ ጋር በብዙ ይመሳሰላል። የሚርቱና የአስማቱም እደጋገምና አደራረግ የመናፍስቱም ስምና ሥራ ከእነዚህ ጋር የሚመሳሰል አለ። የኮከብ አቆጣጠሩም ዐውደ ነገሥቱም የባህረ ሃሳቦችንም አካሄድና አሠራር ስናይ ከፋርሱ ዞሮአስትር አቆጣጠር ከዞዴአክ ጋራ በመጠኑ በመገናኘቱ ከዚያ የተቀዳ ነው ያሰኛል። የዚህ ዓይነቱ የከፋ መናፍስት አሠራር በአገራችን በኢትዮጵያ ከባላገሮችም ክደብተራዎችም ዘንድ አልተነቀለም። አንዳንድ ሰዎች ጥዋት ጥዋት ቤተ ክርስቲያን ከሰዓት ደግሞ በየጠንቋዩ ቤት ዘንዶን (ሰይጣንን) እንደሚያመልኩ በስፋት ይወራል። ይህም ትልቅ ስህተትና ጥፋት ነው።

የጥንቆላና የውቃቢ ሥራ እግዚአብሔር ባልፈቀደው መንገድ መንፈሳዊ ኃይልን መፈለግ ነው። ከጥንት ጀምሮ ጠንቋዮች የነገሥታት

አማካሪዎች ነበሩ። የዘንዶ አሠራር የሰይጣን ጥልቅ ሥራን ይገልጻል። ምዋርተኛ፥ ሞራ ገላጭ፥ አስማተኛ፥ መተተኛ፥ በድግምት የሚጠነቁል ደጋሚ፥ መናፍስት ጠሪ፥ ሙታን ሳቢ ጠንቋዮች በዓለም ላይ እንዳሉ ሁሉ በአገራችንም ይገኛሉ።

እነዚህ እርኩስ መናፍስትና የሙታን መናፍስትን በመጠየቅ ምስጢራውያን አስማትን በመድገም ልዩ ልዩ መስዋዕትን በማቅረብ የእንስሳትን ሆድ ዕቃና ሌሎችንም ነገሮች በመመልከት የሚመጣውን ነገር እንናገራለን የሚሉ ናቸው። (ዘዳ. 18፥9-14)

ኢትዮጵያ ክርስቲያን መሆንዋን ካስታወቀች ከ140 ዓመታት ያህል በኋላ እንኳን የክርስትና ሃይማኖት የተመሠረተበት ነው በሚባል በአክሱም አካባቢ በየጊዜው ሰው የሚገበርለት ዘንዶ ይመለክ እንደነበረ ይታወቃል። ከተሰዓቱ ቅዱሳን አንዱ ናቸው የሚባሉት የአቡነ ገሪማ (ይስሐቅ) ገድል እንደሚተርከው ተጠቃሹ አቡን ዘንዶውን በጸሎታቸው ገደሉት ይላል። ይሁን እንጂ የሕዝቡ አምልኮት በአብዛኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዘንዶ አምልኮ ሊላቀቅ እንዳልቻለ ይነገራል።

ይህንን የሚመስል የዘንዶ (የሰይጣን ሥራ) እግዚአብሔር አጥብቆ የሚጠላው ስለሆነ በገጠርም ሆነ በከተማ አውቀው በድፍረትም ሆነ ሳያውቁ በስንፍና ለጠላት ዲያቢሎስ የሚሰግዱና የሚያሰግዱ ሁሉ ንስሃ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሱ የሚጠብቃቸው የዘለዓለም ፍርድ ነው። በተለይም ደግሞ ሰይጣን «እኔ ሰይጣን ነኝ» ብሎ ሳይሆን በመላዕክትና በቅዱሳን ስም ገብርኤል ሳይሆን ገብርኤል ነኝ ሚካኤል ሳይሆን ሚካኤል ነኝ ማርያም ሳይሆን ማርያም ነኝ ወዘተ. እያለ ስለሚያታልል ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ እውቀት ስለሌላቸው እየገበሩለት ሰይጣን የውሸት አባት መሆኑን ባለማወቅ ይስታሉ ሌሎችንም ያስታሉ። መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። (ማቴ. 22፥29)

1.5 የደብረ ዳሞ ዘንዶና አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል)

ወደ ኢትዮጵያ መጡ ከሚባሉት ከዘጠኙ መነኮሳት (ተሰዓቱ ቅዱሳን) አንዱ የሆኑት አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) ለጥሞና ጸሎት ወደ ደብረ ዳሞ አካባቢ ሄደው ሳሉ ወደ አንድ ተራራ ጫፍ ለመውጣት ሲፈልጉ በአምባው ላይ ይኖር የነበረው ትልቅ ዘንዶ እየተምዘገዘገ ወርዶ ከእግር እስከ ወገባቸው ተጠምጥሞና ጠልፎ በመያዝ አምባው ላይ

እንዳወጣቸው በመጽሐፈ ገድላቸው መገለጹ «የኢትዮጵያ ሥልጣኔ» በሚል መጽሐፍ ገጽ 99 ላይ ተጠቅሶአል።

እኚህ ሰው በአምባው ላይ አጼ ገ.መስቀልን ቤተ ክርስቲያን እንዲያሠሩላቸው ጠይቀው ንጉሡ ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት ወደ ተራራው የሚያስወጣ ደረጃ አሠርተው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መንገዱን ጨርሰው ቤተ ክርስቲያኑን በትንንሽ ጥርብ ድንጋዮችና በጥርብ እንጨት አስጊጠው ካሰሩ በኋላ ንጉሡ «ደረጃውን ላፍርሰው ወይስ እንዳለ ይቆይ?» ብለው አቡነ አረጋዊን ሲጠይቁ «ዳሕምሞ» አሏቸው ማለትም <u>አፍርሰው</u> ማለት ነው። ከዚያም በኋላ አምባው «ደብረ ዳሕምሞ» ተብሎ ተጠራ። በቀን ብዛት ግን <u>ደብረ ዳሞ</u> እየተባለ መጠራት ጀመረ ይባላል።

የደብረ ዳሞ ገዳም የተተከለበት ተራራ በተንጣለለ ሜዳ ላይ በእግር ተራምዶ ለመውጣት ስለማይቻል ወደ አምባው የሚወጡ ሰዎች አቡነ አረጋዊን አወጣ በሚባለው ዘንዶ አምሳያ በተገመደ ጠፍር ከእግር እስከ ወገብ እየታሠሩ ነው። ይህም መጫኛ ገመድ (ጠፍር) ርዝመቱ 16 ሜትር ሲሆን ውፍረቱ ደግሞ ዘንዶ ያህላል። በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ተንጠልጥሎ መውጣት እጅግ አስፈሪና አስቸጋሪም ነው። በአምባው ላይ ሰፊ የእርሻ መሬት ባለመኖሩ በገዳሙ የሚኖሩ ቁጥራቸው ከ600 በላይ የሆኑ መነኮሳት ቀለባቸውን የሚያመላልሱት ዘወትር በዚሁ በዘንዶ አምሳያ በተጐነጐነው ጠፍር በመታሠርና በመንጠልጠል ነው። ሴቶች ወደገዳሙ እንዲገቡ የማይፈቀድላቸው ቢሆንም ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ብቻ ሬሳቸው በዚሁ በዘንዶ አምሳያው ጠፍር ታስሮ በማውጣት እንዲቀበሩ ይደረጋል። የደብረ ዳሞ አምባ በአካባቢው ነዋሪዎች «አራዳ አቡነ አረጋዊ» ተብሎ ይጠራል። (የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከበላይ ግደይ)


ከዚህ ቀጥሎ ሐሙስ ታህሣሥ 17 ቀን 1989 ዓ.ም «እውን ደብረ ዳሞን መብረቅ፥ አዲስ ዓለም ጽዮን ማርያምን ጢፍ አቃጠላቸውን?» በሚል ርዕስ ሳምንታዊው መብሩክ ጋዜጣ በመጀመሪያው ገጽ ላይ ያወጣውን ሥዕል ከግርጌ ይመልከቱ።



አቡነ: እሬ ጎቂ ዘጫለሬ: ቅ ሞ

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ዘንዶን የሚያመልኩ፥ እሥብ የሚቀልቡ፥ የሚለማምኑ፥ የሚጠነቁሉ ሰዎች እንዳሉ ይነገራል። ከነዚህም በተጨማሪ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች አንዱ በነበረችው በኤርትራ ክፍለ ሀገር መንደፍራ ጋብር ዳርዓንቶ (አቦ ጠበል) ሊጠመቁ የሚሄዱት ሰዎች ለመመሪያ ተቀባይ ካህን ዘንዶ ሲፈቅድ ብቻ ወደ ጠበሉ እንደሚገቡና እንደሚስተናገዱ እስከ ቦታው ሄደው ከተመለሱት ሰዎች ለማረጋገጥ ተችሎዋል። ያም ሆነ ይህ ዘንዶ የሰይጣን ተጠሪ እንጂ የእግዚአብሔር መልዕክተኛና አገልጋይ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። እርሱን የሚያመልኩና የሚከተሉም የክፋቱ ሥራ ተካፋይ ከመሆን በስተቀር ለሌላ ለምንም አይሆኑም። «አባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ዘፍ. 3፥1» «ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። ያዕ. 4፥7-8»

ይህ በዚህ እንዳለ በደቡብ ጐንደር ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም በ582 ዓ.ም. ንጉሥ አጼ ገብረ መስቀልና አቡነ አረጋዊ እንዲሁም ያሬድ ከደብረ ዳሞ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ከዚች ቦታ ይዘው መጥተው መውጫ አጥተው ከተራራው ጥግ ሆነው ሲጸልዩ ኡራኤል መልአክ ከመሬት ወርዶ ዙር አባ መንገድ ምስራቅ ብሎ ከተራራዋ ላይ ካለችው መስክ አሳረፋቸው የሚል በ29/8/86 ዓ.ም ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድሳት እርዳታ ለማሰባሰብ በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጾአል። ደብዳቤው በከፊል እነሆ :-



ቁጥር፡፲፡ክዛ/ጽ/ጋ/ቲ/ክ/ፈ ቀን ፫፯/፲፩/፲፯፻፭ ዓ.ም..

ለ.....

ለ/አስባ ፤

በደጋብ ጐንደር የሚገኘው ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም በ582 ዓ.ም ገዳሙ አጼ ገብረ መስቀልና ቅዱስ አቡነ አረጋዊ ቅዱስ ያሬድ ከደብረ ዳሞ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ከዚች ቦታ ይዘው መጥተው መውጫ አጥተው ከተራራው ጥግ ሆነው ሲጸልዩ ኡራኤል መልአክ ከመሬት ወርዶ ዙር አባ መንገድ ምሥራቅ ብሎ ከተራራዋ ላይ ካለችው መስክ አሳርፎ ቤተ ክርስቲያኗ ከዚያው ላይ ታገሳ ትኖራለች ::

ይከውም በጽርሳነ ኡራኤል በሰነ ወር ከፍል በገጸ[illegible]ታሪኩ ተመዘገቦ ይኾል ቅዱስ ያሬዶ ለእርሳ የደከሰ ቤተ ክርስቲያን መገለገያ የሆነውን ሰብል ተ አገዘለ ብቁር 3 ዓመት ተምሮ ያደረሰበተ ነው :: ዛሬም መሳ ኢተ ፍለያ ልዘ ተደከሰ ቤተ ክርስቲያን የሚገለገለው ቅዱስ ያሬዱ ከዚያችው ቦታ ሆኖ በደረሰው ያለ አገዛ አብሬ ነው አሁንም ምስጋናውን በየጊዜው በየበዓላቱ የሚያደርሱት ሊቃውንቱች ከዚች ቦታ እየተማሩና እያሰመሰከሩ የሚወጡት ናቸው ይች ቦታ የመሳ ኑተ ፍለያ ልዘ ተደከሰ ክስ ተሞደ ተከታይ እያገለገሉ ትኩረት የሚያደርጉለትና የሚያከብሩት ሀገረ ስብከታችንም ሁሉ በቅ አስተሰሰብ ቤተ ክርስቲያኗ መሰሳሱን ለማስደስ አስተየጸለ የሚያደርገለት እንጂ በተወሰኑ ሰዎች ሃሳብ ብቻ የምትደገፍ አይደለችም

በሌላ ታሪክ ግን ቅዱስ ያሬድ ሚያዝያ 5 ቀን 493 ዓ.ም ተወልዶ ግንቦት 11 ቀን 568 ዓ.ም በሰባ አምስት ዓመቱ እንደ ሞተ ተጠቅሷል

(የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ገጽ 132 -141) ታዲያ ከሞተ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ እንዴት ተነስቶ ከአቡነ አረጋዊና ከአጼ ገብረ መስቀል ጋር ወደ ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም እንደ አቡነ አረጋዊ በዘንዶ ሳይሆን በኡራኤል መልአክ እርዳታ ሊወጣ እንደቻለ ሲገናዘብ ከታሪክ አኳያ ግልጽ አይደለም። ቢሆንም በዚህ አንጻር እውነቱን ለመግለጽ የሚፈልጉ ቢኖሩ ግልጽ ቢያደርጉ አንባቢው ሕዝብ እውነትን አውቆ ከስህተትና ከመወናበድ ሊጠበቅ እንደሚችል እሙን ነው።

1.6 ስለ ዘንዶ የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ምን ይላል?

ዘንዶ አስፈሪ አውሬና የሰይጣን ምሳሌ እንደሆነ በአዲስ ኪዳን በዮሐንስ ራዕይ 12፥3 እና 20፥2-9 እንዲሁም በብሉይ ኪዳንም ዘንዶ የምድር ወይም የባህር አውሬ ሊሆን እንደሚችል ተጠቅሶአል። መዝ. 90፥13 ኢሳ. 27፥1 በራዕይ 20፥9 ላይ የተጠቀሰው «ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» ይላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 10፥18 «... ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ የሚጐዳችሁ ምንም የለም» ብሎአል። በራዕይ 13፥3-4 «ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ ለዘንዶውም ሰገዱለት ...» ይላል። ይህም ዘንዶው የተባለው ዲያብሎስ ለሐሰተኛው ክርስቶስ ሥልጣን እንደሚሰጠው ብዙ ሕዝብ ለዚህ የዘንዶ ሥርዓት አውቆም ሆነ ሳያውቅ ተገዥ እንደሚሆን እንዲሁም ለዚህ ሥርዓት የማያጐበድድ ምልክቱንም ሆነ የስሙን ቁጥር የማይቀበል ማንም ቢኖር ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል ይናገራል። ምልክቱ ወይም የአውሬው ቁጥር የተባለው 666 ሲሆን ይህም የሰው ቁጥር ነው፥ ይላል ራዕይ 13፥4-18።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ሰዎች ክርስትናን ከዘንዶ ጋር ለማገናኘት መሞከራቸው አጠያያቂ ነውና ራሳቸውን መመርመር እንዲችሉ ጠቢቡ ሰለሞን «የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው» መክ. 2፥14 ይላል። ይህም ማለት የጠቢብ ዓይኑ በጭንቅላቱ ላይ ነው ማለት ሳይሆን ጠቢብ የሌላውን ስህተት ከማየት በፊት ራሱን ይመረምራል ማለት ነው።

2. የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሰፋሪዎችና አምልኮታቸው

በነቢዩ ሶፎንያስ በኩል «በዚያን ጊዜ አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሕን ልሳን እመልስላቸዋለሁ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል» (ሶፎ. 3፥9-10) ብሎ እግዚአብሔር የተናገረው ትንቢታዊ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊያን ሠፋሪዎች አምልኮትም በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ከነበረው የአምልኮት ዓይነት ተለይቶ አያውቅም። ይልቁንስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተመሳሳይነት ያለው ነው እንጂ። ይህም የሆነበት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የገቡት ሕዝቦች የራሳቸውን ባህልና እምነት ይዘው እንደገቡና እንደሠፈሩ የታወቀ ነው። ቀደም ሲል ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የኩሽ ነገዶች ሲሆኑ እነርሱም በአካባቢያቸው በሚገኙት በትላልቅ ተራሮች በወንዞች፥ በኮረብቶች፥ በእንስሳት፥ በአራዊት፥ በአእዋፍ፥ በእባብ፥ በዛፎችና በድንጋዮች የማምለክ ባህል እንደነበራቸው ይነገራል። በተጨማሪም ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው ለሚታዩት ለፀሐይ፥ ለጨረቃ ለከዋክብት ... ይሰግዱና ያመልኩ የነበሩት ነገደ ሴም እንደነበሩ ለማረጋገጥ ከደቡብ ዐረቢያ የተገኘ የአምልኮት ቅርስ ለአምልኮቱ ተመሳሳይነት ፍንጭ ይሰጣል።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን የሁለቱን ዝሪያዎች አምልኮት ለንመለከት በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች በማየትና በማድነቅ ከሚሰግዱላቸው ከነገደ ኩሽ ይልቅ ራቅ ብለው የሚገኙትን ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ከዋክብትን የሚያመልኩት ነገደ ሴም ለአምልኮት የነበራቸው አመለካከት በመጠኑ ላቅ ያለ እንደሆነ ያሳየናል።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የገባው የተስፋ ቃል ኪዳን ግን ከዚህ ሁሉ ያለፈ እጅግም ደስ የሚያሰኝ ነው።

3.1 ጥንታዊው የአክሱም ሥልጣኔና የሥነ ጥበብ ዕድገት

ከክርስቶስ ልደት ከ539-484 ዓ.ዓ ገደማ ሔሮዶቱስ የተባለ ጽርዓዊ (ግሪካዊ) ታሪክ ጸሐፊ ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፍ በአዜብ (በስተደቡባዊ ምዕራብ) በኩል በጣም ራቅ ብሎ የሚገኝ አገር ኢትዮጵያ ነው። በአገሩም ትልልቅ የሆኑ ዝሆኖች አሉበት ልዩ ልዩ ትላልቅ ዛፎች በየቦታው በቅለው ይገኛሉ። ሰዎቹም ከዓለም ሕዝብ ሁሉ በውበት የበለጡና ረጅም ዕድሜም ያላቸው ናቸው ብሏል።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ በተመዘገበበት በክብረ ነገሥት «ኩሽ ወልዱ ለኢትዮጲስ ዘውእቱ አባሆሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ» በአማርኛ ሲተረጉም «ኩሽ ኢትዮጲስን ወለደ፥ ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ አባታቸው ነው» የሚል ተመዝግቦ ይገኛል።

የአክሱም ከተማ የተቆረቆረውና የተሰየመው በኢትዮጲስ ልጅ በአክሱማይ ስም እንደሆነ ይነገራል። ብዙ ገናና ነገሥታት ከጥንት ጀምሮ በአክሱም ግዛት ላይ እንደነገሡና ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ ዓመት በፊት የነገሡት ንግሥተ ሳባ መንበረ - መንግሥቷ በአክሱም ሲሆን ከአክሱም ከተማ ወደ አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል ገደማ በምዕራብ አቅጣጫ የሚገኘው የቤተ መንግሥቷ ህንፃ ፈራርሶ ጠፍቶ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ገበሬዎች ለእርሻ ይጠቀሙበት የነበረውና መሬት ውስጥ ተቀብሮ አፈር ለብሶ የቆየው ቤተ መንግሥት በቁፋሮ መሠረቱ ወጥቶ አንድ ሰፊ ክፍል ዙፋን ችሎትና 56 የተለያዩ መጠን ያላቸው ክፍሎች ያሉበት መሠረት ተገኝቷል። ይህም በአሁኑ ጊዜ ዙሪያው በግንብ ታጥሮና በእንክብካቤ ተይዞ የቱሪስቶች መጐብኛ ሆኖአል። የቤተ መንግሥቱ የውስጥ ቁፋሮና ጥናቱ ገና የሚቀጥል መሆኑ ሲታወቅ እስካሁንም የወጡት በአክሱም ሙዚየም ውስጥ ይገኛሉ። በተለይም ብርቅየ የንግሥቲቱ መጠጫ ብርጭቆዎች እስካሁን ድረስ በዓለም ላይ እንደዚህ ዓይነት ብርጭቆ ሠርቶ ያወጣ ፋብሪካ ከኢትዮጵያ በስተቀር እንደሌለ ሲነገር በዘመኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረ የሥልጣኔ ዕድገት ከሁሉ በላይ ከፍተኛ መሆኑን ያረጋግጥልናል። በተጨማሪም በቁፋሮ የተገኙት የሸክላና የብረት ዕቃዎች ለተመሳሳይ ምርምር የሚጋብዙ ናቸው።

3.2 የአክሱም ጥንታውያን ነገሥታትና ያሠሩአቸው ገንዘቦች


ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው የባዝን የመታብር ሀውልት የሚገኘው በአክሱም ከተማ ውስጥ ነው። እንደ/ ኢዛና የመሳሰሉ ነገሥታትም በአክሱም ከተማ ሥራቸውን በድንጋይ ላይ ጽፈው አኑረዋል። ሌሎችም በርካታ ነገሥታት እንደ እንደቢስና አፊላስ የመሳሰሉት ደግሞ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስማቸው የተቀረጸባቸውን የብርና የወርቅ ገንዘቦችን አሰርተዋል።

ሜልቪን ጂ ኮሽል የተባለ ደራሲ «ኢትዮጵያ ትሬዠር ሀውስ አፍ አፍሪካ» «ኢትዮጵያ የአፍሪካ የምርጥ ቅርስ ግምጃ ቤት» በተሰኘ መጽሐፉ «በኢትዮጵያ በሰባት መቶ ሃምሳ ዓመታት ውስጥ አንዱ ሲወድቅ ሌላው እየተነሳ በገዙ በሃያ አራት ነገሥታት ዘመን ገንዘቦች ተሠርተዋል» ይላል። ፍራንሲስ አንፍሬይ ደግሞ ከዚህ በታች ስማቸውና የነገሡበት ዘመን የተጠቀሰው 24 የአክሱም ነገሥታት የተለያዩ የመገበያያ ገንዘቦችን እንዳሠሩ ለዓይነት ጠቅሰዋል። የአንዳንዶቹ ነገሥታት ስም በክብረ ነገሥት ከተጠቀሰው ስም ጋር አንድ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ነገሥታቱ ሁለት ስሞች ስለነበራቸውና ከሁለት አንዱ ስም ብቻ በመወሰዱ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ተ.ቁ	የነገሥታቱ ስም	ያሠሩአቸው ገንዘቦች ብዛት በአይነት	የነገሡበት ክፍለ ዘመን
1.	እንደቢስ	ሦስት የወርቅ	3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
2.	አፍላስ	አንድ የወርቅ ሁለት የብር አምስት የነሐስ	3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
3.	ቀዳማዊ (ኡዛናስ)	ሁለት የወርቅ ሁለት የብር	3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
4.	ዋዜባስ ቀዳማዊ	አንድ የወርቅ	4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
5.	ኢዛና አረማዊ እያለ፤ ኢዛና ክርስቲያን ሆኖ	ስምንት የወርቅ ሁለት የብር፤ ሦስት የነሐስ ስምንት የወርቅ	4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
6.	ኤዎንቢስ (አናፍዮን)	ዘጠኝ የወርቅ	4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
7.	ኤዝባኤል (ሕዝባኤል)	ሠላሳ ስምንት የወርቅ	4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

8.	ካሌብ	ሃያ አምስት የወርቅ ሥስት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
9.	እስራኤል፤ (ካሌብና ተከታዮቹ)	አንድ ዓይነት (የወርቅ) ሠላሳ ስምንት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ 5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
10.	ዋዜባስ ዳግማዊ	አሥራ አምስት የነሐስ (መዳብ)	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
11.	ግሃዮገስ/መሀየገስ	ሰባት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
12.	አላሊ ሚራስ	አንድ የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
13.	ኢዛና	አንድ የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
14.	ኡዛስ	አሥር የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
15.	ኔዛና	የወርቅና የብር	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
16.	ኢዩኤል	ሁለት የወርቅ ሃያ አምስት የመዳብ (ነሐስ)	6ኛው መቶ ክፍለዘመን
17.	ኤላ ገበዝ	ሥስት የወርቅ	6ኛው መቶ ክፍለዘመን
18.	ኤናዮብ	ሥስት የብር	7ኛው መቶ ክፍለዘመን
19.	ላዝሊያ (ያትልያ)	ሁለት የወርቅ አንድ የብር	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
20.	አርማህ	አንድ የወርቅ አንድ የብር ሠላሳ ስምንት የመዳብ (ነሐስ)	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
21.	ዘየ እብዮ ለመድህን (ሐይወ አብ ለመድህን)	አንድ ዓይነት	በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
22.	ኡዜና (ዋዜና)	አሥራ አንድ የመዳብ	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
23.	ገርሶም	ሥስት የወርቅ አራት የመዳብ (ነሐስ)	8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
24.	ሐታዝ 2ኛ	ሠላሳ ስድስት የነሐስ (መዳብ)	8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ክላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ከክርስትና በፊት የተሠሩት የአክሱም ገንዘቦች በነገሥታቱ ምስል አናት ላይ ከፍ ብሎ የሚታየው የጥንት የሳባውያን የጣዖት አምልኮ ምልክት የሆነው የጨረቃና የኮከብ ምልክት ሲሆን ከክርስትና በኋላ ግን አናታቸው ላይና በአንዳንዶቹም ገንዘቦች መካከል የመስቀል ምልክት ለመኖሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰሌዳ ይታያል።



8.	ካሌብ	ሃያ አምስት የወርቅ ሦስት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
9.	እስራኤል፣ (ካሌብና ተከታዮቹ)	አንድ ዓይነት (የወርቅ) ሠላሳ ስምንት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ 5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
10.	ዋዜባስ ዳግማዊ	አሥራ አምስት የነሐስ (መዳብ)	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
11.	ማሃዮገስ/መሀየገስ	ሰባት የነሐስ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
12.	አላሊሚራስ	አንድ የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
13.	ኢዛና	አንድ የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
14.	ኡዛስ	አሥር የወርቅ	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
15.	ኔዛና	የወርቅና የብር	5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
16.	ኢዩኤል	ሁለት የወርቅ ሃያ አምስት የመዳብ (ነሐስ)	6ኛው መቶ ክፍለዘመን
17.	ኤላ ገበዝ	ሦስት የወርቅ	6ኛው መቶ ክፍለዘመን
18.	ኤናዮብ	ሦስት የብር	7ኛው መቶ ክፍለዘመን
19.	ላዝሊያ (ያትልያ)	ሁለት የወርቅ አንድ የብር	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
20.	አርማህ	አንድ የወርቅ አንድ የብር ሠላሳ ስምንት የመዳብ (ነሐስ)	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
21.	ዘየ እብዮ ለመድህን (ሐይወ አብ ለመድህን)	አንድ ዓይነት	በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
22.	ኡዜና (ዋዜና)	አሥራ አንድ የመዳብ	7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
23.	ገርሶም	ሦስት የወርቅ አራት የመዳብ (ነሐስ)	8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
24.	ሐታዝ 2ኛ	ሠላሳ ስድስት የነሐስ (መዳብ)	8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ከላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ከክርስትና በፊት የተሠሩት የአክሱም ገንዘቦች በነገሥታቱ ምስል አናት ላይ ከፍ ብሎ የሚታየው የጥንት የሳባውያን የጣዖት አምልኮ ምልክት የሆነው የጨረቃና የኮከብ ምልክት ሲሆን ከክርስትና በኋላ ግን አናታቸው ላይና በአንዳንዶቹም ገንዘቦች መካከል የመስቀል ምልክት ለመኖሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰሌዳ ይታያል።



3.3 በጥንታዊው የአክሱም ገንዘብ ላይ የተገኘ አርማና ጽሑፍ

በዚሁ ነገሥታት የወርቅ፥ የብርና የነሐስ ገንዘቦች በፊትና በጀርባቸው ላይ የተጻፉ ጽሁፎች በዘመኑ የነበረውን የነገሥታት አቋምና የህብረተሰቡን ሁኔታ የሚያሳዩ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ከነዚህም በአክሱም ከነገሡት ነገሥታት መካከል አንዳንዶቹ በዘመነ መንግሥታቸው ባሠሩአቸው ገንዘቦች ላይ ያሰፈሩት ጽሑፍ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል።

1ኛ) ንጉሥ ኡዛናስ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ ኡዛናስ በእግዚአብሔር ፀጋ ይህ ለእዝቡ የሚጠቅም ይሆን ዘንድ»

የተሰራው ገንዘብ የወርቅና የብር

2ኛ) ንጉሥ ኢዛና በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«የሰማይ ጌታ መንግሥቴን ጠንካራ ያድርግልኝ»

የተሰራው ገንዘብ የወርቅና የብር

3ኛ) ንጉሥ አላሊሜሪስ በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ አላሊሜሪስ ፦ የሎኤ ነገድ»

የተሠራው ገንዘብ የብር

4ኛ) ንጉሥ ኢዛና በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ኢዛና በእግዚአብሔር ፀጋ»

የተሠራው ገንዘብ የወርቅና የብር

5ኛ) ንጉሥ እሥራኤል በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«እስራኤል ፦ የአክሱሞች ንጉሥ ምህረት ለሕዝቡ»

የተሠራው ገንዘብ የወርቅ

6ኛ) ንጉሥ ዋዜና

«ንጉሥ ዋዜና ፦ በሕዝቡ ዘንድ ሞገስ ያገኝ ዘንድ»

የተሠራው ገንዘብ የነሐስ (መዳብ)

7ኛ) ንጉሥ ኢዩኤል በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ ኢዩኤል ክርስቶስ ከእኛ ጋር ነው»

የተሰራው ገንዘብ የወርቅ የብር የነሐስ (መዳብ)

8ኛ) ንጉሥ አናዮብ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ አናዮብ ፦ ምሥጋና ለፈጣሪ»

የተሠራው ገንዘብ የብር

9ኛ) ንጉሥ አርማህ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ አርማህ ፦ ደስታና ሰላም ለሕዝቡ»

የተሠራው ገንዘብ የወርቅ የብር የነሐስ (ሚዳብ)

10ኛ) ንጉሥ ገርሶም በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ ገርሶም ፦ ከክርስቶስ ጋር ድል ታደርጋለህ»

የተሠራው ገንዘብ የነሐስ (መዳብ)

11ኛ) ንጉሥ ዳግማዊ ሐታዝ በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሠ

«ንጉሥ ሐታዝ ፦ ፀጋ ከሕዝቡ ጋር ይሁን»

የተሠራው ገንዘብ የነሐስ (መዳብ)

ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ገንዘብ በስሙ አሠርቶ ያወጣ የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደቢስ (225-235 ዓ.ም) እንደነበረ አርኪዎሎጂስቶች ይገምታሉ። ቀጥሎም በስሙ ገንዘብ ያሠራ ንጉሥ አፈላስ እንደሆነም ማረጋገጫ ያቀርባሉ። በመጨረሻም ከንጉሥ ሐታዝ በኋላ ገንዘብ የማሠራትና የመጠቀም ጥበብ ከኢትዮጵያ ምድር ጠፋ።

የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ የነገሡት ነገሥታት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስላላቸው እምነትና ስለ ክርስትና ሃይማኖት በዘመነ መንግሥታቸው ባሠሩአቸው ገንዘቦች ላይ የመስቀል ስዕል በማሳል ለፈጣሪ ያላቸውን አክብሮትና ለሕዝቡም የሚመኙለትን ምኞት ጠቅሰዋል።

ከአክሱም የጥንት ገንዘቦች ጥቂቶቹ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ብሔራዊ ሙዚየም ለናሙና ቀርበው የሚገኙ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን በውጭ አገር በሚገኙ ሙዚየሞች በተለይም በቪየና፥ በፓሪስ፥ በለንደን፥ በበርሊን፥ በቦምቤይ፥ በሌኒንግራድ፥ በኒዮርክ፥ በፍራንክፈርትና በኤደን ሲገኙ ጥቂቶች ደግሞ የተለያየ ገንዘብ በሚያጠራቅሙ ግለሰቦች እጅ ይገኛሉ። በተለይም በኤደን (ደቡብ የመን) ከ1000 የበለጡ ከወርቅ ከብርና ከነሐስ የተሠሩ የተለያዩ የአክሱም ገንዘቦች እንደሚገኙ ተረጋግጦአል። ይህም ምናልባት

ኢትዮጵያ ለብዙ መቶ ዓመታት የመንን ትገዛ ስለነበረ ለወታደሮች ደመወዝ መክፈያና ለመገበያያም ሲጠቀሙበት የነበረ እንደሆነ ይገመታል።

የእንደቢስና የአፈላስ የወርቅ ሳንቲሞች ከ2.4 እስከ 2.75 ግራም ሲመዝኑ የኢዛና ግን ከ1.70 እስከ 2.90 ግራም የሚመዝኑ ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ የወርቅ ሳንቲሞችን አሠርቶ የማውጣቱ ጥበብ እስከ 8ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ብቻ እንደቀጠለ ተረጋግጧል። ከዚያ ዘመን በኋላ በተለይም ከንጉሥ አርማህ መንግሥት ጀምሮ በወርቅ ተሠርተው የነበሩት ገንዘቦች ለጥቂት ዓመታት በብርና በመዳብ መልክ እየተተኩ ቆይተው ከዚያም ጨርሶ እንደጠፉ ተመልክተናል። ይህም ውድቀት ያለ በቂ ምክንያት የተከሰተ አይደለም። ለምን እንደሆነ ግን መመርመርና ማወቁ ተገቢ ነው።

ሎሪንስ ብራውን «ኮይንስ ስሩ ዘ ኤጅስ» (በዘመናት ውስጥ የሳንቲም ገንዘቦች) በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ሲገልጽ «ባለፈው ረዥም የታሪክ ዘመን ሁሉ የተመልካችን ዓይን የሚስቡና ልዩ የሆኑ ሳንቲሞች አሠርተው በማውጣት የኢትዮጵያ ንጉሣዊ ግዛት ተለይቶ ሊጠቀስ ይገባዋል።» በማለት አድናቆቱን ገልጾአል።

3.4 ስለ ገንዘቡ የተደረገ ጥናትና ምርምር

ስለ አክሱም ጥንታዊ ገንዘብ የተረጋገጠ መረጃ የተገኘው እ.ኤ.አ በ1840 ዓ.ም ነው። ይኸውም ዶክተር ኤድዋርድ ሩፕል የተባሉት የፍራንክፈርት ሰው እ.ኤ.አ ከ1931 እስከ 1934 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ ስላደረጉት ጉዞና ጥናት ሲተርኩ አክሱም ላይ ስለተገኘው ንጉሥ አፍላስ በተጨማሪም አዱሊስ ላይ ስለተገኘው ስለ ገርሶም ንጉሥ የወርቅ ገንዘቦች ዝርዝር መግለጫ መስጠታቸው ታውቆአል። ሊቁ በአናስታሲ ስብሰባ እስክንድርያ ላይ ስላዩት ስለ ንጉሥ አርማህ የመዳብ ገንዘብም መግለጫ ሰጥተዋል። በተጨማሪም ብእሴ አና አፈ ዎን የሚል ጽሑፍ ስላለበት የወርቅ ገንዘብ እ.ኤ.አ በ1845 ዓ.ም ደብዳቤ ጽፈው «ኑሚዝ ማቲክ ክሮኒክል» በተባለው የገንዘብ ምርመራ መጽሔት ላይ ታትሞ እንዲወጣ በማድረጋቸው ለዚህ ምርምር በር ከፋች ሆኖ ተገኝቶአል።

ገንዘቦቹ ለብዙ ዘመናት ተቀብረው ከቆዩ በኋላ በቁፋሮ ሲገኙ እንደ አንድ ተዓምር የሚቆጠሩ ስውር ነገር ገላጮች ሆነዋል። ይኸውም የብዙዎቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ በዘመን ርዝመት ምክንያት


እንኳንስ ሥራቸውና ሞያቸው ሊታወቅ ቀርቶ ስማቸውም ተረስቶ ከታሪክ ሰሌዳ ተሰርዘው ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ ገንዘቦች «ንጉሥ እገሌ አሰራን፥ በንጉሥ እገሌ ዘመን አገለገልን» ሲሉ ነገሥታቱን ከመረሳት ወደ መታወስ ሕይወት ጠርቶ ማስነሳት ያህል ሥራ ፈጽመዋል ለማለት ይቻላል።

በገንዘቦቹ ላይ ከፊትና ከኋላ የሚታዩ ቅርጾች የዘመኑንና የነገሥታቱን እምነት ገላጭም እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ ሌሎች ነገሥታትም ሆኑ ንጉሥ ኢዛና አረማዊ እያለ ያሰራቸው ገንዘቦች የጥንት የሳባውያን የአምልኮ ምልክት የነበረው ግማሽ ጨረቃ ያለባቸው ሲሆን ከክርስትና በኋላ ግን በግማሽ ጨረቃው ምትክ ትእምርተ መስቀል ይገኝባቸዋል።

የጨረቃ ግማሽ በጠቅላላው በጥንታውያን ገንዘቦች ላይ በተለይም በእስያ ክፍለ ዓለም ብዙ ጊዜ የሚገኝ ምልክት ነው። ለምሳሌ በደቡብ ዐረብ፥ በምድረ ዔላም በፋርስ (ኢራን) በባቢሎንና (ኢራቅ) በጻርቴ ይገኛል። የግማሽ ጨረቃው ምልክት በአንዳንድ የአክሱም ሀውልቶች ጫፍ ላይ ተቀርጾ መገኘቱም የታወቀ ነው።

በገንዘቦቹ ላይ የተቀረጹት የመስቀል ምልክቶች ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ገንዘቦቹ የተሰሩት ከክርስትና በኋላ መሆኑን የሚገልጹ ሲሆን ከምልክቶቹም ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ባለው ሰሌዳ የሰፈሩ ናቸው።





3.5 የገንዘቡ አሠራር

የአክሱም ገንዘብ አሠራር ምንጩ ከሮማውያን አሠራር የተቀዳ ነው። የተሠሩትም በአብዛኛው በወርቅ ነበር። የካሌብና የናዛና የወርቅ ገንዘቦች የተገኙ ሲሆን የተሠሩት በደቡብ አረብ ነው። ጥቂት የብር ገንዘቦችም ተሠርተዋል።

በ575 ዓ.ም ከባህር ማዶ የነበረው ግዛታቸውን ፋርሳውያን ከወሰዱባቸው ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ እስልምና ተነስቶ የኢትዮጵያን የባህር ጠረፎች ሁሉና ግብፅን በመያዙ ምክንያት አገሪቱ ብቻዋን ተከባ በመቅረትዋ የነገሡ ነገሥታት ያሰሩአቸው ገንዘቦች ከመናኛ ማዕድን የተሠሩ ናቸው።

ቀደም ሲል የወርቅ ገንዘብ ያሠሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለምሳሌ የእነ እንደቢስ የአፈላስና የውሳንናስ የወርቅ ገንዘቦች ሚዛናቸው ከ2.40 እስከ 2.75 ግራም ይደርሳል። ሚዛኑ 0.32 ግራም ከሆነው ከአንድ ልዩ የአፈላስ ገንዘብ በስተቀር በሦስተኞቹ መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ የሮማ ንጉሠ ነገሥት ዲዩቅለስያኖስ ካሰራቸው የወርቅ ገንዘቦች ጋር በጣም የሚመሳሰሉ ናቸው።

ሌላው ደግሞ ንጉሥ ኢዛናና ከእርሱ በፊት የነበሩት አረማውያን ነገሥታት ያሰሯቸው ገንዘቦች በዘመን ብዛት ተበልተው የጐደለባቸው ተሞልቶ ሚዛናቸው 1.70 እስከ 2.19 ግራም የሚደርሱ ሲሆን ቁስጠንጢኖስ በ306 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከተሠሩት የወርቅ ገንዘቦች ጋር የሚነጻጸሩ ናቸው።

በአረመኔነት ዘመን የነበሩ ነገሥታት ባሠሩአቸው ገንዘቦች ላይ የግማሽ ጨረቃና ኮከብ ምልክት አለባቸው። ከክርስትና በኋላ ግን በገንዘቦቹ ላይ የመስቀል ምልክት ተቀርጸባቸው ይታያል። የግማሽ ጨረቃ ምልክት በጠቅላላ በጥንታውያኑ የአስያ ክፍለ አህጉር ገንዘቦች ላይ ብዙ ጊዜ የሚገኝ ነው። ምልክቱን እስላሞች አሁንም በሃይማኖት አርማነት ይጠቀሙበታል። ይህም የሳባውያን የአምልኮ ምልክት ስለነበረ አክሱማውያንም ይህንኑ በአረመኔነት ዘመን መጠቀማቸውን ያሳየናል።



3.5 የገንዘቡ አሠራር

የአክሱም ገንዘብ አሠራር ምንጩ ከሮማውያን አሠራር የተቀዳ ነው። የተሠሩትም በአብዛኛው በወርቅ ነበር። የካሌብና የናዛና የወርቅ ገንዘቦች የተገኙ ሲሆን የተሠሩት በደቡብ አረብ ነው። ጥቂት የብር ገንዘቦችም ተሠርተዋል።


በ575 ዓ.ም ከባህር ማዶ የነበረው ግዛታቸውን ፋርሳውያን ከወሰዱባቸው ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ እስልምና ተነስቶ የኢትዮጵያን የባህር ጠረፎች ሁሉና ግብፅን በመያዙ ምክንያት አገሪቱ ብቻዋን ተከባ በመቅረትዋ የነገሡ ነገሥታት ያሰሩአቸው ገንዘቦች ከመናኛ ማዕድን የተሠሩ ናቸው።

ቀደም ሲል የወርቅ ገንዘብ ያሠሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለምሳሌ የእነ እንደቢስ የአፈላስና የውሳንናስ የወርቅ ገንዘቦች ሚዛናቸው ከ2.40 እስከ 2.75 ግራም ይደርሳል። ሚዛኑ 0.32 ግራም ከሆነው ከአንድ ልዩ የአፈላስ ገንዘብ በስተቀር በሦስተኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ የሮማ ንጉሠ ነገሥት ዲዩቅለስያኖስ ካሰራቸው የወርቅ ገንዘቦች ጋር በጣም የሚመሳሰሉ ናቸው።

ሌላው ደግሞ ንጉሥ ኢዛናና ከእርሱ በፊት የነበሩት አረማውያን ነገሥታት ያሰሯቸው ገንዘቦች በዘመን ብዛት ተበልተው የጐደለባቸው ተሞልቶ ሚዛናቸው 1.70 እስከ 2.19 ግራም የሚደርሱ ሲሆን ቁስጠንጢኖስ በ306 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከተሠሩት የወርቅ ገንዘቦች ጋር የሚነጻጸሩ ናቸው።

በአረመኔነት ዘመን የነበሩ ነገሥታት ባሠሩአቸው ገንዘቦች ላይ የግማሽ ጨረቃና ኮከብ ምልክት አለባቸው። ከክርስትና በኋላ ግን በገንዘቦቹ ላይ የመስቀል ምልክት ተቀርጾባቸው ይታያል። የግማሽ ጨረቃ ምልክት በጠቅላላ በጥንታውያኑ የእስያ ክፍለ አህጉር ገንዘቦች ላይ ብዙ ጊዜ የሚገኝ ነው። ምልክቱን እስላሞች አሁንም በሃይማኖት አርማነት ይጠቀሙበታል። ይህም የሳባውያን የአምልኮ ምልክት ስለነበረ አክሱማውያንም ይህንኑ በአረመኔነት ዘመን መጠቀማቸውን ያሳየናል።

ግማሽ ጨረቃው የሌለባቸው ገንዘቦች ግን በእርሱ ፈንታ ትእምርተ መስቀል እንደተቀረጸባቸው ከዚህ በፊት ተገልጾአል። ይህም የክርስትና ሃይማኖት በጊዜው ወደ አገሪቱ መግባቱን የሚያረጋግጥ ነው። ትእምርተ መስቀሉ የዘመነ ክርስትና ምልክት ከመሆኑም በላይ በአብዛኛዎቹ ከመዳብ በተሠሩት ገንዘቦች ላይ ከኋላቸው የሚገኝ ዋና መታወቂያቸው ነው።



በመጨረሻም በ9ኛውና በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራው ገንዘብ የንጉሥ ሐታዝ ዳግማዊ ሲሆን በ920 ዓ.ም ገደማ የላስታ ዛጔዎች የአክሱምን መንግሥት ገልብጠው አገሩን ለ300 ዓመታት ገደማ ገዝተዋል። ስለሆነም ከሐታዝ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ለረዥም ዘመናት በኢትዮጵያ ውስጥ ገንዘብ የማሰራትና በገንዘብ የመገበያየት ልማድ ፈጽሞ ጠፍቶ በብረታ ብረት ቁርጥራጮች በዛጐሎች በጥይቶችና በአሞሌ ጨው እንዲሁም አንዱን ዕቃ በሌላው በመለዋወጥ መገበያየት ተጀመረ።

በመጨረሻም በማሪያ ተሬዛ ግርሾችና እንደ እነርሱ ምንዛሪዎች በሚታሰቡት ዕቃዎች መገበያየት ተለምዶ የነበረው ቀርቶ በዳግማዊ ምኒልክ ስም ገንዘብን የማስቀረጽ ልማድ እንደገና ተመለሰ። ከዚያ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የ01 የ05 የ10 የ25 የ50 ሳንቲም ዝርዝር ፍራንክ (coins) ከመዳብ ተሠርተዋል። የወረቀት ብሮች የ1.00 የ5.00 የ10.00 የ20.00 የ50.00 እና የ100.00 ብር ኖቶች ተሠርተዋል። እነዚህ ዲናሮችና (ፍራንኮችና) የወረቀት ብሮች በየካቲት 66 በተጀመረው

አብዮት መስከረም 2/67 ንጉሡ ከሥልጣን ወርደው ከታሠሩና ከሞቱ በኋላ በ1969 ዓ.ም በጦር ኃይሎች በፖሊስ ሠራዊትና በብሔራዊ ጦር ደርግ መንግሥት ተቀይረዋል። በደርግ የተቀየሩት ዝርዝር ፍራንኮች በሙሉና የወረቀት ብሮች የ1.00 የ5.00 የ10.00 የ50.00 እና የ100.00 ሲሆኑ የብር 20 ኖት አልተባዛም።

እነዚህ የተቀየሩት ገንዘቦች ኢሕአዴግ የደርግን መንግሥት ገልብጦ ከያዘበት ከግንቦት 20/83 ዓ.ም በኋላም እስከ 1989 ድረስ ሲሠራባቸው ቆይቶ የኢሕአዴግ መንግሥት በደርግ ጊዜ ሲያገለግሉ በነበሩት የወረቀት ብሮች ብቻ ለውጥ በማድረግ ዝርዝር ፍራንኮቹ በሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጐ ይህ ጽሑፍ በተዘጋጀበት ወቅትም በዚህ መልኩ እየተሠራበት ይገኛል።

4.1 የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት

ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት የመጨረሻ አሥር ዓመታት ጀምሮ የአክሱም ኢኮኖሚያዊ ይዘት ማሽቆልቆል ጀመረ። በመጀመሪያ ፋርሶች ቀጥሎም የአረብ እስላሞች የየመን ግዛትና ቀይ ባህርን በቁጥጥራቸው ሥር ስላዋሉ አክሱም በምጣኔ ሀብት ረገድ ጠቃሚ የሆነውን ግዛቷንና ወደ ሩቅ ምሥራቅ የሚዘልቁትን የንግድ መስመሮችዋን ተነጠቀች። አዋሳኝ የሆኑ ግዛቶች በእስላሞች እጅ መውደቅና በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከእስላሞች ገዥዎች ጋር ግጭት ከተፈጠረ በኋላ የቀይ ባህር ጠረፍዋ መያዙም የአክሱምን ሥልጣኔና ምጣኔ ሀብት እንዲያሽቆለቁል አድርጓል።

አንዳንድ የኢትዮጵያ ነገሥታት እስልምና እንዲስፋፋ ምክንያት ሆነዋል። በተለይም መሐመድ በወገኖቹ በቁራይሾች በተሰደደና ከመካ ወደ መዲና በሸሸ ጊዜ የቅርብ ዘመዶቹን ነፃ ግዛትና ሰላማዊ አገር ወደ ሆነችው ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አርማህ ሂዱ ብሎ ልኮ እንደነበረ ይታወሳል። በዘመኑም አንድ አዲስ ሃይማኖት በፋርስ ተነስቶ ማኔ የተባለ ሰው «ፈጣሪ አምላክ አንድ ሳይሆን ሁለት ነው ሴት አምላክም አለች» በማለት ሲሰብክ የነበረበት ወቅት ነበር። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ንጉሥ አርማህና የወቅቱ የቤተ ሃይማኖት ሃላፊዎች እነዚያን ስደተኞች አነጋግረው «በአንድ አምላክ ነው የምናምነው» ስላሉ በየዋህነትና በእንግዳ ተቀባይነት ፈቅደውላቸው በአገሪቱ በነፃነት ሊቀመጡና ሃይማኖታቸውን ሊያስፋፉ ችለዋል። እስልምናና ታላቁ ነቢይ መሐመድ በተሰኘና በሐጂ መሐመድ ሳኒ ሀቢብ በተዘጋጀ መጽሐፍ እንደተገለጸው በአረቦች <u>አስማህ</u> በአማርኛ ደግሞ <u>አርማህ</u> ተብሎ በሚጠራው የኢትዮጵያ ንጉሥ በ7ኛው ክፍለ ዘመን በቁጥር 107 የሆኑ የመጀመሪያዎቹ የመሐመድ ተከታዮች በሦስት ዙር ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ተጠቅሶአል።

4.2 በእስልምናና በሌሎች የድንበር ግጭት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በተሰኘና በበላይ ግደይ በተዘጋጀ መጽሐፍ ገጽ 82 ላይ ከንጉሥ አርማህ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የኢትዮጵያ (የአክሱም) ሥልጣኔ እያሽቆለቆለ እንደሄደ ተብራርቶአል። ንጉሥ አርማህ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ተማክሮ ለእንግዶቹ ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው በኋላ እዚህ በሰላም እንዲቀመጡ ተፈቅዶላቸው በነፃነት ለአስራ አምስት ዓመታት ቆይተዋል። ከሊፋ ዐሊ የተባለውን የሙሐመድ ተከታይ ገድለው ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው የመጡትም ወላስማዎች በይፋትና ደዋሮ አካባቢ ተቀምጠው ነበር። ወላስማ ማለት እስላም ያልሆነ ማለት ነው። እስላሞቹ በከፊል መሐመድ በጦር መሣሪያ ድል አግኝቶ ጠላቶቹን ድባቅ መትቶ አረብን በሙሉና አካባቢውን ሲቆጣጠር ወደ አገራቸው ሊመለሱ ችለዋል። ይሁን እንጂ መንገዱን ስላጠኑ በንግድና በሌላ ግንኙነት ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ሌሎች እስላሞች ደግሞ በቀይ ባህር ዳርቻና በመሃል አገር ሰፍረዋል። በኋላ ግን ግጭቶች እየተፈጠሩ ኢትዮጵያን እንዳትወጉ የሚለውን የመሐመድን ቃል በመሻር ከአክሱም ገዥዎች ጋር በመዋጋት የቀይ ባህርን ጠረፍ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉት። ይህም ሁኔታ የአክሱምን ምጣኔ ሀብት በይበልጥ ከማላሸቁም በላይ ኢትዮጵያ ከባዛንታይን ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛትና ከሜዲትራኒያን አካባቢ አገሮች ጋር የነበራት ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርጓል።

ቀጥሎም የቤጃ ጐሳዎች በማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ማፈንገጥና የፈላሻ ወገን የሆነችው የዮዲት (ጉዲት) ያካሄደችው ወረራ በሥልጣኔ የመጠቀችውንና በገናናነቷ በዓለም ደምቃና አሸብርቃ ትታይ የነበረችውን አገርና የአክሱም መንግሥት እያዳከመው በመሄዱ ተንኮታኩቶ ወደቀ። እጅግ የሚያስደንቀው ዓለም እንደ ዛሬ ባልሠለጠነችበት ወቅት የወርቅ፥ የብርና የነሐስ ገንዘቦች አሠርቶ ለመገበያያ ይጠቀም የነበረው ገናና ሕዝብና መንግሥት በአሞሌ ጨው፥ በጨርቃ ጨርቅ፥ በብረት ቁርጥራጮች በብዮችና በዛጐሎች ልውውጥ የመገበያየት ሥርዓት መጀመሩ ነው።

ሕዝቡ ቀደም ሲል የነበሩ ገንዘቦችን ለጌጣጌጥ እያቀለጠ ከመጠቀም በስተቀር ለመገበያያና ለንግድ እንቅስቃሴ ሊገለገል አልቻለም። ከዚህም የተነሣ የአክሱም መንግሥት ንግድ ወደቀ። በግለሰቦች እጅ የነበረውንም

ገንዘብ ሕዝቡ ካለመረጋጋቱ የተነሳ ሥጋት ስላደረበት ግጭቱና አደጋው እስኪያልፍ ድረስ እያለ በመደበቁና በመሬት በመቅበሩ እዚያው ሊጠፋ ችሎአል።

ስለዚህ ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ውስጥ እላይ እንደተጠቀሰው ገንዘብ በመሥራትና በገንዘብ መገበያየት ተረስቶ አገሪቱ በሥልጣኔ ሳይሆን በኋላ ቀርነት እየቀደመች ሄደች። የኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ወዘተ. ውድቀት በር ከፋች የሆኑት የወቅቱ ነገሥታትና የቤተ ሃይማኖት መሪዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ሳያጤኑ በጋበዙአቸው ሰዎችና እምነታቸው እንዲሁም በእነዚሁ ወረራ ምክንያት እንደሆነ በብዙ የታሪክ ዘጋቢዎች ይገመታል።

5.1 ቋንቋ ፊደልና ሥነ ፅሑፍ በኢትዮጵያ

የጥንት ቅርሳ ቅርስ ሊቃውንትና ታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚያረጋግጡት በኢትዮጵያ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺ ዓመት ቀደም ብሎ ነው ይባላል። ነገር ግን የጽሑፍ መሠረት የሆነው ፊደልና የጽሑፍ ስልት በደንብ የታወቀው ደግሞ የክርስትና እምነት ከገባ በኋላ እንደሆነ ታሪክ ያረጋግጣል። በዚህ መሠረት ከአክሱም ዘመነ መንግሥት በፊት የሳባውያንና የአግዓዝያን ፊደላት በጎብረት ይሠራባቸው እንደነበረ ታውቆአል። በዘመነ አክሱም ግን የግዕዝ ፊደልና የግዕዝ (የአግዓዝያን) ቋንቋ እያደገ ስለመጣ በክርስቲያን ነገሥታት አክሱም ዘመን በሐውልቶችና በሌላም ነገር ማለትም በተለያዩ የገንዘብ ፍራንኮችና ወዘተ. ላይ የተጻፉ ጽሑፎች በግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ነበር።

ለማንኛውም ጽሑፍና ቋንቋ መሠረቱና መነሻው ፊደል መሆኑ የታወቀ ነው። ፊደል ያልተቀረጸለት ጽሑፍ ያልተሰጠው ማንኛውም ቋንቋ ሁሉ መሠረት ስለሌለው የሚሰጠው አገልግሎት ያን ያህል ነው። ከዚህም የተነሣ አንድ ቋንቋ ታሪካዊ ቋንቋ ነው ተብሎ የሚሰየመው ፊደል ተቀርጾለት የሥነ ጽሑፍ መሠረት በመሆን በጽሑፍ ለትውልድ ሲተላለፍ ብቻ ነው።

5.2 የግዕዝ ሳባዊ ፊደል መሠረት

በኢትዮጵያ ቀደምት ነዋሪዎች የነበሩት የነገደ ኩሽ ዘሮች በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት የኖሩ መሆኑ ስለሰው ዝርያ መኖሪያነት አገሪቱን በቀዳሚነት ደረጃ ቢያስቀምጥም የታሪክና የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች በጽሑፍ የቆየ ነገር ባለመኖሩ የነዚህን የካም ነገድ ሥልጣኔ ለማወቅ አልቻሉም። ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ሳባዊ ስልጣኔ ይቀድማል ተብሎ የሚታመነው በአገሪቱ ቀደም ሲል ነዋሪ የነበረው ነገደ ኩሽ (ካም) ፊደልና ሥነ ጽሑፍ የሌለው መሆኑ የሚያሳዝን ነገር ነው። ምክንያቱም በዘመኑ ምን እንደተሠራ ለማወቅ እንኳን አልተቻለም። ወደፊት ግን ምናልባት በሙያው ባለቤቶች አዲስ ግኝት ቢኖር ደስ ይለናል።

በኢትዮጵያ ሳባዊ ፊደል እንዴት እንደተጀመረ ለማወቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭና በተለያዩ ሐውልቶችና ቅርሳ ቅርሶች ላይ ተጽፎ በተመራማሪዎች ከተገኙት የታሪክ ምንጮች ልንመለከትና ልናረጋግጥ እንችላለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቋንቋ ስርጭት የሚገለጸው ከጥፋት ውሃ ኖህና ልጆቹ ከነሚስቶቻቸው በመርከብ በመግባት ተርፈው በምድር ላይ እንደተባዙ ነው። እነዚህም ሰዎች ስማቸውን ከፍ ለማድረግ ስለፈለጉ ወደ ሰማይ የሚደርስ የስማቸው ማስጠሪያ ግንብ መሥራት ጀመሩ። በጅማሬያቸው ላይ ሥራው ሁሉ ተሳካላቸው በቀላሉም ያከናውኑ ነበር። እግዚአብሔርም ቀደም ሲል ለአዳምና ለሄዋን በገባው ቃል ኪዳን መሠረት «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም» ያለውን ባለመተግበር ባንድ ሥፍራ ተቀምጠው የእኔነትና የትዕቢት ሥራ መጀመራቸውን አውቆ አንዱ ሌላውን እንዳይሰማው ቋንቋቸውን አደባለቀባቸው።

«ምድርም ሁሉ አንድ ንግግር ነበረች፤ ... ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ። እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ። ... አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ አደባለቀው። ... በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው። ... ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ። ... የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና» ዘፍ 11፥1-9

ብዙ የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙበት በዛፍር (የመን) የመጀመሪያዎቹ ሳባውያን ሰፋሪዎች «ሳባ» የሚል መንግሥት መሥርተው ለሴማዊ ቋንቋቸው ሳባዊ ፊደል ቀርፀው ሥልጣኔያቸውን ማስፋፋት ጀመሩ። እነዚህ ሳማውያን ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ ሲገቡና በአገሪቱ ከነበሩት ከኩሻውያን ጋር የተደባለቁት ይህንኑ ሥልጣኔያቸውን ይዘው በመምጣት ነው።

ነገር ግን ይህ ሴማውያን ይዘው የመጡት ሳባዊ ፊደል «ግዕዝ» ተብሎ የሚታወቀው የመጀመሪያው ፊደል ብቻ ስለነበረ በአነባብ ላይ ችግር ነበረበት። ይህ የግዕዝ ፊደል የተገኘው ወይም የተመሠረተው ከራሱ ከግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ያለው ግንኙነት ከሳባውያን ከአብራይስጥና የዐረብኛ ፊደላት ጋር ነው ይባላል። በሌላ በኩል ደግሞ ፊደሉም ሆነ ቋንቋው የሥነ ጽሑፍ መሠረት ስለሆነ ግዕዝም ራሱን የቻለ ከሴም ቋንቋዎች አንዱ ነው የሚሉ ሲኖሩ ፊደሉም የዚሁ ቋንቋ መሠረት በመሆን የተገኘ ነው በማለት አጠቃላይ ሀሳብ ይሰጥበታል። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ደግሞ የግዕዝ ፊደል ተገኘ የሚሉት በሄኖስ ዘመን ነው። ሄኖስ እግዚአብሔር አምላክን በማገልገል የታወቀ ደግ ስለነበረ ለደግነቱ

መታወቂያ ይሆነው ዘንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሥነጽሑፍና የህግ መሠረቱ የሚሆነው የግዕዝ ፊደል በጸፍጸፍ ሰማይ ተገልጦ ተጽፎ ታይቷል። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፊደልን ለሥነጽሑፍ ፣በር መክፈቻ በማድረግ ተጠቅመውበታል ስሙንም ጽሑፍ ለማለት ፊደል ብሎታል ይላሉ።

ነገር ግን ማንኛውም የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ የሆነ ፊደል ሁሉ መሠረቱ የራሱ መሆኑ እየታወቀ ፊደል ወይም የፊደል ጽሑፍ በተዓምር ተገኘ የሚለው ሀሳብ በብዙ ሊቃውንት ተደጋፊነት የለውም። ስለዚህ የግዕዝ ፊደል የተገኘው ከራሱ ከግዕዝ ቋንቋ መሆኑ አያጠራጥርም።

የድሮ ሳባውያን የፊደል ፈጠራ ሥራ የሚደነቅ ቢሆንም ለግዕዝ ቋንቋ አገልግሎት እንዲሰጥ አሻሽለው የቀረጹት አባቶች በአገሪቱ ሥነ ጽሑፍ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል።

ከላይ እንደተገለጸው ሳባዊው የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት በአንደኛው ክፍል ከ «ሀ» በመጀመር ሀ. ለ. ሐ. መ. ሠ. ረ. ሰ. ቀ. በ. ... እያለ እስከ መጨረሻው ፊደል ማለት እስከ «ፐ» ድረስ ያለው ነው። ይኸውም እንደ እብራይስጡ ፊደል እያንዳንዱ በድምፅ ሰጪ ነቁጦች ወይም ነጥቦች አማካይነት ካዕብ፥ ሣልስ፥ ራብዕ ... እየተባለ ይነበባል። ከ«ሀ» የሚጀምረው የሳባውያን (የግዕዝ) ፊደል ቁጥሩ ከ «ሀ» እስከ «ፐ» ሃያ ስድስት ፊደላት ይሆናሉ። የድምፅ ሰጭ ነጥቦች ቢጨመሩ ግን እያንዳንዱ ሰባት ፊደል ይሆናል ወይም ሰባት የተለያየ ድምፅ ይሰጣል።

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ይጠቀሙበት የነበረው የግዕዝ (የመጀመሪያው) ፊደል በመሆኑ ትርጉም አልነበረውም። ለምሳሌ አብርሃም ለማለት <u>አበረሀመ</u>፥ ዮሐንስ ለማለት <u>የሐነሰ</u>፥ ኢየሱስ ለማለት <u>አየሰሰ</u>፥ ዳዊት ለማለት <u>ደወተ</u>፥ ተብሎ ይጻፍ ነበር። ይህንንም በጥንት ሳንቲሞችና በአክሱም አካባቢ በሐውልት ላይ ተጽፈው ወይም ተቀርጸው ከተገኙት ጽሑፎች መረዳት ይቻላል።

5.3 በግዕዝ ፊደል ላይ የአናባቢ ቅጥያዎች ድርሻና ጠቃሚነት

ፍሬምናጦስ በ330 ዓ.ም. አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተብሎ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ከኩሻያውያን፥ ከሳባውያንና ከእስራኤላውያን መካከል ብዙዎች በክርስትና ሃይማኖት አምነው ተጠመቁ። ከዚያም ለክርስትና እምነት

ትምህርት መሠረት የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ቋንቋቸው እንዲተረጉሙላቸው አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን ተረዱና አሰቡበት።

ይሁን እንጂ ከላይ እንደተጠቀሰው ሳባዊ ሥነ ጽሑፋቸው በዛሬ አቀማመጡ ግዕዝ የምንለው አንደኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው ብቻ በአናጋሪነት የነበረ እንጂ ከካዕብ እስከ ሳብዕ (ከሁለተኛ እስከ ሰባተኛ) የሚያናግሩት ድምጻ ፊደላት አልነበሩትም።

በግሪክና በአብራይስጥ ተለምደው ከቆዩት የሃይማኖት ቃላትና ስሞች መራቅን እንዳያስከትል ለፊደላቱ ቅርጽና ድምፅ እንዲሰጡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሰለተገኘ ቅዱሳት መጻሕፍት በቋንቋቸው እንዲተረጐሙ የፈለጉት ሳባውያን ከፍሬምናሮስ ጋር በመመካከር በፊደላቸው ቅጥያና ድምፅ አሰጣጥ ላይ በማተኮር ያላቸውን የራሳቸውን ፊደል አሻሽለው መጻፍን መረጡ እንጂ የራሳቸውን ፊደል ትተው የውጪ አገር ቋንቋና ፊደል ሊሸምቱ አልባዘኑም። ስለሆነም ከ335 ዓ.ም እስከ 350 ዓ.ም ድረስ ባሉት አሥራ አምስት ዓመታት በሰባ ሊቃውንት የግዕዝ አናጋሪ ፊደላት ተሻሽለው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከጽርዕ (ከግሪክ) ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተረጐሙ።

ስለዚህ ጥንታዊና ባህላዊ ሳባዊ ፊደላቸው መልኩና የቅርጹ ይዘት ሳይለወጥ መደቡን እንደያዘ በቅጥያዎቹ (ቫዎሎቹ) አናጋሪነት ከካዕብ እስከ ሳብዕ (ከሁለተኛ እስከ ሰባተኛ) ድምፅ ሊያናግሩና ቅጥያ ሊያበጁ ወሰኑ። ከዚህም የተነሳ በግዕዙ (የመጀመሪያ) ፊደላት ላይ የድምፅ ሰጪ ነጥቦች በዘመኑ በነበሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ መሠረት ተጨምረው አንዱ ፊደል ሰባት የተለያየ ድምፅ ሊሰጥ ቻለ። ለምሳሌ፤

ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ

ለ ሉ ሊ ላ ሌ ል ሎ

እንግዲህ ከ ሀ እስከ ፐ ድረስ ያሉት ፊደላት በጠቅላላው 26X7 = 182 ይሆናሉ። (ሃያ ስድስት ሲባዛ በሰባት ይሆናል አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት)።

በተጨማሪም የግዕዝ ቋንቋ አናጋሪ ፊደሎች የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ

ኰ ጐ ቈ ጐ የሚባሉ እያንዳንዳቸው 5 (አምስት) ድምፅ ሰጪ ነጥቦች ያላቸው ፊደላት አሉ።

ሁለተኛው የግዕዝ ክፍል ፊደል ደግሞ እንደሌሎቹ የሴም ቋንቋዎች በ« አ» የሚጀምር ፊደል ነው። ይኸውም አ. በ. ገ. ደ. ... እያለ እስከ ፐ ፊደል ይደርሳል። ጠቅላላ የፊደሉ ቁጥር እንደ መጀመሪያው ሃያ

ስድስት ሲሆን ሰባት ድምፅ ሰጪ ነጥቦች እየቀጠሉባቸው የተፈለገውን ዓይነት ድምፅና ንባብ በመስጠት ያገለግላሉ።

ሌሎች የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት እየተባሉ የሚጠሩ ሰባት ፊደላት አሉ። እነርሱም ሸ. ቸ. ኘ. ኸ. ዠ. ጀ. ጨ. የተባሉ ሲሆኑ እንደ መጀመሪያው ክፍል ድምፅ ሰጪ ነጥቦች አማካይነት ሰባት የተለያየ ድምፅ በመስጠት ይሠራባቸዋል።

5.4 የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ለሥነ ጽሑፍ ያበረከተው ድርሻ

ፍሬምናሮስ ለጀመረው የክርስትና እምነት ትምህርት መስፋፋት ሥራ ይረዳው ዘንድ ከዘመኑ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር ተማክሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ የመተርጐምን አስፈላጊነት ሲረዳ ሥር ነቀል መፍትሄ መፈለግ ግድ ሆነበት። ስለሆነም ከላይ እንደተገለጸው የግዕዙ ፊደላት አናባቢ (ቫዎል) አለመኖር ግድግዳ ሆኖ ሥራውን በማሰናከል እቅዱ ግቡን እንዳይመታ እንደሚያደርግ በመገንዘቡ ባሉት ሃያ ስድስት ፊደላት ላይ ቅጥያ ተጨምሮባቸው የተለየ ድምፅ እንዲሰጡ አድርገዋል። በአብዛኛዎቹ የግዕዝ ፊደላት ላይ የድምፅ አናባቢነት እንዲሰጡ የተቀጠሉት ምልክቶች በግዕዝ ፊደሎቹ ላይ ከራስ፥ ከመኻል፥ ከግርጌ፥ የሚቀጠሉ ሲሆኑ አንዳንዱ ፊደል ግን ሰባራ፥ አንካሳ ሆኖ እንዲጻፍ ሲያደርጉ አንዳንዱም ራሱን እንዲያዘነብል አደረጉ።

ይህም በመደረጉ በሥነ ጽሑፍ ረገድ በቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጐም ላይ የተደቀነው ችግር ተወገደ። ከዚህም የተነሳ ፍሬምናሮስና የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን ሕዝቡ ወደሚጠቀምበት ወደ ግዕዝ ቋንቋ ሊተረጉሙ ቻሉ። ስለሆነም ግዕዝ የተሻሻለ (የታደሰ) ሳባዊ ቋንቋ ሲሆን ነፃ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ጋር አብሮ በቀል ነው ለማለት ይቻላል።

የአንድ አገር ሕዝብ ማንነት የሚመዘነው፥ ጥንታዊነቱና ሥነ ጥበቡ የሚደነቀው፥ በራሱ ፊደልና ቋንቋ እንደዚሁም በራሱ ሥነ ጽሑፍ ታሪኩ የተመዘገበ ሆኖ ሲገኝ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም በራሱ ሊቃውንት በተሻሻለና ከጥንት ጀምሮ የራሱ የሆነ ፊደል ያለው ሲሆን እነዚህንም ፊደላት ለሥነ ጽሑፍ ዕድገት፥ ለታሪክ ምዝገባ ለመጠቀም መቻሉ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው። ይህም በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ለኢትዮጵያ በጊዜው የተሰጣት ትልቅ ስጦታ ነው። ይህንንም ስንል ሰው

ድርሻ የለውም ማለት ስላልሆነ ሰውም ስጦታውን በጥንቃቄ መጠቀም መቻል ተፈላጊ ነገር ነው።

የአገሪቱ ሊቃውንት በተለያዩ ዘመናት የጻፉአቸው በርካታ መጻሕፍት የተጻፉት በዚሁ በግዕዝ ቋንቋ ነው። ለምሳሌ፥ የታሪክ፥ የፍልስፍና፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ባህላዊ አተረጓጐም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ በርካታ የቅዳሴ፥ የቅኔ፥ የዜማ፥ የአዋልድ እና የቅዱሳን ገድል የተባሉ መጻሕፍት ወዘተ. የተጻፉት በተጠቀሰው በግዕዝ ቋንቋ ነበር።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጥንታዊነትና ባህሏ፥ የነገሥታቶችዋና የሕዝቦችዋ አኗኗር እንዲሁም የአገሪቱ ጥንታዊ ሥልጣኔ ምን ይመስል እንደነበረ ለማወቅ የሚቻለው በሥነ ጽሑፍ አማካይነት በመሆኑ ለዚህ ተግባርም ትልቅ አስተዋፅዖ ያደረገው የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ነው። በአሁኑ ጊዜ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ የታሪክ፥ የሕግ፥ የግጥምና፥ የሰዋሰው፥ የፍልስፍናና የመድሃኒት ቅመማ ወዘተ. መጻሕፍት የተጻፉትና የተዘጋጁት በግዕዝ ፊደል ነው።

ይሁን እንጂ ይህ የግዕዝ ፊደል ቅርጽ ይዘትና መልክ የያዘው ፍሬምናጦስ በሕይወት እያለ ሲሆን ይህም በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መካከል በ442 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ በተለይም በዲዮስቆሮስና በልዮን የሀሳብ ልዩነት ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በመባባል አለመግባባት ተፈጥሮ ለሁለት ከመከፈላቸው በፊት ስለነበረ በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ክርስቲያን ተብሎ በሚጠራበት ወቅት ነበር። ነገር ግን ዘመናት እየጨመሩ ሲሄዱ ሰይጣንና «እኔ ያልኩት ካልሆነ» የሚል የግለሰቦች ሥጋዊ እልከኝነት እየተስፋፋ ይህንን እውነት በማዛባት የስህተት አሠራር ሊሰፍን ችሎአል።

አሁንም በኢትዮጵያ የፊደልና የቋንቋ አጠቃቀም ሪገድ ሊተኮርበት የሚገባ ስለሆነ ከውጪ አገር የላቲን ፊደል ለመሸመት ከመሄድ ይልቅ ከዛሬ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዓመታት ገደማ በፊት በኛው ሰዎች ከላይ በተገለጸው መሠረት ብዙ ተደክሞበት ተሻሽሎ ሲሠራበት እስካሁን የቆየውን የግል መጠሪያችን፥ ሀብታችንና ንብረታችን የሆነውን ሳባዊ የግዕዝ ወይም በጥቅሉ የኢትዮጵያችንን ፊደልና ቋንቋ ባሉን ምሁራን የበለጠ አሻሽለን አስፈላጊ ከሆነ ቅጥያ በሚያስፈልገው ጨምረን የሚቀነስም ካለ ቀንሰን ካልተጠቀምን ውሎ አድሮ ግብጾች የራሳቸው የነበረውን ፊደልና ቋንቋ (ቅብጥን) በዐረብ ተጽዕኖ ትተው ዛሬ በዐረብኛ በመጠቀማቸው ቋንቋቸውና ፊደላቸው ሞቶ እንደተቀበረው ዓይነት እንዳይሆን ያሰጋል።

በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የተስፋፋው የአማርኛ ቋንቋም ፊደላቱን የወሰደው ከሳባዊ ወይም ከግዕዝ ቋንቋ ስለሆነ የቃላቱ መሠረት ያው ከግዕዝ ይፈለጋል። ስለዚህ ከላይ እንደተብራራው የግዕዝ ቋንቋና ፊደሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኔ አሻራ ስለሆነ ልንከባከባቸውና ልንገለገልባቸው የሚገባ ነው። በተለይም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ቋንቋዎች እየተተረጐሙ ጥቅም ላይ እየዋሉ እንዳሉ ሁሉ በትምህርት መጻሕፍት ረገድም በተመሳሳይ መንገድ እንደ አስፈላጊነቱ የግዕዝን ፊደል መጠቀም ቢቻል ሲሠራበት የቆየና የተለመደም በመሆኑ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም።

6. የአጎዝ እና የቁጥር ስልት በኢትዮጵያ

አብዛኛዎቹ የዓለም ሕዝቦች የሚጠቀሙበት አጎዝ ወይም የቁጥር ስልት የዐረብኛ መሆኑ ግልጽ ነው። በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዛት የሚሠራበት ይኸው የዐረብኛው ቁጥር ነው።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሳባውያኑ የግዕዝ ፊደል ከፍ ባለው ክፍል በተገለጸው መሠረት ለሥነ ጽሑፍ አሠራር አመቺ እንዲሆን ቅጥያዎች ተጨምረው መልክና ሥርዓት ባለው ሁኔታ በተዘጋጀበት ወቅት ከዚሁ ሥራ ጐን ለጐን የተሠራው ሥራ የቁጥር ስልት ነው።

ይህም ቁጥር ከአንድ እስከ ቢሊዮን የሚደርስና ከዚያም በላይ በሚያልፍ የቁጥር መንገድ ወይም ስልት የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነበር። በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዘመናት ሲጠቀምበት የቆየ ሲሆን አሁንም ከዐረብኛው ቁጥር ጐን ለጐን እየተሠራበት ይገኛል።

ለምሳሌ፥ ከ፩ እስከ ፱ ቁጥር በኢትዮጵያ በቁጥር ስልት (ከአንድ እስከ አንድ መቶ)

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲ ፲፩ ፲፪ ፲፫ ፲፬ ፲፭ ፲፮ ፲፯ ፲፰ ፲፱ ፳ ፳፩ ፳፪ ፳፫ ፳፬ ፳፭ ፳፮ ፳፯ ፳፰ ፳፱ ፴ ፴፩ ፴፪ ፴፫ ፴፬ ፴፭ ፴፮ ፴፯ ፴፰ ፴፱ ፵ ፵፩ ፵፪ ፵፫ ፵፬ ፵፭ ፵፮ ፵፯ ፵፰ ፵፱ ፶ ፶፩ ፶፪ ፶፫ ፶፬ ፶፭ ፶፮ ፶፯ ፶፰ ፶፱ ፷ ፷፩ ፷፪ ፷፫ ፷፬ ፷፭ ፷፮ ፷፯ ፷፰ ፷፱ ፸ ፸፩ ፸፪ ፸፫ ፸፬ ፸፭ ፸፮ ፸፯ ፸፰ ፸፱ ፹ ፹፩ ፹፪ ፹፫ ፹፬ ፹፭ ፹፮ ፹፯ ፹፰ ፹፱ ፺ ፺፩ ፺፪ ፺፫ ፺፬ ፺፭ ፺፮ ፺፯ ፺፰ ፺፱ ፻ ፼ ፽

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 20 30 40 50 60 70 80 90 100

እያለ እስከ ሚሊዮንና ቢሊዮን ድረስ የሚደርስ በቁጥር ስልት የተገኘውም ከላይ እንደተገለጸው በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አማካይነት ነው።

7. የኢትዮጵያ የዓመታት አቆጣጠር፥ የዕለታትና የአውራኅ (ካሌንደር)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር የታሪክ፥ የሃይማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው፥ በኢትዮጵያ ራሳቸውን የቻሉ ልዩ ልዩ ጥንታውያን ባህሎች እንዳሉና እነዚህም ጥንታውያን ባህሎች ሊገኙ የቻሉት በቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ጥረት እንደሆነ ያብራራል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ካስገኘቻቸው ባህሎች መካከል የሚያስደንቀው ራሱን የቻለ የዘመን አቆጣጠር ስልትና ሥፍረ-ሰዓት በኢትዮጵያ መኖሩ ነው ይላል። በጽሑፉ ላይ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር (ካላንደር) ልዩ የሆነውንና ጥንታዊውን ስልት ይዞ የሚጓዝ ሲሆን ይህም ጥንታውያን አገሮችና አብያተ ክርስቲያናት ይሠሩበት እንደነበረ ይጠቅሳል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ጥንታውያን ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናትም ተለይታ በዚህ እጅግ ጥንታዊ በሆነ የዕለታትና የዘመናት አቆጣጠር በመጠቀም ላይ ትገኛለች።

በዚህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት አቆጣጠር መሠረት ይህ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለው ዘመን (7492 - ሰባት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት) ዘመን (ዓመታት) ይሆናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለው ዘመን 1992 ዓመት ሲሆን አዳምና ሄዋን ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጌታ ልደት ድረስ ደግሞ (አምስት ሺ አምስት መቶ) ዘመን ነው ይልና ይህም ዓመተ ፍዳ (ኵነኔ) ሲባል ከጌታ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ሥጋዌ (ዓመተ ምሀረት) ይባላል። ሁሉም ግን ዓመተ ዓለም ይባላል ይላል።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር በአንድ ዓመት ውስጥ አሥራ ሁለት ወራት ሲኖሩ በየወሩ እኩል ሠላሳ ቀናት አሉ። አሥራ ሁለቱ ወራት ከመስከረም እስከ ነሐሴ 30 ቀን ሲሆኑ በነሐሴ ወር መጨረሻና በመስከረም ወር መግቢያ እንደ አንድ ወር የሚቆጠሩ አምስት ቀናት ያሉበት ወር <u>ጳጉሜን</u> ይባላል። በየአራተኛው ዓመት ግን ጳጉሜን ስድስት ቀናት ይኖሩታል። ይህም ዘመነ <u>ሉቃስ</u> ተብሎ ይጠራል። በዘመነ ሉቃስ

የዓመቱ ቀኖች (ሦስት መቶ ስድሳ ስድስት) ሲሆኑ በዘመነ ማቴዎስ ማርቆስና ዮሐንስ ግን (ሦስት መቶ ስድሳ አምስት) ናቸው።

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ሰባት ዓመት ወደ ኋላ ይዘገያል። ለምሳሌ ያህል አሁን ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ዘመን በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1992 ዓ.ም ሲሆን በአውሮፓውያኑ 1999 - 2000 መሆኑ ነው። የእያንዳንዱ ወር አከፋፈል በሠላሳ ቀን ስለሆነ የአውሮፓውያን የቀን አቆጣጠር በየወሩ ከሰባት እስከ አሥር ቀን ይቀድማል። ይህም ማለት የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ከአውሮፓውያን የቀን አቆጣጠር ከሰባት እስከ አሥር ቀናት ወደ ኋላ ይዘገያል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ መስከረም 1 ቀን 1992 ዓ.ም በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሴፕተምበር 12 - 1999 ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ የአውሮፓውያኑ ዘመን መለወጫ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ታህሣሥ 22 ቀን 1992 ዓ.ም ሲሆን በአውሮፓውያኑ ግን ጃኑዋሪ 1፥ 2000 ነው። ይህም የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ከተከበረ ከሦስት ወር ከሃያ ሦስት ቀን በኋላ መሆኑ ነው።

8.1 ሃሳበ ዘመን በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የዘመናት፥ የዓመታት፥ የወራት፥ የሳምንታት፥ የዕለታት፥ የሰዓታትና የደቂቃ ጊዜያት የተዘጋጀው በግብፃዊው በዮሐንስ አቡሻክር ስለሆነ የእርሱ የሃሳብ አቀራረብ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ዝነኛና የተወደደ በመሆኑ የሃሳበ ዘመን ድንጋጌም በዚሁ ሊቅ ስም ተጠርቶአል። እርሱም ይህንኑ ያዘጋጀበት ዘመን ከ1240-1250 ዓ.ም ነው።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንደ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ አድርጋ በተቀበለችው ዕዝራ ሱቱኤል ም፬. 13፥10-13 እንደተገለጸው የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር «ዘመነ ዓለም» የሚጠራበት ጊዜም እንዳለና ይህም የሰው ልጅ ማለት ዓለመ አዳምን በሚመለከት ታሪክ የሚቆጠረው የዘመን አቆጣጠር የተሰጠው ስያሜ እንደሆነ ተገልጸአል።

በተጨማሪም በሰንክሳር ላይ ከተገለጸው ሌላ ከ200-224 ዓ.ም ገደማ የነበረው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ድሜጥሮስ በዐላትንና አጽዋማትን ለመወሰን ጊዜያቸውን ለማስተካከልና የቁጥር ሕግ ለመወሰን ተመኝቶ ሱባዔ ገብቶ ተገልጦለታል፤ ይህም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ሲሠራበት ቆይቷል የሚሉ አፈ ታሪኮችም አሉ። በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሃሳበ ዘመን አመጣጥ ከፋርስ፥ ከአሰራኤልና ከእስክንድርያ እንደሆነም ይገመታል።

ከላይ እንደተገለጸው የዓመተ ዓለም አቆጣጠር በሰባ ሊቃናት በተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ 5500 ዓመተ ዓለም መሆኑ ተጠቅሶአል።

8.2 ስምንተኛው ሺ የተባለው ዘመን

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንደተጠቀሰው አፄ ናኦድ «ስምንተኛው ሺ አታድርሰኝ» እያለ ሲጸልይ ቆይቶ ስምንተኛው ሺ መስከረም ሊገባ ሲል ነሐሴ 7 ቀን ስለ ሞተ ጸሎቱ ተሰማለት ተብሎ ተጽፎአል። ይህም ቀመር ከላይ ከተጠቀሰው 5500 ጋር ሲደመር እንደሆነ ታውቆአል።

በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ድጋፍ በተፃፈው «መጽሐፈ ሚላድ» ገጽ 110 ላይ «ክርስቲያናዊ ሰው ሆይ፥ ዳግመኛ ይህን ስማ ከ7000 (ከሰባት ሺ) ዓመት በኋላ በቀመር የማይቆጠር ብዙ ዓመት በዚህ ዓለም አለ የሚሉ ውሸተኞች ናቸው» ይላል። ምክንያቱም «'በስምንተኛው ሺ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል» ተብሎ በብዙ ባህታውያን ሲነገርና ሲጻፍ እንደነበረ ታውቆአልና ነው። ስለዚህም መጽሐፈ ሚላድ የነሐሴ 29 ቀን ምንባብ ገጽ 30 ላይ ከአዳም እስከ ክርስቶስ 5500 ዓመት መሆኑንና ስምንተኛው ሺ ዘመን መግቢያው ሰባተኛው ሺ መቆጠር ሲጀምር እንደሆነ በማሳየት 1500 ዓ.ም የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ብለው አስተምረዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን አባባል አይደግፈውም። ምክንያቱም የመጨረሻውን የዓለም ፍጻሜ ማንም እንዲያውቅ ሥልጣን አልተሰጠውም።

ይህን አስተሳሰብ የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ የሚኖርበት ዘመን ግለትም ምድራዊ የሰው ዝርያ ሕይወት የሚያበቃበት ዘመነ አዳም ሰባት ሺ ዓመት የዓለም መጨረሻ ነው ብለው ከወሰኑ ከድሮዎቹ ሠራዕነ ሕግ ፍልስፍና ጋር ሀሳባቸውን በማስማማት እንደሆነ ታውቆአል። ይህንንም አስተሳሰባቸውንና እምነታቸውን ያልተቀበለውን በመንቀፍና በማሳደድ ተጽዕኖ ያደርጉበት እንደነበረ ታሪክ ይዘግባል።

የሳይንስ ሊቃውንት የሰው ዝርያ በምድር ላይ መኖር ከጀመረ 5 ሚሊዮን ዓመታት ሆነዋል ስለሚሉ፤ ምናልባት ይህንን አስተሳሰብና አባባል ስንመለከት ዛሬ እንደቀላል ነገር እንቆጥር ይሆናል። ነገር ግን በዚያን ዘመን የነበሩት ሰዎች በግድም ሆነ በውድ ይህንኑ የግለሰቦችን ሀሳብ በማመንና በመቀበል ኖረዋል። እኛስ በዚያን ዘመን ብንኖር ኖሮ ምን እናደርግ ነበር? አሁንስ ቢሆን አንዳንድ ሰዎች ከእውነት የራቀ የውሸት ተረት ሊግቱን ሲሞክሩ ምን ምላሽ እንሰጣለን? ለመኖር ያህል አሜን ብለን እንቀበላለን? ወይስ መጠየቅ ዋጋ የሚያስከፍል እንኳን ቢሆን እንዴት? እና ለምን? ብለን እንጠይቃለን?

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታህሣሥ 29 ስለ መከበሩ የተጠቀሰ ሀሳብ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሚያከብሩበት ወርና ቀን አታከብርም። ይኸውም ከእስክንድሪያ አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር በተመሳሳይ ቀን እንደምታከብርና ለብዙ ዘመናት በዚሁ አኳኋን ስታከብር መኖርዋን በአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ «ሃሳብ ዘመንና ታሪኩ» በሚል ርዕስ በተጻፈ መጽሐፍ ላይ ተገልጾአል። ይህንንም ታህሣሥ 29 ቀን በልደት በዐልነት እንዲከበር የነገሩን ምንጭ አጥንቶ ያቀረበው የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አቤል ሄሬም እንደሆነ በአቡሻከር አንቀጽ 64 መጠቀሱም ተመልክቶአል።

ከዚሁ ጋር በተጨማሪ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀንም ሆነ የዘመን መለወጫ መስከረም 1 ቀን መሆኑ የተቀመረውም ከዮሐንስ መጥምቁ የመፀነስ ብሥራት ጀምሮ እንደሆነ ታውቆአል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ዘመን መለወጫና ስለ ጌታ ልደት በዓል እንደማስረጃነት የምትቀበለው «በአንተ ልደት ድንግላዊ» በሚል ርዕስ የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አቤል ሄሬም የጻፈውን ጽሑፍ ሲሆን በዚሁም ጽሑፍ መጥምቁ ዮሐንስ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የመንገድ ጠራጊና በፊቱ የሚሄድ መልዕክተኛ ስለመሆኑ በነቢያት የተነገረ እንደሆነ ይገልጻል። (ኢሳ. 43፥5 ሚልክ. 3፥1)

በዚሁ መሠረት መጥምቁ ዮሐንስ የተፀነሰበት ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማኅፀን ለተፀነሰበትና ለተወለደበት ቀን መነሻ ሆኖ ቀርቦአል። ይህንኑ ወንጌላዊ ሉቃስ ከጻፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ለአብነት ያቀርባሉ።

«በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር፥ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበር። (ሉቃ. 1፥5) እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ይጸልይ ነበር። የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካርያስ ባየው ጊዜ ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት። መልአኩም እንዲህ

አለው ፦ ዘካርያስ ሆይ፡ ጸሎትህ ተሰምቶአልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ተድላም ይሆንልሃል። በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል ...» ይላል። (ሉቃ. 1፥8-15)

መልአኩ ገብርኤል ለዘካርያስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ያበሠረበት ቀን በዕብራውያን ዘንድ (በዓለ ሥርየት) ተብሎ ይከበር የነበረ ቀን ነው። በታሪክ (ጥቅምት 10ኛው ቀን የሚውል ታላቅ በዓል ነበር። ይኸውም በአሪት ሕግ (በሰባተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን ራሳችሁን <u>አስጨንቁት</u>። ያገር ልጅም በእናንተ መካከል የተቀመጠ እንግዳም ሥራ ሁሉ አትሥሩበት በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢአታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ። ታላቅ ሰንበት ይሆንላችኋል ራሳችሁንም ታዋርዳላችሁ ... ይላል። ዘሌ. 16፥29-34፤ 23፥27-32፤ ዘኍ. 29፥7-11።

ከላይ እንደተጠቀሰው ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በዕብራውያን ዘንድ ታላቅ በዓል የሆነው በዓለ-ሥርየት የሚከበርበት ቀን በተለየ ሁኔታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተወለደበት ቀን ታሪካዊ የአጎዝ መነሻና የመሠረት ድንጋይ መሆኑን እየጠቆመ አሳይቶአል ይላል ከአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ የተጻፈ ሃሳበ ዘመንና ታሪኩ በገጽ 155 ላይ።

ይህም ዘካርያስ የተበሠረበት ቀን በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር ጥቅምት አሥር ቀን ለመሆኑ በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዮሐንስ አፈወርቅና ማር ዮሐንስ ወንጌለ ሉቃስ ምዕራፍ አንድን ሲተረጉሙ ሰፋ ባለ ሐተታ እንደገለጹት ተብራርቶአል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ መተርጉማን ስለ ዘመን መለወጫ መስከረም አንድ እና ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ቀን ታህሣሥ ሃያ ዘጠኝ አከባበር ሲወርድ ሲዋረድ በተወራረሰ የሊቃውንት ትርጓሜ መልአኩ ገብርኤል ለዘካርያስ ዮሐንስ መጥምቁን እንደሚወልድ ያበሠረበትን ቀን መሠረት በማድረግ እንደቀመሩ ይጠቁማል።

ስለዚህም ከላይ የተጠቀሰው ከአዳም እስከ ክርስቶስ የተቀመረው የአምስት ሺ አምስት መቶኛ ዓመተ ዓለም ከነዚህ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በተሰጠው ስመ ተጸውዖ ዘመነ <u>ዮሐንስ</u> ይባላል። የዘመን መለወጫ አዲሱ ቀን ወይም ርዕሰ ዐውደ ዓመቱ ዕለት (ቅዱስ ዮሐንስ) የጨረቃ አወጣጥ ሠረቀ ሌሊት ... በሚባሉ የራሳቸው የዘመን መቀመሪያ ስሌት ያመጡታል።

በዚህም ቀመራቸው ሊቃውንቱ መልአኩ ገብርኤል በናዝሬት ወደምትኖር ወደ ድንግል ማርያም ተልኮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን

እንደምትጸንስና እንደምትወልድ ያበሰራት በኢትዮጵያ አቆጣጠር መጥምቁ ዮሐንስ ከተወነሰበት ዕለት ጀምሮ ስድስት ወር ሲቆጠር መጋቢት 29 ቀን ነው ይላሉ። በዚህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሐንስ መጥምቁ የመወለድ ብሥራት ጀምሮ ሲቀመር መጋቢት 29 ቀን ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተጸንሶ ታህሣሥ 29 ቀን በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በቤተልሔም በረት እንደተወለደ ተገልጾአል። ስለዚህም ዘካርያስ የተበሰረበትን ቀን ኮከባዊ ቀን ነው በማለት ፋናውን እየተቆጣጠረች በመከታተል የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል እንዳደረሳት በማመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታህሣሥ 29 ቀን በታላቅ ምሥጋና ታከብራለች ይላል ሃሳበ ዘመንና ታሪኩ።

በዲድስቅልያ አንቀጽ 29 ገጽ 37 ላይ «የመጀመሪያው በዐል የክርስቶስ ልደት ነው። ይኸውም በዕብራውያን አቆጣጠር በዘጠነኛ ወር በ25ኛው ቀን እርሱም በግብፃውያን አቆጣጠር ታህሣሥ 29 ቀን ታደርጋላችሁ» ተብሎ ተወስኖአል።

ይቤ ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ የተባለ ሊቅ ከአዳም እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የተቀመረው ቁጥር 5500 ዓመት መሆኑንና ቅድስት ድንግል ማርያም መጋቢት 29 ቀን ፀንሳ ታህሣሥ 29 ቀን ማለት በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደወለደችው ገልጾአል።

በተአምረ ማርያም የዘወትር መቅድም ላይ ስለ ሠላሳ ሦስቱ የማርያም በዐላት አከባበር ሲገልጽ ቁጥር 17 ላይ <u>ታህሣሥ 28 ቀን ማርያም ጌታን የወለደችበት</u> ይልና <u>ታህሣሥ 29 ደግሞ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችበት ቀን ነው ይላል</u>። ጌታ ኢየሱስ የተወለደው ታህሣሥ 28 ወይስ ታህሣሥ 29 ነው? ወይስ በዓሉ ታህሣሥ 28 እና 29 እንዲከበር ብቻ ታስቦ ነው? ለዚሁ ይሆናል በአገራችን ስለዚህ በዐል አከባበር ከአፄ ሠይፈ አርዕድና ከእጨጌ ፊልጶስ ዘመን ጀምሮ የጌታ ልደት ታህሣሥ 28 ወይስ 29 ይሁን የሚል ጭቅጭቅ ብዙ ባህታውያንን ጭምር ሲያበጣብጥ እንደነበረ የሚነገረው። በዚህ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረዥም ጊዜያት ጠብ እየተነሳ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ፥ ከመቀራረብ ይልቅ መራራቅን ፈጥሮአል። መሠረተ ነገሩ ሲታይ ግን ጉዳዩ የሚያቃቅርና የሚያጣላም አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም የተወለደውና ሥጋ ለብሶ የመጣው በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ፍቅር የተለየውን የሰው ልጅ ወደ ቀደመው ክብሩ ለመመለስና የሰውን የሞት ዕዳ ለመክፈል እንጂ ጥላቻ ለመዝራት አይደለም።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ ከመራራቅና ከመለያየት ይልቅ መቀራረብን፥ በጠላትነት ከመተያየት ይልቅ የወንድማማች ፍቅርን በማነልበት፥ የሰይጣንን ሥውር ሴራ ቢያከሽፉና እግዚአብሔርን ቢያከብሩ ተልዕኮአቸውን ፈጸሙ ማለት ነው። ይህ ካልሆነ ግን «ስም አለህ ነገር ግን ሞተህማል» (ራዕይ 3፥1) ያለው ይፈጸምባቸዋል። ምክንያቱም በስም ክርስቲያን በተግባር ግን ሌላ የሆነ ማለት ነው።

10.1 የዘመን መለወጫ (ርዕሰ ዐውደ ዓመት)

በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ርዕሰ ዐውደ ዓመት የሚቆጠረው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ ሲሆን የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ግን እስከነ ስሙ ቅዱስ ዮሐንስ በመባል በቤተ ክርስቲያን የዘመናት ቀመር መሠረት በዮሐንስ መጥምቁ ጽንስና ልደት ይቀመራል። ይህም መስከረም 1 መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በበኩላቸው የአውሮፓውያኑ ዐውደ ዓመት ጥንት ጣዖቶቻቸውን ያከብሩ የነበረ ዕለት ስለሆነ የኛ ነው ትክክለኛው ዐውደ ዓመት ይላሉ።

የዘመን መለወጫ ወይም ርዕሰ ዐውደ ዓመት (ዓ.ም.) መቆጠር ያለበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ መሆን ሲገባው የኢትዮጵያ ሊቃውንት ለምን ከዮሐንስ መጥምቁ ልደት እንደ ቀመሩት ዝርዝሩ ከዚህ በላይ ተጠቅሶአል። ቀመር ማለት የተወሰነ ቁጥር የያዘ ሀጋዊ መለኪያ ወይም በልክ እየሆነ የተደነገገ የቁጥር መደብ የሚል ፍቺ አለው።

ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምህረት ይባላል። ይህም ሰው በምህረትና በአምላካዊ ቸርነት የሚኖርበት የጸጋ «ዘመነ ብሥራት» «ዘመነ ወንጌል» ነው። ዓመተ ምህረት ትንቢት ተነግሮላት፥ ሱባዔ ተቆጥሮላት በቀጠሮ ስትጠበቅ የቆየች ናት እንጂ እንዳጋጣሚ የደረሰች እንግዳ ዘመን አይደለችም። በነቢዩ ኢሳይያስም ትንቢት «የተመረጠችውን የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል።» ይላል (ኢሳ. 61፥2፤ ሉቃ. 4፥17-21) ይህም የሚገልጸው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ስለወንጌል የምስራች ቃል ነው። በተጨማሪም በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመድሃኒትም ቀን ረዳሁህ ተብሎ ተጠቅሶአል። (ኢሳ. 49፥6፤ 55፥3-6፤ 2 ቆሮ. 6፥2 ኤር. 31፥31-34)

መልአኩም እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ። ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ሲል የጌታን ልደት አስታውቋል። (ሉቃ. 2፥10-11)

ስለዚህ ለዓመተ ፍዳና ለዓመተ ኩነኔ ማክተሚያና መደምደሚያ የሆነው የክርስቶስ ልደት እንጂ የዮሐንስ መጥምቁ ልደት አይደለም።

የዕለታትን አቆጣጠር በተመለከተ ዐውደ ዕለታት የሚባሉት ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ያሉ ሰባት ዕለታት አውራጎንን (ወሮችን) ለማስገኘት በዚህ አቋም ሲመላለሱ ይኖራሉ። እነዚህም ሰባት ዕለታት ከጥንት ሥነ ፍጥረት ታሪክ ጀምሮ በዚሁ ስምና መደብ ቀመር ሆኖ እናገኛቸዋለን። ዐውደ ወርኀ (ወር) ዘወትር በፀሐያዊ ቀን ሠላሳ ሠላሳ እየሆኑ በጨረቃ ግን አንድ ጊዜ ሠላሳ፥ ሁለተኛው ሃያ ዘጠኝ በመሆን እየተፈራረቁ ዓመታትን ለማስገኘት በዚሁ አቋም ሲመላለሱ የሚገኙበት ነው።

ዐውደ ዓመት የሚባለው በፀሐያዊ ቀን አቆጣጠር 365 1/4 በጨረቃ 354 እየሆኑ የዓመትን ሙሉ ዑደት (ዙር) የሚያስገኝ ነው። ወራቱ በፀሐያዊ ዕለት ተቀምረው በ30 በ30 እየሆኑ አሥራ ሁለት ወራት ሲሆኑ አምስት ቀን ከሩብ ደግሞ ጳጉሜን ተብላ ትጠራለች። ይህ አቀማመር ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የምትጠቀምበት እንዲሁም ዓመተ ኖኅ በሚል ዘይቤ ሊነገርለት የቆየ የኢትዮጵያና የግብፅ (የምስር) ጥንታዊ ባህል መሆኑ ከዚህ በላይ የተገለጸ ነው።

የዓመቱ ዐውደ ዕለታት ሃምሳ ሁሉት ናቸው። ይህም የሚያሳየው መጀመሪያ የሳምንት ዕለታት ሰባት እንደመሆናቸው መጠን በአንድ ዓመት ውስጥ ሃምሳ ሁለት ጊዜ እየተመላለሱ ስለሚገኙ ሃምሳ ሁለት ሱባዔ ዕለታት ይባላሉ። ይህም ወደ ዕለታት ዝርዝር ሲተነተን (52X7 = 364) ቀን ይሆናል። ለአራቱም ወቅቶች ቢከፈል (364÷4 = 91)። ዘጠና አንድ ዘጠና አንድ ቀን ይደርሳቸዋል ማለት ነው።

10.2 የአራቱ ወቅቶች (ክፍለ ዘመናት) አቀማመር

1ኛ) ከመስከረም 26 እስከ ታህሣሥ 25 ዘመነ መፀው (ጥቢ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።

2ኛ) ከታህሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ዘመነ ሀጋይ (በጋ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።

3ኛ) ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ዘመነ ፀደይ (በልግ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።

4ኛ) ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ዘመን ክረምት ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።

ይሁን እንጂ 91X4 = 364 ስለሆነና የዓመቱ ቀኖች ግን 365 1/4 ስለሆኑ ሊቃውንቱ ሲቀምሩ ሠላሳ ሰዓት ይጐድላል፤ በአራቱ ክፍለ ዘመናት 91÷ 91 ቀናት እየሆኑ ቢመደቡም በእያንዳንዳቸው የሰባት ሰዓት ተኩል ጊዜ ትርፍ አለባቸው። እነዚህ ሰዓቶች ማለትም (7.30X4 = 30 ሰዓት) ሲሆን ይኸው ተደምሮ 364 ቀን ሲደመር ሠላሳ ሰዓት (አንድ ቀን ከስድስት ሰዓት) = 365 1/4 ቀን ይሆንና ፍጹም ዐውደ ዓመት ያስገኛል። የየዓመቱ ስድስት ሰዓት (የዕለት ሩብ ደግሞ በአራት ዓመት 24 ሰዓት ወይም አንድ ዕለት ስለሚሆን በየአራተኛው ዓመት 366 ቀን እንዲሆን ያደርገዋል። ስለሆነም በአራቱም ክፍለ ዘመናት የመፀውና የሀጋይ የፀደይና የክረምት ወቅቶች የአየር ጠባይ ከተመደቡባቸው ወራት እንዳይፋለሱ ይጠበቃሉ። ይህም ለዓመተ ወንጌላውያኑ መነሻ መሠረት ነው። ዓመተ ወንጌላውያን የሚባለውም እንደሚከተለው ነው፤

1ኛ) ዘመነ ዮሐንስ፥ ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 5 ቀን ነው።

በዚህም 365 ቀን ከስድስት ሰዓት (የዕለት ሩብ) ይገኛል።

2ኛ) ዘመነ ማርቆስ፥ ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 5 ቀን ነው።

በዚህም 365 ቀን ከስድስት ሰዓት (የዕለት ሩብ) ይገኛል።

3ኛ) ዘመነ ማርቆስ፥ ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 5 ቀን ነው።

በዚህም 365 ቀን ከስድስት ሰዓት (የዕለት ሩብ) ይገኛል።

4ኛ) ዘመነ ሉቃስ፥ ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 6 ቀን ነው።

በዚህም 366 ቀኖች ይገኛሉ። ዓመተ ወንጌላውያኑ በዚህ ሁኔታ ሲመላለስ ይኖራል። መፋለስ እንዳይገጥመውም ርእሰ ዐውደ ዓመቱ (ዕለተ ዮሐንስ) የሚባለው የሚውልባቸው ቀኖች ይቆጣጠርለታል።

10.3 መስከረም 1 ለምን «ርዕሰ ዐውደ ዓመት» ተባለ?

ርዕሰ ዐውደ ዓመት ወይም የዘመን መለወጫ መስከረም 1 ቀን ለምን ይሆናል? ሶለቱስ ለምን ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል? ቀመሩ እንደሚከተለው ተመልክቷል።

መስከረም 1 ርዕሰ ዐውደ ዓመት መሆኑና ዕለቱ ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ መሰየሙ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሆኖ ጥንታውያን ሕዝቦች የሚታየውን የወቅቶች ልዩነትና የአየር ጠባይ መፈራረቅ አይተው የሃሳብ ወሰን በማድረግ እንደሚጠቀሙበት የኢትዮጵያም ሊቃውንት ከዮሐንስ መጥምቁ ጀምሮ ሲቀምሩ የተገኘው መስከረም 1 ስለሆነ ይህንኑ የዘመን መለወጫ ርዕሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ እንዲጠራ ወስነው እየተሠራበት ይገኛል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የዐውደ ዓመቱ የመጀመሪያ ቀን መስከረም 1 እንዲሆን ሲወስኑ ለዘመነ ወንጌል የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው የሚሉት የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ አንድን ነው። በዚህም «የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል» መጀመሪያ እነሆ መንገድህን የሚጠርግ መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ። የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ።» እያለ በምድረበዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ እንደተነገረ የሚጠቅሱት ዮሐንስ በምድረበዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ሥርየት እየሰበከ መጣ የሚለውን ነው። (ማር. 1፥14፤ ኢሳ. 40፥3-4)

የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል በር ወይም መነሻ በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አበው የበዐላትን ድንጋጌ በወሰኑበት ወቅት ነቢየ ልዑል የተሰኘው ሰው የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰቢያ በዐል የኢትዮጵያ ርእሰ ዐውደ ዓመት በሚሆን በመስከረም አንድ ቀን እንዲከበር አደረገ።

ይህም የልደቱን መታሰቢያ ቀደም ሲል ከሐምሌ አራተኛው ቀን ወደ ሰኔ ሠላሳ ቀን እንዳደረጉት ሁሉ ይህንንም በዐል የሥራውን ምስጢር አንፀባርቆ ሊያሳይ ይችላል በማለት በርዕሰ ዐውደ ዓመቱ ሊከበር እንደሚገባ አስበው ያደረጉት ነው እንጂ በሰማዕትነት የተገደለበት ቀን ይኸው በመሆኑ አይደለም ተብሎአል።

ይህም ሁኔታ በሰፊው ታትቶ የተጻፈው በድርሳነ ዮሐንስ መጥምቅና በቅዱስ ያሬድ «ብፁዕ አንተ ዮሐንስ» በሚባሉ የዮሐንስ ድጓና የዜማ መጻሕፍት እንዲሁም «ውስተ ርእሰ ዐውደ ዐመት ተጽሕፈ ተዝካርከ» የዓውደ ዓመት ራስ በሚሆን ቀን መታሰቢያ እንዲደረግ ተጻፈ በሚባሉት መጻሕፍት ነው። ስለሆነም የዘመን መለወጫ የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ወይም ርዕሰ ዐውደ ዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል። ይህም በሃሳበ ዘመን ሊቃውንት አጠራር ዕለተ ዮሐንስ ተብሎም ይጠራል። ስለዚህ የዓመተ ምህረት ጅማሬ በክርስቶስ መሆኑ እየታወቀ የኢትዮጵያ ሊቃውንት

የዘመኑ ቀመር ከምህረት ባለቤት ከክርስቶስ ልደት ጋር በተያያዘ መልኩ አለመቀመራቸው በዘመን አቆጣጠር ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እውነታ ላይም ጥያቄ ምልክት ሳያስቀምጥ የሚቀር አይደለም። ይህንን የመሰለ የዘመናት ቀመር የሚያውቁ ሊቃውንቱና ምናልባትም ሌሎች ጥቂቶች የቤተ ክህነት ሰዎች እንጂ ሰፊው ጎብረተሰብ ስለማያውቀው እውነተኛውን ታሪክ ለሚገልጡ ምሁራን ፈንጠቅ፥ ገለጥ ማድረጉ ለጥናት ይጋብዛልና የበለጠ ተጠንቶ ትክክለኛው ሀሳብ ቀርቦ ለንባብ ቢበቃ የሚከፋ አይደለም። ምክንያቱም የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከአጠቃላዩ እውነታና ከሌላው ዓለም እስከ መቼ ተለይቶ ሊቆይ ይችላል?

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን (ውል) ለዓለም ሁሉ

11.1 የቃል ኪዳን አስፈላጊነት

ቃል ኪዳን ወይም ውል በሁለት ወገኖች መካከል ለተደረገ ስምምነት ማጽኛ የሚቆም መተማመኛ መሠረት ነው። ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎችም በአንድ መሠረታዊ ነገር ላይ ሲስማሙ ነገሩን ለማጽናት በመካከላቸው ውል ይዋዋላሉ። ቃል ኪዳን የሚለው ቃል በግዕዝ ቋንቋ «ተካየደ» ከሚለው ጋር ዝምድና ያለው ነው። ትርጉሙም ተዋዋለ ወይም ተማማለ እንደማለት ነው።

እግዚአብሔር ዓለሙንና መላ ፍጥረቱን የሚያስተዳድረው በቃል ኪዳን (በውል) ሥርዓት ነው። በማናቸውም ቃል ኪዳን (ውል) ውስጥ የቃል ኪዳን (ውል) ሰጪ፥ ውል ተቀባይ፥ የውሉ መቀበያ ምልክት (ማህተም)፥ የቃል ኪዳኑ ተስፋ እንዲሁም የተስፋው ኪዳን ምልክት (ማህተም) ይገኙበታል። እግዚአብሔር በሰው ደግነት ሳይሆን እንዲሁ በጸጋው ቃል ኪዳኑን ፈቅዶ ይሰጣል። ሰዎችም ቃል ኪዳኑን ተቀብለው ቢታዘዙለት የቃል ኪዳኑን በረከት ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ። ቃል ኪዳኑንም ሲቀበሉ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ማህተም የሆነውን የሚታይ ምልክት ያደርጋል።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የክብር ስፍራ ሰጥቶት በመልኩና በምሳሌው በእጁ የፈጠረው ፍጡር ቢኖር ሰው ብቻ ነው። ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ የሕይወት እስትንፋስ እፍ የተባለበት ሕያው ነፍስ ያለው ነው። (ዘፍ. 1፥26) እግዚአብሔር ኤደን ገነት የተባለውን መልካምና ውብ ስፍራ ያዘጋጀውም ለሰው ጥቅም ሲል ነው። (ዘፍ. 2፥8-9) እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ ከትልቅ ፍቅር የተነሳ ቅምድር ላይ በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ላይ ገዥ እንዲሆን ሾመው። ሰው ግን ከፈጣሪው የኑሰጠውን ትዕዛዝ በመጣስ በኃጢአት በመውደቁ ከኤደን ገነት ተባረረ። (ዘፍ. 3፥1-24) ይህ ክፍል የመጀመሪያው አመጸኛና ኃጢአተኛ በመሆኑ ከእግዚአብሔር መንግሥታትና ከክብሩ ስፍራ ወደ መሬት የተጣለው ዘንዶው (ሰይጣን) ሄኖንን ማሳቱንና በሄዋን አማካይነት አዳም መሳቱን የሚገልጽ ሲሆን ከዚህም የተነሳ የሰይጣን መልዕክተኛ የሆነውን እባብን የረገመበትን ሁኔታ የሚያብራራ ነው። «... ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ በሆድህም ትሄዳለህ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ።

በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኩናውን ትቀጠቅጣለህ።» (ዘፍ. 3፥14-15)

ሰው እግዚአብሔር ካስቀመጠው የክብር ስፍራ የሰይጣንን ድምፅ ሰምቶ የተጣለው እንደ እግዚአብሔር መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ በመፈለጉ ምክንያት ነው። ከዚያም ሰው በፈቃዱና በምርጫው ካደረገው ኃጢአት የተነሣ ምድር ተረግማ እሾህና አሜከላ ታበቅላለች፥ ሰው በፊቱ ወዝ በድካምና በጥረት ምግቡን እንደሚያገኝ እንዲሁም ሞት ገዥው ሆኖ ሊቆጣጠረው እንደቻለ ሲገልጽ፤ በሰውና በተፈጥሮ መካከል የነበረው ግንኙነት መልካም እንዳልሆነ ግልጽ አድርጐታል። ይህም በመሆኑ በሰውና በፈጣሪው መካከል የነበረው መልካም ግንኙነት በኃጢአት ምክንያት ተቋረጠ።

እግዚአብሔር አምላክ ግን የእጁ ፍጡር የሆነው ሰው የእርሱን ትዕዛዝ በመጣስ እንደ እርሱም አምላክ ሆኖ መልካምንና ክፉን ለማወቅ ጉጉት አድሮበት በኃጢአት ቢወድቅም ከእርሱ አእምሮ በላይ በሆነ ፍቅሩ አይቶ አዘነለት። የተቋረጠውንም የግንኙነት መስመር ለማደስና ይህንን ደካማ ሰው ለማዳን እግዚአብሔር በፈቃዱ ርኅራሄ በማድረግ ከሰው ጋር እንደገና የምሀረት ውል በልጁ አማካይነት ሊዋዋል እንመለከታለን። (ዮሐ. 3፥16)

ይሁን እንጂ ቃል ኪዳን (ውል) ሰጪው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በተደጋጋሚ የሰጠውን የፍቅርና የተስፋ ቃል እስከ ለዘላለምም እንደማይለውጠው ተስፋ ሰጥቶአል። ሰው ግን ከፈጣሪው የተሰጠውን የእምነት፥ የተስፋና የፍቅር ቃል ኪዳን ተቀብሎ መኖር እያቃተው ውሉን ሲያፈርስና አምላኩንም ሲያሳዝን ይገኛል።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያትና ዘመናት ትእዛዙን በሚያደርጉና በሚታዘዙለት ታማኝ ሰዎች አማካይነት በዘመኑ ለነበሩት የሰው ልጆች የተስፋ ቃል ኪዳን (ውል) እንደላከ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል። ይሁን እንጂ በውል ሰጪው በእግዚአብሔር በኩል ሳይሆን በውል ተቀባዩ በሰው አለመታዘዝና የልብ እልከኝነት ምክንያት ውሉ በሥራ ላይ ውሎ የእግዚአብሔርን ልብ ሲያሳርፍ አይታይም።

ምንም እንኳን ሰው የተሰጠውን የፈጣሪ ትዕዛዝ እየጣሰ ቢያስቸግረውም ለሰው ያለው የእግዚአብሔር የፍቅር ሃሳብ ግን አልተለወጠም። ከመጀመሪያውም ጀምሮ እግዚአብሔር ሰውን በጸጋው የተመለከተው ሲሆን ከሰው በኩል የሚፈለገው እምነትና መታዘዝ ነው። እነዚህ ነገሮች ዘመን ሲለዋወጥ የማይለወጡ ናቸው። (ገላ. 3፥15-18) ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን እየገለጠ ሲሄድ ምልክቶች ይለወጣሉ። (2 ቆሮ. 3፥6-18፤ ዕብ. 8፥6-13)

በሚከተለው መንጠረዥ የእግዚአብሔር ጸጋ በቃል ኪዳኑ እንዴት እንደተገለጠ ልናይ እንችላለን።

እግዚአብሔር ለሰው ቃል ኪዳን መስጠቱን የሚገልጽ ክፍል	የቃልኪዳኑ (የውሉ) ተቀባዮች	ቃል ኪዳን (ውል) የመቀበላቸው ምልክት (ማኅተም)	ተስፋ	የተስፋው ምልክት ማኅተም
1. ዘፍ. 2፡8-17፡ ሆሴ. 6፡7	አዳምና ሄዋን	መልካምና ክፉን የሚያሳውቅ የዛፍ ፍሬ አንዳይበሉ	በሕይወት መኖር	የሕይወት ዛፍ
2. ዘፍ. 9፡1-17	የዓለም ሕዝብ በኖህ አማካይነት	መርከብ መሥራት፡ ከጥፋት ውሃ ማምለጥ	በምድር መኖር	ቀስተ ደመና
3. ዘፍ. 17፡1-21፡ ሮሜ 4፡11	አብርሃምና ዘሩ	ግዝረት	የአሕዛብ በረከት የከነዓን ምድር	የይስሐቅ መወለድ
4. ዘፀ. 19፡5-6፡ 24፡7-8፡ ሕዝ. 20፡10-17	የእስራኤል ሕዝብ በሙሴ አማካይነት	ግዝረትና የለንበት ዕረፍት	ሕይወት በአገራቸው	የፋሲካ መታሰቢያ
5. መዝ. 132፡10-12፡ የሐ.ሥ 2፡29-35	ዳዊትና ዘሩ	መታዘዝ	የማይናወጥ ዙፋን	
6. ኤር. 31፡31-34፡ ዮሐ. 3፡16፡ 1ቆሮ. 11፡23-26	በክርስቶስ ያመኑ	ጥምቀት (የሞቱና የትንሳኤው ምልክት)	የዘላለም ሕይወት በመንግሥተ ሰማያት	ቅዱስ ቁርባን

ከላይ የተጠቀሱት ቃል ኪዳኖች (ውሎች) በብሉይ በተሰጠው ተስፋ መሠረት በሐዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ሲሆን የቀረውና የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሕዝብ እንደተስፋ ቃሉ በናፍቆት የሚጠብቀው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የክብር መገለጥ ወይም ዳግም ምፃትና የዘላለም እረፍት ነው ቲቶ 2፡11-14።

11.2 እግዚአብሔር ለአዳምና ለሄዋን የገባው ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ መካከል ልዩ በሆነ ፍቅር የወደደውና የሚንከባከበው ሰውን ነው። ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ ሲሆን በዔደን ገነት ውስጥ በውብ ስፍራ ያስቀመጠው እንደነበረ ከዚህ በላይ ተገልጾአል። (ዘፍ. 1፡26) ነገር ግን ሰው የሰይጣንን ድምፅ በመስማትና ምክሩ መልካም መስሎት እንደ አምላክ ክፉውንና ደጉን ለማወቅ ከመፈለጉ የተነሳ ትዕዛዝ ጥሶ በኃጢአት ወደቀ። ራቁትነቱን ሲያይም ሃፍረተ ሥጋውን ለመሸፈን ቅጠል ቆርጦ ለመልበስ ሞከረ፤ ግን ለዘለቄታ እንደማያዋጣው እግዚአብሔር አውቆ ለአዳምና ለሔዋን የቁርበት ልብስ አደረገላቸው። (ዘፍ. 3፡21)

ቃል ኪዳንም የገባላቸው ውሳኔውና ቀደም ሲል የተናገረው ትዕዛዝ ከተጣሰ ሞትን እንደሚሞቱ በገለጸላቸው መሠረት ነው። ምንም እንኳን ሰው ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ውጪ በመሆን በኃጢአት ቢወድቅም ከሚያስደንቀው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ የሰው በምድር ላይ መኖር አልተቋረጠም።

በዘፍ. 3፡15 ስለ ሴቲቱ ዘር በተሰጠው የተስፋ ቃል ኪዳን በሴቲቱ ዘርና በእባብ መካከል ጠላትነት ተፈጥሮ የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥና አሸናፊ እንደሚሆን ተነገረ። በሁለቱም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ያለው እግዚአብሔር ነው። በመጀመሪያ ሰው በፈተና የወደቀው በሴቲቱ አማካይነት ሲሆን ከኃጢአትና ከመተላለፍ ዕዳ ዋጋ ተከፍሎ ነፃ የሚወጣውም በሴቲቱ ዘር ነው ማለት ነው። ሴቲቱ የተባለችው ድንግል ማርያም ስትሆን ዘርዋ የወንድ ዘር የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ቆላ. 2፡15፤ 1 ቆሮ. 15፡22፤ ገላ. 4፡4) ስለዚህ እግዚአብሔር ለአዳም የገባው ቃል ኪዳን ጌታ ከሴቲቱ ተወልዶ እርሱንና ዘሩን እንደሚያድን እንደሆነ እንመለከታለን።

11.3 እግዚአብሔር ለኖህ የገባው ቃል ኪዳን

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ በዘመን ብዛት በምድር ላይ ክፋት እየበዛ መሄዱን ከዚህ በላይ ተመልክተናል። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ፈራጅ በመሆኑ በኃጢአት ላይ ተገቢውን ፍርድ ሳይሰጥ አያልፍም። በኖህ ዘመን እንደምንመለከተው የሰው ልጅ የሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርን እጅግ ከማስቆጣቱ የተነሳ ሰውን በመፍጠሩ የተፀፀተበትና ያዘነበት ጊዜ ነበር። ከዚህም የተነሳ በሰው በደልና መተላለፍ ምክንያት እግዚአብሔር ሰውንና በምድር ላይ የፈጠራቸውን ፍጥረታት በሙሉ በውሃ ለማጥፋት ወሰነ። (ዘፍ. 6፥17)

ነገር ግን በዚያ አስቸጋሪና ጠማማ ትውልድ መካከል ኖህ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋንና ሞገስን አገኘ። ኖህ ከአመጸኛው ሕዝብ ጋር እንዳይጠፋ እግዚአብሔር መርከብ እንዲሠራና ሊመጣ ካለው የጥፋት ውሃ እርሱና ቤተሰቡ እንዲድኑ ዕቅድ አወጣ። ወደዚህ ሰው ወደ ቤተሰቡም እግዚአብሔር ቀርቦ እንዲህ አለ «ቃል ኪዳኔን ካንተ ጋር አቆማለሁ» (ዘፍ. 6፥18) በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ኖህና ልጆቹ (ሴም፥ ካምና ያፌት) የራሱና የልጆቹ ሚስቶች በድምሩ ስምንት ሰዎች በእግዚአብሔር ዕቅድ (ጥላን) በኖህ እጅ በተሠራው መርከብ ከጥፋት ውሃ ሊድኑ ቻሉ። በተጨማሪም የእንስሳት ዝሪያ ተባትና እንስት (ወንድና ሴት) እየሆኑ ከየወገኑ ወደ መርከቡ እንዲገቡ ታዝዘው ሊተርፉ ችለዋል። (ዘፍ. 6፥17-22) የቃል ኪዳኑንም ዓላማ በመግለጥ፥ «ሥጋ ያለው ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውሃ አይጠፋም ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውሃ አይሆንም (ዘፍ. 9፥11) በማለት ለእርሱ ቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን <u>ቀስተ ደመናን</u> አደረገ። ስለዚህ ቀስተ ደመና በታየ ጊዜ ሁሉ የምድር ፍጥረታት በውሃ እንደማይጠፉ ማረጋገጫ ይሆናል፤ ከሞት ፍርሃትም ነፃ ይሆናሉ። ለዚህ ቃል ኪዳን ኖህ ያደረገው የግሉ ጥረት ወይም ሌላ ሰው ያማለደለት ነገር የለም። ነገር ግን እግዚአብሔር በፈቃዱ ከሰው ጋር ኅብረት ለማድረግና የራሱን ሃሳብ ለማከናወን ይህንን ሲፈጽም እንመለከታለን። (ዘፍ. 9፥9)

እግዚአብሔር ለኖህ የገባለት ቃል ኪዳን ፍጥረተ ዓለምን በሙሉ የሚመለከት ነው። የጥፋት ውሃ ዓለም አቀፍ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ መሠረት ያቀደው ደህንነትም መላ ዓለምን የሚያቅፍ ነው። ይህም ቃል ኪዳን በተለይ በዘፍጥረት ምዕራፍ 10 ላይ የተጠቀሱትን ሕዝቦች ይመለከታል። እነዚህ ሕዝቦች ከሦስቱ የኖህ ልጆች የተገኙ ወገኖች ናቸው። እነርሱም በምድር ላይ እየበዙ ሄዱ። በጆሮአቸው ብቻ

የሰሙት እንኳን ቢሆን ሊረሱት ይችሉ ነበር። ነገር ግን በፊታቸው በዓይን የሚታይ ምልክትን ማድረጉ እግዚአብሔር ምን ያህል ለሰው ልጆች ደህንነት ጥንቃቄና ጥበቃ እንደሚያደርግ ያሳያል። «በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመና ትታያለች በእኔና ባንተ መካከል ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ» (ዘፍ. 9፥14-15) ይላልና። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አያፈርስምና እርሱን ተስፋ የሚያደርጉ ደግሞ አያፍሩም።

11.4 እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን

ስለ አብርሃም ከዘፍጥረት ምዕራፍ አሥራ ሁለት ጀምሮ እስከ ዘፍጥረት ሃያ አምስት ያለውን ክፍል ስናነብ ከዑር ከለዳውያን ምድር የወጣ ሰው እንደሆነ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦለት «ከአገርህ ከዘመዶችህ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ብሎ ሲጠራው ይህንን ቃል በመታዘዝ በተስፋና በእምነት ወጣ።» (ዘ. 12፥1)

እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ በመፈለጉ ነው። (ዘፍ. 15፥18) አብርሃምም ቢሆን በዚህ ቃል ኪዳን ለእግዚአብሔር ከመታዘዙ በስተቀር በራሱ ያደረገው አስተዋጽዖ አልነበረም። ይህም እግዚአብሔር ለኖህ ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር አብርሃም ሳያስበው ሳይፈልገውና ሳያቅደው ካንተ ጋር ቃል ኪዳን አቆማለሁ ብሎ ቀረበው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል።

1ኛ) ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ አለው (ዘፍ. 12፥2)

2ኛ) ታላቅ የሆነው ይህ ሕዝብ የከነዓንን ምድር እንደሚወርስ ተናገረው (ዘፍ. 12፥7፤ 13፥15)

3ኛ) በአብርሃም ዘር የምድር ወገኖች ሁሉ እንደሚባረኩ ተናገረው። (ዘፍ. 12፥3) እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት በእግዚአብሔር የሚባረክ አዲስ ሕዝብ የሚፈጠር መሆኑን እንመለከታለን። ይህ አዲስ ሕዝብ ተባርኮ በእርሱ አማካይነት ደግሞ የምድር ወገኖች ሁሉ እንደሚባረኩ ያሳያል። በአዲስ ኪዳን ይህ ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙ ተብራርቶአል።

11.5 ለሙሴ የተሰጠ - የሲና ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች ሰውን ለማዳንና ወደ ራሱ ለመሰብሰብ ፍቅሩን ገልጾለታል። ከዚህ በላይ እግዚአብሔር ለአዳም፥ለኖህና ለአብርሃም በተለያዩ ዘመናት ቃል ኪዳን መግባቱን የተመልከትን ሲሆን ከዚህ በታች ደግሞ የሲናን ቃል ኪዳን ይዞታና ትርጉም በአጭሩ እናያለን።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባለትና የተመረጠው ሕዝብ «እስራኤል» ተብሎ የተጠራው በ ዘፍ. 32፥22-32 እንደተገለጸው ታሪኩ ያዕቆብ ከመሰጴጦምያ ወደ ከነዓን ለመመለስ በመንገድ ላይ የተገናኘው እግዚአብሔር እንደሆነ ተገነዘበና «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» ብሎ ተናገረ ቁጥር 26። ከዚያም ስሙን ተጠይቆ ያዕቆብ ነኝ ካለ በኋላ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ ያዕቆብ አይባል «እስራኤል» ይባል እንጂ ብሎ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባለት። ስለሆነም የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ከመሆኑ የተነሳ ታሪኩ ከሌላ ሕዝብ ታሪክ የተለየ ነው።

እግዚአብሔር ጥንት ከአብርሃም ጋር ባደረገው ቃል ኪዳንና በሲና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሙሴ አማካይነት ባደረገው ቃል ኪዳን መካከል የተቀራረበ ግንኙነት መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስ ያሳያል። ለአብርሃም የተሰጠ ተስፋ ፍጻሜ ያገኘ ዘንድ የሲና ቃል ኪዳን አስፈላጊ የሆነ ተከ ታይ በመሆኑ ነው። ይኸውም ለዓለም ሕዝቦች መዳን የተዘጋጀላቸው ከአይሁድ (ከእስራኤል) ወገን በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የሚጠቁም ነው። (ዮሐ. 4፥22)

በሲና ተራራ አቅራቢያ በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ በገለጠ ጊዜ ለአባቶች የተነገረውን ቃል በማስታወስ ነው። «እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሃቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ» አለው። (ዘፀ. 3፥6) እንዲህ ማለቱም እግዚአብሔር ለአባቶች የገባውን ቃል ኪዳን የማይረሳ መሆኑን ያሳያል።

ሙሴም እግዚአብሔር የገባለትን ቃል ኪዳንና ለሕዝቡ የሰጠውን ተስፋ በመጨበጥ ሕዝቡን ከባርነት ቀንበር ለማላቀቅ ሲነሳ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ሙሴንም ሆነ ወንድሙን አሮንን ተቃውሞአቸዋል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ድንቅና ታምራት በግብፅ ምድር ላይ አድርጐ በእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤት በግ ታርዶ ደሙ በቤቱ ጉበንና በመቃኑ ላይ እንዲቀባ ትዕዛዝ በመስጠት ከንጉሡ እስከ ግዞተኛው፥ ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ

በግብፃውያን ቤት በኩር የሆነውን ሁሉ በሞት መቅሰፍት ከቀጣ በኋላ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባርነት በድል እንዳወጣው የታወቀ ነው። ሕዝቡ ወደ ከነዓን ለመድረስ በመንገድ ላይ እያለ እግዚአብሔር ሊመራበት የሚገባውን ሕግና ሥርዓት ሰጠው። የእስራኤል ልጆች በሲና ተራራ አጠገብ በቆዩበት ጊዜ የተጠቀሱ ሕግጋት ተሰጥተዋቸዋል። ይኸውም ከዘጸአት 20 እስከ ዘኍልቍ 10 ድረስ ያለው ታሪክ በሙሉ በተራራው ሥር የቆዩበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው። በተጠቀሰው ረዥም ክፍል ውስጥ ተጠራቅመው የሚገኙት ትዕዛዛትና ሕግጋት ሁሉ በዚያን ጊዜ የተሰጡ ናቸው። ከነዚህም ሕግጋት ዋና ዋናዎቹ በዘጸአት 20-23 ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆን ከዘጸአት 20፥1-17 አሥርቱ ትዕዛዛት ቀዳሚውን ስፍራ ይዘው ይገኛሉ። ከዚያም ቀጥሎ ከዘጸአት 20፥23-33 ያሉት የሕዝቡን ማህበራዊና መንፈሳዊ ኑሮ የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕግጋት የተጠቀሱባቸው ናቸው። በዘጸአት 24፥7 ላይ የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ የሚለውን አባባል እናገኛለን። ይህም ለእነዚህ ሕግጋት የተለመደ መጥሪያ ስም ሆኖ ከዘጸአት 20፥23 እስከ 23፥33 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ተብለው ተጠርተዋል። ለእነዚህም መሠረታዊ ሆነው የሚገኙት በአሥርቱ ቃላትና በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ የተጠቀሱት ሕግጋትና ትምህርቶች ናቸው። እነዚህም ድንጋጌዎች ወደፊት የሚሆነውን ጊዜ እንጂ የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ የቆዩበትን ጊዜ አያመለክቱም።

ሙሴ ከሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ያመጣላቸው ሕግጋት ሁለት ዓይነት ሲሆኑ አንደኛው አሥርቱ ትዕዛዛት፥ ሁለተኛው የቃል ኪዳኑ ሕግጋት ናቸው።

አሥርቱ ቃላት (ትዕዛዛት) በእግዚአብሔር አፍ በቀጥታ የተነገሩ ከመሆናቸውም በላይ፤ ተወዳዳሪ የሌላቸው በሁለቱ ጽላቶች በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉ ናቸው። (ዘጸ. 31፥18፥ 34፥1-28)

11.6 ለዳዊት የተሰጠ ቃል ኪዳን

ዳዊት ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ የሆነ ንጉሥ ሲሆን ዘመነ መንግሥቱም 1011-971 ከክርስቶስ በፊት ነበረ ተብሎ ይገመታል። ዳዊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንግሥቱ የመሲሁ መንግሥት ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሶአል። መሲሁ ራሱም ብዙ ጊዜ በዳዊት ስም ተጠቅሶ ይገኛል። (2ሳሙ. 7፥8-17፤ ኢሳ. 9፥7፤ ኤር. 23፥5-6፤ 33፥14-17፤ ሕዝ. 34፥23፤ 37፥24)

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የዳዊት ልጅ በሚለው ስም የሚጠራው በዚህ ምክንያት ነው። (ማቴ. 9፥27፤ 12፥23) በትውልድ መጽሐፉም ላይ ከዳዊት ቤትና ወገን የተወለደ መሆኑ ተነግሮለታል (ማቴ 1፥1)።

ነቢዩ ናታን ዳዊትን «እግዚአብሔር ካንተ ጋር ነውና ሂድ በልብህ ያለውን አድርግ ... ለሕዝቡ ለእስራኤል ስፍራ አደርግለታለሁ። ... ቤት እሰራልሃለሁ ...። ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሳለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ... ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘላለም ይጠነክራል ዙፋንህ ለዘላለም ይፅናል ...» (2ሳሙ. 7፥3-17) «ሕፃን ተወልዶአልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ... በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል ...» (ኢሳ. 9፥6-7) እነሆ ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጥ የማስነሳበት ዘመን ይመጣል ይላል እግዚአብሔር እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል ይከናወንለታልም በምድር ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። (ኤር. 23፥5-6፤ 33፥14-15) እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ቃል ኪዳን ፈጽሞታል። ይኸውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ በሥጋ ከዳዊት ዘር ተወልዶ መጥቶ ዓለምን ለማዳን በመስቀል ላይ ተሰቅሎአል።

11.7 ኪዳነ ምህረት

በክርስቶስ ኢየሱስ ለሰው ሁሉ የተሰጠ የምህረት ቃል ኪዳን

ኪዳነ ምህረት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሰው የኃጢአት ዕዳ ተከፍሎ በእምነት የተቀበለ ሁሉ ዳግም ተወልዶ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ተስፋ ያገኘበት የምህረት ቃል ኪዳን (ውል) ነው። (ዮሐ. 1፥12፤ 3፥16፤ ሐ.ሥ. 4፥12)

እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ ምትና የዘላለም ፍርድ የሚገባው ቢሆንም ከአእምሮ በላይ በሆነ ሰማያዊ ፍቅር ሕይወት ሊሰጠው ቃል ኪዳን ገባለት፤ ከስጦታ ሁሉ በላይ የሆነውን ስጦታ አንድያ ልጁን በመስጠት ወደደው፤ ፍቅሩንም በተግባር ገለጸ።

በተለያዩ ዘመናት እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ከአመፅና ከልብ ደንዳናነት ተመልሶ ታዛዥና ትሁት እንዲሆን መልዕክቱንና ትዕዛዙን የልቡን ሃሳብ በሚያሳርፉ ሰዎችና በተለያዩ ነቢያት አማካይነት ለሕዝቡ ሲያስተላልፍ ቆይቷል።

ነገር ግን የሰው ልጅ እውነትን እንዳያውቅ ሰይጣን ዲያቢሎስ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ከሕይወት ይልቅ ሞትን እንዲመርጥ እያደረገው አንዱ በሌላው ላይ ክፋትንና ተንኮልን በመፈላለግ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሲጥስና ሌላውንም ወገኑን ሲያቆስል ይታያል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው የህሊና ሕግ እየከሰሰው፥ መንፈስ ቅዱስም እየወቀሰው በእምቢተኝነት እንደሆነ የታወቀ ነው። ቢሆንም ከዚህ በላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያትና ዘመናት ሊመጣ ያለውን የዘላለም ተስፋና በክርስቶስ ደም የተደረገውን የኃጢአት ሥርየት ሲገልጽ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተብራራው፤

1ኛ) ለአዳምና ለሄዋን - በኃጢአት በወደቁ ጊዜ የተሰሩ ቃል ኪዳን ገባላቸው (ዘፍ. 2፥8-17፤ ሆሴዕ 6፥7)

2ኛ) ለኖህ - በምድር ላይ የነበሩ የሰው ዝርያዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው እግዚአብሔር ኖህንና ቤተሰቡን አስቀርቶ ሌላውን ሕዝብ በጥፋት ውሃ ከጨረሰ በኋላ የገባው ቃል ኪዳን (ዘፍ. 9፥1-17)

3ኛ) ለአብርሃም - ከሚኖርበት ሰፈርና ከአመፀኛ ሕዝብ መካከል እንዲለይ ካደረገው በኋላ የገባለት የተስፋን ቃል ኪዳን (ዘፍ. 17፥1-21፤ ሮሜ 4፥11)

4ኛ) ለሙሴ - የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ ሃላፊነት ከሰጠው በኋላ ግርና ወተት ወደምታፈስሰው አገረ ከነዓን ሊገቡ በመንገድ ላይ በነበሩበት ወቅት የተሰጠ የአሥርቱ ቃላት ቃል ኪዳን (ብሉይ ኪዳን) ዘጸአት 19፥5-6፤ 24፥7-8)

5ኛ) ለዳዊት - የእስራኤል የመጀመሪያው ንጉሥ ሳዖል እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ከሥልጣን ከወደቀ በኋላ እግዚአብሔር እንደልቡ የሆነውን የእሴይን ልጅ ዳዊትን አግኝቶ የገባለት የዘላለም መንግሥት (የክርስቶስ መንግሥት ምሳሌ) የሆነ ቃል ኪዳን 2ሳሙ. 7፥8-17፤ ኢሳ. 9፥7፤ ኤር. 23፥5-6፤ 33፥14-17፤ ሕዝ. 34፥23፤ 37፥24)

6ኛ) ለአሕዛብና ለእስራኤል በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ አማካይነት የተደረገ የምህረት ቃል ኪዳን (አዲስ ኪዳን) ሲሆን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የገባውን የኃጢአት ግድግዳ አፍርሶ በደሙ እርቅና ሰላም እንዲሆን ባደረገው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ጣርና ሞት ዕዳ የተከፈለበት

ውል ኪዳነ ምህረት ይባላል። በዚህ የእርቅ ውል መሠረት ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል መድሃኒቱና ጌታው አድርጐ የተቀበለ ሰው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል ዮሐ. 1፥12። የእግዚአብሔርም ልጅ የሆነ መንግሥቱን ይወርሳል። ከዚህ ውጪ ግን ሰው በራሱ ጥረት የሚያደርገው ማንኛውም በጐ ምግባርና ተግባር ለዘላለም ሕይወት ሊያበቃው ስላልቻለ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ደህንነት ያዘጋጀለት ኪዳነ ምህረት ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። ይህ የአዲስ ኪዳን ወይም ኪዳነ ምህረት በሌሎች ፍጡራን ሳይሆን በራሱ በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ በመሆኑ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ብቸኛ መንገድም እርሱ ነው እንጂ በሌሎች ፍጡራን አማካይነት ፈጽሞ ሊገባ የሚችል የለም። (ዮሐ. 3፥16፤ ሐ.ሥ. 4፥12)።

ታቦት

12.1 የታቦቱ አሠራር

ታቦት ማለት የቃሉ ትርጉም ማኖሪያ፥ ማደሪያ ወይም ማስቀመጫ ማለት ሲሆን ታቦት የሚለው ቃል የግዕዝ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመባል የሚታወቀው የእስራኤል ሕዝብ ከዮሴፍ እስከ ሙሴ ዘመን ድረስ ለአራት መቶ ሠላሳ ዓመታት ገደማ በግብፅ አገር በባርነት ተገዝተው ኖረዋል። (ዘፀ. 1፥1-22፤ 2፥1-25)

እግዚአብሔር አምላክም በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ይደርስ የነበረውን መከራና ሰቆቃ በማየቱና በማወቁ የሕዝቡንም የለቅሶ ድምፅ በመስማቱ ነፃ ሊያወጣቸው ወሰነ። የግብፅ መንግሥት ለግል ጥቅሙ ሲል የእስራኤልን ሕዝብ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባይሆንም እግዚአብሔር ግን በበረታች እጅና በጸናች ክንዱ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፥ ለይስሃቅና ለያዕቆብ ቃል ኪዳን ወደ ገባላቸው ወደ ተስፋይቱ አገር ወደ ከነዓን ከብዙ ፈተና በኋላ እንዲገቡ እንዳደረጋቸው የታወቀ ነው። (ዘፀ. 14፥28-31)

ሙሴ የፈርዖን ሴት ልጅ ከተጣለበት ውሃ ውስጥ አንስታው ወስዳ የንጉሡ የልጅ ልጅ እየተባለ በተአምር አድጐ የእስራኤል ሕዝብ መሪ በመሆን እንዲያገለግል በኪነ ጥበቡ እግዚአብሔር የመረጠው ሰው ነው። እርሱንም ሕዝቡ በማህበራዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሥርዓት ያለው እንዲሆን እግዚአብሔር አምላኩን በማወቅና በመፍራት እንዲሁም እርሱን ብቻ እያመለከ እንዲኖር የቃል ኪዳን መመሪያ እንዲቀበል አዘዘው። ሙሴም ወደ ሲና ተራራ ወጥቶ በፆምና በጸሎት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ካሳለፈ በኋላ እግዚአብሔር በሁለት በኩል የተጻፉ ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን ሰጠው። በጽላቶቹ ላይ የተጻፉት አሥርቱ ቃላት የሚከተሉት ናቸው :-

1. ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። ዘፀ. 20፥2-3፤ ዘዳ. 5፥6-7

2. በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ካለው የማናቸውም ነገር ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው አታምልካቸውም ... እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ። ዘፀ. 20፥4-6፤ ዘዳ. 5፥5-8

3. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውም። ዘፀ. 20፥7፤ ዘዳ. 5፥1

4. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። ዘፀ. 20፥8-11፤ ዘዳ. 5፥12-15

5. አባትህንና እናትህን አክብር። እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም። ዘፀ. 20፥12፤ ዘዳ. 5፥16

6. አትግደል ዘፀ. 20፥13፤ ዘዳ. 5፥17

7. አታመንዝር ዘፀ. 20፥14፤ ዘዳ. 5፥18

8. አትስረቅ ዘፀ. 20፥15፤ ዘዳ. 5፥19

9. በባልንጀራህ ላይ በሀሰት አትመስክር ዘፀ. 20፥16፤ ዘዳ. 5፥20

10. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፥ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም የባልንጀራህን ገንዘብ ሁሉ አትመኝ ዘፀ. 20፥17፤ ዘዳ. 4፥21 የሚሉ ናቸው።

እነዚህ ሁለቱ ጽላቶች ከግራር ተጠርቦ በወርቅ በተለበጠ ታቦት ውስጥ እንዲቀመጡ እግዚአብሔር አዘዘ። ይህም ታቦት የሆነው የተጠቀሰው የግራሩ ምሳሌ ጠማማና አስቸጋሪ የሆነውን የሰው ልጅ እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ ዳግም በመቤዠት የከብሩ መግለጫ፥ የቃሉ መኖሪያ ማድረጉ አስደናቂ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ፍቅር በምስጢር ይገልጻል። ስለሆነም በአዲስ ኪዳን ታቦት የሆነው የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ዳግም የተወለደ አማኝ ሲሆን (ዮሐ. 14፥23) ቃላቱ የተጻፉበት ድንጋይ ደግሞ የሰው ልብ ነው። (ኤር. 31፥31)

እነዚህንም አሥርቱን ቃላት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለት አጠቃሎአቸዋል። ይኸውም ፈሪሳውያን ከትእዛዝ ሁሉ ፊተኛይቱ

ማንኛይቱ ናት? ብለው በጠየቁት ጊዜ ሲመልስላቸው ፊተኛይቱ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ሃሳብህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትዕዛዝ የለችም ብሎ መልሶአል። (ማር. 12፥18-31፤ ዘሌ. 19፥18)

12.2 የእስራኤል ታቦትና የማደሪያው ድንኳን አቀማመጥ

እስራኤላውያን አርባ ዓመት ሙሉ በምድረበዳ ሲጓዙ እግዚአብሔር በመካከላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የገባው ቃል ኪዳን በሁለት ገበታ (ፅላት) በድንጋይ ላይ ተጽፎ በታቦት ውስጥ እንዲቀመጥና ታቦቱ በሥርየት መክደኛ እንዲከደን በድንኳንም እንዲከለል ተደርጐአል።

የማደሪያውን ድንኳን አሠራር ስንመለከት ቀደም ሲል እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን ፈጥሮ በገነት አስቀምጦአቸው ሳለ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ተለይተዋል። ይህም ማለት እግዚአብሔር በየጊዜው ወደ እነርሱ እየቀረበ በማነጋገር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላላቸው ነበር። እነርሱ ግን በቅድሚያ የሰሙትን የእግዚአብሔርን ድምፅ ችላ በማለት የጠላት (የሰይጣንን) ድምፅ በመስማት ራሳቸው አምላክ ለመሆን ካላቸው ከውስጥ ፍላጐት የተነሳ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ጠንቅ ከገነት ከመባረራቸውም በላይ ከፈጣሪያቸውና ከተንከባካቢያቸውም ተለይተዋል።

ስለሆነም አዳምና ሄዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ እግዚአብሔር ድምፁን ከማሰማት በስተቀር እንደቀድሞ ከእነርሱ ጋር ለመሆን አልፈቀደም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ሕብረት የለውምና ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለማደርና የማዳን ዕቅዱን ለመግለጽ ወስኖ ድንኳን ይስሩልኝ ማለቱ በአሪት መጻሕፍትና በዕብራውያን መልዕክት <u>በሃምሳ ምዕራፎች</u> ላይ ተጠቅሶአል። ይኸውም አሪት ዘጸአት ውስጥ አሥራ ሦስት ምዕራፎች ላይ፥ በአሪት ዘሌዋውያን አሥራ ስምንት ምዕራፎች፥ በአሪት ዘኁ ልቊ አሥራ ሦስት፥ በአሪት ዘዳግም ሁለት እንዲሁም በዕብራውያን መልዕክት አራት ምዕራፎች ናቸው። እግዚአብሔር ይህንን መግለጫ የሰጠበት ምክንያት የማደሪያ ድንኳንም ሆነ በዚያ ውስጥ የሚደረገው አምልኮና አገልግሎት በዘመናት ውስጥ ሊመጣ ስላለው የዘለዓለም ደህንነት የሚያሳይ የእውነተኛው ነገር ጥላ ወይም ምሳሌ ነው።

የማደሪያው ድንኳን - የመገናኛ ድንኳን የምስክሩ ድንኳንም ተብሎም ይጠራል።

«ቃልም ሥጋ ሆነ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን። (ዮሐ. 1፥14) በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በማደሪያው ድንኳን አማካይነት በሕዝቡ መካከል እንዳደረ የተገለጸ ሲሆን በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ አማካይነት በእኛ ውስጥ አደረ ይላል። የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ክብር በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ከሩቅ ተመለከቱት። ዛሬ ግን በክርስቶስ በኩል፥ «እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን። ይህ ሊሆን የቻለው እርሱ በክብሩ በእኛ ውስጥ ስለሚኖርና እኛም በእርሱ አማካይነት የእግዚአብሔር መኖሪያ ስለሆንን ነው። ሰው የእግዚአብሔር መኖሪያ የሚሆነው ሃይማኖተኛ ስለሆነ ሳይሆን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና ጌታው አድርጐ ሲቀበልና የእግዚአብሔር ልጅ ሲሆን ብቻ ነው። ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ይላልና (ዮሐ. 1፥12) «በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ። በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ያረጋግጥልናል። በሌላ ስፍራ ደግሞ «እኛ የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁ እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፥ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።» (ዘጸ. 25፥8፤ 29፥44-45፤ ዮሐ. 3፥18፤ ኤፌ. 2፥22፤ ፊል. 3፥3) ስለዚህም ጌታ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩስንም አትንኩ ...» 2 ቆሮ. 6፥17-18 ሲል መለየት ወይም መቀደስ ከኛ ሳይሆን ከእርሱ እንደሆነ እንረዳለን፤ ምክንያቱም «ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ ...» ይላልና። የሚቀድስ ጌታ ከሆነ ደግሞ «በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ ...»› የሚለውን ልንዘነጋ አይገባም።

የማደሪያው ድንኳን እስራኤላውያን በምድረ በዳ በጉዞ ላይ እያሉ እንዲሠራ በእግዚአብሔር የታዘዘ እንጂ ወደ ከነዓን ከገቡ በኋላ የተሰጠ አይደለም። ይህም ድንኳን አስፈላጊነቱ ለዘለቄታ ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ መሆኑን ያመለክታል። ጉዞውን ፈጽመው ከነዓን ከገቡ በኋላ ቤተ መቅደስ እንጂ ድንኳን አላስፈለጋቸውም። «... ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ

ለምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሰራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለም ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።» (ዘኍ. 9፥16-23፤ መዝ. 78፥72፤ ሕዝ. 11፥16፤ ማቴ. 6፥31-32፤ ፊል. 4፥19፤ ዕብ. 9፥8-12)

የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ በጉዞ ላይ እያሉ ታዝዘው በሠሩት ድንኳን ውስጥ እግዚአብሔር ከነሙሉ ክብሩ ለማደር እንደወደደ እንዲሁ ደግሞ ቃል ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን። በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል፤ ያለው ክርስቶስ ሥጋ መልበሱን አምላክ ሆኖ ሳለ ሰው መሆኑንና በሰው ልብ ውስጥ ሊኖር ፈቃደኛ መሆኑን ያሳያል።

የማደሪያው ድንኳንም ሆነ ቤተ መቅደስ ያለ ዓላማ የተሠሩ አይደሉም። ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉትን አሥርቱን ትዕዛዛት የያዙ ሁለት የድንጋይ ፅላቶች ያሉበት ማደሪያ ወይም ማኖሪያ ሣጥን (ታቦት) የሚቀመጠውም እዚያው በማደሪያ ድንኳን ውስጥ ነው። ይህም የቃል ኪዳኑ ምልክት እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ራሱ ለማቅረብ የሰጠውን ውለታ የሚያሳይ ነው። ስለሆነም እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው ወደ ከነዓን በሚሄዱበት ወቅት በመንገድ ላይ በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኙ የሚችሉት በመገናኛ ድንኳን በሊቀ ካህኑ አማካይነት ብቻ ነበር።

የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር በሩ እኔ ነኝ (ዮሐ. 10፥9) መንገድና እውነት ሕይወትም እኔ ነኝ በኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም (ዮሐ. 14፥6) ብሎ በእርሱ አማካይነት ብቻ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንደሚቻል ግልጽ አድርጐታል።

12.3 የእስራኤል የቃል ኪዳን ታቦት የት ደረሰ?

እግዚአብሔር ሕዝቡን በራሱ ደንብና ሥርዓት ለመምራትና ለማኖር በመፍቀዱ ለሙሴ አሥርቱን ትዕዛዛት በሲና ተራራ ከሰጠው በኋላ የእነዚህ አሥርቱ ትዕዛዛት ወይም ሁለት የፅላት ገበታዎች ማኖሪያ ከግራር እንጨት የተሠራ ሳጥን ታቦት ተብሏል። የዚህም ሙሴ ያሠራው ታቦት ርዝመቱ 125 ቁመቱ 75 ሳንቲ ሜትር ያህል ነበር። ዘጸ. 25፥16-22፤ ዘዳ. 5፥5-22፤ 10፥1-5፤ 2 ዜና 5፥10።

ሕዝበ እስራኤል በጽላቱ ላይ የተጻፈውን ቃል ቢጠብቁ ከእግዚአብሔር የሚሰጣቸውን በረከት ያገኛሉ። ካልሆነና ባለመታዘዝ ባይጠብቁ የሚወርድባቸውን የቁጣ መቅሰፍት ስለሚቀበሉ ይህ የቃል ኪዳን ጽላት (የውል ሰነድ) ወይም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የምስክሩ ጽላት በመባል ይታወቃል (ዘጸ. 31፥18፤ ዘዳ. 4፥13)።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ተሰርቆም ይሁን በስጦታ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ሲባል ጽላቱን የያዘው ታቦት እንደሆነ ወይም ጽላቱ ብቻ እንደሆነ በትውፊታዊ አፈ ታሪኮች በጉልህ አልተገለጸም።

ወደዚህ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ግን ሊጤን የሚገባው ቃል ኪዳኑ በመጀመሪያ የተገባው ለማን ነበር? ማን ከማን ጋር? የትና መቼ? ለምንስ የተዋዋለው ነው? ብሎ መጠየቁ አስፈላጊ ይሆናል። በብሉይ ኪዳን በጥላነት የተገለጠው ፅላትና ታቦት በአዲስ ኪዳን በአካል ሲገለጥ ማንን ያሳያል? ብሎ መጠየቅ በደፈናው «አትመራመር» ለሚሉት ለአንዳንዶች አይዋጥላቸውም እንጂ አግባብነት ያለው ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትም መርምሩ ፈትኑ መልካሙን ያዙ ይላልና።

እግዚአብሔር ይህንን ቃል ኪዳን በቃልና በጽላትም በመጻፍ የተዋዋለው ከማንም አሕዛብ ጋር ሳይሆን ሕዝቤ ብሎ ከሚጠራቸው ከእስራኤል ልጆች ጋር ነበር። ዘጸ. 4፥6-8፤ 34፥27-28፤ ዘሌ. 25፥55፤ 26፥1-46፤ ዘዳ. 5፥1-3፤ 6፥6-11፤ ዘጸ. 24፥4-8።

እንግዲህ የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን አምላኬ ብሎ በሚጠራውና እግዚአብሔርም ሕዝቤ ብሎ በሚያውቀው በእስራኤል ሕዝብና በአምላኩ መካከል ለተደረገው ቃል ኪዳን (ውለታ) ምስክር የሆነው የኪዳኑ ታቦት በአንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች ወደ ኢትዮጵያ ተሰርቆ መጥቶአል ተብሎ የተጻፈ ስለሆነ ቢሰርቁት ምን ጥቅም አለው? ሰረቁ የተባሉትን ወገኖች በሌብነት ያስጠይቅ ይሆናል እንጂ ሌላ ፋይዳ የለውም። ወይም ደግሞ ያልሰረቁትን ሰዎች ስም ለማጥፋት ሰረቁ ከተባለም ይህ የብሉይ ቃል ኪዳን ከእስራኤል ልጆች ነገድ ውጪ ለሆኑት ለሌሎች አያገለግልም፤ አይጠቅማቸውምም። (መዝ. 147፥8-9) ስለሆነም እንደ ትውፊቱ አባባል የእስራኤል ታቦት ወይም ጽላት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ቢሆን ኖሮ እስራኤሎች የግል ንብረታቸውን ሊወስዱ በተገባቸው ነበር።

ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶአል ተብሎ በተጻፈውና የኢትዮጵያን የነገሥታት ሥልጣን ከዛጉዬ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ለመመለስ በተደረሰው የታሪክ ድርሰትና ለይኩኖ አምላክ

ሥልጣን ማስጨበጫ ሲባል በተዘጋጀው የፍትሐ ነገሥት ጽሑፍ እንደተቀነባበረው ቢሆንና እግዚአብሔር ከወሰነለት ስፍራ ከኢየሩሳሌም ተሰርቆ ቢሆን ኖሮ በፍልስጥኤማውያን ላይ የደረሰው የመቅሰፍት ዓይነት በሰራቂዎቹ ላይ በወረደ ነበር። 1ሳሙ. 4፥10፤ ምዕ. 5 እና ምዕ. 6 ይነበብ።

በእግዚአብሔርና በእስራኤል ልጆች መካከል ለነበረው የቃል ኪዳን ታቦት ማደሪያ የሚሆን መቅደስ እንዲሠራበት በእግዚአብሔር የተመረጠው ቦታ ኢየሩሳሌም ስለነበረ ከዚያ ያለ እግዚአብሔር ትዕዛዝ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር ሲደረግ ቅስፈትን ባስከተለ ነበር። ዘዳ. 14፥22-25፤ ዘዳ. 26፥1-2፤ 1 ነገ. 8፥15-21፤ 1ዜና 21፥18-30፤ 22፥1-2፤ 2 ዜና. 3፥1።

በድፍረትም ሆነ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም እንደተባለው በስርቆት ታቦቱ ከኢየሩሳሌም እንዲንቀሳቀስ ቢደረግ ኖሮ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ በተሰጠው ነበር። ይህ ባለመሆኑ ስለ ሁኔታው የበለጠ ትኩረት በመስጠት ታቦቱ እንግዲያው የት ደረሰ የሚለውን ጥያቄ ያጠናክራል።

እስኪ እንመልከት - ከሴሎ ወደ አቤንኤዜር ከዚያም ወደ አዛጦን ጌት አስቀሎና ሲወሰድ እንደገናም ለእስራኤል ልጆች ተመልሶ ወደ ቤትሳሚስ ከዚያም አሚናዳብ ቤት ሲቀመጥ መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ይተርካል። 1 ሳሙ. 4፥3 እስከ ምዕ. 7፥2። ቀጥሎም ከአሚናዳብ ቤት ወደ አቢዳራ ቤት ሲዛወር ከዚያም ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ጽዮን አምባ ሲመጣ ዝርዝር ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተብራርቶአል። (1 ሳሙ. 6፥1-17) ይህ ሁሉ ሲሆን ታቦቱ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ወደዚያ እንዲገባ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ በድንኳን ውስጥ ይቀመጥ ነበር።

«ታቦቱ ተሰርቆ ተወሰደ» ከተባለበት ከሰለሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ 359 ዓመት ዘግይቶ በንጉሡ በኢዮስያስ 18ኛ የግዛት ዘመን ይኸው ታቦት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ተቀምጦ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ያስረዳል። 2ዜና. 35፥1-19 ታዲያ የመጽሐፍ ቅዱስን ወይንስ የቃልና የቅብብሎሽ ትውፊት እውነት ነው ብለን እንቀበል? መቼም የታቦቱ በቤተ መቅደስ አለመኖር ከሰው ተሰውሮ ኖረ ቢባል እንጂ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሊሰወር አይችልም። (ኤር. 3፥23-24)

እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ በሙሴ የተዘጋጀውን ታቦት ማለተ የጽላቱን ማደሪያ ከግራር ተሠርቶ በወርቅ የተለበጠ ሳጥን እንዲሠራ ለሙሴ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ሌላ ሰው አስመስሎ ሠርቶ ማዘጋጀት ይችል ይሆናል። ነገር ግን ጽላቱን በተመለከተ ሙሴ ጠርቦ ካዘጋጀ በኋላ እግዚአብሔር ሕጉን ጻፈባቸው። ከዚያም በኋላ ሙሴ በታቦቱ (በሣጥኑ) ውስጥ አስቀመጣቸው እንጂ ርዝመታቸው፥ ወርዳቸው፥ ውፍረታቸው ምን ያህል እንደሆነ አልተገለጸም።

እንደ እውነቱማ በዓይን የማይታየው በጆሮ ብቻ የሚደመጠው ከእግዚአብሔር አፍ የወጣው ቃል የተጻፈበት ጽላት የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በሥጋ ተገልጾ የሚታይ እንደሚሆን የሚያመለክት ተምሳሌት ስለ ነበረ በሥጋ የተገለጸውን ቃለ እግዚአብሔር ወልድን (ቃል ሥጋ ሆነ የሚል እምነትን) የተቀበሉ ክርስቲያኖች በምሳሌነቱ ይቀበሉታል። «ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩ ለሄዘግቡር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሔር ቃለ ዘኮነ ሰብዕ።» «ሁለንተናው በወርቅ የተለበጠ ከማይነቅዝ እንጨት የተሠራ ታቦት ሰው በሆነው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ይመሰልልናል» ይላል። ስለዚህ ይህ የአዲስ ኪዳን ውል በማንም ሌባ ሊሰረቅ የሚችል አይደለም።

12.4 የቀኖና (ዲድስቅልያ) መጻሕፍት ስለ ታቦት ምን ይላሉ?

ሀ. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፥ ታቦተ ፅዮን በባቢሎናውያን ተማርካለች ይላል። (ዕዝራ ሱቱኤል 9፥22-23) እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቤተ መቅደሱ ውስጥ በኢየሩሳሌም ሰለምን ከሞተ በኋላ እስከ 391 ዓመት የታቦትን በቦታው መኖር ይገልጻል። ምክንያቱም ጠፋች የሚለው በባቢሎናውያን ነውና።

ለ. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ፥ ታቦተ ጽዮን በኢዮስያስ ዘመን ሰሎሞን ባሰራው ቤተ መቅደስ እንደነበረች ይገልጻል። (ዕዝራ ካልዕ 1፥3-4) በዚሁም ተሰረቀች ከተባለበት ጊዜ ማለትም ከሰለሞን ዘመነ መንግሥት 359 ዓመት ዘግይቶ መሆኑን ስንመለከት ይህ ሀሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል ልንል እንችል ነበር። ነገር ግን በዚሁ መጽሐፍ ምዕ. 1፥54 ላይ ታቦተ ጽዮን ከቤተ መቅደሱና ከቤተ መንግሥቱ ዕቃ ጋር ወደ ባቢሎን ተማረከች ይላል። ይህንን ሲል ደግሞ ከዕዝራ ሱቱኤል ጋር ይስማማል።

ሐ. ተረፈ ኤርምያስ - ባሮክና ኤርምያስ ቤተ መቅደሱን ከነሙሉ ዕቃው ምድር እንድትውጠው አደረጉ ይላል። ምዕ. 8፥13-19 ይህ አባባል ደግሞ ከሁሉም ጋር የሚስማማ ሀሳብ አይደለም። እንግዲህ የቀኖና (ዲድስቅልያ) መጻሕፍት ራሳቸውን በራሳቸውና አንደኛው ሌላውን የሚቃረኑ ሲሆን የኢትዮጵያንም የትውፊት ታሪክ የማይደግፉ ከመሆኑም በላይ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ግኝት አስተማማኝ የታሪክ ማስረጃ እንደሌለ ማረጋገጥ ይቻላል።

12.5 የእስራኤል ታቦት አቋም

ይህ በእግዚአብሔርና በእስራኤል ልጆች መካከል የተደረገው የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጣ ከተባለ በኋላ 359 ዓመት ዘግይቶ ታቦቱ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ወደ ባቢሎንም ካልተማረከ በአንድ ሌላ ቦታም ካልተደበቀ እንግዲያው የት ደረሰ? የሚለው ጥያቄ መመለስ እንዳለበት የታመነ ቢሆንም ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ ግምታዊ ይሆናል። ከቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚጠቅሙአቸውን ዕቃዎች ባቢሎናውያን ከወሰዱ በኋላ ቤተ መቅደሱን እንዳቃጠሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። (2 ነገ. 25፥8-9፤ ኤር. 52፥12-13፤ 2ዜና 36፥17-19)

ባቢሎናዊው ወታደር በድፍረት ታቦቱን ከቤተ መቅደሱ ለማውጣት ቢሞክር ኖሮ እንደ ኦዛ በተቀሰፈ ነበር። (2ሳሙ 6፥6-7) ስለሆነም ታቦቱ ከቤተ መቅደሱ ጋር ሳይቃጠል አልቀረም የሚል ግምታዊ መልስ አለ።

በሌላ በኩል ደግሞ ታቦቱ ወደ ባቢሎን ቢማረክ ኖሮ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የተማረከው ንዋየ ቅድሳት ሁሉ ለአይሁድ እንዲመለስላቸው ሲያደርግ የቃል ኪዳኑንም ታቦት በመለሰላቸው ነበር። (ዕዝ. 1፥1-11) ወይም ናቡከደነፆር ገና ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት ላይ በነበረበት ጊዜ ካህናቱ በምስጢር ደብቀውት ቢሆን ኖሮ ከባቢሎን ምርኮ በተመለሱ ጊዜ ከመከከላቸው የዕድሜ ባለጸጐች ስለ ነበሩ (ዕዝ. 3፥12) ከተደበቀበት እንዲወጣ ጥቆማ ባደረጉ ነበር። የደበቁት ሰዎች ሁሉ ቢሞቱ እንኳን የቃል ኪዳኑ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር በነቢያቱ በእነ ሐጌ በኩል ይጠቁማቸው ነበር ተብሎ ይታመናል። እንግዲያውስ ከቤተ መቅደሱ ጋር ተቃጥሎ ይሆናል የሚለውን መላምት ሁኔታው ያጠናክረዋል።


የታቦት ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ለሕዝቡ የተሰጠው አንድ ጊዜ ነው እንጂ ብዙ ጽላቶች አልተባዙም። የመጀመሪያውን የድንጋይ ጽላት ሙሴ ሲሰብር በድጋሚ የተሰጠውም አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከባቢሎን የተመለሱ አይሁድ ከመማረካቸው በፊት በተነገረው ትንቢት መሠረት በኢየሩሳሌም አዲስ ቤተ መቅደስ ሠሩ። (ኢሳ. 44፥24-28፤ ዕዝ. 1፥1-4፤ 6፥14-18።

ይህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ የተከናወነ ሲሆን ታቦት እንደገና እንዲቀርጹ ወይም እንዲያባዙ እግዚአብሔር አላዘዛቸውም ነበር። የይሁዳና የብንያም ልጆች ገና ወደ ባቢሎን ከመማረካቸው በፊት አሥሩ ነገደ እስራኤል ወደ አሦር ከፈለሱ በኋላ በነቢዩ በኤርምያስ በኩል እግዚአብሔር ባስተላለፈው መልዕክት፥ የአሥሩን ነገድ ልጆች ከአሦር የሁለቱን ነገድ ልጆች ከሌላ ከተማ ወደ ጽዮን እንደሚመልሳቸው ተናገረ፤ ዳሩ ግን ወደ ጽዮን ቢመለሱና አዲስ ቤተ መቅደስ ቢሠሩም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት መቅረጽ እንደማያስፈልጋቸው ገልጾላቸው ነበር። «... ወደ ጽዮን አመጣችኋለሁ ...። በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም። ልብ አያደርጉትም አያስቡትምም አይሹትምም። ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም። በዚያን ዘመን ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ዙፋን ብለው ይጠሩአታል ...» (ኤር. 3፥6-18) ይህ ትንቢት የተነገረው ታቦቱ በኢየሩሳሌም በነበረበት በኢዮስያስ ዘመን ነበር። ልብ በሉ፤ ወደ ኢትዮጵያ ተሠርቆ ተወሰደ ከተባለ ከ359 ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው።

ስለዚህ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሲታይ የተላለፈላቸው ትንቢት ግልጽ ስለ ነበረ እንደገና በሠሩት ቤተ መቅደስ ታቦት ቀርጾ ማስገባት አላስፈለጋቸውም።

ቤተ መቅደስ በሕጉ መሠረት መታነጽ የነበረበት በኢየሩሳሌም ብቻ ቢሆንም ለእግዚአብሔር ቃል ጥናትና እርስ በርስ ለመተናነጽ ለመጽናናትና ለመወያየት የሚገለገሉበትን ምኩራብ ለአምልኮና ለሌላም ማህበራዊ ጉዳይ ሲባል አሥር ወንዶች አይሁድ ባሉበት ቦታ ሁሉ ይቋቋም ነበር። ምኩራቡ መጸለያ ቤት ቢሆንም መስዋዕት ግን አይቀርብበትም፤ ታቦትም ዛሬ በአንዳንድ ቦታ እንደሚደረገው እየተቦዛ አልገባበትም።

የእስራኤል ታቦት ቀጥሎ የተመለከተውን ሥዕል ይመስላል። (ሥዕሉ የተወሰደው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ካዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ነው)



ታቦት

12.6 ታቦቱ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶአልን?

ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ስለ መኖራቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ነገደ እስራኤል ደግሞ ወደዚህች አገር ከገቡትና ከሰፈሩት የሴም ነገዶች ይመደባሉ። እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ከሰሜን እስከ መሃል አገር ተቀምጠው ስለ ነበረ በብሉይ ኪዳን

ትምህርት መሠረት በኢትዮጵያ የአምልኮተ እግዚአብሔር መገኘት ምክንያት ሆነዋል።

እንግዲህ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ነገደ እስራኤል በአክሱም፥ በሽሬ፥ በላስታ፥ በሰሜን፥ በጭልጋ፥ በቋራ . . . ሰፍረዋል። እነዚህ ነገደ እስራኤል በብሉይ ኪዳን እምነታቸው እንዳሉ ክርስትና በኢትዮጵያ በተሰበከበት ጊዜና ከዚያ በኋላ ከመካከላቸው ክርስትናን የተቀበሉ እንደነበሩ ይተረካል። ይሁን እንጂ የእስራኤላዊነት መታወቂያቸው የሆኑትን ባህሎች ለምሳሌ እንደ ግዝረት ያሉትንና ሌሎችንም ባለመተው ከክርስትና እምነት ጋር በማደባለቅ ይዘው ኖሩ። በተጨማሪም ከእስራኤላዊ መታወቂያነት አልፎ ከአረማውያን መካከል ክርስቲያን የሆኑት ኢትዮጵያውያንም ይህንኑ ተመሳሳይ ባህል ተጋርተዋል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ክርስትና ገና ከመጀመሪያው ከእስራኤል ባህል ጋር የተደባለቀ ሆኖ እናገኘዋለን። ከክርስትና በፊት በኢትዮጵያ በሕገ አሪት የተመራ አምልኮተ እግዚአብሔር ነበር ስለሚባለው ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመነሳት በእርግጥ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከመጡት አይሁዳውያን ጀምሮ እንደሆነ ስንመዝን እንደሚከተለው ይሆናል።

1ኛ) ሰለሞን በነገሠ በአራት ዓመት ከሁለት ወሩ ቤተ መቅደስ ለመሥራት መሠረት አኖረ።

(1 ነገ. 6፥11፤ 2ዜና 3፥1-2) 4 ዓመት ከሁለት ወር

2ኛ) የቤተ መቅደሱ ሥራ ሰለሞን በነገሠ በ11 ዓመት ከስምንት ወር ተጠናቀቀ።

(1 ነገ. 9፥36-37) ሥራው የወሰደው ጊዜ 7 ዓመት ከ6 ወር።

3ኛ) ከዚያ በኋላ ሰለሞን የራሱን ቤተ መንግሥት አሳነጸና በነገሠ በ20 ዓመት አጠናቀቀ።

(1 ነገ. 9፥10፤ 2ዜና 8፥1-2) ሥራው የወሰደው ጊዜ 13 ዓመት።

4ኛ) ሰለሞን ከዚህ በማከታተል ለአገርና ለመንግሥት የሚጠቅሙ ሥራዎችን አሠርቶአል።

(2 ዜና 8፥1-18፤ 1 ነገ. 9፥10-28) ሥራዎቹ በምን ያህል ጊዜ እንደተጠናቀቁ አልተጠቀሰም።

5ኛ) ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የሰለሞንን ጥበብ ለማየት የሄደችው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር። የቤተ መቅደሱን ሥራና የአገልግሎቱን ሥርዓት አድንቃለች። የቤተ መንግሥቱንም ውጭና የውስጥ ድርጅት ጉብኝታለች። (1 ነገ. 10፥1-13፤ 2 ዜና 9፥1-12) የጉብኝቱ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ አልተጠቀሰም። ነገር ግን ኢየሩሳሌም በገባች ዕለት ከሰለሞን ፀነሰች ተብሎ ቢታሰብና የእብነ መለክ (የቀዳማዊ ምኒልክ) መወለጃ ጊዜ ዘጠኝ ወር ቢደመርና እንዲሁም፤

6ኛ) እብነ መለክ (ቀዳማዊ ምኒልክ) በ20 ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ አገሩ ተመለሰ ስለሚባል ሂያ ሦስት ዓመት ሲደመርበት አርባ ስምንት ዓመት ከአምስት ወር ይሆናል። ነገር ግን የሰለሞን የግዛቱ ዘመን አርባ ስምንት ዓመት ከአምስት ወር ሳይሆን አርባ ዓመት ብቻ እንደነበረ የተረጋገጠ ነው። (1 ነገ. 11፥41-43፤ 2 ዜና 9፥30-31) እብነ መለክ (ቀዳማዊ ምኒልክ) ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከአባቱ ከሰለሞን ጋር ተዋወቀ የተባለበት ጊዜ ሰለሞን ከሞተ አምስት ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ አልፎ ነበር። መንግሥቱም ለሁለት ከተከፈለ በኋላ የይሁዳ መንግሥት (የይሁዳና የቢንያም ነገዶች) በሰለሞን ልጅ በሮብዓም እየተመራ ነበር። የቀሩት አሥሩ የእስራኤል ነገዶች ደግሞ በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም አመራር ሥር ነበሩ።

ስለዚህ እብነ መለክ (ቀዳማዊ ምኒልክ) ከአባቱ ከሰለሞን ጋር ተዋወቀ፥ ሦስት ዓመትም ሥርዓተ መንግሥቱንና ሥርዓተ አምልኮን አጠና የተባለው ጊዜ ሊገጣጠም የማይችል ሆኖአል። በተጨማሪም እብነ መለክ (ቀዳማዊ ምኒልክ) የእስራኤልን የቃል ኪዳን ታቦት ተሰጥቶት ወይም አሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ አመጣ፤ ያመጣውም በዚሁ ወቅት ነው ተብሎ ስለሚተረክ ምናልባት ትረካው ከሰው አእምሮ በድርሰት መልክ የተዘጋጀ የፈጠራ ታሪክ እንደሆነ የጊዜው አለመገጣጠም ራሱ ያሳየናል።

ምናልባትም ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ፀሐፊው ለማያያዝ የሞከረው ከሊቀ ካህኑ ከአዛርያስ ጋር ነው። ሊቀ ካህኑ አዛርያስ በኢየሩሳሌም ቤተ ክህነት ሲቆጠር የዘር ሐረጉ እዚያው እንደነበረ ስለሚታወቅ ይህ ሰው በውስጥ አዋቂነቱ ታቦቱን ሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶአል የሚሉም አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ በስርቆትም ሆነ በስጦታ ስለ መፍለሱ የጠቀሰው ማረጋገጫ ነገር ምንም የለም።

በተቃራኒው ግን ሰለሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለግል የነበረው አዛርያስ እዚያው በኢየሩሳሌም ትውልዱን እስከ ፍልሰተ ባቢሎን አስቆጥሮአል። (1 ዜና. 6፥10-15) የአይሁድ ምርኮኞች ከባቢሎን በተመለሱ ጊዜም ከካህናት በኩል ዋና ሆኖ የተመለሰው ዕዝራ የዚሁ የአዛሪያስ ተወላጅ እንደነበረ በመጽሐፈ ዕዝራ 7፥3፤ 10 ተጠቅሶአል።

በአገራችን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ታቦታት እንደተሠሩና እየተሰረቁ ለዐረቦችና ለቱሪስቶች እንደሚሸጡ በየጊዜው በዜና ማሰራጫዎችና በጋዜጦች የሚጠቀስ አርእስተ ዜና ነው። የአዲስ ኪዳን ታቦት 2 ቆሮ. 6፥16-18፤ 1 ቆሮ. 3፥16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ማለት በክርስቶስ ያመነ ሰው ነው።

ለሙሴ የተሰጠው የድንጋይ ጽላቶች የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው ሕዝበ እስራኤል ወደ ከነዓን በሚያደርገው ጉዞ በሥርዓት እንዲሄድ ማርና ወተት የምታፈሰሰውን ምድራዊ ከነዓን እንዲወርስ የተሰጠው የብሉይ ቃል ኪዳን ሲሆን በኪዳነ ምህረት (በኢየሱስ ክርስቶስ) የተሰጠው የአዲስ ኪዳን ውል ግን ምድራዊ ከነዓንን ሳይሆን ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ለመውረስ የተጠሩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ዳግም የተወለዱ የቅዱሳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚጠብቱት ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ የፍቅር ቃል ኪዳን ነው።

አንዳንድ ሰዎች እስከ አሁንም የብሉይንና የአዲስን ውል ባለ መለየት ወይም ቃሉን በማጣመም እንደ ልባቸው ሃሳብና ምኞት በመመላለስ እግዚአብሔርን ያመለኩ እየመሰላቸው ይገኛሉ። ቁጥር 15 የጮራ መጽሔት ከገጽ 12 ጀምሮ በአገራችን ታቦት ብለን የምንጠራው ከብሉይ ኪዳን ታቦት ጋር ተመሳሳይነት የሌለው ስለ መሆኑ ባቀረበው ጥናት ሲያብራራ ታቦት ማለት ከድንጋይ ተቀርጾ፥ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉና ለሙሴ የተሰጡ የሁለት ጽላት ማኖሪያ ነው። ነገር ግን በአገራችን ታቦት በመባል የሚጠራው የጽላት ማስቀመጫው ሳጥን ሳይሆን ዝርግ የሆነና እንደ ባለሙያው አሠራር ከዕብነ በረድ ወይም ከእንጨት ተጠርበው የሚሰሩና በመጠናቸው የሚለያዩ ሰሌዳዎች ናቸው። እነዚህም እንደ ብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ታቦት ተብለው የሚጠሩ ሳይሆን በተለያዩ መናፍስትና «እነርሱስ ከማን ያንሳሉ?» በተባሉ ግለሰቦች ስም የተቀረጹና የተሰየሙ ናቸው። የታቦትን አጀማመርና አገልግሎት ከኢትዮጵያ ትውፊታዊ ታሪክ በመነሳት የግዕዝ ሊቃውንት ቤተ አደረ፥ አቤተ አሳደረ፥ አስተዳደረ በማለት ይነሱና

ታቦት የሚለውን ዘር ያወጣሉ። በእነርሱ አባባል ታቦት ማለት ማደሪያ፥ መተዳደሪያ፥ ማሳደሪያ፥ ማስተዳደሪያ ማለት ነው ይላል።

ባለ ታቦት መሆን ባለ መተዳደሪያ ባለ ማስተዳደሪያ የመሆንን ብቃት የሚያመለክት ቃል ነው። ቻርተር ያለው የተሰጠው ቻርተርድ ለመሆን ብቃት ማግኘትን ያመለክታል። ይኸውም አንድን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ሲታሰብ ከአካባቢው ምዕመናን ለመንበረ ጵጵስናው ጥያቄ ይቀርባል። ሁኔታው ተጠንቶ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሊቋቋም የሚችለው ተገቢ የሆኑ መስፈርቶች ሲሟሉ ነው። ለምሳሌ በምዕመናን ብዛትና ብቃት እንዲሁም በገንዘብ አቅም ወዘተ. ማለት ነው። ይህ ከተሟላ የፈቃድ ማስረጃ ይሰጥ የነበረው እንደ ዛሬ በወረቀት ደብዳቤ ሳይሆን በዘመን ብዛት እንዳይቀደድና እንዳይጠፋ ታስቦ ጽሑፉ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የተቀረጸ በግዕዙ «ታቦት» በአማርኛ የተቀረጸ መተዳደሪያ ቻርተር ነበር። በዚህ መመዘኛ በኩል አልፎ ከማዕከል ፈቃድ ማውጣት ጊዜ የሚወስድና የሚያንገላታ ሲሆንባቸው የአጥቢያ ተወካዮች በአቋራጭ ታቦት (የፈቃድ ሰሌዳ) እያስቀረጹ ወይም ተቀርጾ ለሽያጭ የተቀመጠውን እየገዙ መጠቀም ጀመሩ። በእነዚህም የፈቃድ ሰሌዳዎች (ቻርተር) ላይ በ1ኛው ገጽ 1) አህያ ሼር አህያ 2) ኤልሻዳይ 3) አዶናይ ጸባኦት የተባሉ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሱ ስሞችና 4) አልፋ ኦሜጋ (አልፋ ወያ) 5) የውጣ (ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ የስሙ መጀመሪያ በግሪክ ፊደል) የተጻፉ ሲሆን በ2ኛው ገጽ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ስያሜ (ስም) የፈቃጁ ጳጳስ ስም፥ በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ስም፥ አንዳንድ ጊዜም የዕጨጌው የቤተ ክርስቲያኑ ገብዝና የምስለኔው ወይም የባላባቱና የሞቃ ሹሙ ስም ይጻፍበት ነበር በማለት ገልጸታል።

ነገር ግን የሙሴ ፅላት የሚለው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱ ከየት እንደሆነ ለሰው አእምሮ ባልታወቀ የድንጋይ ጽላት በራሱ ዕቅድ ትዕዛዛቱን በእጁ ጽፎ ለሙሴ በሲና ተራራ እንደሰጠው ከዚህ በላይ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ሲሆን ይህንኑም በመጽሐፍ ቅዱስ በዘፀአት 31፥18 የምንመለከተው ነው። ይህንኑ ፅላት ለመቀበል ሙሴ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት በጾምና በጸሎት ከቆየ በኋላ የቃል ኪዳኑን ፅላት ይዞ ወደ ሕዝቡ ሲወርድ የእስራኤል ሕዝብ አሮንን አስገድዶ ጣዖት አሠርቶ ሲሰግድ አይቶ ፅላቶቹን ከተራራው በታች ወርውሮ ሰባበራቸው። ቀጥሎም በዘፀአት 34፥1-17 እንደተጠቀሰው ሙሴ ድንጋይ ጠርቦ እንደገና ወደ ሲና ተራራ እንዲወጣ ካዘዘው በኋላ እግዚአብሔር ራሱ ቃሎቹን በእጁ ጻፈበት።

የብሉይ ኪዳን ጽላት ለአዲስ ኪዳን (ለአዲስ ውል) ምሳሌ ነው። የመጀመሪያውና የተሰበረው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ዓለምን ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥቶ ከምድር አፈር አዳምን ከፈጠረና ሄዋንን ከጐኑ አንድ አጥንት ወስዶ ከፈጠረለት በኋላ እነርሱ ግን በራሳቸው ምርጫ ትዕዛዙን በመተላለፍ መውደቃቸውን ያሳየናል። ሁለተኛው ጽላት ከመሬት ድንጋዮች አንዱን ወስዶ ሙሴ የጠረበውና በኋላም እግዚአብሔር ቃሉን ያኖረበት ምሳሌ በመጀመሪያ የነበረው ቃል ሥጋ ሆነ ፀጋንና እውነትን ተሞልቶ በኛ አደረ (አማኑኤል) እግዚአብሔር ከኛ ጋር፥ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ የተባለው መፈጸሙንና (ቃል) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠማማና ግራር የሆነውን የእኛን ሥጋ መልበሱንና አምላክ የሰውን ልጅ ለማዳን ሰው በመሆን የተገለጸበትን ሁኔታ በጥላ ወይም በምሳሌ የሚያሳይ ነው።


ይህ በዚህ እንዳለ በአገራችን በዜና ማሰራጫዎች እንደምንሰማውና በጋዜጣ እንደምናነበው ከሆነ በዚህ ቦታ ሌቦች የሙሴን ጽላት ሰርቀው ተያዙ፤ ተፈረደባቸውም... ይባላል። ለምሳሌ መስከረም 12/87 ዓ.ም በወጣው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የተጻፈው ይህንኑ የሚገልጽ ሲሆን የአሁኑን የታቦት ፅላት (የፈቃድ ሰሌዳ) አቀራረጽ ከሙራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 15 ገጽ 15 ያገኘነውን ከዚህ ቀጥሎ ለአብነት አቅርበናል፤

ከዚህ ወጪም በሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር ክቃ ያገብርኤልና ከጌራ ምድር ወረዳዎች ፅላቶችን የሠረቁ ሁለት ግለሰቦች የእምስትና የ፬ ዓመታት እስራት እንደተወሰነባቸው ፍርድ ቤት አስታወቀ ።

የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት እንደገለጠው ከሁለቱ ግለሰቦች ጠካከል በ፲፪ኛ ሙቶ ክፍለ ዘመን (በ፯፪ ዓመታት በፊት) እንደተሠራ የተገመተው የሙሴ ፅላትን ደብቆ የተገኘው አሸናፊ ቦጋለ የተባለው ግለሰብ በ፭ ዓመት እስራት እንዲ ቀጣ ሰሞኑን ወስኗል ።

እንዲሁም በጌራ ምድር ወረዳ በዜሮ ፬ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር የሚገኘውን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የበር ቁልፍ በመገንጠል ፅላት የሠረቀው አልታሰብ ይገዙ ፣ የተባለ ግለሰብ ደግሞ በ፬ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የወረዳው ፍርድ ቤት መወሰኑን አስታወቋል ።

እነዚሁ ሌቦች ፅላቶቹን ሠርቀው የተያዙት በሐምሌ መሆኑን ፍርድ ቤቶቹ ገልጠዋል ።



በዚህ ፣ ዘመን ፣ ያለውን ፣ የታቦት ፣ ጽላት ፣ አቀራረጽ ፣ ይህ ፣ ሥዕል ፣ ያመ
ል ፣ (ከቁሉ ፣ ዲምቁ ፣ በቅርቡ ፣ የተገኘ ፣)

ክፍል አሥራ ሦስት

13.1 ሰው ከሞተ በኋላ ለሬሳ የሚደረግ ልዩ ልዩ ሥርዓትና አገናነዝ

በሞት ጊዜ የሚደረጉ ሥርዓቶችን በተመለከተ አገር በቀል የሆኑና ከባዕድ አምልኮ የተወረሱ ባህሎች ጥቂቶች ባይሆኑም፤ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ናቸው በማለት እየተሻሻሉ በመስፋፋት ችግር እየፈጠሩ ያሉ ከክርስትና ውጪ የሆኑ ባህሎችም በርካታ ናቸው።

ለሞቱ ሰዎች ስለሚደረግ ጸሎት የቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ነው የሚባለው ፍትሐ ነገሥት፥ በፍትሐ መንፈሳዊ በዲድስቅልያ አንቀጽ 22 የተጠቀሰውን ያጸናል። ይኸውም በመጽሐፈ ግንዘት ካህናቱ ለሞቱት ሰዎች ሊጸልዩላቸው በመስዋዕትና በቍርባን ሊያስቡአቸው ይገባል ይላል። ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ መላእክት ነፍሳቸውን ለመቀበል ይወርዳሉ። ኃጢያተኞችም ከሆኑ ስለ ሥርየተ ኃጢያት ይለምኑላቸዋል፤ ይማልዱላቸዋል። ንጹሐን ከሆኑ ደስ ይላቸዋል የሚያቀርቡት ምስጋናና ደስታ ስለ ሰው ልጅ ደኅንነት ነው ተብሎ ተጽፎአል። (ሃ.መ. ገጽ 21)

1ኛ) ሰው ሲሞት ማቅ (ጥቁር የሀዘን ልብስ) መልበስ በኢትዮጵያ መቼና እንዴት እንደ ተጀመረ ባይታወቅም ባሁኑ ጊዜ በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠርም እየተለመደ፥ የሚች ቤተ ሰብና የቅርብ ዘመዶች ማቅ ሲለብሱ ይታያል። በተጨማሪም ነጠላ አዘቅዝቆ ማሸረጥ፥ በርኖስ መገልበጥ፥ ፎጣ መደረብ፥ የጥቁር ጨርቅ እራፊ በልብስ ላይ መለጠፍ፥ ጸጉር ተላጭቶ ሴቶች ጥቁር ሻሽ፥ ወንዶች ጥቁር ኮፊያ ማድረግ፥ ፂምን ማሳደግ፥ በመቃብር ላይ አበባ መከመር፥ ሐውልት ማቆም ... የተለመደ ባህል እየሆነ መጥቷል።

ነገር ግን በክርስትና ሃይማኖት ያመነና በክርስቶስ ዳግም የተወለደ ሰው ተስፋው ትንሳዔና ሕይወት ስለሆነ እነዚህን የአሕዛብ ልማዶች ሊከተል አይገባውም። ምክንያቱም ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም የሌለው ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ቃል አንጻር ሊጤን ይገባዋልና ነው።

ከዚህ ይልቅ ሚች ወደ ተሻለው አገር ስለሄደ ነጭ ልብስ ቢለበስ መልካም በሆነ ነበር።

2ኛ) በአገራችን ሰው ሲሞት የተለያየ አይነት የአገናነዝ ሥርዓት ተሠርቶአል፤

ሀ) ሚች ካህን ከሆነ የክህነት ቀሚሱን እንደለበሰ እጆቹ በትእምርተ መስቀል ተመሳቅለው በአዲስ ልብስ ይገነዛል። በድኑ በአዲስ ልብስ ከተጠቀለለ በኋላ በሦስት ክር (ማዕተብ) ይታሠራል። በተጨማሪም ሰባት ትእምርተ መስቀል ያለበት ማዕተብ (ክር) ተሠርቶ ከሰባት ቦታ ላይ ይቋጠራል። ይኸውም አንዱ በራስ፥ አንዱ በእግር፥ አንዱ በቀኙ፥ አንዱ በግራ፥ ሦስቱ በመካከል ሆኖ ይቋጠራል። ይህም ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ አሥራ ሁለት መብራት ይበራል።

ለ) ሚች መነኩሴ ከሆነ እጆቹን በዓይኖቹ ላይ ጭኖ ይገነዛል። ይህም በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ በዓይኖቹ የዚህን ዓለም ክፉ ነገር ከማየት መታቀቡን ለመግለጽ ነው። የፈትሉ፥ የከፈኑና የመግነዙ፥ የመብራቱም ሥርዓት ለቄሱ እንደሚፈጸም እንደ ማዕረጉ ይፈጸማል።

ሐ) ሚች ዲያቆን ከሆነ ግን እጆቹን ግራና ቀኝ አስተላልፎ በሰቅ (ቀበቶ) መልክ በትጥቅ መዋያው ላይ በማሳረፍ ይገነዛል። ይህም ዲያቆን በሕይወት ዘመኑ ለአገልግሎት መፋጠኑን ያመለክታል በማለት ነው። በድኑ በአዲስ የከፈን ጨርቅ ተጠቅልሎ በሁለት ፈትል ክር (ማእተብ) ይታሠራል። የፈትሉ አስተሳሰር የሚደረገው ለቄሱ እንደሚደረገው ይሆናል። ይህም በሚፈጸምበት ጊዜ ሰባት መብራት ይበራል።

መ) ሚች ሕዝባዊ (ተራ ሕዝብ) ከሆነ ግን አውራ ጣቶቹ ታሥረው፥ እጆቹን በብልቱ ላይ ጭኖ ይገነዛል። ይህም በሕጋዊ ጋብቻ ተወስኖ መኖሩን የሚገልጥ ነው። ሥርዓቱ ለሁለቱም ጾታ የሚደረግ ነው። በድኑ የሚታሠረው ግን በአንድ ክር (ማዕተብ) ነው። ለሕዝባዊ የሚበራው መብራት አራት ነው። በማለት «ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም» በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ መጽሐፍ ይገልጻል። በተጨማሪም ይህ መጽሐፍ ከላይ ለተዘረዘረው የአገናነዝ ሥርዓት የጠቀሰው በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 11፥44 ያለውን የማርያምንና የማርታን ወንድም

የአልዓዛርን ሞትና መገነዝ፥ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 19፥4 «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በአይሁድ የአገናነዝ ሥርዓት ከሽቱና ከተልባ እግር ልብስ ከፈኑት» የሚለውን እንደ ዋቢ በማቅረብ በቤተ ክርስቲያኒቱም የሚፈጸመው ሥርዓተ ግንዛት ይህንኑ ትውፊት የተከተለ እንደሆነ ይገልጻል። ስለዚህ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አብዛኛዎቹ የሃይማኖትና የአምልኮትም ሆነ የባህል ሥርዓቶች ከአይሁድ (ከእስራኤላውያን) የተወረሱ እንደሆነ ግልጽ ያደርግልናል።

13.2 ሕያዋን ለሙታን፥ ሙታን ለህያዋን ይጸልያሉን?

ስለ ጸሎተ ፍትሐት በመጽሐፈ ሄኖክ 12፥34 ያለውን በመጥቀስ ከላይ የተገለጸውና «ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም» የሚል መጽሐፍ ሙታንና ሕያዋን በጸሎት እንደሚገናኙና ሕያዋን ለሙታን፥ ሙታንም ለህያዋን እንደሚለምኑ ይገልጻል። ነገር ግን ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር የሚጋጭ ነው። በሉቃስ ወንጌል 16፥19-31 ባለው ክፍል ስለ አንድ ባለጠጋ ሰውና አልዓዛር ይባል ስለ ነበረው በቅስል የተመታ ድሃ ሰው ሞት ጌታ ኢየሱስ በምሳሌ ሲናገር «. . . ድሃውም ሞተ መላዕክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት። ባለጠጋውም ሞተና ተቀበረ። በሲዖልም በስቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ፥ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን ልጄ ሆይ፥ አንተ በህይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ አልዓዛር . . . በዚህ ይጽናናል አንተም ትሰቃያለህ።» በማለት በመካከላቸው ገደል መኖሩን እንደገለጸለት እንመለከታለን። ከዚህ በኋላ የሞተው ሀብታም ሁለተኛ ጥያቄ ለአብርሃም ያቀርባል። «. . . እንኪያስ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ አምስት ወንድሞች አሉኝና እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ስቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ። አብርሃም ግን ሙሴና ነቢያት አሉአቸው እነርሱን ይስሙ አለው። እርሱም መልሶ . . . ከሙታን እንኳን አንድ ቢነሳ አያምኑም አለው» ይላል። ስለዚህ ሙታን ለህያዋን ህያዋን ለሙታን ይጸልያሉ (ይለምናሉ) የሚለውን ሃሳብ መጽሐፍ ቅዱስ አይቀበለውም።

«ተግሣፅና ምክር» በሚልና በዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ በተጻፈው መጽሐፍ «ሕያዋንና ሙታን አይተዋወቁም» በሚል ርዕስ ጻድቃን ከሞቱ በኋላ ምንም ብንለምናቸው ሊሰሙን እንደማይችሉ ተጠቅሶአል።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ስንመለከት ሕያዋን በአፀደ ሥጋ ያሉና ሙታን በአፀደ ነፍስ ያሉ ጨርሶ እንደማይገናኙ እንመለከታለን። በአፀደ ነፍስ ያሉት ሙታን እንኳንስ ባዕዳንን አባት እናቶቻቸውንና ዘመዶቻቸውንም አያውቁአቸውም። (ኢዮብ 7፥10-19፤ 14፥21)

ስለዚህ ታላቁና ነጩ ዙፋን ተዘርግቶ ፍርድ እስኪከናወን ድረስ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖችና በወንጌል ምክንያት የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ጻድቃን ሰማዕታት የዕረፍት ስፍራ በሆነው በገነት ከጌታ ጋር በደስታ ይቆያሉ። ነገር ግን ለወንጌል ባለመታዘዝ በእግዚአብሔር ያላመኑና በቃሉ ያመፁ ኃጥአን በሲዖል ውስጥ በመሆን ፍርዳቸውን ይጠባበቃሉ እንጂ ከሕያዋን ጋር የመገናኘት መስመርና መንገድ የላቸውም። (መክ. 9፥3-6 ኢዮብ 14፥12 ኢሳ. 38፥10-18 ራዕይ 20፥11-13፤ 22፥11-15)

አንዳንድ ሰዎች ፃድቃን ሰማዕታት እንደሚያማልዱአቸው በተነገራቸውና በተማሩት መሠረት ቢያምኑም በመጽሐፍ ቅዱስ ግን በክርስቶስ ከተገኘ ጽድቅ በቀር ከሰው ዘር ፃድቅ አንድ እንኳ እንደሌለ (በሮሜ 3፥10-18፤ ኢሳ. 64፥6) ተገልጾአል።

ጥቂት ሰዎች ደግሞ በፃድቃን ስም ሌሎችን ብታበሉና ብታጠጡ ወይም ማናቸውንም ነገር በስማቸው ብታደርጉ የፃድቁን ዋጋ ትቀበላላችሁ ብለው ያስተምራሉ። የእግዚአብሔር ቃል ግን የምታደርጉትን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት ይላል። ፍጡራን ለፍጡራን የማይገባቸውን ክብር እንዲሰጡ አልታዘዙም። በተጨማሪም «ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» (ራዕ. 22፥12)። «አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና» (ገላ. 6፥7)።

ከጳውሎስ የበለጠ እስከ ሦስተኛ ሰማይ የተነጠቀ ጻድቅ ማነው? እርሱ እንኳን ያንን ሁሉ የእግዚአብሔር ምስጢር ያየና ጸጋ የተሰጠው ሆኖ ሳለ ለእርሱና ለበርናባስ ክብር መስዋዕት ሊያቀርቡላቸው ሲያዘጋጁ ሰዎቹን ተቆጥተው ይህንን ማድረግ እንደማይገባቸው ተናግረዋል እንጂ የኛን ስም እያነሳችሁ ብሉ ጠጡ ብለው ጨርሶ አላስተማሩም። እንግዲህ ከጳውሎስ ወዲያ የትኛው ሐዋርያና ጻድቅ ተገኝቶ ነው በስሙ ድግስ ተደግሶ በማብላት ለመጽደቅ የሚሞክረው? ሌሎችን ለማብላትና ለማጠጣት የማይችልና የኑሮ ችግር ያለበት ደሃ ብቻ ሊፈረድበት ነው ማለት ነዋ! (1ቆሮ. 10፥31፤ ሐሥ. 14፥13-18፤ 1ቆሮ. 3፥6፤ 10፥31)

13.3 ሰው ከሞተ በኋላ ሬሳን የማጠብና የሽቱ ማርከፍከፍ ሥርዓት

በኢትዮጵያ ውስጥ ክብሉይ ኪዳን ተወርሶአል በሚባልና አሁንም ሥር ሰድዶ እየተሰራበት ያለ መጤ ባህል ሰው ሲሞት መጀመሪያ በተራ ውሃ ይታጠባል። ቀጥሎም በተፀለየበት ውሃ ይታጠባል ይላል። በውሃው ላይ ስለሚፀለየውም የፀሎት ዓይነት «ሃይማኖት የለያየንን መቃብር አንድ አያደርገንም» በሚል መጽሐፍ እንደተገለጸው፤

1ኛ) በአንተ ደኅነተ ነፍስ (ለነፍስ ደህንነት) የሚለው መስተበቊዕ፤

2ኛ) መቶ ሃምሳው መዝሙረ ዳዊት፤

3ኛ) አሥራ አምስቱ መኃልየ ነቢያት፤

4ኛ) አምስቱ መኃልየ ሰለሞን፤

5ኛ) ወንጌል ዮሐንስ፤

6ኛ) ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን ናቸው ይላል።

በዚህ መልኩ የህጽበት ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ሽቱ ይቀባል (ይርከፈከፋል) ይህም መልካም ሽቱ የመልካም ሥነ ምግባር ምሳሌ ስለሆነ በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩ ሰዎች ሥጋቸው ፈርሶ፥ በስብሶ በመቃብር የማይቀርና ነፍሳቸውም በመዓዛ ገነት የምትኖር መሆኑን ለማመልከት ነው ይለናል።

ነገር ግን የክርስትና ሃይማኖት መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃልና ...።» (1 ዮሐ. 1፥7) ይላል እንጂ ሰው ከሞተ በኋላ ወይም በህይወት እያለ በውሃ በመታጠቡ የነፍስ ደህንነት ያገኛል አይልም።

በሌላም በኩል አንድ የሃይማኖት ክፍል በተመሳሳይ ሁኔታ ሥርዓት አድርጐ እያንዳንዱ የሃይማኖቱ ተከታይ በቀን አምስት ጊዜ ከጸሎት በፊት እጁን፥ እግሩን፥ ፊቱን (ዓይኑንና ጆሮውን) አፉን፥ እንዲሁም የመጸዳጃ የሰውነት ክፍሉን በውሃ ታጥቦ ነጽቶ ወደ ፈጣሪ እንዲጸልይ ያዛል።

ያም ሆነ ይህ የተፈጥሮ ውሃ ለነፍስ ደህንነት ምንም ዓይነት እገዛ ሊያደርግ አይችልም። ይልቅስ የውስጥ ንጽህና እንጂ የውጪ ጽዳት ለጽድቅ ስለማይሆን እግዚአብሔር ባዘጋጀው የደህንነት መንገድ በንስሐ ህይወት ከአመጽ፥ ከክፋትና ከበደል በመመለስ ከእግዚአብሔር ጋር

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እርቅ መፈጸም ያዋጣል። ልጁ (ወልድ) ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። (1 ዮሐ. 5፥12)

በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያኒቱ ፈቃድ በተዘጋጀው በዚሁ ከላይ ስሙ በተጠቀሰው መጽሐፍ ስለ ሐውልት ምረቃ ሲጠቅስ በሙታን መቃብር ላይ በተገነባው ሐውልት ዙሪያ ሕዝብ ተሰብስቦ ሐውልቱን ግምጃ በማልበስ ፀሎተ አኰቴት እንደሚደረስ ተጠቅሶ ይህ ባህል ግን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያልተፈቀደ እንደሆነ ተገልጾአል። እንደዚህ ዓይነት የሙት ቤት መበዝበዣ የሃዘን ማደሻና የሬሳ መወደሻ በመቃብር ላይ የድንጋይና የዕብነ በረድ ክምር አሠርቶ ፍታት፥ አርባ ወይም መቃብር ምረቃ የሚባለው ባዕድ ባህል ከጣዖት አምልኮ ባልተለየ ሁኔታ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን፥ ሕዝቡንም የሚጐዳ ነው። ስለዚህ ውግዘቱ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ቢተረጐም መልካም እንደሚሆን ስለሚታመን ሕዝቡም እውነትን ተረድቶ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት እንዲያመልክ ያደርገዋል።


13.4 ስለ እምነት ነፃነት የተላለፈ መመሪያና ተጻራሪዎቹ

ከኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ግንቦት 14/1984 ዓ.ም. በቁጥር ጀ10/55 «በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን ለማረጋገጥ» በሚል ርዕስ ያለፈው መንግሥት የሕዝቦችን የሃይማኖት ነፃነት በመግፈፍ በገዛ አገራቸው እንዲሰደዱና እንዲጨነቁ በማድረግ በሃይማኖቶች መካከልም ልዩነትና ግጭት ይፈጠር እንደነበረ በመጥቀስ የዚህ ዓይነቱ የሰብዓዊ መብት ረገጣ አገሪቱን በወጪው ዓለም ሲያስወቅስ መኖሩን ይገልጻል። ይሁን እንጂ የሽግግር መንግሥት ባጸደቀው ቻርተርና በተቀበለውም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ውሳኔ መሠረት የእምነት ነፃነትና በሰላም የመሰባሰብ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ ተደንግጐ ሳለ በአንዳንድ ስፍራዎች ፀረ-ሰላም ኃይሎችና በሃይማኖት እኩልነት የማያምኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ከእነርሱ እምነት የተለየ እምነት ተከታዮች በሆኑት ላይ አለመግባባትና ያልሆነ ቅራኔ በመፍጠር ለሰላምና መረጋጋት ጠንቅ መሆናቸው መደረሱን ገልጸዋል።

ከዚህም የተነሳ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የሃይማኖትን እኩልነትና የቻርተሩን መንፈስ በሚገባ ባልተረዱ ክፍሎች አድማ አነሳሽነትና ፀረ-እኩልነት አቋም የተነሳ ለሌሎች የመቃብርና

የመሰብሰቢያ ቦታ እንዳይሰጣቸው፣ እስከማድረግ እንደተደረሰ በመግለጽ ይህ ሁኔታ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከተጐናጸፉትና ከሚታገሉት የዲሞክራሲ መብቶች አኳያ በምንም ዓይነት መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል በማሳወቅ ማንኛውም ክፍል ፀረ-ሰላም አቋም እስከሌለው ድረስ የእምነት ነፃነቱ ሙሉ በሙሉ የተከበረ መሆኑ ታውቆ ይህንን በሚቃረን ማንኛውም ፀረ-እምነት እንቅስቃሴ ላይ አስፈላጊው ጥንቃቄና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱና ከአቅም ውጪ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ሪፖርት እንዲላክልን እናስታውቃለን በማለት ለክልሎች በሙሉ ሲገለጽ በግልባጭ ለጠቅላይ ቤተ ክህነትና ጽ/ቤት፣ ለእስልምና ጉይማኖት ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ፣ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤትና ለወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ተገልጾአል።

ከላይ የተጠቀሰው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ደብዳቤ ከተላለፈ ከአንድ ወር ተኩል ገደማ በኋላ ከአዲስ ዓለም ርዕሰ አድባራት ደብረ ፅዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በወንጌል አማኞች ላይ አመጽና ፀረ-ዲሞክራሲ የሆነ አድማ ለማነሳሳት በአካባቢው ለሚገኙት ዕድሮች ሰኔ 26 ቀን 84 ዓ.ም. በቁጥር 310/84 በተጻፈ ደብዳቤ ጥሪ አድርገው የተጻፈላቸው ግለሰቦች ሳይሰበሰቡ ስለቀሩ በድጋሚ ሐምሌ 7 ቀን 1984 ዓ.ም በቁጥር 334/84 የተጻፈ ተመሳሳይ የአድማ ደብዳቤ ከእነርሱ ሃይማኖት የተለየ እምነት ተከታይ የሆነ የወንጌል አማኝ ቢሞት እንዳይቀበር ወደ ሌላም ቦታ ሬሳው እንዳይጓጓዝ እንዲከለከልና እቤቱ እንዲበሰብስ ይደረግ በማለት ያስተላለፉትን ኢሰብዓዊ የአድማ ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ይመልከቱ።



ቁጥር 334/84

ሐምሌ 7 ቀን 1984 ዓ.ም

ለ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት

ጉዳዩ ስብሰባ ስለማድረግ

ከላይ በተጠቀሰው ጉዳይ ለመወያየት ሰኔ 29 ቀን 84 ዓ.ም. በቁጥር 310/84 የፀፍ ጉባኤያችሁን ያስተወሰን፣ ስለሆነም በተመለከተው ቀጠሮ ባለመገኘታችሁ እንደገና ቀጥሮ ለመላክ ተገደናል።

ስለዚህ ቅርንጫፍ የሆኑ ሁሉ ለሐይማኖቱ ተቀፅር ቃል ሲገቡ ስብሰባ ሲፈቀድላቸው ተገቢ ባለመሆኑ በጥር ቁ. ሰ/ጉ/ሥ/ቢሮ ተሰጥቶአችሁ ሁለት ሁለት ሰባልሰኞች በመጠመመር ሦስት(3) ሪፖርት ባለመሆን ሐምሌ 13/84 ዓ.ም ጥዋት በደ ሰዓት ስብሰባ አለማዳደር ይህንን ደረሰ እንደተሰጠ፣ ስብሰባ ማድረግ አይቻልም!!

ለተላኩ፡-


① - ማንም፡ ከገንዘቡ ጋር፡ ሳይሰጥ ሳይቀበል፡ ሆነ፡ ሰጭ ግራ ቻ፡ እንዲሁም ከተ
- ማንም፡ ለሌላ ሰው፡ መሬ ማ፡ እንዲያስረክብ፡ ከሆነ፡ ሰጭ፡ እንዲያገኘ
- ሟ ንም፡ ለሰጭ፡ ጉዞ፡ ላይ፡ ከጉዞ ቻ ሁ፡ ሳይ ቃ ለን

② - ከተገኙ ሰው፡ በተገኘ ው፡ ቃ ው፡ ሪፖርት፡ እንዲ ለጉ

③ - ለ ው፡ ከሚ ተሰ ው፡ ነገሮች፡ ይመ፡ እንዲ ያ ጉ ሪ፡ ወዲ ሬ ላ ም፡ ቦታ፡ እ ጋ ጉ ለ
እንዲያደ ጉ ሪ፡ መ ከ ለ ከ ለ፡ (የሰ ቤ ተ ሰ ው፡ ይ ገ ለ ጽ ለ ን)።

«አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» (ዘፍ. 3፥19) ተብሎ የተጻፈውን በመቃወም አንዳንድ የሃይማኖት ተከታዮች ነን ባዮች «ከእኛ ሌላ . . .» በማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ ስፍራ መንግሥት ለሕዝብ መካነ መቃብር በከለለውና ለእነርሱ ብቻ ተብሎ ተወሰኖ ካርታና ፕላን ባልተሰጣቸው፥ ግብርም በማይከፍሉበት መሬት ሙታን እንዳይቀበሩ በማን አለብኝነት የመንግሥት መሬት ባለ ቤት፥ ባለ ንብረትና ባለ ይዞታ እንደሆኑ በመቁጠር ግርግር ሲያነሱና አንዳንድ የሙታን አስከሬኖችንም ከተቀበሩበት ቆፍረው በማውጣት ለጅብ ሲጥሉ አልፎ አልፎም በእሳት ሲያቃጥሉ ተስተውለዋል። ይህም በመሠረቱ የከፋ ኃጢአት ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መቃወም ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ የተጠቀሰው የእምነት ነፃነትና የሃይማኖት እኩልነት ማረጋገጫ ከተላለፈ ከሦስት ወራት ገደማ በኋላ ነሐሴ 24/1984 ዓ.ም. በዱብቲ ከተማ «በመስጅድ ሰላምና በቅድስት ማርያም ኮሚቴዎች የወጣ የአቋም መግለጫ» በሚል ርዕስ የሁለቱ ሃይማኖት ተወካዮች ተፈራርመው ከእነርሱ እምነት የተለየ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ሆኖ የተገኘ ሰው በማንኛውም ማኅበራዊ ኑሮ እንዳይሳተፍ ሲሞት እንዳይቀበር . . . በማለት የመንግሥትን መመሪያ በመቃረን በተዘጋጀ ባለስድስት ነጥብ የአድማ ውሳኔ ላይ የሁለቱም ሃይማኖቶች ማህተሞች ጐን ለጐን ታትመዋል። ማህተሞቹ የተደረጉበት የተወካዮቹ የጋራ መግለጫ ነው የተባለው የአድማ ውሳኔ ከዚህ በታች የተመለከተው ነው።



ቀጥሎም ይኸው የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ደብዳቤ ከተላለፈ ከአንድ ዓመት ተኩል ገደማ በኋላ የአሶሳ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የ1986 ዓ.ምን. የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በዐል ምክንያት በማድረግ መንፈሳዊ ኮንፍራንስ ያዘጋጀች መሆኑን በመግለጽ ፈቃደኛ የሆነ ማንም ሰው በነፃ መካፈል እንደሚችል ለማስታወቅ ከአራት መስመር ያልበለጠ ደብዳቤ ጽፈዋል።

የአሶሳ ሙሉ ወንጌል አማኞች
ቤተ ክርስቲያን
ASOSSA FULL GOSPEL
BELIEVERS CHURCH

ለ፡ _____

ለጠቅላይ

ጉዳዩ፡_ በዐ_ወጋኔፋጋዐ_ፕፅ_ይሠኔዐ::

የአሶሳ ሙሉ ወንጌል አማኖች ቤተክርስቲያን ከታህሣሥ 28 ቀን 1986 ዓ.ም እስከ ጥር 1 ቀን 1986 ዓ.ም ድረስ የሚቀጥል መንፈሳዊ ሰብሰባ አዘጋጅ ስለሆነ::

ስለዚህ ክ/ከተማ ሠራተኞች ስገናፉገሱን መከፈል የሚችሉ ወሀነን በደ በታ አየገለጸገ ገርገፉ የሚደምረው በ28 /4/86ዓ.ም ከቀኑ በ9:00 ሰዓት ይሀናል:://xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx//

"ከመላዎታ ጋር"

ከለፉ አለያስ

የአሶሳ ሙሉ ወንጌል አማኖች ቤተክርስቲያን ያገ የበላገለያም ሽገን ሰብሰባ

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው ።
ዕብራ. ፲፫፡፰
JESUS CHRIST IS THE SAME YESTERDAY TODAY AND FOR EVER.
HEB 13:8

ነገር ግን ለዚህ ደብዳቤ ምላሽ ነው ተብሎ ከአሶሳ ሀገረ ስብከት በ27/4/86 ዓ.ም. በቁጥር 420/2704/86 የተጻፈ አንድ ገጽ ሙሉ ብርቱ ማስጠንቀቂያ አንባቢያን እንዲያገናዝቡ እነሆ፤

ቁ/ጉ 420/2704/86

ከአገልጋዩ የሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን አማኞች

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

ባለሥልጣኑ አብ ሠመልድ መመንፈስ ቅዱስ ይ ኢምላክ ከሚሄን! በመጽሐፍ ለማቅም ምዴርን ባቃሉ ያፀና ፤ ቃሉ የማያልፈው ኢምላክ ፣ ይህኑ የሙቅ ምህረቱ ቀሰፃ ፣ ቁጣው የዘገየ አልፋመ ከሚጋ የሆነው ኢምላክ ሳቁጣጥንን አስር ሕዝብ ከርስቲያንን ወዴ አንዲት ሳዴማ ምት ወደ አንዲት ቤተክርስቲያን ጉባ ሠራ ለማታ ባስጠቦ ቃሉ ፣ ቦዘርዊ ሳዴሠን በመንፈሳዊ የሚንዐሩ ቃለ መንንልን ስያሠቃቅ ብቻ ሳንሆን በተግባሩ ተሠጊሚዎቹ ያዴርገን ዘንዴ እርቱን ቤዛዴት አብቃን አማላጅንት በመቢያነ ቅዱሳን መሰ እንስትንና ፃዴቃን ለማፅ ታትን ተሠፋኪነት በ ማመን ዴሩን ደብዳቤ ፀፎነዋቸኋል::

በመሠረቱ ከሁሉ የምንረዳዎና የጀሚያሳዝነው እናንተ የሉተር ልጆች የትነት የ ሂደ ኢምላት አመት ሪድሚ ያነቡሙ በኑሩቁ ቴምህርትን ማማገር የታደላቸሁ በዚቂደ ሉትሩስን አባቶቹ ተመማቹ አከማቹ ከአማታቹሁ ከአርዮስ ጋር ከእንዲት ቤተ ክርስቲያን ጉባ ሠረ የታነሊሁ ችሁ አማኞች መሆናቸሁን እያመሰከቹሁ ቁጻማዊዉንና ደዛራዊዉን የአሥዮዴደ ኦር ዮክስ መሥፋሀይ ቤተ ክርስቲያን ቃለ አማዚአኩሩር እናሰ ተሠጠቹሁ ሃሪ ታህሳስ ፳፯/86 በቁጥር ፮፰፬-ወ/ሠፋ/86 የተፃፈ ደብዳቤ መሰደደጻችሁን ምን ያህል ግምት ብቻ ሰጥታቹሁ ከመዲሁ የሉሳን ሳለሆነ ለእንዴና ሰመጽፍሮች ከሠራሀ ግሩነት ምግባር የመጣታቹሁ ከሆነ ያ ሕገኔያ የሰደራ ፅዋ አንዲወሰት ንግገሙ እንዲትሊዱት እየገለፀንላቹሁ ፡፡ ልጅ እናቷን ምጥ አስተዛዚ ፫" የተገለጠ ተሊት በእናንተ ላይ የተዴፀመ ስለሆነ እናንተም ወዴፉቹ ሳይሆን በፅተርተናው- ዴሷ ተሰሎስ ታድላቹሁ ሊት ታቀን ስለምትሠራውዴ እና ደግሞ መጋጸላቹን ከእናንተ አመንርሞ ከሆነ ያ ከእህቶቻቹን ጋር ሳይሆን ሐዋርያው ጠርሳነ ዓሊም ቅዱስ እውለሰስ ለኤፌሶን ሰዎች እንዲህ ሲል ካለው ጋር ስለሆነ እንድትሊዱትና ወዴ ቀድሞው የእጊታቹሁ ቤት እንድትመለስ በተ ክርስቲ ያንተ አስፍቀን ዘርጊታ በርዋን ሸፍታ እየጠበቀቹሁ መሆኑን ከመ ዲሉ አነገልፃለን፡፡

የእግሬ ቃል ኤር፲:9-10 እንዲህ ይላል:: እግዚአብሔርም እነሆ ቃሉን በአፌህ አደረ ሰጥሁህ ዘንድ ፤ እነሆ ሕዝቦችንና መንግሥታትን ላይ ዛሬ አሾርሬሃለሁ ፤ ታፈርሳለህ ታፈራርሳለህ ታጠፋለህ ትገለብጣለህ፡፡ ዛሬ በጴጥሮስ አማር ቁጥጥተው ሚስዲኖ መሰክታት ሚስተሚሩና መገለጫ ማቴ ፲6፡ ፲9 ቃል ዛሬ ላሉት ካህናት እነሩ እንድ ይርስ እሥኮነኝ ይርሶ መንፈስ ሰጥቶ እኛ ለምሰው ለእርዮስ ልጆች ይናተሳጠ መ ሆኑን እንዲትሊዱት እየገለፀንላቹሁ ቅዱስ ጳውሎስ "የመጀመሪያ ኢምኒታቹሁን አስክ መመጨረሻ ጉድን ቀጥ ሠንጠብቅ የእርለቶስ ተካፋዮቹ ሀነኖል" ፩ጠ ፫:፲፭ ብሎ ይህን ጽር በመነሳት ቅዱስ ተሰፃኖቹ የፃፍሳቹሁ ይናተሳጠ መሆኑን እንዲትሊዱት እና እናንተ የምሠሊቹን ቃለ ሰታስ ተላፊሉ ያለተ መሆናቹሁ መሆኑቹሁን አውቃቹሁ ከእንዲህ ሳዴነቱ ስያመናሮ ጉሬ እንድ ቴታቀቡ ኣየኳሳስጡን ይህ ግዴነን ግን በቅሎ ማሰሪያ [illegible] በራሳ ላይ አሳጠርቹ የተገለበጡ እናንዲትቀቡ እናሳስባለን::

መሰከበዚት ለእግዚአብሔር
የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ
ኢ/መልአክ ይልማ እንየው ሙሉ

13.5 በተቀበረ ሬሳ ላይ የተደረገ ኢሰብዓዊ ድርጊት

በአማራ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር በደብረ ሲና ከተማ አሰለፈች መንገሻ የተባለች የ25 ዓመት ወጣት በ26/1/91 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ለወንጌል አማኞች ከመንግሥት ለመካነ መቃብር ተከልሎና ድንጋይ ተተክሎ በተሰጠ መሬት ላይ ስትቀበር የሟች ቤተሰቦች የመቃብር ሐውልት አሠርተው ነበር።

ይሁን እንጂ መሬቱ የኛ ነው ባዮች ቀብሩ እንዳይፈጸም ቢያውኩም አስከሬኑ በአካባቢው ፖሊስ እገዛ ተቀበረ። ከአስር ቀናት በኋላ የተሠራው የመቃብር ሐውልት ተፈነቃቅሎ ፈርሶ አስከሬኑ ከመቃብር ወጥቶ ስለተገኘ ሁኔታው ለአካባቢው ፖሊስና ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ተደረገ። ፖሊስና ቤተሰብ እንዲሁም ለጉዳዩ ተቆርቋሪ የሆኑ ግለሰቦች በየዋሻውና በየገደሉ ሲፈልጉ ሰንብተው አስከሬኑ በአንድ ገደል ውስጥ ተጥሎ በጉቶ እንጨት ላይ ተንጠልጥሎ ተገኘ። ሬሳው በስፍራው በድጋሚ ቢቀበርም ቀደም ሲል ሲያዉኩና ሲፎክሩ የነበሩ ግለሰቦች ሁለተኛ ጊዜ አውጥተው እንዳይጥሉ በመስጋት ራቅ ወዳለ ስፍራ ቤተሰቦችዋ ወስደው ለሦስተኛ ጊዜ እንዲቀበር አድርገዋል። የወንጌል አማኞቹ ይህንኑ ኢሰብዓዊና ሕገወጥ ድርጊት በየደረጃው ላሉት የመንግሥት አካላት በተለይም ለጣርማ በር ወረዳ በ16/2/91 ዓ.ም. አመልክተው ይህንን አሳፋሪ ድርጊት የፈጸሙትን ግለሰቦች ተከታትሎ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ሲገባ የተሰጣቸው ምላሽ ለወደፈቱ ጥበቃ አድርጉ የሚል እንደነበረ በመግለጽ ሕገ መንግሥቱ ባጐናጸፋቸው የእምነት ነጻነት መሠረት የሕግ ጥበቃና ክትትል እንዲደረግላቸው ለሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ህዳር 2/1991 ዓ.ም. አመልክተዋል።

ከሽግግር መንግሥት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ስለ ሃይማኖቶች እኩልነትና ስለ ሰብዓዊ መብት አከባበር በተላለፈው መመሪያ መሠረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለእንዲህ ዓይነቱ ኢሰብዓዊ ድርጊት ትኩረት በመስጠት ክትትል ካላደረጉ መመሪያው በጽሑፍ ብቻ የተላለፈ ሆኖ ይቀራል እንጂ ተግባራዊነት ሊኖረው አይችልም።

በተጨማሪም ይህንኑ ድርጊት በፈጸሙ ወንጀለኛ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ትምህርታዊ ቅጣት ካልተሰጠ ተመሳሳይ እኩይ ተግባር የሚያስፈጽሙ የሚፈጽሙና ለመፈጸም የሚቃጡ ከአድራጐታቸው ሊታቀቡ እንደማይችሉ በገሃድ የታወቀ ስለሆነ ከሰው ልጅ ክቡርነትና

ከሰብዓዊ መብት አኳያ የሚደረገውን ምርመራና የሚወሰደውን የአፈጻጸም እርምጃ በመከታተል ላይ ያሉ ብዙ ሰዎች ናቸው።

ስለዚህ በ1948 እ.ኤ.አ. የወጣውንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተቀበለውን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ የኢትዮጵያ መንግሥት ሙሉ በሙሉ የተቀበለው በመሆኑ በዜጐች ሕልውናና መብት ላይ እየተደረገ ያለው ኢሰብዓዊ ድርጊት እንዲወገድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ሕዝቡ ሊያተኩሩበት እንደሚገባ የታመነ ነው። ስለዚሁ ጉዳይ «ሕይወት» መንፈሳዊ ጋዜጣ ታኅሣሥ 1991 ዓ.ም «በደብረ ሲና አንድ አስከሬን ሦስት ጊዜ ተቀበረ» በሚል ርዕስ ያጠናቀረውን ዜና በከፊልና የሚች ፎቶግራፍ እነሆ፣

በደብረሲና አንድ አስከሬን ሦስት ጊዜ ተቀበረ

መስከረም 25 ቀን 1991ዓ.ም ጌታን አምና የነበረች ውጣት አሰለፈች መንገሻ አዚህ ሚሳም በሞት ዘመዳዊ መንግስት በሰጠን ቦታ ላይ የቀበር ስነ ስርዓቷን ፈፅመን የሚች ቤተሰብም የመታሰቢያ ሐውልት አሰርተው ነበር። ይሁን እንጂ መቃብሩን በመፈንቀል ከተቀበረችበት ከአስር ቀናት በኋላ አስክሬኑን ጨማውጣት መጣሉን ሰማን። ይህም መሆኑን ስናውቅ በስተማይቱ ያለን አማኞች ተሰብስበን በጌታ ፊት በመውደቅ የተጣለበትን ቦታ ጌታ እንዲመራንና እንዲረዳን አስክሬኑንም ፀአሽችን እንዲሰጠን በመጠየቅ ፍለጋ ወጣን። ከፀፀ ፍለጋ በኋላ አተቀበረችበት በግምት ከ150-200 ሜትር ርቀት በሚሸፐ የደል አፋፍ ላይ ተጥሎ ያልምንም ችግር አስክሬኑን ከነሳጥኑ አገኘነው። ከዚያም የፖሊስ አርዳታ በመጠየቅ ቀከተጣለበት ቦታ የፎቶግራፍ መረጃ በማድረግ አስክሬኑን ወደ ነበረበት እንዲመለስ አድርገን ለሁለተኛ ጊዜ ጥቅምት 18 ቀን1991 ዓ.ም ፖሊስ ባለበት የቀበር ስነ ስርዓቷ ተፈፅሟል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጠላታችን ሰይጣን ስራውን ጌታ ስላፈረሰበት በሌላ መልኩ ሰደቱን ለመቀጠል ሞክሯል። ህፃረተሰቡን ለፅድር በማሳደም ከአማኞች ጋር ያለውን ማንኛውንም ማህበራዊ ግንኙነት እንዲያቋርጡና እንዲሁም ፀርነግ ፅልትሰና በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች ምንም ዓይነት ህፃረት እንዳያደርጉ ግዴታ እንዲገቡ ተደርገዋል። ከእነዚህም ግዴታዎች መካከል የሞቱ አማኝ ዘመዳቸውን እንዳይቀብሩ እንዳያዝኑና፣ እንዳያስተዛዝኑ ምንም ዓይነት የፅድር ዕርዳታ እንዳያገኙ የግዴታ ውል ፈርመዋል።

በአሁኑ ጊዜ ፀደብረሲና የመካነ ኢየሱስ፣የመሰረተ ክርስቶስና የሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያናት ፀመንፈሳዊ ፀከተማው የምንሸሽ ክርስቲያን አማኞች የተፈፅመውን ሁኔታ በሚመለከት የደም ፅሁት በማወደ የዲያቢሉስን ፅትድና ዓላማ እገዚአብሔር እንዲያፈርስና እንዲገልጥ በፅሎት በእንድ ልብ አቅርበናል። ከዚህ በተረፈ ለወረዳው ፖሊስ ፅ/ቤት ለክፍለ-ከንፅፍ ለወረዳው ምክር ቤት ለዞን መስተዳደርና ለዞን ፖሊስ መምሪያ ሪፖርት በማድረግ ወንጀሉን የፈጸሙትን ሰዎች ተከታትሎ እንዲይዝና ርምጃ እንዲወስድ ጠይቀናል።



ለመንግስት በኩል ሽወረጓው የሚገኙ ፖሊስ፡ ምክር ቤትና ሌላም የሚመለከተው ክፍል ምንም ዓይነት እርምጃ አስካሁን ድረስ አልወሰደም።

የዞን መስተዳደርና የዞን ፖሊስ መምሪያ የወሰደው ርምጃ ለወረዳው ፖሊስና ምክር ቤት ደብዳቤ በመፃፍ ወንጀሉ ፀትክክል ተፈፅሞ ከሆነ ወንጀሉን የፈፀሙትን ተከታትለው ፀመያዝ ለሕግ እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ልከዋል። ሆኖም ይህ ሁኔታ ለውጥ ያላሳየ በመሆኑና አሁንም ፀድጋሚ የተቀበረውን አስክሬን ለማውጣትና የማንደርስበት ቦታ ለመጣል ወፊና ሻቻ መኖሩን የሰሙት የሚች ቤተሰቦች አስጋት አሰፊኑን ፀማውጣት ክስተግው ፀ5 ኪሎ ሜትር ርቀት ፀሚሸፐ ክተማ ለሦስት ጊዜ እንዲፀቀፁ ጥያርጓል፡የሚች ቤተሰብ አእንግዲህ የምንቀበረው አዚሁ ይሆናል በማለት ሲናገሩ በመሰማታቸው አኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሰዎች ተልከው አስክሬን ከተቀበረበት ቦታ ኣውጥተው ፀእነርሱ መቃብር ፀድጋሚ እንዳይቀብሩና ቁርባኗንም እንዳያውጡ ቤተሰቦቿ ተጠይቀው ነበር። ነገር ግን ቤተሰቦቿ «አፈር አፈር ነውና አንድ ጊዜ ቀብረናል አውጥተን አናመጣም» በማለት ምላሽ በመሰጠታቸው እነርሱን ሳለመድረስና ፀመንገድ፣ ፀገዚያና ፀየስፍራው በማንንጠጥና በመሳደብ ሊያሰፍሩአቸው ይሞክሩ ነበር። ይህ ሁሉ ስላልተሳካቸው ቆፍረው አስክሬን ለማውጣትና ለመጣል በቁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈውን የሚያትቱ የማደናገሪያና የፈጠራ ጽሑፎች

14.1 የባሃኡላህ ጥሪ ፓምፍሌትና «ባሃኡላህና አዲሱ ዘመን» የሚል መጽሐፍ ይዘት

«ባሃኡላህና አዲሱ ዘመን» በሚል መጽሐፍ ገጽ 51 ላይ ዕርገት በሚል ርዕስ ስር ህዳር 12 ቀን 1817 ዓ.ም በኢራን አገር፥ በቴህራን ከተማ የተወለደው በቀድሞ ስሙ ሚርዛ ሁሴን ዓሊ የተባለው ባሃኡላህ ግንቦት 29/1892 ዓ.ም በድንገተኛ ህመም በሰባ አምስት ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ይገልጻል። ቀጥሎም በገጽ 70 ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ በማለት ፈንታ ዐረገ ይለዋል።

የባሃኡላህ ጥሪ የሚል ፓምፍሌት ጽሑፍ «ኢየሱስ እኔ ብሄድ ይሻላችኋል እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ ብሎ በዮሐንስ ወንጌል 16፥7 የተናገረው ባሃኡላህን ማለቱ ነው» ይላል። «ይኸውም በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ቃል የተገባለት ሁሉንም ጥበብ ይገልጽ ዘንድ መጥቶአል።» (ወርልድ ኦርደር አፍ ባሃኡላህ 104/5 «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» ብሎ በዮሐንስ ወንጌል 16፥13 ኢየሱስ ያስተማረው ስለ ባሃኡላህ ነው ይላል። (ታብሌት አፍ ባሃኡላህ 12 ...) «በእውነቱ እርሱ የእውነት መንፈስ ወደ ሁሉም እውነት ሊመራችሁ መጥቶአል። እርሱ የሚናገረው በራሱ ፍላጐት ሳይሆን ሁሉን አዋቂው፥ የሁሉም ጠቢብ በሆነው በእርሱ ትዕዛዝ ነው» ይላል።

ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ባሃኡላህ የተናገረው አንዳችም ነገር የለም። እርሱ ግን የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። ያለው ስለ መንፈስ ቅዱስ እንጂ በአንድ ወቅት ታይቶ ስለሚጠፋና ስለሚሞት ሥጋ ለባሽ አይደለም። ያም ሆነ ይህ ሰውየው ሥጋ ለባሽ ስለሆነ መሞቱ የታወቀ ነው። ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ በዮሐ

14፥16 ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር «... ለዘላለም ከእናንተ ጋር የሚኖር ...» አለ እንጂ ሟች ነው አላለም። የሞተ ሰው በህይወት ያለውን ሊያጽናና ሊደግፍና ሊረዳው በጭራሽ አይችልም። ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነት ግልጽ ስህተት መመለስና የእውነትን መንገድ መያዝ ትልቅ ጥበብና በእግዚአብሔር ዘንድም የተወደደ ነው።

«ፈሪሳውያን ያለ ምንም ማስረጃ ኢየሱስን እንደተከራከሩት እናንተም ባሃኡላህን እንዳትከራከሩ ተጠንቀቁ፤ ምክንያቱም በዮሐንስ ወንጌል 16፥4 ኢየሱስ እርሱ ያከብረኛል ያለው ባሃኡላህን ነውና» ይላል። መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። (ማቴ. 22፥29) ተብሎ የተጻፈውን ቃል ቢያጤኑ ኖሮ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀሰውን ስለ አንድ ግለሰብ የተጻፈ ነው ባላሉም ነበር።

«የልባችሁን በሮች ከፈቱአቸው እርሱ መንፈስ (ክርስቶስ) በፈታችሁ ቆሞአልና። ... ክርስቶስ በመጀመሪያ ጊዜ ከመጣበት እርሱ በእውነት ከመንግሥተ ሰማያት ዳግመኛ መጣ» (ታብሌት አፍ ባሃኡላህ 11)። በ1 ዮሐ. 4፥1-3 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ከእግዚአብሔር አይደለም። ይላልና፤ ይህ የባሃኡላህ ትምህርት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው የሚል ስለሆነ በቃሉ አንፃር ሲመዘን ከእግዚአብሔር እንዳልሆነና እንዲያውም የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል።

«መንፈስ (ክርስቶስ) በመጣ ጊዜ እነርሱ እንዴት እንዳስወገዱት አስተውሉ። ... ዛሬ ሥልጣንና የበላይነት ያለው ሰው ክርስቲያን በሚለው ስሙ ራሱን ያኩራራል ...» ይላል።

በተጨማሪም የክርስትናን ሃይማኖት መሪዎችና ተከታዮች ሲያጥላላና የራሱን እምነት ከፍ ከፍ ሲያደርግ እንደሚከተለው በማቅረብ ወደ እርሱ እምነት እንዲፈልሱ ፈልጐ ከ1ኛ እስከ 10ኛ ባለው ክፍል የተጠቀሰውን ጥሪ ያቀርባል፤

1ኛ) ሠራዊተ ቀላውስት! «ደወሎቹን አሳርፉአቸውና ከቤተ ክርስቲያኖቻችሁ ወደ እኔ ኑ። በዛሬ ቀን ፍጹም ታላቁን ስም በአገሮች ሁሉ እንዲታወጁ ታዞአልና። ... ወደ እርሱ የሚጣደፈው ሰው የታደለ ነው» ይላል። (ዘ ፕሮሚስድ ደይ ካም 105)

2ኛ) ነገሥተ ክርስቲያን ሆይ! «የአምላክ መንፈስ የሆነው ኢየሱስ የተናገረውን አልሰማችሁምን? ይመጣል የተባለው ወደ ሁሉ

እውነት የሚመራችሁ የእውነት መንፈስ ሲመጣላችሁ ፈታችሁን ወደ እርሱ ለመመለስ እንዴት እንደ ተሳናችሁ ተመልከቱ። ... በራሳችሁ ድክመት የአምላክን ትንፋሽ በላያችሁ ላይ እንዳይነፍስ ጋረዳችሁ» ይላል። (በሃይ ዎርልድ ፈዝ 38)

3ኛ) የወንጌል ሕዝቦች ሆይ! «በዛሬ ቀን እናንተ በበሩ ስታዘግሙ እነዚያ በመንግሥቱ ውስጥ ያልነበሩ አሁን ገብተውበታል» ... ይላል።

4ኛ) የወልድ ተከታዮች! «ተጠንቀቁ ቃሌን በስተጀርባችሁ እንዳትጥሉ ፈጥናችሁ አጥብቃችሁ ያዙት። ይህ ከማንኛውም ከያዛችሁት ይበልጥባችኋልና። ... ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ዕውቀትና ከምርጥ መላዕክት የደበቅነው ያ ሰዓት አለፈ» ይላል። (ዘ ታብሌት ኦፍ ባሃኡላህ)

5ኛ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ! «... ከሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በወዳጅነት መንፈስ ተቀላቀሉ። (ግሊ. 43)»

6ኛ) ሕዝብ ሆይ! «እግዚአብሔር ምስክሬ ነው እነሆ የአምላክ እስትንፋስ በላዬ ላይ ነፍሶ ከእንቅልፌ እስከቀሰቀሰኝ ድረስ በአልጋዬ ላይ አንቀላፋ ነበር። ቀስቃሽ መንፈሱ ነፍስ ዘራብኝ ጥሪውን እንድሰማ ምላሴን አፍታታው። በእግዚአብሔር ላይ ሕግ ተላልፈሃል ብላችሁ አትክሰሱኝ በራሳችሁ አይን ሳይሆን በራሴ ተመልከቱኝ» ይላል። (ጥሪው የማን እንደሆነ ባይታወቅም ጥሪውን እንዲሰማ የተፍታታው ጆሮው ሳይሆን ምላሱ መሆኑን ልብ በሉ።)

7ኛ) እናንተ የዓለም ሕዝቦች ሆይ! «ያልታሰበ መዓት እየተከተላችሁ መሆኑንና አስፈሪ ቅጣትም እንደሚጠብቃችሁ በእርግጥ ዕወቁ የፈጸማችኋቸው ተግባራት በእኔ ዘንድ የተረሱ እንዳይመስላችሁ (ግሊ. 103)» እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱ ማስፈራሪያ ከቅዱስ መንፈስ ነው ወይስ ከእርኩስ መንፈስ?

8ኛ) እናንተ በምድር የምትኖሩ ሆይ! «ይህን ልውል ራዕይ ከሌሎች ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያደርገው ታላቁ ጠባዩ በአንድ በኩል በሰው ልጆች መካከል ሁከትን ተንኮልንና ብጥብጥን ያመጣ የነበረውን ማናቸውንም ነገር ከአምላክ ቅዱስ መጽሐፍ ማስወገዳችን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለስምምነት ለመግባባት ለተሟላና ለዘላቂ አንድነት በቅድሚያ የሚያስፈልጉትን መዘርጋታችን ነው ...።» (ገሊ. 43) ይላል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ካሉት ቃላት አንዳች ማጉደል ወይም መጨመር የመጨረሻ ቅጣት የሚያስከትል ለመሆኑ በራዕይ 22፣ 18-19 የተጻፈውን ቢያነብብ አይሻለውም?

9ኛ) እናንተ ትክክለኞች ነን ባዮች! ለትንሽ ጊዜ አሰላስሉ። ከዚያም የአሁኑ ሁኔታ እናንተ እንዲኖረው ከምታስቡት ደረጃ ወሰን በሌለው እጅግ የበለጠ እንደሆነ ትረዳላችሁ። የሃይማኖት መሪዎች የሃይማኖት ምሁሮች ጠቢባንና ሊቃውንቶች ያላቸው ነገር ሁሉ ፈጽሞ ከሌለበት ቤት ውስጥ እምነቱ ይገለጽ ዘንድ የኃያሉ አምላክ ፈቃድ ወስኖታል። (ገሊ. 45) ይላል።

10ኛ) ሕዝቦች ሆይ! እነዚህን ጥቅሶች ከካዳችሁ በምን ማስረጃ በአምላክ አመናችሁ? እናንተ የውሸት መንጋዎች ሆይ ማስረጃችሁን አቅርቡ ...። ምንም እንኳ ፍጹም ግልጽ ማስረጃዎቹ የእምነቱን እውነት ቢያረጋግጡም ምንም እንኳ የባሃኡላህ ትንቢቶች ቢፈጸሙም ይህ ትውልድ የርሱን ሥልጣን እንዴት እንደጠላና በእርሱም እንዳመጸ ተመልከቱ። በአትኩሮት እይታና በአንጸባራቂ ልብ ያለፉትንና አሁንም በመሆን ላይ ያሉትን ማየት ትችሉ ዘንድ እንዲሁም በልባቸው ውስጥ በማሰላሰል በዚህ ቀን አብዛኛዎቹ ሰዎች ማየት የተሳናቸው ለማየት አምላክ ያግዛቸው። (ገሊ. 58) ይላል።

በተጨማሪም «ባሃኡላህና አዲሱ ዘመን» በሚል መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ የምስራች ቃል በሚል ርዕስ ሥር «ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ የተሰጠው ተስፋ ተገለጸ። የዓለም ሕዝቦችና ማህበሮች ሁሉ የእግዚአብሔርን መገለጽ ይጠባበቁ ነበር። እነሆ እርሱ ባሃኡላህ የሰው ልጅ ሁሉ ቀዳማዊ መምህርና መሪ ነው» (አብዱል ባሃ ...) ይላል።

የባሃኡላህ መልዕክት በሚል ሥር፣ «ባሃኡላህ ከጥንት ጀምሮ እንዲመጣ ይጠበቅ የነበረው የሰዎች መሪ መምህርና ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ የላቀ ያንድ ግሩም ጸጋ መታያ ነው»። (ገጽ 7)

በመጽሐፉ ላይ እንደተጠቀሰው ለባሃኡላህ መንገድ ጠራጊ የሆነው ባብ በቀድሞ ስሙ ሰዒድ (የነቢዩ መሐመድ ዘር ማለት ነው) የተወለደው በኢራን ጥቅምት 20 ቀን 1819 ዓ.ም ሲሆን ነቢይ ነኝ ብሎ መነሳቱን 18 ደቀመዛሙርት (ሕያዋን ቃላት) ብሎ ማስከተሉንና በ1850 ዓ.ም. በተቃዋሚዎች መገደሉን ይገልጻል። ቀጥሎም ባሃኡላህ መነሳቱንና የባብ ተከታይ የነበሩትን ባቢዎች ጥቂት ጊዜ እንዳስተማረ ከዚያም «በሃኢ» የሚል ሃይማኖት እንዳቋቋመና እንደ ሞተ ከእርሱ በኋላም ልጁ አብዱል ባሃ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ የሃይማኖት መሪያቸው እንደሆነ ይገልጻል።

ይህንንም ፓምፕሌትና መጽሐፍ ለምሳሌ የጠቀስነው አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሰይጣንን ተልዕኮ ለማሳካት መጠቀሚያው ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማስገንዘብ ነው።

ማንኛቸውም በሃይማኖት ስም የሚጻፉ ድርሰቶች በቃሉ (በመጽሐፍ ቅዱስ) ሊመዘኑ እንደሚገባ መታወቅ አለበት። ይህ ካልሆነ ባለማጤን ስህተት ውስጥ ከገቡ በኋላ ከዚያ መውጣቱ ቀላል አይሆንም።

14.2 «ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው» የሚል መጽሐፍ ይዘት

በዓለም ላይ ትክክለኛውን የታሪክና የእምነት ገጽታ የሚተነትኑ ጽሑፎች በብዙ ጥናትና ድካም መጻሕፍት ጽፈው ለትውልድ የግበርከታቸውን ያህል አንዳንድ ጽሑፎች ደግሞ ከታሪክና ከእውነት ውጪ የሆኑ የማደናገሪያ መጻሕፍት አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ጽፈው በግስነበብ ላይ ይገኛሉ።

የጸሐፊውን ማንነት እንደ መስተዋት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው በጽሑፍ ያሰፈረው የእውነት ወይም የውሸት ሃሳብ ነው። ጽሐፊው አንድን ጽሑፍ ሲያዘጋጅ የጽሑፉ አንባቢ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ሰው ስለ ጽሑፉ የየራሱ የሆነ የሃሳብ፥ የአስተያየትና፥ የአመለካከት ዳኝነት ለመስጠት የሚችል መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። ምናልባት ፀሐፊው ሰው ሁሉ በእኔ ጭንቅላት ያስባል፥ በእኔ ጆሮ ይሰማል፥ በእኔ ዓይን ያያል፥ እንደገደል ግሚቶ እኔ ያልኩትን ይላል ብሎ የሚጠብቅና እንደፈረስ ጋሪ ወደራሱ ሊጐትት የሚሞክር ከሆነ በአንባቢው ዘንድ ሚዛናዊነት የሌለው ጸሐፊ እንደሆነ ያስገምተዋል።

«ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው፤

የተዋህዶ አንበሣም መድሃኔዓለም

ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» በሚል ርዕስ አባ ሰይፈ ሥላሴ ሞገስ የተባሉት ሰው በ1988 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሐፍ ጥናቱን ያቀረቡበትን ምክንያት በገጽ 19 ላይ ሲገልጹ «... እኔም ኢትዮጲስ በሚል ርዕስ በ1985 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ለሚያጐድፍ ለሐሰተኛው ግርማ ዘውዴና ለሌሎችም መሰል ከሐዲዎች በቂ የሆነ መልስ የሚሆን ይህን አጭር ጥናት አቅርቤአለሁ ...» ይላሉ።

ይሁን እንጂ በኢትዮጲስ መጽሐፍ ከተጻፉት ርዕሶች ጠቅሰው ለጸሐፊውም ሆነ ለአንባቢ ትምህርት እንዲሆን ወይም እንዲመራመሩ

መንገድ እንዲከፍት የጻፉትና የተቃወሙት አንዳችም ነገር የለም። ይህም የሆነበት ምናልባት ኢትዮጲስ መጽሐፍ የተዘጋጀው በድርሰት ወይም በተረት መልክ ሰውን ለማሳመን ታስቦ ሳይሆን ከብዙ የዓለምና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍት ተጨምቆ ከነመረጃው የቀረበ ጥናት በመሆኑ ስህተት አለበት እንኳን ቢሉ ከእውነት ሸሽቶ ማምለጥ እንደማይቻል ስለተረዱ ይመስላል። አንድን ሰው ጥፋተኛ ስህተተኛ ወይም ወንጀለኛና ሀሰተኛ የሚያሰኘው ድርጊቱ ወይም ተግባሩ እንደተባለው ሆኖ ለመገኘቱ በበቂ መረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ያለአግባብ በጽሑፉም ሆነ በቃል ስም ማጥፋት በመንፈሳዊ መንገድ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ሲሆን በሕግ አኳያም ተሳዳቢውን በወንጀል የሚያስጠይቅ ከሚሆን በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም።

ተጠቃሹ ጸሐፊ ኢትዮጲስ የተባለውን መጽሐፍ ለመቃወም አዘጋጀሁ ባሉት በዚህ መጽሐፋቸው ፍሬ ነገር ነው ብለው በብዙ ገጾች የጻፉአቸውን ሀተታዎች ከዚህ ቀጥሎ ለማስነበብ እንሞክራለን። ይህንንም የምናደርገው አንባቢው ጉዳዩን አገናዝቦ የህሊና ዳኝነት እንዲሰጥ እንጂ የመልስ ጽሑፍ ብቻ ለማዘጋጀት ታስቦ እንዳልሆነ በትህትና ለመግለጽ እንወዳለን።

በመጽሐፉ በተለያዩ ክፍሎች ሐዋርያትና ነቢያት ኢትዮጵያውያን ናቸው ከማለታቸውም በላይ በገጽ 5 ላይ ቅድስት እምቅዱሳን ንጽሕት እምንጹሓን እመ አምላክ ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ እናት ናት ብለው በገጽ 30 ላይ ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ራሷ በዜግነት ኢትዮጵያዊት ነች ብለዋል። ለዚህም ስለ ማርያም የትውልድ ሐረግ ኢትዮጵያዊነት የሚናገር ከመጽሐፈ ነገሥት አስቀድሞ ምስጢረ ካህናት ዘኢያሱ በሚል ርዕስ 1500 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፈ ጽሑፍ ይገኛል፤ ይሉና ቋንቋው ግን ከግዕዝ በፊት በነበረው ሳባዊ ነው ከማለት በስተቀር ማን ተርጉሞ እንዳስረዳቸው አልጠቀሱም።

በገጽ 33 ስለ ኃጢአት አጀማመር ሲገልጹ ... ዲያብሎስ (ሰይጣን) በእባብ ተመስሎ እባብ ደግሞ በሄዋን ተመስላ አዳም የአምላኩን ትዕዛዝ እንዲያፈርስ በውጤቱም በመከራና በፍዳ ውስጥ እንዲወድቅ ምክንያት እንደሆነ ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ «እባብ በሄዋን ተመስላ ነበር» የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ ያሰፈሩት የግላቸው የሆነ የፈጠራ ተረት ነው። በቃሉ ግን (በዘፍ. 3፥1) ላይ የተጻፈው እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ይልቅ ተንኮለኛ ነበረ። ሴቲቱንም :- «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዞአልን?» አላት ... የሚል ነው። በዚሁ ገጽ 33

መጨረሻ ላይ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ጌታ ኢየሱስ በአይኑ ላይ ጭቃ አድርጐ ስለ ፈወሰው ዓይነ ሥውር ሲገልጹ ሰውየው ለጉድ የተፈጠረ ቅንድብና የአፍንጫ ቅርጽ የሌለው፥ አፍንጫው ከአፉ ጋር የተያያዘ በአፉ የሚተነፍስ የተደመጠ መጅ የሚመስል ደረቅ ግንባር ሆኖ፥ አራት አይና ጉሽ አይነ ልቡናው የሚያበራ አእምሮው በምስጢረ ተዋሕዶ የተሞላ ሰው ነበር ይላሉ። ይህንንም ሰው 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ወዳለው ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ ሄዶ እንዲታጠብ ላከው። አምኖስ የተባለው ይህ የ25 ዓመት ጐልማሳ ዓይነ ስውር ልብሱን አወላልቆ በውሃ ውስጥ ገብቶ ተጠመቀ ድኖ ሲመለስም ግራ ጀሮው ላይ ምልክት ነበረውና ሌሎች ሰዎች እርሱ ነው? አይደለም? የሚል ንትርክ ፈጠሩ፤ በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈውን የፈጠራ ድርሰት ስለ እርሱ ብቻ ከገጽ 33-41 ድረስ ጽፈዋል።

በገጽ 22 በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ «እንደ አይሁዶች ስድባቸውን ሁሉ አስወግዶ የእናት ኢትዮጵያ ምርጥ ሕዝብ ላደረጋቸው ለጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሙሉ በኢትዮጵያውያን አምላክ በሕያው እግዚአብሔርና በንጽሕት ቅድስት እናቱ በድንግል ማርያም ስም ሳመሰግናቸው በጣም ከፍተኛ የሆነ የልብ ደስታ እየተሰማኝ ነው» ብለዋል። ይህንን ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ጉራጊኛ ተናጋሪዎች ምን ስድብ ነበረባቸው? አሁንስ እንዴት ተወገደላቸው? ለአንባቢያን ግልጽ ቢያደርጉ!

በገጽ 46 በክፍል 5 «የእምነት ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ?» በሚል ሥር የሐሰትና የኑፋቄ ትምህርት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲገባና ልዩነት እንዲፈጠር ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ናቸው ሲሉ፤

1ኛ) ከኢትዮጵያውያን ዘር በሊቢያ የተወለደው አርዮስ እግዚአብሔር ወልድ ፍጡር ነው በማለቱ 318ቱ አባቶች በኒቂያ አውግዘው ለዩት ይላሉ።

2ኛ) በእናቱ ኢትዮጵያዊ በአባቱ ግሪካዊ ሆኖ በካይሮ የተወለደው ዴዮስቆሮስ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባህሪይ ነው ብሎ በ442 (በ451) በመለየቱ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ተከፈለች ብለዋል። ከዚያም ቀጥሎ በዘር ኢትዮጵያውያን ናቸው ያሉአቸው፤

3ኛ) ገጽ 45 ላይ ከኢትዮጵያውያን ዘር የሚወለደው ፊልጶስ አብን አሳየንና ይበቃናል ... ሲለው ኢየሱስ መልሶ ሃያ ሰባት ዓመት በሙሉ ከእናንተ ጋር ስኖር አላወቅኸኝም አለው ብለዋል። ለመሆኑ

ሐዋርያት ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለ27 ዓመታት አብረው ኖረዋል?

4ኛ) አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ የባረከውና አብርሃም ደግሞም ከሁሉ አሥራት ያካፈለው መልከጼዴቅ (ዘፍ. 14፥17-20፤ ዕብ. 7፥1-10) የተባለው ሰው ኢትዮጵያዊ ነው ይላሉ።

5ኛ) የንግሥተ ሕንዳኬ ታናሽ ወንድምና ባለሙሉ ሥልጣን ጃንደረባ አልጋ ወራሽ መልከጼዴቅ 2ኛ ሲሆን እርሱም ኢትዮጵያዊ ነው ይሉና በዓለም ላይ በመጀመሪያ የተጠመቀ እርሱ ነው በማለት ጽፈዋል። በመቀጠልም በገጽ 50 በመጨረሻው አንቀጽ ይኸው ኢትዮጵያዊ ሰው ከትንሳኤ በኋላ በ8ኛው ቀን ፀሐይ ሲጠልቅ ጋዛ እንደደረሰ ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ይህ ሰው በሥርዓቱ መሠረት ሊሰግድና የፋሲካን በዓል ሊያከብር መጥቶአልና ቀርበህ አነጋግረው ብሎ አዘዘው የሚል በቅዱስ ቃሉ የሌለ ጨምረው ጠቅሰዋል።

እውነቱ ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሳኤው በኋላ አርባ ቀን እየታያቸው፥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ህያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው። ትዕዛዝም ሰጣቸው ከላይ ኃይልን እስክትቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ... እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ... ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ፥ በሰማርያ፥ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (ሐሥ. 1፥3-8) ከዚያም በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 12-14 ባለው ክፍል ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው በጸሎት ይተጉ እንደነበረ፥ በምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉና መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች እንደተናገሩ ተጽፎአል። ይህም በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን ሲሆን ከትንሳዔው በኋላ ሃምሳኛ ቀን መሆኑ ነው። ስለዚህ ጸሐፊው ከትንሳዔ በኋላ በ8ኛው ቀን ያሉት ተሳስተው ከሆነ ቃሉን አንብበው ያርሙ፥ ካልሆነ ራሳቸው ተሳስተው አንባቢውንም የባሰ ስህተት ውስጥ መክተት በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅ ጉዳይ ነው። ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ (1ጢሞ. 4፥16፤ 1ጢሞ. 6፥20-21)።

መንፈስ ቅዱስ የወረደው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጸው ጌታ ባረገ በአሥር ቀኑ ሲሆን ከትንሳዔ ቀን ጀምሮ ሲቆጠር በሃምሳኛው ቀን መሆኑ ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው ስለ ጃንደረባው ሲገልጹ አንድ ጊዜ የአሪት መምህርና ካህን ነው ሲሉ ሌላ ጊዜ ደግሞ የንግሥቲቱ ወንድምና አልጋ ወራሽ ባለሙሉ ሥልጣን መልከጼዴቅ 2ኛ ነው ይሉታል። ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8፥26-39 ባለው ክፍል የተጠቀሰ ስለሆነ እውነቱን ከቃሉ አንብቦ መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው። ይህም ሰው ሐዋርያት ወንጌልን ሰብከው አሳምነውና አጥምቀው ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት ካደረጉ በኋላ የተጠመቀ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለምሳሌም ያህል በሐሥ. 2፥41 ቃሉን የተቀበሉም ተጠመቁ፤ በዚያን ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ ... ይላል። እሳቸው ግን የመጀመሪያው ተጠማቂ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው ብለዋል።

ቀጥሎ ባለው ክፍል ደግሞ በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ከተሳተፉት 27 ኤጲስ ቆጶሳት መካከል 12ቱ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ግን ኢትዮጵያዊው ዲዮስቆሮስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባህሪይ በማለቱ ስብሰባውን ረግጦ ትቶ በመውጣቱ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ተከፍላለችም ብለዋል።

ከዚያም ከገጽ 60-64 ባለው ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን መከፈል ሉተር ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዘጠና አምስት አርቲክሎችን አቅርቦ ተለየ ካሉ በኋላ ካቶሊክም ሆነ ሉተር ሃሰተኞች ናቸው ብለዋል። ጽሐፊው ካቶሊክንም ሆነ ሉተርን በደፈናው ሃሰተኞች ናቸው ያሉበትን ምክንያት ከቃሉ ጠቅሰው ማረጋገጫ ሊያቀርቡ አልቻሉም። በዚሁ ክፍል ስለ ቅዱስ ቁርባን አሰጣጥ ሲጠቅሱ ደግሞ በዓለም ላይ ትክክለኛው ቅዱስ ቁርባን የሚሰጠው በእናት ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነውና ስለዚህ ከፍ ያለ ኩራት ይሰማኛል ይላሉ።

14.2.1 ከሰው አእምሮ ውጪ የሆነ የመናፍስት አሠራር ሲጋለጥ

ጸሐፊው አባ ሠይፈ ሥላሴ በገጽ 61 ላይ ከሰው አእምሮ ውጪ ወደ ሆነው ወደ ልዩ ዓለም ውስጥ በመግባት ከየትና እንዴት እንደተረዱት ባይገልጹትም ትዕዛዝ ተቀባዮች ናቸው የሚሉአቸውን እንደሚከተለው ያቀርባሉ፤

1) በመሬት ያለውን ትዕዛዝ የሚቀበል ሱርያኤል

2) በውሃ ያለውን ትዕዛዝ የሚቀበል ሰዳካኤል

3) በእሳት ያለውን ትዕዛዝ የሚቀበል ሰላታኤል

4) በንፋስ ያለውን ትዕዛዝ የሚቀበል አናንያኤል ናቸው ይላሉ። ትዕዛዝ ሰጪው ማን እንደሆነና ተቀባዮቹም የጨለማ ወይስ የብርሃን መላዕክት እንደሆኑ በጽሑፋቸው አላብራሩም። ቀጥሎም በአራቱ ማዕዘን ያለውን ክፍት ቦታና በዓለም ዙሪያ ያለውን ሁሉ የሚቆጣጠር አፍኒናኤል ከ99ኙ ሠራዊት (ነገደ መላዕክት) ጋር ነው ብለዋል።

በአይን ሲታዩ የሚያስደንቁ ኃይሎች 1) የሰው መልክ 2) የበግ መልክ 3) የአሞራ መልክ 4) የአንበሳ መልክ 5) የተኩላ መልክ ሲሆን እነዚህ ኃይሎች በዓለም ውስጥ በጣም አስደናቂ የሆኑ ሥራዎችንና ሥነ ጥበቦችን የሚሠሩና የሚያሠሩ መሆናቸውን የሥነ ከዋክብትና የሥነ ፍጥረት ተመራማሪዎች የሆኑት የጥንት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ወይም አባቶች ጽፈዋል ብለው አስፍረዋል። ይህስ አባባል እውነት ነው? አንባቢ ያመዛዝን።

በገጽ 86 በክፍል 13 ደግሞ «በእናት ኢትዮጵያ መሬት ውስጥ የተቀበሩ የፒራሚድና ሌሎች ከተሞች ማን እንደሠራቸው» በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመሬትና በባህር ሥር የተደበቁ ወይም የተቀበሩ ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸው ህንፃዎችና የፒራሚድ ወይም የባለ ሦስት ማዕዘን ከተሞች መኖራቸውንና የተለያየ ቅርጽ ያላቸው ሀውልቶች መኖራቸውን ጠቅሰዋል። እነዚህም እንዴትና በማን እንደተሠሩ አብዛኛው ምስጢር እንደተጠበቀ ነው ይላሉ። በ2ኛው ተራ ቁጥር ደግሞ የጥንት የኢትዮጵያ ወደብ በነበረው አዶሊስና በቀይ ባህር አካባቢ የተሠሩ የፒራሚድ ከተሞች የተሠሩት በራሱ በራፋኤል እጅ በ9630 ዓመት ከክርስቶስ በፊት የኃይሉ ማረፊያ እንዲሆን ነው በማለት ጠቅሰዋል። በተራ ቁጥር 3 ደግሞ ከዘብል ራማ በሃዳር በአሰብ አፋር እስከ ጅቡቲ ድረስ የሚገኙ ሦስት ከተሞች የተሠሩት በ9600 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በራፋኤል ፈቃድ በኪሩቤልና በሱራፌል እጅ ነው ይላሉ። በገጽ 86 ላይ ስለ እነዚህ ከተሞች ሲያብራሩ በሱራፌልና በኪሩቤል የሚታዘዙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ነገደ መላዕክት በገዛ ኃይላቸው እንዳይቃጠሉ የመሬት ስበት የሚያገኙባቸው ከተሞች ናቸው። መላዕክት እንደሌላው ፍጥረት ሁሉ የመሬት ስበት ያስፈልጋቸዋል። ይህ ባይሆን ግን በገዛ ኃይላቸው ይቃጠላሉ። ስለዚህ ለዘላለም ለመኖር እንዲችሉ ስበት ያስፈልጋቸዋል ብለዋል። ይህንን ሲሉ ምን ለማለት እንደፈለጉ ግልጽ ባይሆንም መላእክት ቅዱሳንም ሆኑ ርኩሳን ሥጋዊ አካል አላቸው ማለታቸው ነው? ጽሐፊው የጠቀሱአቸው እነዚህ መናፍስት የተባሉትን የፒራሚድ

ከተሞች ወይም አካባቢውን ፈጠሩ የሚሉት በቃላቸው «ይሁን» ብለው ነው ወይስ ግንበኛ አናጺና መሃንዲስ ሆነው በእጃቸው ነው?

በቤተ ክርስቲያኒቱ በሚታወቀው የዘመን አቆጣጠር ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ነው የሚለውን አሳቸው ወደ ሳይንቲስቶቹ ሃሳብ በመመለስ አሻሽለው ነው ከላይ ያሰፈሩአቸውን ዘመናት ከክርስቶስ ልደት 9630 ዓመት በፊትና ወዘተ. ብለው የጻፉት?

14.2.2 «ሣጥናኤል ከተማ ሠርቶአል» ይላሉ ጸሐፊው

ጸሐፊው በመጽሐፋቸው በገጽ 87 ላይ ከሚሌ ዱፍቲ አንስቶ የአዋሽ ወንዝ መጨረሻ፤ ከፑንቲ በርበራ እስከ ሕንድ ባህር ድረስ ሦስት ፒራሚድ ከተሞች የተሠሩት በ8300 (B.C.) በሣጥናኤል እጅ ነው ብለዋል። ከእነዚህም ከተሞች ቅዱሳንና ርኩሳን መላዕክት እንዲሁም ሥጋ የለበሱ ርኩሳን የሆኑ መናፍስት የሚኖሩባቸው ናቸው። እነዚህ ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን መሥራት እንዲችሉ በአእምሮአቸው ውስጥ የሚሰሉና በቀዶ ጥገና የሚያስተካክሉ የጥበብ ኃይሎች ናቸው። ስለዚህ የፈጠራ ሥራ (ፍልስፍና) የሚመርጡአቸው ሰዎች ከማንኛውም እምነት የማይወግኑትን ብቻ ነው፤ ይህም የሚሆነው በጥቁር ፒራሚድ ከተማ ነው። በነጩ ፒራሚድ ከተማ ተወስደው አመጽንና ግፍን ማንኛውንም ርኩሰት ሥራ እንዲፈጽሙ በቀዶ ጥገና በአእምሮአቸው ውስጥ የሚቀርጽላቸው ሰዎች ደግሞ ከአይሁድ ከክርስትና ጀምሮ የማንኛውም ሃይማኖትና እምነት ተከታዮች ከሆኑት ሰዎች ነው። ለምሳሌ፥ ጨካኞችና ደም አፍሳሾች የሆኑ ነገሥታትና ዲክታተሮች የነበሩትና ወደፊትም የሚነሱት ከኢትዮጵያ መሆኑ የታወቀ ነው ብለው ውሉን ያጠፉታል።

ቡናማ የሆነ ፒራሚድ ከተማ ተወስደው የሚሠለጥኑት ከክርስቲያኖች ጀምሮ የማንኛውም ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ ሠልጥነው ሲወጡ ፍጹም መንፈሳውያን ሆነው ልዩ ልዩ የሃይማኖት መጻሕፍትን የሚጽፉና ልዩ ልዩ የሆኑ የሃይማኖት ተቋሞችን የሚሠሩ እንዲሁም በየቋንቋ ልዩ ልዩ በጣም የሚያስደስቱ መንፈሳዊና ሥጋዊ የሆኑ መዝሙሮችንና ጨዋታዎችን (ዘፈኖችን) የሚደርሱና የሚያዘጋጁ የጥበብ ኃይሎች ይሆናሉ ብለዋል። ደግሞም ሣጥናኤል ሠራቸው የሚሉአቸው የፒራሚድ ከተሞች የሚሰጡ ሥልጠናዎች ለሰው ልጅ የፈጠራ ሥራና ፍልስፍና እንዲሁም ለሥነ ጥበብ ሥራዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው ከማለታቸው በስተቀር እነማን በየትኛው ሙያ እንደሠለጠኑ

አላብራሩትም። በመጽሐፋቸው ላይ እነዚህ የፒራሚድ ከተሞች በሰብዓዊ ፍጡር ዓይን የማይታዩ ናቸው ብለዋል። እሳቸው እንደ.ት ወይም በምን ኃይል አይተው ሊጽፉ እንደቻሉ ለአንባቢያን ግልጽ ቢያደርጉ መልካም እንደሚሆን እንገምታለን።

14.2.3 ጸሐፊው በሰው ሬሳ ሽታ የሚታደሱ ናቸው የሚሉአቸው መናፍስት

በዓይን ሲታዩ በሚያስደንቁ ኃይሎች የተሠሩ ከ4300-3412 እና በ2780-2100 1510 (B.C.) የምስር (የግብፅ) ዓይነት የፒራሚድ ከተሞች የሚገኙት በላዕላይ ግብፅ፥ በኑቢያ፥ በናፓታ፥ በመርዌ እንዲሁም በታይታይ ግብፅ ሲሆኑ አሰራራቸው ባለሦስት ማዕዘን ወይም ትሪያንግል ሆኖ ያለ ሲሚንቶና ሞታ ሰው ሊሸከመው በማይችል በትላልቅ ድንጋይ ተቀጣጥለውና ተነባብረው በሚያስደንቅ ሁኔታ የተሠሩ እንደሆኑ ገልጸዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ፒራሚዶች የተሠሩት በሰው ኃይልና ጥበብ ነው የሚሉ የዓለም ታሪክ ፀሐፊዎችና የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች (አርኪዎሎጂስቶች) እንዲሁም የግብፅ ተራኪዎች እንደሚያነበንቡት አይደለም ብለዋል። እነዚህ የግብፅ ፒራሚዶች የተሠሩት የሰው፥ የበግ፥ የአሞራ፥ የአንበሳ፥ የተኩላ መልክ ባላቸው በዓይን ሲታዩ በሚያስደንቁ 5 ኃይሎች እንጂ ታሪክ ጸሐፊዎችና የመላምት ተራኪዎች «የግብፅ ፈርዖኖች በትንሣኤ ሙታን ስለሚያምኑ መቃብር ቤት እንዲሆናቸው በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሕዝቦች በሰው ኃይል አሠሩት» ተብሎ የተጻፈው ፍጹም ሃሰት መሆኑን ለአንባቢያን እገልጻለሁ፤ ካሉ በኋላ እነዚህ በሰው የሬሳ ሽታ ስለሚታደሱና ከወርቅ፥ ከዕንቁ፥ ከአልማዝ የተሠራ ልዩ ልዩ የሆነ ቅርጻ ቅርጽንና በሐውልቶች የተቀረጸ ልዩ ልዩ ሥዕልን ማየት ስለሚወዱ የኃይላቸው ማረፊያ እንዲሆኗቸው ነው ብለዋል። በመቀጠልም እነዚህን ሥራዎች እንኳንስ በዚያን ዘመን በዛሬውም ዘመን ቢሆን በሰው ኃይል መሥራት እንደማይቻል እሙን ነው ይላሉ።

ከላይ የተጠቀሱት በሰው ሬሳ ሽታ የሚታደሱት 5 ኃይሎች አሁንም ቢሆን በእናት ኢትዮጵያ እንዳሉ ነው፤ ለምሳሌም የደብረ ብርሃን የዓርብዓሐራ ምስጢር ምን ይሁን? ብለው በጥያቄ አበቁ እንጂ በሬሳ ሽታ መታደስ ማለት ምን እንደሆነና እርሳቸውም ከየት እንደተረዱት ለአንባቢያን ግልጽ አላደረጉም። ይህ የጥልቁና የጨለማው መንፈስ አሠራር ሳይሆን እንደማይቀር ስለሚገመት ፀሐፊው የሚያውቁትን ሊያብራሩ የሚችሉ ከሆነ ለንባብ ሊያበቁ ቢሞክሩ አይከፋም። ካልሆነ

ግን ግልጽ ያልሆነና የተምታታ ጽሑፍ አንባቢውንም ሆነ ሰሚውን ያደናግራል እንጂ ፍሬ ነገር አያስጨብጥም።

የአክሱም ወይም አክገዚም ህንፃ ሥራ በሽሬ፥ በዋልድባ፥ በጐንደር፥ በጣና፡ በጉዛም፡ (በወዛም) በወለጋ፡ በመቀደሽ፥ (መቋደሻ) ወይም በመቀድሾ በርበራ ድረስ ያሉ ሰባት ሲሆኑ የተሠሩትም የኃይላቸው ማረፊያ እንዲሆናቸው በሱርያኤል፥ በሰዳካኤል፥ በሰላታኤል፥ በአናንያኤል በአራቱ ነው ብለዋል። የሥራቸውም ዓይነት ከአንድ ድንጋይ ወጥ ሆኖ በአስደናቂ ሁኔታ የታነጹ ሲሆን ባለ 8 ባለ 6 እና ባለ 4 ማዕዘን ሲሆኑ ጣራቸውና ግድግዳቸው ጎብሩ በማይታወቅ ሐረግና በልዩ ልዩ ሥዕል ያሸበረቀና ያጌጠ ነው ይላሉ። የግብፅንና የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔና ዕደጥበብ እድገት ጭራሽ በመሰረዝ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የሥልጣኔ አሻራ ናቸው ተብለው የውጪ አገር ቱሪስቶች ጭምር እየጐበኙአቸው ያሉት ሐውልቶችና ህንፃዎች በሰው እጅ የተሠሩ ሳይሆኑ እሳቸው ከላይ በጠቀሱአቸው አማልክት የተፈጠሩ ናቸው በማለት እጅግ የሚያስገርም አደናጋሪ ሃሳብ በጽሑፋቸው አስፍረዋል።

በሌላ ክፍል ደግሞ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት የመናፍስት አሠራር ሲጠቅሱ ሚካኤል፥ ገብርኤልና ሩፋኤል ለኃይላቸውና ለሠራዊታቸው ማረፊያ እንዲሆናቸው የሠሩአቸው ቤተ መቅደሶችና የቤተ መንግሥት አዳራሾች በልዩ ልዩ መስቀሎችና ሐረጐች እንዲሁም በተለያዩ ሥዕሎች የተዋቡና ያሸበረቁ ናቸው ይሉና፤ እነዚህም የላሊበላ ዓይነት ተብለው በዘመዶ፥ በየጁ፥ በጋይንት፥ በሸዋ፥ በኤረር፥ በዝቋላ፥ በአዳዲ፥ በሐረር፥ በደብረ አሰቦት፥ በአሩሲ፥ በገሙጐፋ እስከ ከፋ ድረስ የሚገኙ ታላላቅ ብቻ አሥር ሲሆኑ ገና ያላለቁና ትንንሾቹ በጣም ብዙ ናቸው ይላሉ። የአክሱም ዓይነቱም ሆነ የላሊበላው ዓይነት በጣም አስደናቂ ህንፃዎች በየትኛው ተራራ በስንት ሜትር አፈር ተቆፍረው እንደሚወጡ ምስጢሩ እንደተጠበቀ ነው። ለመግለጽ ገና ነው። አልተፈቀደም ይላሉ። ፈቃድ ሰጪው ወይም ምስጢር ሆኖ እንዲጠበቅ ያደረገው ማን እንደሆነ ካለመግለጻቸው በላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ህንፃዎች በጭራሽ የሰው እጅ ያልነካቸውና እሳቸው በሰየሙአቸው ኃይሎች የተፈጠሩ እንደሆኑ አትተዋል።

ፀሐፊው ለመረጃ የተጠቀሙበት መጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ የምስጢሩ ቁልፍና ምንጭ ስለሆነ ይህ የተባለው መጽሐፍ በሙሉ ቃል በቃል ቢተረጐም በጣም አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ምስጢር ስላለው ጊዜ ይፍታው ብለዋል። መጽሐፉ በሰይጣን መንፈስ ወይስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ ቢሆን ነው?

14.2.4 ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩት ጳጳሳት አቋም እንደ ጸሐፊው አባባል

ጳጳሳት ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩት ለስለላ ነበር እንጂ ለሃይማኖታዊ ተግባር አይደለም ይላሉ በመጽሐፋቸው ገጽ 99 ላይ። በመቀጠልም ትምህርተ መለኮት ምስጢረ ሥላሴ በግብፅ ኮብቲክ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ አይታወቅም በማለት ከሐምሌ 10-15/1995 እ.ኤ.አ በግብፅ እስክንድሪያ በተደረገው «በአርቶዶክሶችና በወንጌላውያን መካከል ክርስቶስን እንዴት በአንድነት እንሰብካለን?» በሚል ርዕስ በተደረገው ስብሰባ እኚህ ጸሐፊ ከዚህ ተወክለው በሄዱበት ወቅት የግብፅ ኮፕቲክ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተቃውሞ ሃሳብ ማቅረባቸውን ገልጸው ግብፃውያን መጻሕፍትን ሳይመረምሩ በድፍረትና በድንቁርና ተገፋፍተው አላዋቂነታቸውን ገለጹ ካሉ በኋላ፤ እንደ እኛ ወልድ ዋሕድ የሚሉ በዓለም ውስጥ ግብፃውያን አባቶች ብቻ ነበሩ ብለው ለሚያምኑ ለኢትዮጵያ አባቶች ሊቃውንት በሙሉ ይህ አስደንጋጭ የሆነ አዲስ ምዕራፍ ነው ብለዋል።

በመቀጠልም በገጽ 99 ላይ ጳጳሳት ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡበት ምክንያት የግብፅ ሀገርም ሆነ ፈርያኖች በሙሉ እንዲሁም ከቅዱስ ማርቆስ ጀምሮ የግብፅ ፓትሪያርኮችና አብዛኛዎቹ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን ስለነበሩ ሥልጣኑም ሆነ አገሩ የኢትዮጵያ እንደሆነ ስለሚገመት ቀስ በቀስ አገሩን እንደገና እንይዛለን የሚል ዕቅድ ስለነበረና ይህም በኢትዮጵያ ካህናት ነገሥታትና መኳንንት ዘንድ ስለሚታመን መገናኛ መንገድ እንዲሆን ተብሎ ነው ይላሉ።

በማያያዝም ምንም ሥልጣን የሌለው ጳጳስ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣ የነበረው ግብፅ አገራችን ስለነበረ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለማድረግና በእጃችን ለማስገባት ለስለላም እንዲረዳ በምስጢር በመወሰኑ ነው ብለው አስፍረዋል። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ሰዎችና ታሪክ ጸሐፊዎች ይህንን ሃሳብ ምን ይሉታል?

ይህም የግብፅ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የጀመረው በ260 ዓ.ም ሆኖ የተቋረጠው በ1952 ዓ.ም ነው በማለት የሚላከው ጳጳስ ቋንቋችንን አያውቅም፥ እኛም ቋንቋውን አናውቅም፥ የቤተ ክርስቲያናችንንም ሥርዓት ማወቅ ቀርቶ የራሱንም ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ፈጽሞ የማያውቅ የለየለት መሃይም እንደነበረ የማይካድ ሃቅ ነው ብለዋል። ስለሆነም የሁለቱ አገሮች የመገናኛ መንገድ

ሆኖ ለስለላ ከሚያገለግል በስተቀር መብት የሌለው ዝም ብሎ የተቀመጠ ጉልት ነበር። እንዲያውም ከግብፅ የሚላከው ጳጳስ ጨርሶ ችሎታ የሌለው ከመሆኑም በላይ ክርስቲያን መሆኑም ስለማይታመን ግንኙነታችን የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በውስጠ ታዋቂ የፖለቲካ ወይም ምስጢራዊ ጭምር ነበር ይላሉ አባ።

ግብፅን ከኢትዮጵያ ጋር አዋህደን እናስተዳድራለን የሚል ዕቅድ የነበራቸው የአክሱም፥ የላስታ፥ የአንኮበር፥ የጐንደር ነገሥታትና መኳንንት እንዲሁም መንፈሰ ጠንካራ የሆኑ የተዋህዶ ካህናትና ሊቃውንት በማለቃቸው ምክንያት ግንኙነቱ በአምባሳደር ደረጃ ስለሆነ ግብፅን እንደገና እንይዛለን የሚለው የኢትዮጵያ ነገሥታት ዓላማና ምኞት በ1953 ዓ.ም ተቋረጠ፤ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ በመሾማቸው ከግብፅ ጋር የነበረን የረዥም ጊ፡ ግንኙነትም ተበጠሰ ይላሉ። የነገሩን ጭብጥ አቅጣጫ ለማስያዝ ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይህንን ይደግፉታል? ታሪክስ ምን ይላል?

14.2.5 ከነቢያት ከሐዋርያትና ከግብፅ ፓትሪያርኮች አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው ይላሉ

የመጽሐፉ ደራሲ ገብርኤልና ሚካኤል ኢትዮጵያውያን ናቸው አላሉም እንጂ ከነቢያትም ሆነ ከሐዋርያት አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው ከማለታቸውም በላይ ድንግል ማርያምም በዘር ሐረግ ኢትዮጵያዊት ናት ብለው መጻፋቸውን ከላይ ገልጸናል። ይሁን እንጂ የእነርሱ ኢትዮጵያዊ መሆን ወይም አለመሆን ለማናችንም በጽድቅና በቅድስና አንጻር የሚሰጠው ጥቅም ወይም ጉዳት የለውም። ሁሉም የየራሱን ዋጋ ይቀበላልና (ራዕ 22፥12) «እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና»። (ገላ. 6፥7)

እንግዲህ መጽሐፋቸው ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከታሪክ መጻሕፍት ጋር ጨርሶ የማይተዋወቅ ባዕድ ጽሑፍ ሆኖ የቀረበ ድርሰት ነው። በተለይም እውነተኛውን ታሪክ የሚያፋልሰው ይህ መጽሐፋቸው በገጽ 102 ላይ ካተተው ስንመለከት የፍሬምናጦስና የአድስዮስን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ሁኔታ ሲ.ያ፡ረዱ በ210 ዓ.ም ነጋዴዎች በአዶሊስ ባህር በር ሲገቡ ተገድለው ሁለት ሕፃናት ተረፉ። ሕፃናቱም በዕድሜ የአንድ ዓመትና የሁለት ዓመት ነበሩ። እነርሱንም ለአክሱም ንጉሥ በባሪያነት እንዲገዛ አስረከቡ። ከዚያም ንጉሡ ትምህርት አስተምሮ አሳድጐአቸው አንዱን የቤተ መንግሥት ጠጅ አሳላፊና ባለሙሉ ሥልጣን ሲያደርገው 2ኛው ደግሞ ድቁና ምንኩስና እና ቅስና ተቀብሎ

የቤተ መቅደስ አገልጋይ ኃላፊ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ተሾመ። ይህም አባ ፍሬምናጦስ ወይም አባ ሰላማ ከሣተ ብርሃን የተባለ ነው ይልና አባ ፍሬምናጦስ በ210 ዓ.ም ከኢትዮጵያ መነኮሳት ጋር 12 ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ ይላል። አባ ፍሬምናጦስ በ210 ዓ.ም የአንድ ዓመት ህፃን እያሉ ጳጳስ ሆኑ፤ ከዚያም የኢትዮጵያና የግብፅ ፓትሪያርክ በነበረው በኢትዮጵያዊው በቅዱስ አትናቴዎስ ሊቀመንበርነት ጉባዔ ተደርጐ ከምስር ሰዎች ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ አባ ሰላማ (ፍሬምናጦስ) ብቻ በአስቸኳይ ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ሌሎቹ እዚያው ቀርተዋል ይላሉ። የሆነ ሆኖ የክርስትና ሃይማኖት ራሱ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ330 ዓ.ም መሆኑን አላወቁም?

ስለ ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት አባቶችና ስለ ሐዋርያት ኢትዮጵያዊነት በገጽ 99 ላይ ሲጠቅሱ 1) ማቴዎስ 2) ማርቆስ 3) ፊልጶስ 4) ቶማስ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ 5) ያዕቆብ 6) ዮሐንስ 7) ባርናባስ ግማሽ ኢትዮጵያውያን ናቸው ይላሉ። ግን ናቸው? ቢሆኑስ ያስመካል?

በምስር የኢትዮጵያ ፓትሪያሪኮች ነበሩ ያሉአቸው ደግሞ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

1) ማርቆስ - ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ ነው (በፓልስቲን የተወለደ)

2) አትናቴዎስ - ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ ነው (በላዕላይ ግብፅ የተወለደ)

3) ቄርሎስ - በእናቱ ኢትዮጵያዊ በአባቱ የግሪክ የአርመን ተወላጅ ነው።

4) ዲዮስቆሮስ - በእናቱ ኢትዮጵያዊ በአባቱ ግሪካዊ ነው ይላሉ።

እንግዲህ ይህንን ሁሉ የጠቀስነው አንባቢ እውነትን ከውሸት፥ ፍሬን ከገለባ ለይቶ ለመረዳት ትኩረት በመስጠት እንዲያገናዝብ ነው፤ ሐሰተኛው ማን እንደሆነም ለማወቅ ከትክክለኛው የዓለምና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍት ጋር ማገናዘብ የእውነትን ፍንጭ ያስጨብጣልና።

ማንኛውም ነገር በጥሞና ሳይታይ በግብታዊነት መቃወም ወይም በጭፍኑ መደገፍ ጉዳት ነው። ዋጋ የሚያስከፍል እንኳን ቢሆን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት፥ ለሰውም እውነትን ለመግለጽና ለውሸት ከመኖር ይልቅ ለእውነት ለመሳዳት መወሰንና እውነትን አጉልቶ ማሳየት ከእውነተኛ ሰው ይጠበቅበታል። እኚህ ጸሐፊ ተቃውሞ ያቀረቡበት «ኢትዮጲስ» የተሰኘው መጽሐፍ የአንድ ሰው አእምሮ ያፈለቀው

የፈጠራ ድርሰት ሳይሆን በአግርኛና በእንግሊዝኛ በብዙ ጥናትና ምርምር ከተጻፉት ከበርካታ የዓለምና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍት ተጨምቆ የወጣና የጠለለ ጽሑፍ መሆኑን በማንበብ ሚዛናዊ የሆነ የህሊና ፍርድ ይሰጡ ዘንድ እናሳስባለን። እውነት ምን ጊዜም እውነት ነው። ውሸት ግን ሌላ ቀለም ተቀብቶ፥ መልኩን ሊቀይር ቢሞክርና ለጥቂት ጊዜ ቢያደናግርም ውሸት ያው ውሸት ነው። እውነት ሲገለጥ ውሸት ተጋልጦ እርቃኑን ይቀራል።

ስለዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን በማገናዘብ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያጐድፈው ኢትዮጲስ መጽሐፍ ነው ወይስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው . . . የተባለው መጽሐፍ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ያለ አድልዎ እውነትን በእውነትነቱ ለመረዳት እንዲቻል የቀረበ ጽሑፍ መሆኑን ለክቡራን አንባቢዎች በትህትና አሳስባለሁ።

14.3 «መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ ምን ይላል?» የሚል መጽሐፍና ይዘቱ

የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ አባባል በተሳሳተ መልክ በመተርጐም ከተቀነባበሩት መጻሕፍት መካከል በአህመድ ዲዳት ተጽፎ በዘካሪያ መሐመድ በ1985 ዓ.ም የተተረጐመ «መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ ምን ይላል?» የሚል መጽሐፍ ይገኝበታል።

በመጽሐፉ ላይ ጸሐፊው አህመድ ዲዳት «ቄስ ቫንቬርድን የተባለውን ሰው በስልክ አግኝቼው ቀጠሮ በመያዝ በግንባር ከተገናኘን በኋላ ‹መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ ምን ይላል?› ብዬ ጥያቄውን ደነቀርኩት» ይላሉ። ቀጥሎም መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ስለሚከሰቱት ስለ ብዙ ነገሮችና ስለ መጪረሻዎቹም ቀናት ሲተነትን እንዴት ዓለማችንን ላጥለቀለቋት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምዕመናን መከሰት ምክንያት ስለሆኑት ስለ መሐመድ አልተጠቀሰም? በስም ሳይሆን በትንቢት ተናግሯል በማለት አሪት ዘዳግም 18፥18 ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ፥ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝኩትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል የሚለው ስለ መሐመድ የተጻፈ ነው፤ በማለት የሙሴንና የመሐመድን የሕይወት ሁኔታ በማብራራት ሁለቱን አንድ ለማድረግ ይሞክራሉ። ለዚህም ማስረጃ ይሆናል በማለት ብዙ ሀተታ አቅርበዋል። እንደ አንተ ያለ ነቢይ . . . የሚለውን ደረጃ

በደረጃ ለመግለጽ ከአንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጫፍ ወደ ሌላው ተወናጭፈዋል።

በዚህም መላ ምታቸውና በእርሳቸው መረዳት እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ትንቢት የተነገረለት ሙሐመድ ነው። ኢየሱስ ግን በምንም መልኩ ሙሴን አይመስልም ብለው ደምድመዋል።

ቀጥሎም በመጽሐፋቸው በገጽ 21 ላይ ሁሉን መርምሩ በሚል ርዕስ ለክርስቶስ በጐች የምመክራችሁ አለኝ። ማንም ነቢይ ነኝ ብሎ ቢመጣባችሁ መምህሩ ራሱ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ . . . (ማቴ. 7፥16-20) ብሎአልና ተጠንቀቁና መዝኑ። ታዲያ ለምንድነው የሙሐመድን ትምህርቶች ለመቀበል የምትፈሩት? ከፈጣሪ በተወረደው የመጨረሻው ኪዳን ቅዱስ ቁርአን ውስጥ ዓለም በእጅጉ የሚናፍቃቸውንና ሰላምና ደስታ የሚያሰፍኑትን ታገኛላችሁ ብለዋል።

ጸሐፊው ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ያምናሉ? እንግዲያውስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑና የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል መሆኑን የሚቀበሉ ከሆነ ከላይ የጠቀሱት ዘዳግም 18፥18 የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንደ እርሳቸው በይመስላል ሳይሆን ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንግለጽላቸው።

እዚህ ላይ ለሁሉም ግልጽ ሊሆን የሚገባው በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕ. 1፥20-21 እንደተጠቀሰው ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ . . .። የሚል መለኮታዊ ቃል ተጽፎ ይገኛል። በተጨማሪም በራዕይ 22፥18 በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ እኔ እመሰክራለሁ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል። ማንም በዚህ ትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጐድል በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጐድልበታል ይላልና ለግል አመለካከትና ጥቅም በማድላት ትዕዛዙን በመጣስ በቃሉ ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ ፈጽሞ ክልክል ነው።

14.3.1 «ከወንድሞቻቸው መካከል» የሚለው ቃል ትክክለኛው አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ፤

አህመድ ዲዳት በጠቀሱት በዘዳግም ምዕራፍ 18 ከቁጥር 1-18 ባለው ክፍል ብቻ «ወንድሞች» የሚል ቃል አራት ጊዜ ተጽፎ ይገኛል።

ሀ) ቁጥር 1-2 ለሌዋውያን ካህናት ... <u>በወንድሞቻቸው</u> መካከል ርስት አይሆንላቸውም የሚል፤

ለ) ቁጥር 6-7 አንድ ሌዋዊ ሰው ... በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆሙት እንደ <u>ወንድሞቹ</u> እንደ ሌዋውያን ሁሉ በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት ያገለግላል የሚል፤

ሐ) ቁጥር 16 አምላክህ እግዚአብሔር ካንተ መካከል <u>ከወንድሞችህም</u> እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳልሃል፥ እርሱንም ታደምጣለህ የሚልና፤

መ) ቁጥር 18 <u>ከወንድሞቻቸው</u> መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝኩትን ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል ... የሚል ይነበባል።

ስለዚህ እነዚህ ክፍሎች በትክክል የሚያወሱት አህመድ ዲዳት እንዳሉት ስለ እስማኤልና ስለ ይስሐቅ ሳይሆን ወንድማማቾች ስለሆኑት ስለ አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተላለፉ ሕጐችና የትንቢት ተስፋዎች እንደሆኑ ግልጽና የማይታበል ሐቅ መሆኑን ከቃሉ መገንዘብ ያሻል። <u>ለነገሩማ</u> በራዕይ 22፥18 ላይ እንደተጠቀሰው ... የተጻፈውን የትንቢት ቃል « <u>ለሚሰማ</u>» እኔ እመሰክራለሁ ነው የሚለውና የሚሰሙና እውነትን በእውነትነቱ ለመረዳት የሚፈልጉ ሆነው ከተገኙ ከላይ የተጠቀሰው ክፍል (ዘዳ. 18፥18) ስለ ሙሐመድ ሳይሆን ስለ ኢየሱስ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ምላሽ ይሰጣል። ይኸውም በአዲስ ኪዳን የሐዋርያት ሥራ ምዕ. 3፥17-26 ... እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው። እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና። ሙሴም ለአባቶች፥ ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሳኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሳላችኋል። በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት። ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። ሁለተኛም ከሣሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ። እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን

አስነስቶ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው። ይላል።

ይህ በሐዋርያት አገልግሎት እግዚአብሔር ቀደም ሲል በሙሴ አማካይነት በዘዳግም 18፥18 የተናገረው የተስፋ ትንቢት በክርስቶስ ኢየሱስ መወለድ መፈጸሙ በገሃድ የተገለጠው ገና መሐመድ ከመወለዱ ከአምስት መቶ ሠላሳ ስድስት ዓመታት ገደማ በፊት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ነው። ምክንያቱም ሙሐመድ የተወለደው በ570 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነውና።

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያየ የግል አመለካከትና የዕውቀት ደረጃ ሊኖራቸው ይችል ይሆናል እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን ማንም እንደገዛ ፈቃዱ እየቀለበሰ እንዳይተረጉም ከፍ ብሎ በራዕይ መጽሐፍ እንደተመለከተው በማስጠንቀቂያ የተዘጋ ነው። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እየጠቀሱ ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን መበረዝና አንባቢን ማደናገር ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ነው።

ለአህመድ ዲዳት ጽሑፍና ለመሰል ጽሑፎች የማሳስበው ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድን አንቀጽ ወይም ቃልና ጥቅስ ብቻ ይዞ ሁለንተናው ይህ ነው ብሎ መደምደም የስህተት ትምህርት ስለሆነ በጥንቃቄ ምዕራፉ በሙሉ ምን እንደሚል በጥሞና አንብቦ ትክክለኛውን ፍሬ ሃሳብ መጨበጥ ይጠቅማልና መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስን እገዛ በጸሎት ይጠይቁ። ይህ ካልሆነ ጸሐፊዎች ራሳቸው ስተው ሌሎችንም የሚያስቱ ይሆናሉ። «... በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር»። (ማቴ. 18፥6 ማር. 9፥42 ሉቃ. 17፥1-2)

«ነገር ግን ሃሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ መካከል ነበሩ ... እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳን ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ፤ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል» ይላል። (2ጴጥ. 2፥1-2)

ስለዚህ በዘዳ. 18፥18 የተሰጠው ትንቢታዊ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ ሰው ሆኖ በመምጣቱ ስለ መፈጸሙ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በማያሻማ ሁኔታ እውን ስላደረገው ሙሐመድን በኢየሱስ ቦታ ለማስገባት አህመድ ዲዳት ጥቅስ በመጥቀስ የሞከሩት ሙከራ አልተሳካላቸውም። ደግሞም ኢየሱስ ራሱ እኔ ብሄድ ይሻላችኋል እኔ

ባልሄድ አጽናኙ አይመጣም በማለት ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል ...። (ዮሐ. 14፥15-18) ያለው ስለ «ሙሐመድ» ነው የሚሉም አሉ። እነዚህ ደግሞ ሙሐመድን በመንፈስ ቅዱስ ቦታ ሊተኩ የሚጥሩ ናቸው። ጌታ ኢየሱስ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ይላክላችኋል ያለውን ስለ አንድ ሥጋ ለባሽ ሳይሆን ስለ ትክክለኛውና ከሦስቱ የመለኮት አካላት አንዱ ስለሆነው ስለ አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ነው። ምክንያቱም እርሱ ዘላለማዊ አምላክ ነውና።

ስለዚህ መምህር ኪዳን ማርያም ጌታሁን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ የሚለው ምንም ነገር የለም ብለው በጻፉት መጽሐፍም እንደተገለጸው በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ብዙ ነገሮች በግልጽ በምስጢር፥ በኃላፊና በትንቢት የሚናገር ቢሆንም ስለ ሙሐመድ ግን የሚለው ምንም ነገር የለም።

14.4 ሽህ አህመድ ዲዳት ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ክርስትና እምነት ምን እንዳሉ ያውቃሉ?

14.4.1 የይሆዋ ምስክር ነኝ ከሚል ሰው ጋር ያደረጉት ክርክር

በዚግንታቸው ደቡብ አፍሪካዊ የሆኑትና እ.ኤ.አ በ1918 ዓ.ም የተወለዱት ሽህ አህመድ ዲዳት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስንና አማኞቹን «ከእግዚአብሔር አይደሉም» ለማለት ከጻፉአቸው መጻሕፍት ውስጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "IS THE BIBLE GOD'S WORD?" (መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን?) በሚል ርዕስ የተጻፈ ይገኝበታል። ተጠቃሹ ግለሰብ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞችንና የሥነ መለኮት አስተማሪዎችን እንዲሁም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው ያሉአቸውን ሰዎች ስም በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ግለሰቦች ያዘጋጁት የሰዎች የሃሳብ ውጤት ስለሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ሊባል አይችልም ብለው በድፍረት ጽፈዋል። ለዚህ ጽሑፋቸው መነሻ ምክንያት ሲጠቅሱ በአሁኑ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን የሚሉትንና የይሆዋ ምስክሮች የሚባሉት (WATCH TOWER) «መጠበቂያ ግንብ» "AWAKE" «ንቁ» በሚል ርዕስ ሴፕተምበር 8/1957 ባዘጋጁት መፅሄት በገፅ 13 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሃምሳ ሺህ ስህተት አለበት ብለው ፅፈው ያሰራጩትን በመጥቀስ ነው። ይኸውም ከዕለታት አንድ ቀን የዚሁ የመጠበቂያ ግንብ (Watch Tower) አባል የሆነ ግለሰብ በራቸውን አንኳኩቶ ከገባ በኋላ ስለ ሃይማኖቱ

ሊያስተምራቸው በመፈለጉ በእጁ ይዞት የነበረውን የድርጅቱን መጽሔት እንዲያነቡ ይሰጣቸዋል። ሰውየው የመጠበቂያ ግንብ አባል መሆኑን ሲረዱ ከሃያ ሶስት ዓመት በፊት በድርጅቱ የተዘጋጀውንና «ንቁ!» በሚል ርዕስ የተፃፈውን መጽሔት ካስቀመጡበት ቦታ እንዳመጡለትና በመጽሔታቸው ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሃምሳ ሺህ ስህተት አለበት ብላችኋል አሁን ስለዚህ ልትነግረኝ ነው? ብዬ ጠየኩት ይላሉ። እርሱም መልሶ አሁን አብዛኛዎቹ ስህተቶች ተወግደዋል ሲላቸው መልሰው ታዲያ ስንቶች ስህተቶች ተወግደው ስንት ቀሩ ብለው ሲጠይቁት መመለስ አቅቶት ሌሎቹም አባሎቻቸው እንደሚያደርጉት ይቅርታ ያድርጉልኝ ቀጠሮ ከሰጡኝ ከኔ የበለጠ የሚያውቁትንና ጥያቄዎን ሊመልሱ የሚችሉትን ሌሎች ሰዎች ይዤ እመጣለሁ ብሎ እንደሄደና በዚያው ሳይመለስ እንደቀረ ጠቁመዋል።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ሽኹ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት ሆኖ ሳለ የመጽሐፉ ሊቃውንትና የሥነ መለኮት መምህራን ሕዝቡን ለማሳመን ሲሉ በጭፍን መጽሐፍ ቅዱስ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው ይላሉ ብለዋል።

በአጠቃላይ የአህመድ ዲዳት ጽሑፍ ዋና ዓላማና ትኩረት የክርስትናን እምነት ከሥር ለመናድና መጽሐፍ ቅዱስን የሰው ሃሳብ ነው ለማለት እንደሆነ ግልፅ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለመቃወም የተለያዩ የቁርዓን ጥቅሶችን በእንግሊዘኛና በዐረብኛ ቋንቋ ጽፈዋል። በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስህተት ናቸው የሚሉአቸውንና ከመጠበቂያ ግንብ አባላት ስህተት አለበት ተብሎ በ«ንቁ» መጽሔት ላይ የተሰራጨውን በማገጣጠም ከእርሳቸው የእምነት አመለካከት ጋር የማይጣጣመውን የእግዚአብሔር ሃሳብ ወይም የእግዚአብሔር ቃል አይደለም በማለት ተቃውመዋል።

14.4.2 ኢየሱስ ፈጣሪም አምላክም አይደለም ይላሉ ጸሐፊው

አህመድ ዲዳት «ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነው?» በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ደግሞ ኢየሱስ ፈጣሪና አምላክ አይደለም ለማለት የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች እየቀነጫጨቡ ሥር ያልሰደደ ሰው ካገኙ ለማፍረስና ለመናድ መሠረተቢስ ሃሳብ ጠቅሰዋል። ይህንኑ መጽሐፍና የጸሐፊውን የተሳሳተ አመለካከት በመቃወም መምህር ኪዳን ማርያም ጌታሁን «አዎ ኢየሱስ ፈጣሪ ነው» በሚል ጽሑፍ ለአህመድ ዲዳት የተሰጠ መልስ በማለት በየርዕሱ ልብ ለሚል ተገቢ ምላሽ ሰጥተዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያውቁ የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑት ክርስቲያኖች እንጂ አንድ ድንበር ዘለል

ሙስሊም ነኝ ባይ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እኔ አውቅላችኋለሁ ለማለት ያስደፈራቸው የትኛው መንፈስ ነው? ለመሆኑ አንድ ክርስቲያን እርሳቸው እንዳደረጉት ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከሌላ መጽሐፍ እየጠቀሰ እስልምናና ቁርዓን ስህተት አለባቸው ብሎ ቢጽፍ ደስ ይላቸዋል? እንደዚህ ዓይነቱ የማፍረሻ ጽሑፍስ ወደ ፍቅር ወይስ ወደ ጥላቻ ያመራል? ብለው ከወዲሁ መገመት ነበረባቸው። አህመድ ዲዳት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው የሚያምኑትን ሰዎች አጉል የዋህነት ያለባቸው ደንቆሮዎች፥ ዲዳዎችና እውሮች ሲሆኑ የእውነትን ብርሃን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን እናምንበታለን የሚሉት መጽሐፋቸው የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለመሆኑን እንኳን አያውቁም ብለው፤ ቁርዓን 2፥18ን ለመረጃ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም የካቶሊክ የአርቶዶክስና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሚያምኑበትን የክርስቶስን መለኮታዊነትና የሥላሴን (የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ) ትምህርት የሚቃወሙ ግንብ ጠባቂ የሚባለው (watch tower) ድርጅት አምሳ ሺህ ስህተት አለበት ብሎ የጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም የኪንግ ጀምስ ቨርሽንና ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርሽን ነው ብለዋል። ከዚህም በመቀጠል ሸኹ የዚህን የእምነት ክፍል ባህርይና የከፈተውንም ቀዳዳ በዚሁ አጋጣሚ በመጠቀም ተቃውሞአቸውን በመጽሐፍ ቅዱስና በክርስቲያኖች ላይ አነጣጥረዋል።

14.4.3 የመጽሐፍ ቅዱስን ሃሳብ በቁርዓን ጥቅስ ለማፍረስ ሲሞክሩ

የተቃውሞ ጽሑፍ አዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ እየጠቀሱ በቁርዓን ሃሳብ በማፍረስ ለምሳሌ፥ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳ. 7፥14) ብሎ ነቢዩ ኢሳያስ ከክርስቶስ ልደት ሰባት መቶ አምሳ ዓመታት ገደማ በፊት የተነበየውንና «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3፥16) ተብሎ የተጠቀሰውን እንዲሁም በ 1ኛ ዮሐ. 5፥7 ላይ ያለውን የአብን የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ አንድነት በመቃወም ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው በቁርዓን 4፥171 የተጻፈው ብቻ ነው ብለው ለክርስቲያኑ ሕዝብ ቁርዓንን ለማስተማር ይሞክራሉ።

ሼህ አህመድ ዲዳት የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን መጻህፍት እየጠቃቀሱና አንዱን ክፍል ከሌላው ጋር እያነፃፀሩ የቁጥርም ሆነ የሃሳብ ልዩነት አለ የሚሉበትን እያስፋፉ

ለተቃውሞአቸው ማጠናከሪያነት ተጠቅመዋል። በቁርዓን 2፥79 ያለውን እንደ መረጃ በመጥቀስ «መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት የእግዚአብሔር ቃል ነውን?» የሚለውን ክርስቲያኖቹ ራሳቸው ያስቡበት። ይልቅስ ቁርዓን ትክክለኛና የተአምሮች ተአምር ነውና ሰው ሁሉ ሊያነበው ይገባል በማለት ይህንኑ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊተነትኑ እንደሚችሉ ዘግበዋል።

በማጠቃለያም መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ቁርዓን ከሰማይ የወረደ ሳይሆን ሰዎች ከሃሳባቸው አውጥተው በእጃቸው የፃፉት ነው በማለት ደምድመዋል።

14.4.4 የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች የተሰኘ ቡድን ያሠራጨው ፓምፍሌት ይዘት

ይህ በዚህ እንዳለ «የጁምአው መልዕክት» በሚል ርዕስ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ተብሎ በሚጠራው ድርጅት የሚሠራጭ ነው የሚባለው ፓምፍሌት ቅጽ 1 ቁጥር 004/1985 እንደጠቀሰው ክርስቲያኖችን «በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ቅዱስ ነውን?» ብሎ ይጀምራል። ከዚያም በመቀጠል በጥያቄና መልስ በማስመሰል ሙስሊሙን ጠያቂ ክርስቲያኑን መልስ ሰጪ አድርጎ አቅርቦአል። በዚሁ ቲያትር መሰል ጥያቄና መልስ ሙስሊሙ ክርስቲያኑን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አኳያ እንደረታውና መልስ እንዳሳጣው ይገልጻል። ይህንንም ከአህመድ ዲዳት መጻሕፍት የቀሰሙት እንደሆነ ይታወቃል። አላማና ሃሳባቸውም አንድ ነው። በተለይም በ2ኛ ሳሙኤልና በ1ኛ ዜና መዋዕል የተጠቀሱትን ጦርነቶችና ለጦርነቱ የተሰለፉትን ሰረገላንና የፈረሶችን ቁጥር በማነፃፀር ቁጥሩ በሁለቱም መፃህፍት እኩል አሀዝ ያልሆነው መጽሐፍ ቅዱስ «ቅዱስ» ባለመሆኑ ነው ይላል። የተጠቀሰው የወጣቶቹ ድርጅት ነው የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች ከአንድ ቦታ በመጥቀስና ከሌላው ክፍል ጋር ለማጋጨት በመሞከር መጽሐፍ ቅዱስ «ቅዱስ አይደለም» ካሉ በኋላ የመጨረሻው አሻንጉሊታዊ ጥያቄ «ብዙ ለማወቅ ትፈልጋለህ?» መጽሐፋችሁ ቅዱስ ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ይህ አይበቃም? በማለት በማያገባቸው ገብተው በአንድ በኩል ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ትክክለኛነት የሚከራከሩ ተሟጋቾች ሲመስሉ በሌላ በኩል ደግሞ «መጽሐፋችሁ ቅዱስ አይደለም» ብለው የክርስትናን ሃይማኖት ከሥር ሊነቅሉ ይሞክራሉ። «በአለት ላይ የተመሰረተች ቤተ ክርስቲያን ግን የገሃነም ደጆች አይችሉአትም።» (ማቴ. 16፥18)

አንዳንድ መናፍቃን ወንጌልን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እያጣመሙ በመተርጎም ሌሎች ደግሞ «ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች

እያሳቱና እየሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ» (2ጢሞ. 3÷13) «ጆሮአቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። (2ጢሞ.4÷3) ተብሎ እንደ ተፃፈ በወንጌል ሃሳብ ከመመራት ይልቅ የወንጌልን ሃሳብ በራሳቸው ሃሳብ ውስጥ መጨፍለቅ ይቃጣቸዋል። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «እኛ ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን (ገላ. 1÷8-9) ያለው።

አህመድ ዲዳት ከዚህ በላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ጽሑፎቻቸው እንደጠቀሱት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስነትና ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት የተምታታባቸው መሆኑ ስለሚታወቅ እንደ እርሳቸው በጠማማ ትርጓሜ ሳይሆን በቀና መንፈስ ለማወቅ ለሚሻ እውነትን ለመግለጽ እንወዳለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ማንም ተነስቶ እኔ አውቃለሁ÷ ያገባኛል ብሎ ሊቀይረው÷ ሊያሻሽለው ወይም ሊሸረው አይችልም። ከላይ እንደተጠቀሰው የሃይማኖት ድርጅትም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ያህል ስህተት አለበት ብሎ መገምገም የሚችል የለም (ራዕ. 22÷18) ቃሉ ህያውና ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች የተባለ ቡድንም ሆነ አህመድ ዲዳት ያሰራጩአቸውን ዓይነት ጽሑፎች በተገላቢጦሽ ክርስቲያኑ ቢጽፍ ምን እንደሚሉ ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

14.5 ክርስትናና እስልምና በኢትዮጵያ

በአገራችን በኢትዮጵያ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ለብዙ ዘመናት በአንድነት ኖረዋል። የሁለቱን ሃይማኖቶች መመሪያ መጻህፍት ግለትም መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርዓንን በምንመለከትበት ጊዜ ልዩነት መኖሩ የማይካድ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ካለው ልዩነት ይልቅ ስምምነቱ ጎልቶ ይታያል።

ሙሐመድ ጣአትን ማምለክ ትታችሁ በአንዱ አምላክ ብቻ እመኑ ብሎ የእስልምናን ሃይማኖት ማስተማር በጀመረበት ጊዜ በመካ ውስጥ የነበሩት የጣኦት አምላኪዎች ይህ ሰው እምነታችንን ሊያፈርስ ነው ብለው በእርሱና በተከታዮቹ ላይ ትልቅ ስደት ስላስነሱ ህፃናት ሳይቆጠሩ

አንድ መቶ ሰባት የሚሆኑ ተከታዮቹንና ዘመዶቹን የክርስቲያን ንጉሥ ወደነበረባት ወደ ኢትዮጵያ በሦስት ዙር ልኮ በአገራችን ውስጥ በነፃነት የሚያመልኩበትና በሰላም ያለ ስጋት የሚኖሩበት ሥፍራ ተሰጥቶአቸው በኢትዮጵያ ውስጥ መቀመጣቸው ከዚህ በፊት ተገልጾአል።

በክርስትናና በእስልምና መካከል የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት እንዳለ አስመስለው የሚያሳዩት አንዳንድ የሃይማኖቱ መሪዎች ናቸው እንጂ የሁለቱ ሃይማኖት መመሪያ የሆኑት ቅዱሳት መጻህፍት ይህንን አይናገሩም። ለምሳሌ በቁርዓን ውስጥ በሱራ (ምዕራፍ) 5÷82 ከአይሁዳውያን ይልቅ ክርስቲያኖች ለእስልምና አማኞች የቀረቡ ወዳጆች እንደሆኑ ይናገራል። ይህም ለምን እንደሆነ ሲያብራራ «እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለእነዚያ ለአመኑት (ለእስላሞች) በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ። ይህ ከእነሱ (ከክርስቲያኖች) ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው» ይላል።

በቁርዓን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ እንደተጠቀሰ እናያለን። የተጠቀሰበትም ዋነኛ ስሙ «ዒሳ» የሚል ነው። በተጨማሪም የማርያም ልጅ አልመሲህ÷ ከአላህ የመጣ ቃል÷ መንፈስ÷ ነቢይ÷ የተከበረ÷ ከአላህ ባለሟሎች የሆነ ወዘተ. የሚሉ ብዙ ስሞች ተሰጥተውታል። በተለይ «ከአላህ የመጣ ቃል» የሚለውን ስም በምንመለከትበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠው ስም እንደሆነ እናያለን። ሱራ 3÷45 «መርየም ሆይ÷ አላህ ከእርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲህ ኢሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጪረሻው ዓለም የተከበረ ከባለ ሟሎቹም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል» ይህንን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ቃል ጋር ስናስተያየው አስደናቂ ስምምነት አለው። በዮሐ. 1÷1 እና 1÷14 «በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ቃልም ሥጋ ሆነ» ይላልና ሁለቱም መጻሕፍት ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የመጣ (የሆነ) ቃል እንደሆነ ይመሰክራሉ። «በዚህ ዓለምና በመጪረሻው ዓለም የተከበረ» የሚለውን ሐረግ በምናነብበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ይህንን የሚደግፍ ቃል እንዳለ እናያለን። ኤፌ. 1÷21 «በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ» ይላል።

ቁርዓን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም እንደተወለደና ምንም ኃጢአት እንደሌለበት ይናገራል። መርየም (ማርያም) በሚለው በሱራ 19 ውስጥ በቁጥር 19 መልአኩ ጂብሪል «ንፁህን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልዕክተኛ ነኝ አላት» የሚል ቃል እናነባለን። ኢየሱስ ክርስቶስ

ከኃጢአት ፍፁም የነፃ እንደሆነ የሚያስረዳ ቃል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም «ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀካህን የለንም» ዕብ. 4፥15 በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት እንደሌለበት ያስረዳናል። በተጨማሪም በቁርዓን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስለ ሞቱና ከሞት ስለ መነሳቱ ይናገራል። በሱራ 19፥33 «ሰላምም በእኔ ላይ ነው፥ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ህያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን» ይላል።

በቁርዓን ውስጥ (ተውራት ዘቡር ኢንጂል) ኦሪት መዝሙረ ዳዊት ነቢያትና ወንጌል ከእግዚአብሔር የተሰጡ ቅዱሳት መጻህፍት እንደሆኑና እነርሱን ማመንና መከተል እንደሚያስፈልግ ያሳስባል። ከዚህ ቀጥሎ ይህንን የሚያረጋግጡ ጥቅሶች ከቁርዓን ቀርበዋል።

ሱራ 3፥3 «ከርሱ በፊት ያሉትን መፃህፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን መፅሐፉን (ቁርዓን) ባንተ (በመሐመድ) ላይ ከፋፍሎ በውነት አወረደ። ተውራትንና (ኦሪትን) ኤንጂልንም (ወንጌልን) አውርዶአል። ሱራ 5፥47 «የኢንጅልም ባለቤቶች (ክርስቲያኖች) በውስጡ አላህ ባወረደው ህግ ይፍረዱ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመፀኞች እነርሱ ናቸው። ሱራ 5፥44 «እኛ (አላህ) ተውራትን (ኦሪትን) በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን። ሱራ 5፥46 «በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበትን በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም (ኦሪትን) የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው» ሱራ 5፥48 «ወደ አንተም መጽሐፉን (ቁርዓንን) ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ (ኢንጅልን) አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን»።

ይህ ጥቅስ በግልፅ እንደሚናገረው ቁርዓን ለመሐመድ የወረደው ተውራትንና ኢንጂልን ለመቃወም ሳይሆን ለማረጋገጥ ነው። ሱራ 41፥43 ካንተ (መሐመድ)በፊት ለነበሩት መልዕክተኞች የተባለው ቢጤ እንጂ ለአንተ ሌላ አይባልም። ሱራ 10፥94 «ወደ አንተም ካወረድነው (ቁርዓን) በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን (ኦሪትንና ወንጌልን) የሚያነቡትን ጠይቅ። በዚህ ጥቅስ መሠረት እስላሞች ኦሪትንና ወንጌልን የምናነበውን ክርስቲያኖችን መጠየቅ ወይም ለራሳቸው ኦሪትንና ወንጌልን አንብበው በውስጣቸው ያለውን ብርሃንና ምሪት መረዳት ይችላሉ ማለት ነው። ሱራ 5፥68 «እናንተ የመጽሐፉ

(የመጽሐፍ ቅዱስ) ባለቤቶች ሆይ ተውራትንና (ኦሪትን) ኤንጂልን (ወንጌልን) ከጌታችሁም ወደ እናንተ የወረደውን እስከምትሰሩባቸው ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንኑ ያስጠነቅቀናል። «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ» (ያዕ. 1፥22) እስላሞች በቁርዓን ብቻ ሳይሆን በመዝሙራት፥ በኦሪትና በወንጌልም ማመን እንዳለባቸው ቁርዓን ያዛል። ሱራ 3፥84 «በአላህ አመንን በኛ ላይ በተወረደውም (በቁርዓን) በኢብራሂምና በኢስማኤልም በኢስሃቅም በያዕቆብም በነገዶችም ላይ በተወረደው ለሙሳና ለኢሳም ለነቢያትም ሁሉ ለጌታቸው በተሰጠው (አመንን) ከእነርሱ መካከል አንድንም አንለይም እኛ ለርሱ ታዛዦች ነን በል»።

ቁርዓን ብርሃንና ምሪት እንዳለበት የሚመሰክርለትንና የመርየም ልጅ ስለሆነው ንፁህ ልጅ የሚናገረውን ኢንጂልን (ወንጌልን) አንብበው በውስጡ ያለውን ብርሃን እንዲመለከቱ እና የዘላለም ህይወት ለማግኘት እውነትን እንዲረዱ እንጠቁማለን።

14.5.1 ኢንጂል (ወንጌል) የሚያስተላልፈው መልዕክት በአጭሩ

1) «ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል»። ሮሜ 3፥23 (ማለትም ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው)

2) የኃጢአት መጨረሻው (ኃጢአት የሚያስከፍለው ዋጋ) የዘላለም ጥፋት (ገሃነመ እሳት) ነው። «የኃጢአት ደመወዝ የዘላለም ሞት ነው» ሮሜ 6፥23

3) እግዚአብሔር (አላህ) በኃጢአታችን እንድንጠፋ ስለማይወድ ለሰው ልጆች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ላከልን። «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ» ሮሜ 5፥8

4) ስለ ኃጢአታችን ንስሃ ገብተን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወታችን በእምነት ከተቀበልነው የዘላለም ህይወት እናገኛለን። ኢየሱስ በኢንጂል (በወንጌል) ውስጥ እንዲህ ይላል። «እነሆ በ(ልባችሁ) ደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም (ልቡንም) ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ»። ራዕይ 3፥20 በተጨማሪም ኢየሱስ እንዲህ ይላል፤ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ። እኔም አሳርፋችኋለሁ። ማቴ. 11፥28

14.6 «ሃይማኖት አይለያየንም» የሚል መጽሐፍ ይዘት

14.6.1 የሊቢያው የጋራ ጉባዔ ዋና ዓላማ

ሃይማኖት አይለያየንም የሚል መጽሐፍ ደራሲ የሆኑት መምህር ኪዳነ ማርያም ገ.ሕይወት በዚህ መጽሐፋቸው በእስልምናና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሊቃውንት መካከል በሊቢያ ዋና ከተማ በትሪፖሊ ውስጥ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት መአመር ጋዳፊ በተገኙበት የተደረሰውን ስምምነት በማስመልከት የእርስ በእርስ መጠላላት እንዲወገድ አስተዋፅኦ ያደርጋል ብሎ የጋራ ስብሰባው የወሰነውን ውሳኔ አቀነባብረው አቅርበዋል።

በመጽሐፉ መቅድም ላይ ስለ ጽሑፉ ይዘት ሲያብራሩ የሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮችም በሃይማኖት ምክንያት አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ ይመለከተው እንደነበረ ገልፀዋል። ከዚሁ ጋር ስለ ሁለቱ ሃይማኖቶች ቅዱሳት መፃህፍት ሲገልፁ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቁርዓን ጥቅሶችን መጥቀስ ሁለቱንም ሃይማኖቶች ከሚያራርቁ ይልቅ የሚያቀራርቡ ነጥቦች እንደሚበዙ ጽፈዋል።

ይህንኑ በተመለከተ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማኅተሚያ ድርጅት ስለ መጽሐፉ ይዘትና በውስጡ ስለተፃፉት ሃሳቦች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለሃጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ የአኑዋር መስጊድ ይማም ሐምሌ 26/1968 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በሊቢያ በተደረገው የሁለቱ ሃይማኖት መሪዎች ስብሰባ ወደ ስምምነት የተደረሰበትን የጋራ መግለጫና ጽሑፉን በሸኚ ደብዳቤ ልከላቸው ነበር። ነገር ግን ሐጂ ሙሐመድ ነሐሴ 5/1968 ዓ.ም በተፃፈ የአስተያየት ደብዳቤ ለአንድነትና ለመግባባት ስንል የምናደርገው ሙከራችን የሌላውን ሃይማኖት መሠረት የሚንድና ምዕመናኑን የሚያናጋ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን በማለት ጽፈዋል። በተጨማሪም የጽሑፉ አዘጋጅ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቁርዓን እየጠቀሱ መፃፉ መልካም ሆኖ ሳለ ቁርዓን ከብሉያትና ከሐዲሳት ተውጣጥቶ የተፃፈ ነው ብለው ደጋግመው ጽፈዋል። ይህም ማለት ቁርዓን እስላሞቹ እንደሚያምኑበት ለነቢዩ ሙሐመድ የወረደ የአላህ ቃል መሆኑ ቀርቶ ከብሉያትና ከሃዲሳት በማጥናት ተውጣጥቶ በሰው የተፃፈ ነው ማለታቸው ነው። በሌላ አነጋገር ነቢዩ ሙሐመድ ቁርዓንን ከብሉያትና ከሃዲሳት አውጣጥተው ጽፈው ኑል እንጂ ከአላህ የተሰጣቸው አይደለም ማለት ነው። ይህ ሃሳብ በእስላሞች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው

በመሆኑና ይልቁንም የሚያቃቅር ስለሆነ ጥንቃቄ እንዲደረግበትና ታርሞ እንዲታተም በማለት ስምምነታቸውን መግለፃቸው ተጠቅሶበታል።

14.6.2 በመጽሐፉ ላይ የተገለጸ ጉባዔው የተስማማበት ሃሳብ

የእስልምናና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሊቃውንት የተገኙበት የሊቢያው ጉባዔ ዋና ዓላማ ሁለቱም ሃይማኖቶች በአንድ አምላክ ፈጣሪነት የሚያምኑ ስለሆነ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማጥበብና በሰላማዊ መንገድ መቀራረብን ለመፍጠር እንደሆነ ተጠቅሶአል።

ይህንኑ ስብሰባ በጊዜው በንግግር የከፈቱት የሊቢያ ፕሬዚዳንት መአመር ጋዳፊ ሲናገሩ «እኛ በክርስቶስ በኩል የነበረውንና ያለውን ያለ ጥርጥር እናምነዋለን። ይኸውም የማሪያም ልጅ ኢሳ (ኢየሱስ) ክብር ይግባውና ከእግዚአብሔር የወረደውን ያለ ጥርጥር እናምናለን። እንደዚሁም ኢየሱስ ራሱ የተናገረውን ቃል እናምናለን። ነገር ግን በእስላሞች ዘንድ እውነተኛ የነቢያት ቃልና እውነት ያልሆነውን በክርስቶስ ስም የተነገረ አስመስሎ የተፃፈ በመኖሩ የተለያየ ሃሳብ በሕዝቡ ዘንድ አሳድሮ ሕዝቡ ተለያይቶ ይገኛል በማለት ተናግረዋል ይላል።

የመጽሐፉ አዘጋጅ የፕሬዚዳንቱን ንግግር ሲያብራሩ በሃይማኖት ተጠግተው ወንድምን ከወንድም በመለያየት የሚጠቀሙ ሰዎች እንደ ነበሩና እንዳሉም በማወቅ ልንከላከላቸው ይገባናል ብለዋል። ነገር ግን ፕሬዚዳንቱ ተናገሩ የተባለውን ስንመለከት ሊገልፁ የፈለጉት እሳቸውም ሆኑ እሳቸው የሚከተሉት ሃይማኖት ተከታዮች በማሪያም ልጅ በኢየሱስና በቃሉ እንደሚያምኑ ቢገልፁም በብሉያትና በሃዲሳት መፃሕፍት ላይ ሰዎች የነቢያት ቃል አስመስለው እንደጨመሩ አድርገው መረዳታቸውን ለመገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይና ሐዲስ) ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እንደፃፉና ፀሐፊዎቹ ሰዎች ቢሆኑም እንኳን እንዲፅፉ ያደረጋቸው እግዚአብሔር ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደሆነ በቃሉ ላይ የተገለፀና ክርስቲያን ሁሉ የሚያምንበት ነው። ስለሆነም ማንም ተነስቶ በቃሉ ላይ ምንም መጨመር ወይም መቀነስ እንደማይችል በመለኮታዊ ትዕዛዝ ተገድቦአል። ራዕይ 22፥18-19

ስለዚህ ፕሬዚዳንት መአመር ጋዳፊ እንደገመቱት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማንም ሰው በክርስቶስ ስም አስመስሎ የጻፈና የጨመረ ስለሌለና ሊያደርግም ስለማይችል ምክንያት ከመፍጠር ይልቅ ቃሉ የሚያዘውን በመቀበል መዳን ቢሆንላቸው መልካም ነበር።

በመጨረሻም በወጣው የጋራ መግለጫ ምሰረት የስምምነት አርማ እንዲዘጋጅ ተወስኖ በመፅሐፉ ሽፋን ላይ የመስጊድና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሆኖ እንዲታይ ተደርጎአል። አርማው የሚገልፀው በግራ ጎን በኩል መጽሐፍ ቅዱስ ከክርስቲያኖች ጋር እንደመሠረት ሆኖ ከጫፉ ወደ ቀኝ ያዘነበለ የቤተ ክርስቲያን ህንፃና እንዲሁም ከበስተቀኝ በኩል መሠረቱ ቁርዓንና እስላሞች ሆነው ወደ ግራ አዘንብሎ ጫፉ ላይ ከቤተክርስቲያን ጉልላት ጋር የተገናኘ የመስጊድ ጫፍ ይታያል። ሥዕሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ይህም የሁለቱ እምነት ተከታዮች በአንድ እግዚአብሔር የሚያምኑ መሆናቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ከዚህ በፊት በመካከላቸው የነበሩትን አለመግባባቶች አስወግደው በአንድ ላይ የሀገር አንድነት የሚጠበቅበትን መሻት አለባቸው በማለት የውሳኔ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።



ደራሲው



14.6.3 ጉባዔው አንዳንድ መጻሕፍትን ለማስወገድና ሌሎችን ለመቀበል የደረሰበት ውሳኔ

አዘጋጂው የክርስቲያኖችንና የእስላሞችን የእምነት መመሪያ መጻሕፍትን በተመለከተ ሲያብራሩ «የሰው ልጆች የሚከተሉትን ሦስት ቅዱሳት መጻሕፍት የሃይማኖታቸውና የሕይወታቸው መመሪያዎች ያደርጉአቸዋል» በማለት መጻሕፍቱ :-

1ኛ) <u>ብሉይ ኪዳን</u>፥ ከጥንት የነበሩ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ተቀብለው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል ሲጠቀሙበት የቆዩ ሲሆን ዛሬም እስላሞችና ክርስቲያኖች ይጠቀሙበታል ብለዋል።

2ኛ) <u>ሃዲስ ኪዳን</u>፥ እነዚህ መጻሕፍት እግዚአብሔር አብ የሰው ልጆች ከወደቁበት የኃጢአትና የሞት አዘቅት ለማዳን ሲል ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ መስጠቱን የሚገልጽ ስለሆነ ሁለቱም ሃይማኖቶች ያምኑበታል ብለዋል።

3ኛ) <u>ቁርዓን</u>፥ ጽሑፉ ከብሉያትና ከሐዲሳት የሚመሳሰል ስለሆነ በተለይ <u>የእስልምና</u> ሃይማኖት ተከታዮች የእምነት መመሪያ በመሆኑ ከሰማይ የወረደ ነው ይላሉ፤ በማለት ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱትን መጻሕፍት ሁለቱም ሃይማኖቶች በጋራ ለመጠቀም መስማማታቸውን ገልጸዋል።

እንግዲህ ክርስቲያኖችና እስላሞች ምንም የተለያዩ ቢመስሉ ቅዱሳት መጻህፍቶቻቸውን ስንመረምር አንድ መሆናቸውን ለመረዳት እንሞክራለን በማለት የሊቢያውን ጉባዔ ዓላማና ውሳኔ ጨምቀው አቅርበዋል።

ይሁንና የሃይማኖት ጉዳይ የነፍስ ጉዳይ በመሆኑ በጉባዔ ተወስኖ እኔ አውቅልሃለሁ በኔ አይን እይ፥ በኔ ጆሮ ስማ የሚባል ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ እንዲመራው መጸለይና ግንዛቤም የየግል ስለሆነ አንባቢ የራሱን አስተያየት ለራሱ ለመስጠት የሚችል መሆኑን የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ይጠቁማል።

በስብሰባው ማጠቃለያ ወቅት የተደረገውን ስምምነት በቃልና በተግባር ለመግለጽ የሁለቱም ሃይማኖት ተወካዮች ከዚህ እንደሚከተለው ተናግረዋል።

ከእስላሞች ሊቃውንት አንዱ ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 ከቁጥር 31-46 አውጥተው ተርቤ አላበላችሁኝም ተጠምቼ

አላጠጣችሁኝም የሚለውን ማንበባቸው ተገልፆአል። ቀጥሎ ግን ከአርቶዶክስ ሊቃውንት አንዱ ተነስተው «አላህ ወአክበር!» በማለት እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ አሳምረው በፀለዩ ጊዜ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ የነበሩት የጉባኤው አባላት በሙሉ ደስታቸውን በጋለ ጭብጨባ መግለፃቸውንና በመተቃቀፍ ሰላምታ መለዋወጣቸውን ፀሐፊው መምህር ኪዳነ ማርያም ገ.ሕይወት ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ኢድ አልፈጥር (ረመዳን) ኢድ አል አድሐ (አረፋ) በዓላት ክርስቲያኑም ሊያከብራቸው የሚገቡ የጋራ በዓላት ናቸው በማለት የጉባዔው አባላት በሙሉ መስማማታቸውን በጽሑፋቸው ላይ አስፍረዋል።

በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 33 2ኛው አንቀጽ ላይ «ለወደፊቱም ቢሆን የክርስቲያኖችና የእስላሞች የሃይማኖት መጻሕፍት እየተመረመሩ ልዩነትን ለማስፋፋት ምክንያት መስለው የሚታዩትን ሁሉ ተባብረው ማስወገድ አለባቸው» በማለት መስማማታቸውን ይገልጻል። ስለዚህ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አህመድ ዲዳት በመጽሐፍ ቅዱስና በክርስትና ሃይማኖት ላይ እያነጣጠሩ ከአርባ ሁለት መጻሕፍት በላይ እንደጻፉ "IS THE BIBLE GOD'S WORD?" «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን?» በሚል መጽሐፋቸው ላይ በዝርዝር የገለጹአቸው መጻሕፍት በሙሉ ተሰብስበው በጋራ ውሳኔው መሠረት መወገድ ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ከዚህ ቀጥሎ ጥቂት ገጾቹ በፎቶ ኮፒ የተመለከተውና በአባ ተስፋ ጊዮርጊስ የተጻፈ ተአምረ ማርያም የተባለው የዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፍ በመባል የሚታወቀውም በዚህ ስምምነት መሠረት ተመሳሳይ እርምጃ የሚወሰድበት ይመስላል።

ለምሳሌ ፲፱፣ ተአምር። (ከገጽ 129-133) ከተራ ቁጥር 1-38 ያለው

፩፣ ተአምሪሃ፡ለአዛዝእትኑ፡ቅድስት፡ድንግል፡በፀአኤ፡ግርያም፡ወለዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡ይሁኑ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፪፣ ስምዑኬ፡ሕዝበ፡ክርስቲያን፡ከመ፡ናይድዕከሙ፡ዘንተ፡ተአምረ፡ንቢየ፡ወመድምመ፡ዘተገብረ፡በቤቱ፡ክርስቲያን፡አግዝእትኑ፡ማርያም፡ዘደብረ፡ምጥማቅ።

፫፣ ወበአሐቲ፡ዕለት፡እንዘ፡ንዑእን፡ውቅተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘደብረ፡ምጥማቅ፡በዓለ፡ይግበሩ፡ክርስቲያን፡ወንጉሠ፡ኢፍርንጊ፡ወንጉሠ፡ሮም፡ወሶርያ፡ወማሮን፡በከመ፡ልማዶሙ፡አመ፡ታስተርኢ፡ሎሙ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ውስተ፡ደብረ፡ምጥማቅ፡ኵሎሙ፡ሰብእ፡ይስእሉ፡ኀቤሃ፡እንዘ፡ይብሉ፡አምጽኢ፡ለነ፡እገሌሃ፡ሰማዕተ፡አው፡ጻድቀ፡አው፡ነቢየ፡ወኵሎ፡ዘፈቀዱ፡እስከ፡ዓርኩሙ፡ወዘመዶሙ።

፬፣ ወትገብር፡ሎሙ፡ፍጡነ፡ከመ፡ቅድበተ፡ዓይን፡በከመ፡ሰአልዋ፡ለ ድንግል።

፭፣ ወይቤዱ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡እምያዕቆብውያን፡ደቤሎሙ፡ለጉቡኣን፡ግበሩ፡ጸሎተ፡ዮም፡ከመ፡ታምጽእ፡ለነ፡መሐመድሃ፡ነቢየ፡ሐሰት።

፮፣ ወሊቀ፡ጳጳሳት፡እንሥአ፡አዕይንቲሁ፡ውስተ፡ሰማይ፡ወሰፍሐ፡ዕደዊሁ፡ወይቤ፡በውዕየተ፡ልብ፡አእግዝእትየ፡ቅድስት፡ድንግል፡በይእ፡ግርያም፡መስተሣህልት፡ወሰማዒት፡ለ እለ፡ያስተበቍዑ፡ኀቤኪ፡እስእለኪ።

፯፣ ወእትሜነይ፡እምነ፡ኂሩትኪ፡ አሰማዒት፡ወእፈቅድ፡ከመ፡ታርእዩኒ፡መሐመድሃ፡ነቢየ፡ሐሰት፡ወነቢዮሙ፡ለተንባላት፡እስመ፡ይቤሉ፡ተንባላት፡ፈድቅ፡ውእቱ፡እንዘ፡ኢ የአምሩ፡ዘከመ፡እፎ፡ውእቱ፡ወዘ ከመ፡እፎ፡አርአያሁ።

፰፣ ልመናዋ፡ከብፁም፡በኋ፡ለዘ ዕዓለም፡ቢውነት፡ይደርብንና፡እም ላክን፡የወለደች፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ የፀናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ያደረገችው፡ተአምር ይህ፡ነው።

፱፣ የክርስቲያን፡ወገኖች፡በደብረ፡ምጥማቅ፡በተሠራች፡በመቤታችን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡የተደረገው፡የሚያስደንቅ፡ፍጹም፡የሚሆን፡ይህን፡ተአምር፡እንንግራችሁ፡ዘንድ፡ስሙ።

፲፣ ከዕለታት፡በአንድ፡ቀንም፡ክርስቲያን፡ከግሮንና፡ከሶርያ፡ከርም፡ነጉሥና፡ከእፍርጊ፡ንጉሥ፡ጋራ፡እንዳስ

ለመዱ፡በዓሉን፡ያከብሩ፡ዘንድ፡በደብረ፡ምጥማቅ፡በተሠራች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውሥጥ፡ተሰብስበው፡ሳሉ፡እመቤታችን፡በደብረ፡ምጥማቅ፡ላይ፡በተገለጸችላቸው፡ጊዜ፡እገሌ፡የሚባል፡ሰማዕትን፡ወይም፡ጻድቅን፡ወይም፡ነቢይን፡የሚሹትንም፡ሁሉ፡እስክ፡በልንጀራቸውና፡እስከ፡ዘመዳቸው፡ድረስ፡የሹትን፡ሁሉ፡እምጭልን፡እያሉ፡ሰው፡ሁሉ፡ወደሷ፡ይለምኑ፡ነበር።

፲፩፣ ድንግል፡እንዴ፡ለመኑዋት፡እንደ፡ዓይን፡ጥቅሻ፡ፈጥና፡ታመጣላቸው፡ነበር።

፲፪፣ ከያዕቆባውያን፡ወገን፡የሚሆን፡አንድ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የተሰበሰቡትን፡የሐሰት፡መምር፡መሐመድን፡በዛፊ፡ቀን፡ታመጣልን፡ዘንድ፡ጸሎትን፡ጸልዩ፡አላቸው።

፲፫፣ ሊቀ፡ጳጳሳትም፡ዓይኖቹን፡ወደ፡ሰማይ፡አቅንቶ፡እጁን፡ዘርግቶ፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የፀናሽ፡ወዳንቺ፡የሚለምኑትን፡የምትሰሚ፡ደቅር፡ባዩ፡ክብርት፡እመቤቴ፡ሆይ፡አለምንሽለሁ፡አለ።

፲፬፣ የለመኑሽን፡የማታስቀሪ፡እመቤቴ፡ሆይ፡ከቸርነትሽ፡ወገን፡እመኛለሁ፡የአስላሞችም፡መምር፡የሚሆን፡የሐሰት፡ነቢይ፡መሐመድን፡ታሳዪኝ፡ዘንድ፡እወዳለሁ፡አሉ፡እንደምንም፡እንደሆነ፡(ሚለት፡) ጻድቅም፡ኃጥአም፡እንደሆነ፡ሳያውቁ፡እስላሞች፡ደግነው፡ይላሉና።

፳፫ወሰበ፡አስተብቍዓ፡ለድንግል፡ ክመዝ፡ ሰቤሃ፡ አምጽአቶ፡ ለዝኩ፡ ዚይ፡ ርኩስ፡ መሐመድ፡ እንዘ፡ ውእቱ፡ ይዜዓን፡ ገመለ፡ እንስትያ ዊተ።

፳፬፡ ወላዕለ፡ ክሣዱ፡ ተዕሢኖ፡ ሰይ ጠን፡ በአምሳለ፡ ሆባይ።

፳፭፡ ወለለሊሁ፡ እሙር፡ እደዊሁ፡ ወ ኣገሪሁ፡ በሰናስለ፡ እሳት።

፳፮፡ ወዲበ፡ ክሣዱ፡ ጋጋ፡ ዘእ ሳት።

፳፯፡ ወመላእክተ፡ መዓት፡ ይዘብ ጥዎ፡ በአብትረ፡ እሳት።

፳፰፡ ወለሊሁ፡ ቁሱለ፡ ርእስ።

፳፱፡ ወአልቦቱ፡ ጸጕር።

፴፡ ወጸሊም፡ ገጹ፡ ከመ፡ አቡሁ፡ ጲያብሎስ።

፴፩፡ወእስኪቱኒ፡እሙር፡በሐብል።

፴፪፡ ወሐብሉኒ፡ እሙር፡ በክሣደ፡ ናቃት።

፴፫፡ ወእንዘ፡ ትስሕቦ፡ ገመል፡ አ ንስቲያዊት፡ እንተ፡ ይእቲ፡ ብአሲቱ፡ መጽአ።

፴፬፡ ወሰበ፡ ርእዩ፡ ክርስቲያን፡ ዘ ንተ፡ ተፈሥሑ፡ ዓቢየ፡ ፍሥሓ።

፴፭፡ ወተንባላትሰ፡ ርእዮሙ፡ መ ሐመድሃ፡ ነቢዮሙ፡ ጎፍሩ፡ ወጎሥሩ።

፴፮፡ እስመ፡ ነበሩ፡ እንዘ፡ ይብል ዎሙ፡ ነቢይነ፡ ጻድቅ፡ ውእቱ።

፴፯፡ ድንግልን፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ በለ መናት፡ ጊዜ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ያንን፡ ርኩ ስ፡ ሐሰተኛ፡ መምር፡ መሐመድን፡ በሴት፡ግመል፡እንደ፡ተቀመጠ፡አመ ጣችው።

፴፰፡ በንገቱ፡ላይም፡በዝንጅሮ፡እም ሳል፡ ሰይጣን ፡ ተቀምጦበት፡ ነበር።

፴፱፡ እሱም፡ እጹን ፡ እግሩን ፡ በእ ሳት ፡ ሰንሰለት ፡ ታሥሮ ፡ ነበር ።

፵፩፡ በንገቱ፡ ላይም፡ የእሳት፡ ዛን ጅር፡ ነበር።

፵፪፡ ለመዓት፡ የታዘዙ፡ ጠላእክ ትም፡ በእሳት፡በትር፡ደመቁት፡ነበር።

፵፫፡ እሱም፡ ራሱ፡ የቈሰለ፡ነው።

፵፬፡ ጸጕርም፡ አልነበረውም።

፵፭፡ ሬቱም፡ እንደ፡ ግብር፡ አባቱ፡ እንደ፡ ዲያብሎስ፡ ጥቁር፡ ነው።

፵፮፡ አባለ፡ ዘሩም፡ በገመድ፡ ታ ሥሮ፡ ነበር።

፵፯፡ገመዱም፡ በግመል፡ አንገት፡ የታሠረ፡ ነው።

፵፰፡ ይህችውም፡ ሚስቱ፡ ናት፡ ሴት፡ ላመል፡ እየሳበችው፡ጠጣ።

፵፱፡ከርስቲያንም፡ይህን፡ባዩ፡ጊዜ፡ ፈጽሞ፡ ደስ፡ አላቸው።

፶፡ እስላሞች፡ ግን፡ መምራቸው፡ መሐመድን፡ እንዲህ፡ ሁኖ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ አፈሩ፡ ተዋረዱ።

፶፩፡ መምራችን፡ ደግ፡ ነው፡ እያ ሉ፡ ያደከሚቸው፡ ነበርና፡

፶፪፡ ወያዕቆብውያንሰ፡ ይብልዋ፡ ለድንግል፡ በአማን፡ ከሃሊተ፡አንቲ፡ ላዕለ፡ ኩሉ፡ ግብር።

፶፫፡ ወባሕቱ፡ አርእዩን፡ግጎደር፡ ለዝኩ፡ ሐሳዊ፡ ነቢይ፡ዘይትሜክሑ፡ በቱ፡ ዐላውያን፡ እንዘ፡ ይብሉ፡ ገነት፡ ግጎደሩ።

፶፬፡ ወድንግልሰ፡ አሜሃ፡ ኣርአ የቶሙ፡ ማኅደሮ፡ ገሃነመ፡ እሳት።

፶፭፡ወቦቱ፡ሀሎ፡ዕፁ፡ዘኢይነውም።

፶፮፡ ወነፅጎቶ፡ ለመሐመድ፡ ም ስለ፡ ናቃት፡ ብእሲቱ፡ ጎበ፡ ኩነኔ፡ ዘለዓለም።

፶፯፡ ወሰበ፡ ነበሩ፡ ክርስቲያን፡ በ ጎረ፡ ተንባላት፡ እንዘ፡ ይሰምዑ፡ነገረ፡ መሐመድ፡ ይብሉ፡ ጻድቅኑ፡ ወሚ መ፡ ኃጥእ፡ ውእቱ፡እስመ ይደክም፡ ሃይማኖቶሙ፡ ለመሃይምናን።

፶፰፡ ወድንግልሰ፡ አርአየቶሙ፡ በደብረ፡ ምጥማቅ፡ ርኵስናሁ፡ለመ ሐመድ፡ ወማኅደሮ።

፶፱፡ ወእምገሠ፡ ተሠወረት፡ እምኔ ሆሙ።

፷፡ ወሰበ፡ ርእዩ፡ እስላም፡ ዘንተ ነገረ፡ ሐሩ፡ ወአስተዋደይዎሙ፡ ለክ ርስቲያን፡ ጎበ፡ ሥልጣኑ፡ ምስር፡ ዘስመ፡ አሸሪፍ።

፷፩፡ ወይቤለሙ፡ አንትሙኑ፡ ትከውኑ፡ ስምዐ፡ በዘርኢክሙ።

፷፪፡ ያዕቆባውያን፡ ግን፡ ድንግል፡ እመቤታችንን፡ አንቺ፡ በሥራው፡ ሁሉ፡ ላይ፡ በውነት፡የሠለጠንሽ፡ነሽ፡ ይሏት፡ነበር።

፷፫፡ አሕዛብ፡ ማደሪው፡ ገነት ነው፡ እያሉ፡የሚመኩበት፡ የዚህን የሐሰተኛ፡መምር፡ ማደሪውን፡ አሳ ዩን፡ ይሏት፡ ነበር።

፷፬፡ እመቤታችን፡ ግን፡ያን፡ጊዜ፡ ማደሪው፡ ገሃነመ፡ እሳትን፡ አሳየቻ ቸው።

፷፭፡ በዚያም፡ የማያንቀላፋ፡ ትል አለ።

፷፮፡ ከሚሰቱ፡ ከናቃት፡ ጋራ፡ መ ሐመድን፡ የዘለዓለም፡ ፍዳ፡ወዳለበ ት፡ወደ፡ገሃነመ፡ እሳት፡ ጣለችው።

፷፯፡ ክርስቲያን፡ በእስላሞች፡ ጎ ረቤት፡ በነበሩ፡ ጊዜ፡ የመሐመድን፡ ነገር፡ እየሰሙ፡ ደግ፡ ነውን፡ ወይስ ኃጥእ፡ ነው፡ እያሉ፡ የምእመናን፡ሃ ይማኖታቸው፡ ይደክም፡ ነበረና።

፷፰፡ እመቤታችን፡ ግን፡ የመሐ መድን፡ የርኵስናውን፡ ማደሪ፡ ገሃ ነምን፡ አሳየቻቸው።

፷፱፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ከሳቸው፡ ተሠወረች።

፸፡ እስላሞችም፡ ይህን፡ነገር፡ባዩ፡ ጊዜ፡ ስሙ፡ አሸሪፍ፡ ወደ፡ ሚባል፡ ወደ፡ ምስር፡ ንጉሥ፡ሒደው፡በክር ስቲያን፡ ነገር፡ ሠሩባቸው።

፸፩፡ ያያችሁትን፡ እናንተ፡ ምስ ክር፡ ትሆናላችሁን፡ አሳቸው።

15.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የሌለባቸው የፈጠራ መጻሕፍት

የክርስትና ሃይማኖት መመሪያ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ የታወቀ እውነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል እንደመሆኑ መጠን አይለወጥም፥ አይጨመርበትም፥ አይቀነስበትምም። (2ጴጥ. 1፥20-21 ራዕይ 22፥18-20)

ነገር ግን በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ከገባበት ከ330 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ብኩል ቀደም ሲል የቆየው የአይሁድ ወግና ባህል በሌላ በኩል ደግሞ የአህዛብ የጣዖት አምልኮ ሥርዓት በሕዝቡ ሥነ ልቡና ውስጥ ሰርፀው በመግባት ትክክለኛውን የእውነት መንገድ እንዳይረዳ ሲያደናግሩት ኖረዋል።


በዚህ ሁሉ ጥቂት ሰዎች ለህዝቡ የእውነትን መንገድ ለማሳየት የሚጥሩ መኖራቸው ባይካድም አብዛኛው ሕዝብ በሚደጋገም ውሸት እየተዋጠ ከመጪው ባህልና ሥርዓት በተጨማሪ የተለያዩ የሰዎችና የመላዕክት ድርሳኖች ናቸው የሚባሉት የፈጠራ ድርሰቶች በሕዝቡ ልብ ውስጥ ስፍራ አግኝተው እውነት መስለው ለረዥም ዘመናት ቆይተዋል። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ለሽክም የሚከብዱ ዓይነት ትላልቅ መጻሕፍት ሲሆኑ ሌሎች ትንንሾች ደግሞ መስጥመ አጋንንት ወመርበቢተ ሰሎሞን ከታብ፥ አስማተ መለኮት፥ ፀሎት ባንተ አይነጥላ ጥላ ወጊ ወመስተፋቅር ወዘተ. ከሚባሉት ከትናንሽ ከታቦች ጋር ሲዳመሩ ቁጥራቸውና ዓይነታቸው እንዲሁም የሃሳባቸው ይዘት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይስማማና ቋንቋው እንኳን የማይታወቅ ይልቁንም የተዘበራረቀ ነው። ለምሳሌም ለመጥቀስ ያህል :- « <u>መንገደ ሰማይ</u>» የምትባል በተስፋ ገ.ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ በ1976 ዓ.ም. የታተመች ትንሽ መጽሐፍ አንድ ሰው ገና በእናቱ ማህፀን ሲፈጠር ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለት <u>መልአከ ውቃቢ</u> ይታዘዙለትና አንዱ በቀኝ ሌላው በግራ ሆነው በየዕለቱና በየሰዓቱ የጽድቅና የኃጢአት ሥራ እየጻፉ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሲጠብቁት ይኖራሉ ይላል። ቀጥሎም ኃጢአት የሰራች ነፍስ የታዘዙላት

፻፹፪፣ ወመኑ፡ ይትዋቀሥ።
፻፹፫፣ ወእር፡ ትትናገርዎሙ።

፻፹፬፣ ወበምንት፡ ትከሥቱ፡ ኃፍረቲ፡ ዘርኢኩሙ።
፻፹፭፣ ባሕቱ፡ ይኄይሰክሙ፡ ከመ፡ ኦርዮሙ፡ እስመ፡ አልብክሙ፡ ስምዕ፡ በዘትመውዕዎሙ።
፻፹፮፣ ወእምአሜሃ፡ እስከ፡ ይእዜ፡ ሳሥሩ፡ ተንባላት።
፻፹፯፣ ወእግዚአብሔር፡ ልዑል፡ አ ዮሳኖሙ፡ ለክርስቲያን፡ በትንባሌሃ፡ ለድንግል፡ እመስተዋድያን።
፻፹፰፣ ጸሎታ፡ ወበረከታ፡ የሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፻፹፱፣ ግንስ፡ ይከራከራል።
፻፺፣ እንደ፡ምንስ፡ ትክራከሯቸዋ ላችሁ።
፻፺፩፣ ያያችሁትን፡ ኃፍረት፡ በምን፡ ትገልጻለችሁ።
፻፺፪፣ ነገር፡ ግን፡ ዝም፡ ብትሉ፡ ይሻላል፡ ያምትረቱበት፡ ምስክር፡ የላችሁምና።
፻፺፫፣ ከዚያች፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ <u>እስላሞች፡ ጌሰቆሉ</u>።
፻፺፬፣ ልዑል፡ እግዚአብሔርም፡ በመቤታችን፡ አማላጅነት፡ ምእመናን፡ ከነገረ፡ ሠሪዎች፡ አዳናቸው።
፻፺፭፣ ልመናዋ፡ ከብሯም፡ በኛ፡ ለዘ ለዓለም፡ ባውነት፡ ይደርብን።

ባተጨማሪም ከዚህ በታች በፎቶ ኮፒ ከክፍሏ ስለተመለከተው ትንሽ ከታብ በገጽ 142 በ3ኛው አንቀጽ ይመልከቱ።



ውቃቤ መለዕክት ኃጢአቷንና በደሏን ለጌታ ነግረው ጌታም ሰባት ቀን መንግሥተ ሰማያትን አዙራችሁ አስጐብኙአትና በ8ኛው ቀን ወደ ሲያል አግቧት ብሎ ያዛቸዋል። ከዚያም ውቃቤ መላእክቶቹ በ8ኛው ቀን ይዘው ወደ ሲያል ሲሄዱ 13 ጊዜ ከምድር ወደ ሰማይ እንደ ኳስ እያጓኗት መከራ ሲጸናባት በየተራ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን እየጠራች እንደምትማጸን ጽሑፉ ይተርካል።

1ኛ) በሥላሴ 2ኛ) በጻድቃን ሰማዕታት 3ኛ) በመድኃኔዓለም በተሰቀለው ስትላቸው እነሱን ማወቅ ቀድሞ ነበር በስማቸው መዘከር በዓላቸውን ማክበር እንጂ አሁን ደርሰሽ እንዲህ ብትይ ይሆናልን? ይልቅስ በሏት ቀጥቅጧት በማለት መከራ ያጸኑባታል። በአራተኛው ጊዜ እንደምንም ብላ «በእንተ እግዝእትነ ማርያም ጥቂት አሳርፉኝ» ትላለች በዚህን ጊዜ ማርያም ስሟን ሲጠሯት ፈጥና ደራሽ ናትና ሄዳ ከልጅዋ እግር ወድቃ ልጂ ሆይ የሰጠኸኝን ቃል ኪዳን አስብ ይህች ነፍስ ከሲያል ሆና ስሜን ጠርታለችና ትለዋለች። (ገጽ 26) እርሱም የእናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስምና ጥቂት ጊዜ ስለ እናቴ ብላችሁ አሳርፏት ይላቸዋል ይላል።

በሌላ ክታብ (ትንሽ መጽሐፍ) ፀሎት በእንተ አይነጥላ ወጥላወጊ ወመስተፋቅር መግቢያው ላይ ደግሞ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የሰውን ህሊና ለመሳብ የመስቀል ምልክት የተደረገበት ሲሆን «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» ብሎ ይጀምርና ወደ መሐል ሲደርስ «በስመ ላሂ በስመ ላሂ ወለጥላሂ ወለላሂ» ይላል። በመግለጫው ላይም ይህችን ኪታብ በአንገቱ ያሰረ በኪሱ የያዘ . . . ቀጣፊ ሰላቢ ሌባ ሰይጣን ቡዳ አይነካውም ይላል። በተመሳሳይም ከላይ በተጠቀሱት ግለሰብ ግተሚያ ቤት በ1985 ዓ.ም የታተመች «መስጥመ አጋንንት ወመርበቢተ ሰሎሞን ክታብ» የተሰኘች 3በ4 ሳንቲ ሜትር የሆነች መጽሐፍ «ይህ መጽሐፍ አባቶቻችን ተላላፊና ድንገተኛ በሽታ እንዳይዛቸው በጸሎት እየተጠቀሙ በአንገታቸው አንግተው በኪሳቸው ይዘው ከልዩ ልዩ አደጋ የዳኑበት ስለሆነ ከአጋንንት ከርኩሳን መናፍስት ከሌጌዎን ከጂን ከባሰ ከደስክ ከኤድስ ከነቀርሳ ከትግሪዳ ከመጋኛ ከንዳድ ከምትሃት ከቡዳ ከቂመኛ ከቁርጥማትና ከኤድስ ህመም . . . ይጠበቃሉ ብለዋል። (ገጽ 4-5) ለመሆኑ ስለ እውነት ለመናገር ኤድስ በሽታ በአባቶቻቸው ዘመን ነበር ማለት ነው? ይህችን መጽሐፍ በአንገት ማሠር ወይም በኪስ መያዝ ከኤድስ ያድናል ማለታቸው ነው? ይሁን እንጂ ይህንን አባባልና ሌሎችም ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ተረቶች ጸሐፊው ከየትኛውም መጽሐፍ እንዳገኙአቸው በውል አልጠቀሱም። ስለዚህ ዛሬ

በሰው ዓይን ማየት በሰው ጆሮ መስማትና በሰው አንደበት መናገር እየቀረ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በግሉ በማንበብ ላይ ስለሚገኝ እውነትንና ውሸትን ኃጢአትንና ጽድቅን እየለየ ወደ ሕይወት መንገድ እየገባ በመሆኑ እነዚህ ተራ የተረት መጻሕፍት ተሰብስበውና ተቃጥለው የሚወገዱበትና ለአንዱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ስፍራ የሚለቁበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።

ለምሳሌ በድርሳነ ሚካኤል ገጽ 27 ላይ ልጁን ገ/ሚካኤል ወለተ ሚካኤል ወዘተ. ብሎ በሚካኤል ስም የጠራ (የሰየመ) ሁሉ የጽድቅ ዋጋ ያገኛል የሚል አለበት። በተመሳሳይ ተአምረ ማርያም 12 ቁጥር 39-41 ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን በማርያም ስም የሰየመ በስሟ ቤተ ክርስቲያን የሠራ . . . በጐ ዋጋ ያገኛል ይላል። ክርስቶስ ሰምራ የተባለች ሴት ደግሞ የቡልጋ ተወላጅ ስትሆን ባለ ትዳር የብዙ ልጆች እናትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ የነበረች በአንድ ወቅት መገለጥ አየሁ ብላ ልብሰ ምንኩስና አሰፍታ ቤቷንና ልጆችዋን አገር ቤት ትታ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገባች የተባለች ሲሆን፤ በወቅቱም ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ሙከራ እንዳደረገችና እንዳልተሳካላት በተሰፋ ማተሚያ ቤት በታተመ በገድለ ክርስቶስ ሰምራ መጽሐፍ ላይ ተገልጾአል። ነገር ግን የግስጋሬቁ ሂደት ባይሳካላትም በአንድ ጊዜ አንድ እልፍ ግለትም አስር ሺ(10,000)ነፍሳት ከሲያል አውጥታ በየቀኑ ደግሞ 3000 (ሦስት ሺ) ነፍሳት እንድታወጣ ኮታ (አስራት) የተሰጣት እንደሆነ ስለ እርሷ የተጻፈው ድርሰት ገድለ ክርስቶስ ሰምራ ገጽ 23 ላይ ይገልጻል። ይህም በውል ሲጤን ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳያገኙ መንገድ የሚዘጋ ሰይጣን የዘረጋው ወጥመድ እንደሆነ ግልጽ ነው። በመሆኑም መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ሌላ ስም የለም። (ሐዋ. 4፥12) የሚለውን ያላገናዘቡ ብቻ ያዘጋጁት መጽሐፍ እንደሆነ የታወቀ ነው። ስለሆነም እነዚህና የመሳሰሉት መጻሕፍት የዋሁን ሕዝብ በጨለማ እያደናበሩ ያሉ ሲሆን እውነተኛውን የብርሃን አምላክና ጌታ የሆነውን መድሃኔአለምን እንዳያይ እያደረጉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው እውነት ግን ወደ እግዚአብሔር የዘላለም መንግሥት ለመግባት ፍጡር ለፍጡር ምንም ሊያደርግለት እንደማይችል ነው። ይልቅስ የዘላለም ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና መሪው አድርጐ በመቀበልና የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን የሚገኝ ነው እንጂ። (ዮሐ. 1፥12፤ 3፥16፤ ማር. 16፥15)

መጻሕፍቶቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ከእውነት የራቁ ሲሆኑ ከሌሎች ዘመዶቻቸው ከሆኑት የዲድክቅልያ መጻሕፍት ጋርም

በአንዳንድ ቦታ ይስማማሉ። ለምሳሌ ያህል ስለኖህ የተባለውን ስንመለከት ፦

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕ. 41 ቁ. 2 ላይ «የላሜህ ልጅ ኖህ ሲወለድ እንደ እንቁ ነጭ ሆነ እንደ ጽጌረዳም ቀይ ነው የራሱ ፀጉርም እንደ ነጭ ብዝት ነው ... ዓይኖቹን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እንደ ፀሐይ አበራ ቤቱም ሁሉ ፈጽሞ በራ ከአዋላጂቱም እጅ በተነሳ ጊዜ መናገር ጀመረ» ይልና አባቱ ላሜህ በሁኔታው ክስተት ተደናግጦ ለአባቱ ለማቱሳላ እንደነገረውና ማቱሳላ ደግሞ ለአባቱ ለሄኖክ ይህንኑ እንዳማከረው ይተርካል። ይህ ሃሳብ እውነት ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነት ህፃን ተወልዶና አድጐ ለ120 ዓመታት ያህል ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ሰብከ ሰው ሁሉ ሳይሰማው ቀርቶ ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ጭምር ከሰው ዘር ጋር በጥፋት ውሃ ያልቅ ነበር? በመጽሀፉ እንደተገለጸው የናህ መልክስ እንደ ዕንቁ ነጭ ነው ወይስ እንደ ጽጌረዳ ቀይ ነው? ወይንስ ደግሞ ሁለቱም? በዘፍጥረት ምዕ. 5፥21-31 ባለው ክፍል እንደምንመለከተው ሄኖክ 165 ዓመት ሲሆነው ማቱሳላን እንደወለደና ማቱሳላን ከወለደ በኋላ 200 ዓመት ኖሮ በድምሩ በ365 ዓመቱ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ስለነበረ እግዚአብሔር እንደወሰደው ተጠቅሶአል። በተጨማሪም ማቱሳላ 187 ዓመት ሲሆነው የናህን አባት ላሜህን እንደወለደና ከዚያ በኋላ 782 ዓመት ኖሮ በድምሩ 969 ዓመት መኖሩ ሲገለጽ ላሜህ ደግሞ 182 ዓመት ሲሆነው ናህን እንደ ወለደና 565 ዓመት ኖሮ በጠቅላላው 747 ዓመት መኖሩ ተጽፎአል።

ከዚህ ክፍል በስሌት የምንረዳው ሄኖክ ወደ ሰማይ የተወሰደው በተወለደ በ365 ዓመቱ ሲሆን ናህ የተወለደው ደግሞ ሄኖክ ወደ እግዚአብሔር ከተወሰደ ከአንድ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመት በኋላ መሆኑን ነው። ታዲያ ስለ ህፃኑ ስለ ናህ ሁኔታ ለመጠየቅ ላሜህና ማቱሳላ ወደ ሄኖክ መሄድም ሆነ ማነጋገር እንዴት ቻሉ? እውነትን እውነት ነው ብሎ መናገር ዋጋ ሊያስከፍል ቢችልም ውሸት ግን እውነት ሊሆን ፈጽሞ አይችልም።

15.2 ወይራ፥ ነጭ ሽንኩርትና ዕጣን ስለ ማጤስ

አጭር የጸሎትና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ አዘጋጀሁ የሚሉት ግለሰብ «በሃይማኖትዎ አይፈሩ» «እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ጠባቂ ናት» ብለው በጻፉት መጽሐፋቸው ገጽ 13 ላይ «ስለ ዕጣን ማጨስ አውቀዋል?» በሚል ርዕስ ዕጣን ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትም ዕጣን ማጨስ ከፈለጉ ስዕል ቤት ያዘጋጁ

በፀሎት ጊዜ ለስዕል ማጠን ይቻላል። ለቤትዎ ወይራ ያጢሱ ከአጋንንት ፈተና ይድናሉ አጋንንት ወይራና ነጭ ሽንኩርት አይወድም ቶሎ ብለው ይቅደሙት ይላሉ። ከመጽሐፉም ጀርባ ላይ የጻሐፊው የቁመና ፎቶ ግራፍ ይታያል እንዲሁም «ይህ ፎቶግራፍ ኢየሩሳሌም ቅዱስ ጊዮርጊስ መቃብር ላይ የተነሳሁት ነው። ሁሉም ሰው በኪሱ ይዞ ይጸልይ» ብለዋል።

ከአጋንንት ፈተና ለመዳንስ መፍትሄው ወይራና ነጭ ሽንኩርት ነው? መጽሐፉን በኪሳችን ይዘን መጸለይ ለምን ይጠቅማል? ለክርስቲያኖች ከጌታ የተሰጠ ሥልጣን ግን እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቼአችኋለሁ የሚል ነው።

ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ... በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ...። (ማር. 16፥16-21)

ስለ ወይራና ነጭ ሽንኩርት ከመጥቀስ ይልቅ ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። (ያዕ. 4፥7-8) የሚለውንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምነው አልጠቀሱም?



ፎቶግራፍ ኢየሩሳሌም የቅዱስ ጊዮርጊስ
መቃብር ላይ ልዳ የተነሣሁት ነው ።
ሁሉም ሰው በኪሱ ይዞ ይጸልይ



ዋጋ

ባሕታዊ ገ/መስቀል ኃ/መስቀል

ዋጋው ብር 2.00 ነው

በአንዳንድ ቦታ ይስማማሉ። ለምሳሌ ያህል ስለኖህ የተባለውን ስንመለከት ፦

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕ. 41 ቁ. 2 ላይ «የላሜህ ልጅ ኖህ ሲወለድ እንደ እንቁ ነጭ ሆነ እንደ ጽጌረዳም ቀይ ነው የራሱ ፀጉርም እንደ ነጭ ብዝት ነው ... ዓይኖቹን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እንደ ፀሐይ አበራ ቤቱም ሁሉ ፈጽሞ በራ ከአዋላጂቱም እጅ በተነሳ ጊዜ መናገር ጀመረ» ይልና አባቱ ላሜህ በሁኔታው ክስተት ተደናግጦ ለአባቱ ለማቱሳላ እንደነገረውና ማቱሳላ ደግሞ ለአባቱ ለሄኖክ ይህንኑ እንዳማከረው ይተርካል። ይህ ሃሳብ እውነት ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነት ህፃን ተወልዶና አድጐ ለ120 ዓመታት ያህል ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ሰብኮ ሰው ሁሉ ሳይሰማው ቀርቶ ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ጭምር ከሰው ዘር ጋር በጥፋት ውሃ ያልቅ ነበር? በመጽሀፉ እንደተገለጸው የኖህ መልክስ እንደ ዕንቍ ነጭ ነው ወይስ እንደ ጽጌረዳ ቀይ ነው? ወይንስ ደግሞ ሁለቱም? በዘፍጥረት ምዕ. 5፥21-31 ባለው ክፍል እንደምንመለከተው ሄኖክ 165 ዓመት ሲሆነው ማቱሳላን እንደወለደና ማቱሳላን ከወለደ በኋላ 200 ዓመት ኖሮ በድምሩ በ365 ዓመቱ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ስለነበረ እግዚአብሔር እንደወሰደው ተጠቅሶአል። በተጨማሪም ማቱሳላ 187 ዓመት ሲሆነው የኖህን አባት ላሜህን እንደወለደና ከዚያ በኋላ 782 ዓመት ኖሮ በድምሩ 969 ዓመት መኖሩ ሲገለጽ ላሜህ ደግሞ 182 ዓመት ሲሆነው ኖህን እንደ ወለደና 565 ዓመት ኖሮ በጠቅላላው 747 ዓመት መኖሩ ተጽፎአል።

ከዚህ ክፍል በስሌት የምንረዳው ሄኖክ ወደ ሰማይ የተወሰደው በተወለደ በ365 ዓመቱ ሲሆን ኖህ የተወለደው ደግሞ ሄኖክ ወደ እግዚአብሔር ከተወሰደ ከአንድ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመት በኋላ መሆኑን ነው። ታዲያ ስለ ህፃኑ ስለ ኖህ ሁኔታ ለመጠየቅ ላሜህና ማቱሳላ ወደ ሄኖክ መሄድም ሆነ ማነጋገር እንዴት ቻሉ? እውነትን እውነት ነው ብሎ መናገር ዋጋ ሊያስከፍል ቢችልም ውሸት ግን እውነት ሊሆን ፈጽሞ አይችልም።

15.2 ወይራ፥ ነጭ ሽንኩርትና ዕጣን ስለ ማጤስ

አጭር የጸሎትና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ አዘጋጀሁ የሚሉት ግለሰብ «በሃይማኖትዎ አይፈሩ» «እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ጠባቂ ናት» ብለው በጻፉት መጽሐፋቸው ገጽ 13 ላይ «ስለ ዕጣን ማጨስ አውቀዋል?» በሚል ርዕስ ዕጣን ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትም ዕጣን ማጨስ ከፈለጉ ስዕል ቤት ያዘጋጁ

በፀሎት ጊዜ ለስዕል ማጠን ይቻላል። ለቤትዎ ወይራ ያጢሱ ከአጋንንት ፈተና ይድናሉ አጋንንት ወይራና ነጭ ሽንኩርት አይወድም ቶሎ ብለው ይቅደሙት ይላሉ። ከመጽሐፉም ጀርባ ላይ የጻሐፊው የቁመና ፎቶ ግራፍ ይታያል እንዲሁም «ይህ ፎቶግራፍ ኢየሩሳሌም ቅዱስ ጊዮርጊስ መቃብር ላይ የተነሳሁት ነው። ሁሉም ሰው በኪሱ ይዞ ይጸልይ» ብለዋል።

ከአጋንንት ፈተና ለመዳንስ መፍትሄው ወይራና ነጭ ሽንኩርት ነው? መጽሐፉን በኪሳችን ይዘን መጸለይ ለምን ይጠቅማል? ለክርስቲያኖች ከጌታ የተሰጠ ሥልጣን ግን እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቼአችኋለሁ የሚል ነው።

ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ... በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ...። (ማር. 16፥16-21)

ስለ ወይራና ነጭ ሽንኩርት ከመጥቀስ ይልቅ ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። (ያዕ. 4፥7-8) የሚለውንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምነው አልጠቀሱም?



ፎቶግራፍ ኢየሩሳሌም የቅዱስ ጊዮርጊስ
መቃብር ላይ ልዳ የተነሣሁት ነው ።
ሁሉም ሰው በኪሱ ይዞ ይጸልይ

ጋጅ

ባሕታዊ ገ/መስቀል ኃ/መስቀል

ሉ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋው ብር 2.00 ነው



16.1 የቀኖና ዲድስቅልያ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን

ሰማኒያ አህዱ በመባል የሚታወቀውና ተጨማሪ (ዲዩትሮካኖኒካል) የብሉይ ኪዳን ቀኖና መጻሕፍት ተብለው የተሰየሙ በትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ ከገጽ 721 እስከ 1037 ግለትም ከመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄናክ ድረስ አሥራ ስምንት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን መጨረሻ የተጨመሩበት ይገኛል።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን እንደ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሲቆጠሩ እነዚህ ተጨማሪ መጻሕፍት የሌሉበትና ስድሳ ስድስቱን መጻሕፍት የያዘውን የዓለም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚጠቀሙበትን «ጉደሉ መጽሐፍ ቅዱስ» ብለው ሲጠሩት ይሰማል። ነገር ግን እነዚህ ተጨማሪ የሚባሉት (ዲዩትሮካኖኒካል) መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማሙባቸውንና እርስ በርሳቸውም የሚጋጩባቸውን ነጥቦች ስንመለከት፤ «... ሰውነትህ የምጽዋትህን ዋጋ ታገኛለች፥ ለሞተ ሰው ተገክር ማውጣትን አትተው» (መጽሐፈ ሲራክ 7፥33) ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ (ራዕይ 22፥12) ከሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር ይቃረናል። ምክንያቱም ሰው ከሞተ በኋላ ቤተሰቡ በሚያደርገው ድግስ ነፍሱ ትድናለች ብሎ ስለሚናገር ነው። ሌላው ደግሞ «... ቁርጥ ፍርድ በሚደረግበት ቀን በልውል ዘንድ ጻድቃን ለኃጥአን ማማለድ ... አንዱ ላንዱ መለመን ፈጽሞ የሚችል የለም ሁሉ ዋጋውን ይቀበላልና ሥራውም እየራሱ ነውና ማንም ማን የራሱን ጭንቅ ወደ ባልንጀራው የሚመልስ የለም ...» ይላል። ዕዝራ ሱቱኤል 6፥33-37 ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር ይስማማል።

16.1.1 ተረፈ ኤርምያስ

ተረፈ ኤርምያስ አምስት ምዕራፎች ለያዘው ለሰቆቃው ኤርምያስ ከስድስተኛ እስከ ዐሥራ አንደኛ ምዕራፍ ሆኖ ተዘጋጅቷል።

«ተረፈ» የሚለው ቃል ተርፈ፥ ተረፈ፥ ቀረ ከተባለው የግዕዝ ግሥ እንደ ወጣ ከተቆጠረ ትራፊ ፍርፋሪ፥ ጭላጭ፥ ቀፊ፥ ቅሬታ ... ማለት ነው። ተረፈ ኤርምያስ ተረፈ ያሰኘው ከጥራዝ ስለ ተረፈ፥ ከሰቆቃው

ኤርምያስ ጋር በሃሳብ ስላልተያያዘ በኤርምያስ ስም ቢመዘገብም ግሪጋግጫ ባለመገኘቱ በዕብራይስጥ ከተጻፈው ከሰቆቃው ኤርምያስ ጋር ተጽፎ ባለመተላለፉ ወይም ሌላ ምክንያት ቢኖር መምህራን ጥያቄውን ይመልሱልናል።

ተረፈ ኤርምያስ ለሰቆቃው ኤርምያስ ከምዕራፍ 6 የሚጀምር ተቀጥላ ሆኖ ቢዘጋጅም እንደ አንድ መጽሐፍ ራሱን የቻለ ርዕስ ተበጅቶለታል። ኤርምያስ ለተግረኩ አይሁድ ወደ ባቢሎን የላከው መልዕክት እንደሆነ ርዕሱ ይገልጻል። ኤርምያስ ወደ ባቢሎን ደብዳቤ ከጻፈ በጠላት አለመግረኩን በመግለጹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተስማማ ነበር። ግን ምን ያደርጋል! በምዕ. 8፥21 ኤርምያስ ተግርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ ይላል እንጂ። ከዚህም ሌላ ጉልህ የሆኑና ያልተጨበጠ ትረካ መሆኑን የሚገልጹ ክፍሎች፤

1ኛ) በተረፈ ኤርምያስ ምዕ. 6፥1 «እስከ ሰባተኛ ትውልድ ድረስ በዚያ በባቢሎን ብዙ ዘመን ትኖሩ ዘንድ እግዚአብሔርን ስለበደላችሁበት ኃጢአታችሁ ግርከው ወደ ባቢሎን ወሰዷችሁ» ይላል። ነገር ግን በትንቢተ ኤርምያስ 29፥10 ላይ እንደተጠቀሰው በባቢሎን የሚቆዩበት ጊዜ ለሰባ ዓመት እንደሚሆን ተነግሮ ነበር። አይሁድም ሰባው ዓመት የሚፈጸምበትን ጊዜ ይጠብቁ ነበር። (ዳን. 9፥1-2፤ 2ዜና. 36፥21) ይህ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ሲሆን በተረፈ ኤርምያስ የተጻፈው ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተቃርኖ ያለውና ግልጽ ያልሆነ ሃሳብ ነው። ታዲያ ሰባት ትውልድ የሚለው ቃል ለሰባ ዓመት ጊዜ ከሆነ እያንዳንዱ ትውልድ አሥር ዓመት ብቻ ይኖራል ማለት ነዋ!

2ኛ) በምዕ. 8፥13 «ባሮክና ኤርምያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጪት፥ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው» ብሎአል። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ቤት የነበሩትን የወርቅ፥ የብር፥ ከነሐስ ዕቃዎች ሁሉ ወራሪዎች የከለዳውያን ሠራዊት ወደ ባቢሎን እንደ ወሰዱአቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። 2ነገ. 25፥13-17፤ ኤር. 52፥12-23

3ኛ) በምዕ. 8፥18-20 «... ኤርምያስ የቤተ መቅደሱን መክፈቻ ይዞ ከከተማ ወደ ውጪ ወጣ። ... የቤተ መቅደሱን መክፈቻ ተቀበል ብሎ ከፀሐይ ፊት ጣለው። ... እስከ ብዙ ዘመን ድረስ ደብቀው አለው» ይላል።

ከለዳውያን ብውስጡ የነበሩትን የማገልገያ ዕቃዎች ከወሰዱ በኋላ ቤተ መቅደሱን አቃጠሉት እንጂ ሙቼ ተሰወረ? (2ዜና. 36፥17-19)።

እንደተባለው ዕቃዎቹና ቤተ መቅደሱ ለብዙ ዘመን ተሰውረው ቆይተው ቢሆን ኖሮ ምርኮኞቹ ከሰባ ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሱ ጊዜ :-

ሀ) የተማረኩትን ዕቃዎች ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ማጓጓዝ ባላስፈለጋቸው ነበር። ዕዝራ 1፥7-11

ለ) በቀድሞው ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ ላይ አዲስ ቤተ መቅደስ በመሥራት አይደክሙም ነበር። ዕዝራ 3፥1-13፤ 6፥14-16

የተረፈ ኤርምያስ ደራሲ የዮሐንስንም ራዕይ ያነበበ ይመስላል። ዮሐንስ በራዕይ (11፥19) «በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የኪዳኑም ታቦት ታየ» በማለት በመንፈስ ሆኖ ያየውን በሥጋ ዓይን የተመለከተው ከእንጨት ተጠርቦ ከድንጋይ ተለዝቦ የተሠራ የምድራዊ ቤተ መቅደስ ሕንፃ ስለ መሰለው ለዚህ ለራዕይ ትርጓሜ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ያሰበ ይመስላል።

ዮሐንስ በራዕይ ያየው ያን ጊዜ በኤርምያስ ዘመን የተሰወረውን መቅደስ ነው ለማሰኘት የተቀነባበረ ሳይሆን አይቀርም።

4ኛ) በምዕ. 8፥21 «ኤርምያስ ለወገኖቹ ሲያለቅስ እያዳፉ አወጡት። ከህዝቡም ጋር እስከ ባቢሎን ወሰዱት» የሚል ቃል ተጽፎአል።

ሳይማረኩ በይሁዳ የቀሩት አይሁድ ኤርምያስን አስገድደው የተናገረውንም አንሰማም ብለው ወደ ግብፅ ይዘውት ሸሹ እንጂ ኤርምያስንስ ከለዳውያን አልማረኩትም ነበር። በፈለገበት ቦታ እንዲኖር ወይም ወደፈለገበት ስፍራ እንዲሄድ ነፃነት ሰጥተውት ነበር (ኤር. 40፥1-6፤ 43፥5-13)።

5ኛ) በምዕ. 8፥11-12 «እግዚአብሔር ኤርምያስን ወደ ባቢሎን እስክትሄድ ድረስ ወደ ግብፅ ሄደህ ስታስተምር ኑር ሲል አዞት ነበር ይላል። ነገር ግን ኤርምያስ ወደ ግብፅ እንዲሄድ በእግዚአብሔር ቢታዘዝም በከለዳውያን ወደ ባቢሎን ተወሰደ ለማለት ይሆን? (8፥21)

በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደተነገረው ኤርምያስንና ባሮክን አስገድደው ወደ ግብጽ የሸሹት በባቢሎናውያን አገዛዝ ስር በይሁዳ አንኖርም ወደ ግብፅ መሄድ ይሻለናል በማለት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ያመፁ አይሁድ ነበሩ። (ኤር. 42 እና 43)

6ኛ) በምዕ. 8፥12 እና 10፥2 ባሮክ በኢየሩሳሌም መቃብር ቤት ሆኖ የምርኮን ዘመን አሳልፎአል ተብሎ ተጽፎአል። እንዲሁም፤

7ኛ) በምዕ. 11፥1-24 ባሮክ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ለኤርምያስ፥ ኤርምያስም ከባቢሎን ለባሮክ ደብዳቤ እንደተጻጻፉ ይናገራል። ነገር ግን በቁጥር 6 እና 7 የተገለጸው ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለው ተቃርኖ በተራ ቁጥር 4 እና 5 ተጠቅሶአል።

8ኛ) በምዕ. 11፥25-34 ባሮክ በደብዳቤ ባሳሰበው መሠረት ኤርምያስ ምርኮኞቹን አይሁድ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም እያጓዙ ዮርዳኖስ ሲደርስ ከአቤሜሌክና ከባሮክ ጋራ ሆኖ ከባቢሎናውያን ጋር የተጋቡትን አይሁድ በመለየት ወደ ኢየሩሳሌም አትገቡም በማለት እንደ ከለከሉአቸው የተከለከሉ ሰዎችም ወደ ባቢሎን ቢመለሱ በባቢሎናውያን ደግሞ አንዴ ከአገራችን ወጥታችኋልና አትመለሱም እንዳሉአቸው የተከለከሉት ሰዎችም ወደ ምድረ እስራኤል በመጓዝ አገር አቅንተው እንደኖሩ አገሩንም ሰማርያ ሲሉ እንደሰየሙት ይናገራል።

ይህ የተረፈ ኤርምያስ ትረካ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን ሲመዘን ሚዛን የማይደፋ ሆኖአል ምክንያቱም :-

ሀ) ምርኮኞቹ አይሁድ ከባቢሎን በእነ ኤርምያስ መሪነት ወጡ የተባለበት ዘመን 66ኛው ዓመተ ምርኮ ነው ተብሎ በምዕ. 11፥15 መገለጹንና ከባቢሎን እንዲወጡ የሚፈቅድ አዋጅ ገና አለመውጣቱን በምዕ. 11፥11 ሲገልጽ በምዕ. 11፥35 ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ወቅት ዘሩባቤልና ጓደኞቹም ገና እንዳልተነሱ ተጠቅሶአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደተመለከተው ሰባኛው የምርኮ ዓመት ሲፈጸም ከሜዶናዊው ዳሪዮስ ቀጥሎ የነገሰው ፋርሳዊው ቂሮስ አይሁድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደ። የመጀመሪያው ተጓዥ ቡድን መሪዎች እነ ዘሩባቤል እንደ ነበሩ ተመዝግቦአል። ዕዝ. 1፥1-4፤ 2ዜና. 36፥21-23

ለ) ሰማርያ ስለ ተመሰረተችበት ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ከተረፈ ኤርምያስ ትረካ በጣም የተለየ ነው። በአሥሩ የእስራኤል ነገድ ላይ በቴርሣ ነግሦ የነበረ ዘንበሪ «ሳምር» ይባል ከነበረው ሰው መሬት ገዝና በመሬቱ ላይ የሰራውን ከተማ «ሰማርያ» ሲል ሰየመው። (1ነገ. 16፥23-24) የአሥሩ ነገደ እስራኤል መንግሥት በአሶር ንጉሥ በሰልምናሶር እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ ሰማርያ መናገሻ ከተማ ሆና ቆይታለች። (1ነገ. 16፥29፤ 22፥51፤ 2ነገ. 3፥1፤ 10፥36፤ 13፥1-10)

እንግዲህ ሰማርያ የተከተመችበት ትክክለኛ ዘመን በተረፈ ኤርምያስ ከተጻፈው ዘመን 385 ዓመት ያህል ቅድሚያ አለው።

9ኛ) በምዕ. 11፥40 የመጀመሪያውን የምርኮኞች ቡድን እየመራ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ የተባለው ኤርምያስ ኢየሩሳሌም ሲደርስ (በ66ኛው ዓመተ ምርኮ መሆኑ ነው) ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ፀለየ ይላል። ነገር ግን ቤተ መቅደሱ ከተቃጠለ 66 ዓመታት አልፈዋል። (ኤር. 52፥12-13) የተተኪው ቤተ መቅደስ ሥራም የተጀመረው ከዚህ ጊዜ አምስት ዓመት ያህል ዘግይቶ ነው። ዕዝ. 3፥8-13

16.1.2 መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

ምዕ. 1፥3-4 በሞሪያ ተራራ በጽዮን አምባ ላይ ንጉሥ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕግ ማደሪያ ታቦተ ጽዮን በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ዘመን እንደነበረች ይናገራል። በአገላለጹ ከዜና መዋዕል ካልዕ 35፥3 ጋር ይስማማል። ጊዜው የኢዮስያስ 18ኛ የግዛት ዓመት ስለሆነ (2ዜና. 35፥19) ሰሎሞን ከሞተ 359 ዓመት አልፎአል ማለት ነው።

ምዕ. 1፥54-55 ከለዳውያን የእግዚአብሔርን ማደሪያ ታቦት ማርከው ወደ ባቢሎን እንደ ወሰዱ ይናገራል። ትረካው ግን :-

1ኛ) ታቦተ ጽዮን በሰሎሞን ዘመን ተሠርቃ ተወስዳለች ባዮችን የሚያስደነግጥ እንጂ የሚደግፍ ሆኖ አልተገኘም። መሠረቋን ማወቅ ያልቻለ እንደ ዕዝራ ሱቱኤል ያለ ሰው ነው ካልተባለ በስተቀር። (ዕዝራ ሱቱኤል 9፥21-22)

2ኛ) የተረፈ ኤርምያስ ፀሐፊ ቤተ መቅደሱ በውስጡ ካለው ዕቃ ጋር ተሰወረ በሚለውም ሃሳብ የዕዝራ ካልዕ ፀሐፊ አልተስማማም። (ተረፈ ኤር. 8፥13)

ምዕ. 3፥4 እና 4፥1-13 ዘሩባቤል ከንጉሥ ዳርዮስ ጋሻ ጃግሬዎች አንዱ እንደነበረ ያስረዳል። ከሁለት ጓደኞቹ ይልቅ አዋቂ ያስኘውን የጥበብ ነገር ለንጉሥ ዳርዮስ ተንትኖ በመናገሩ ንጉሡ ደስ እንደተሰኘበት ይተርካል። ቀጥሎም ዘሩባቤልና ጓደኞቹ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በናቡከደነፆር ጊዜ የተቃጠለውን ቤተ መቅደስ እንዲሠሩ ንጉሥ ዳርዮስ የፈቀደላቸው መሆኑን ያብራራል። ዘሩባቤልም ምርኮኞቹን አይሁድ ይዞ በመመለስ የቤተ መቅደሱን ሥራ እንደ ጀመረ ይተርካል። በተጨማሪም የተጀመረው የቤተ መቅደስ ሥራ በቂሮስ ዘመን እንዲቋረጥ መደረጉንና እስከ ዳርዮስ ሁለተኛ ዓመት ድረስ ሥራው መቋረጡን ከምዕ. 4፥13

እስከ ምዕ. 5፥73 ተተንትኖአል። ይሁን እንጂ ይህ የዕዝራ ካልዕ ትረካ ከ2ኛ ዜና መዋዕል ቀጥሎ የሚገኘውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነውን መጽሐፈ ዕዝራንና የዓለምን ታሪክ ይቃረናል። ይኸውም፤

ሀ) በናቡከደነፆር የፈረሰው ቤተ መቅደስ እንደገና እንዲሠራ የፈቀደው በዕዝራ ካልዕ ትረካ በንግሥ ዘመኑ የቤተ መቅደስ ሥራ እንዲቋረጥ ተደረገ የተባለውና አስቀድሞም ትንቢት የተነገረለት ፋርሳዊው ቂሮስ ነውና (2ዜና. 36፥22-23፤ ዕዝራ 1፥1-4፤ ኢሳ. 44፥24-28) በዚህም ዕዝራ ካልዕ በምዕ. 2፥1-14 እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ዕዝራ የተረከውን ያፈርስበታል።

ለ) የባቢሎኑን ብልጣሶር ያስወገደው ፋርሳዊው ቂሮስ በፈቀደው መሠረት ብዙ አይሁድን አሰባስቦ ወደ ኢየሩሳሌም የአጓዘው የመጀመሪያው ቡድን መሪዎች እነ ዘሩባቤል እንደ ነበሩ የመጽሐፍ ቅዱሱ መጽሐፈ ዕዝራ ሲተርክ (ዕዝ. 2፥1-7) እነ ዘሩባቤል ኢየሩሳሌም ከደረሱ በኋላ በሁለተኛው ዓመት የቤተ መቅደሱን ሥራ እንደ ጀመሩ ይገልጻል። (ዕዝ. 3፥8-13)

የይሁዳ ጠላቶች የቤተ መቅደሱን ሥራ ለማስተጓጎል በቂሮስ በተከታዩም በዳርዮስ ዘመን እየተከታተሉአቸው ከቆዩ በኋላ ቀጥሎ ለነገሠው አርጤክሲስ ደብዳቤ በመጻፍ የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዲቋረጥ ማድረጋቸውን ሲያስረዳ (ዕዝ. 4፥1-24)፤

ከአርጤክስስ ቀጥሎ በነገሠው በሜዶናዊው ዳርዮስ ዘመን እነ ዘሩባቤል ሥራውን በመቀጠልና በማጠናቀቅ የቤተ መቅደሱን ሥርዓት ማድረሳቸውን ሲናገር፥ (ዕዝ. 5፥1-5፤ 6፥15-18)

ከዳርዮስ በኋላ በዙፋን ላይ የተተካው ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ዕዝራ ሁለተኛውን ቡድን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም እንደደረሰ በታሪክ ሲያስከትል (ዕዝ. 7፥1-9) በተጨማሪም በአርጤክስስ 20ኛ ዓመተ መንግሥት ሦስተኛው ቡድን በእነ ነህምያ መሪነት ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም እንደተጓዘ (ነህ. 2፥1-12) ከምርኮ የተመለሱትንም ሁሉ በማስተባበር የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደ ታደሰ (ነህ. 2፥17) መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ግን የመጽሐፍ ቅዱሱን ዕዝራ የታሪክ ህንጻ እየናደ ከካልዕ መጻሕፍት የማይጠበቅ ያልነበረ ታሪክ እንደ ነበረ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጐ ለማቅረብ ይሞክራል።

ካልዕ (2ኛ) የተባሉትን መጽሐፈ ሳሙኤልን መጽሐፈ ነገሥትን መጽሐፈ ዜና መዋዕልን ስንመለከት የ1ኛውን (የቀዳማዊውን) መጽሐፍ

ታሪክ ሲያጠናክርና ታሪኩም ተያይዞ ሲብራራ ይታያል እንጂ እንደ ዕዝራ ካልዕ ሲያፈርስ አይታይም።

ምዕ. 7፥3 በሐጌና በዘካርያስ የትንቢት ቅስቀሳ የተለየ ቤተ ክርስቲያን መሠራቱን ይተርካል። በዘመነ ብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ እንጂ ክርስቲያንም ሆነ ቤተ ክርስቲያን አልነበረም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚል ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 16፥18 ነው።

መጽሐፈ ኩፋሌ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ለሙሴ የተሰጡ የእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት የተጻፈባቸው ፅላቶች የዕንቁ እንደሆኑ ይገልጻል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት ሁለቱ የቃል ኪዳን ፅላቶች የተጻፉት በድንጋይ ላይ እንደሆኑ ተጠቅሶአል። ዘዳ. 5፥22፤ ዘጸ. 32፥19-20፤ 34፥1-17፤ 1ነገ. 8፥9።

የኩፋሌን ዕንቁ የተባለውን ወይስ በሌሎች በተለያዩ ክፍሎች የተጠቀሰውን ድንጋይ የሚለውን እንቀበል?

16.1.3 ተረፈ ዳንኤል

ይህ ተረፈ ዳንኤል የተባለው መጽሐፍ ከዳንኤል የትንቢት መጽሐፍ የተረፈ ነው ለማለት በዳንኤል ስም የተሰየመ ቢሆንም ከትንቢተ ዳንኤል ጋር በሃሳብ፥ በቃላት አሰካክ፥ በሐረግ አሳሳብ፥ በዐረፍተ ነገር አቀራረጽ ... የማይመሳሰል ሆኖ ሳለ ተረፈ ወይም ትራፊ ብለው ለምን እንደሰየሙት ግልጽ አይደለም።

ይህም መጽሐፍ ለትንቢተ ዳንኤል 13ኛ ምዕራፍ ነው ተብሎ መዘጋጀቱና መጠረዙ ያስገርማል። የመጽሐፉ ስም ደግሞ ተረፈ ትንቢተ ዳንኤል ሳይሆን ተረፈ ዳንኤል መባሉ ሌላው አጠያያቂ ጉዳይ ነው።

ሕዝብና መንግሥታት ሀገርና ሰዎች የሚነቀሉበትና የሚፈርሱበትን የሚጠፉበትን የሚገለበጡበትን እንደገናም የሚቆሙበትንና የሚተከሉበትን የትንቢት ቃል ይናገሩ ዘንድ እግዚአብሔር በነቢያት ላይ የሚያስቀምጠው ኃላፊነት በትርጉሙ ተወስዶ ሸክም ይባላል። ይህም መልዕክቱን እንዲያደርሱ ለተሰጣቸውም ሆነ ለሰሚዎቹ ሸክም ነው። (ኢሳ. 13፥1፤ 15፥1፤ 17፥1፤ 19፥1፤ 21፥1፥13፤ 22፥1)

ሸክም የሚለው የአማርኛ ቃል በግዕዙ ብሉይ ኪዳን በተለይ በዕንባቆም 1፥1 እና በሚልክያስ 1፥1 ላይ (ራዕይ ወይም ፆር) መባል ሲገባው ተረፈ እየተባለ ተተርጉሞአል። ዳሩ ግን በዚህ መመዘኛም ቢሆን

ተረፈ ዳንኤል ታሪክን እንጂ ትንቢትን ወይም ራዕይን አልያዘም። ስለሆነም ሸክም ተብሎ የመነገር ብቃት የለውም። ይኸውም፤

በምዕራፍ 1 ቁጥር 1-2 «ንጉሥ ዳርዮስ ሞቶ ባባቶቹ መቃብር ከተቀበረ በኋላ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ መንግሥቱን ይዞ ዳንኤልም የንጉሡ የቂሮስ የእልፍኝ አሽከር ነበር። ከባለ ሟሎቹም ሁሉ እርሱ ይከበር ነበር» ተብሎአል። ሆኖም ኢዮአቄም በነገሠ በ3ኛው ዓመት ናቡከደነፆር ወደ ይሁዳ ዘምቶ ከእግዚአብሔር ቤት ከፊል ዕቃዎችን ሲወስድ ወጣቱን ዳንኤልንና ሌሎቹን እንደ እርሱ ያሉ የመሳፍንት ልጆችን ወደ ባቢሎን ይዞ መሄዱ ተረጋግጧል። (ዳን. 1፥1-7) የወጣቶቹ የእነ ዳንኤል ዕድሜ በተማረኩበት ጊዜ ስንት እንደ ነበረ ባይታወቅም ዳንኤል በራሱና በጓደኞቹ ስም ሆኖ አስተያየት ለመስጠት (ዳን. 8፥8-16) ሃሳብ ለማፍለቅና በእምነቱ ለመጽናት ያደረገውን ውሳኔ ስንመለከት የዚያን ጊዜ ዕድሜውን ለመገመት ፍንጭ ይሰጠናል። ዳንኤልና ጓደኞቹ በንጉሡ ቤት በሚበላው ጮማና በሚጠጣው ጠጅ ላለመርከስ መወሰናቸው የተጠቀሰ ስለሆነ የዕድሜው ግምት ቢያንስ ቢያንስ አሥራ አምስት ዓመት ይሆነዋል ለማለት ይቻላል። የኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት አሥራ አንድ ዓመት ስለሆነ እነ ዳንኤል ወደ ባቢሎን የተማረኩበት ሦስት ዓመት ሲቀነስ ከዚያ በኋላ ኢዮአቄም የገዛበት ዘመን (2ዜመ. 36፥5) ስምንት ዓመት እንዲሁም ከኢዮአቄም ቀጥሎ የነገሠውን የዮአኪንን የግዛት ጊዜ ሦስት ወር (2ዜመ. 36፥9) በመተው ቀጥሎ የነገሠው የሴዴቅያስ የግዛት ዘመን (2ዜመ. 36፥11) አሥራ አንድ ዓመት ሲሆን የይሁዳ መንግሥት ከተደመሰሰ በኋላ ምድሪቱ ለሰባ ዓመታት እንድታርፍ በነቢዩ በኤርምያስ በተነገረው መሠረት ምርኮኞቹ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ እስከ ታወጀበት እስከ ፋሪሳዊው ቂሮስ 1ኛ ዓመት ድረስ (2ዜመ. 36፥17-23) ሰባ ዓመት ሲደመር በዚህ ጊዜ የዳንኤል ዕድሜ 104 ዓመት ሆኖት ነበር ለማለት ነው። ዳንኤል በዚህ በአንድ መቶ አራት ዓመት ዕድሜ ላይ በሚገኝበት ወቅት የእልፍኝ አሽከርነት ይሠራ ነበር ብሎ ማቅረብ ከእውነት የራቀ ነው።

እንዲያውም ፋርሳዊው ቂሮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ምርኮኞቹ አይሁድ ወደ አገራቸው ገብተው ቤተ መቅደሳቸውን ሠርተው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ የሚፈቅድ አዋጅ ባወጣላቸው ጊዜ የተወሰኑ አይሁድ ወደ አገራቸው ተጉዘው ኢየሩሳሌም እንደደረሱ በሁለተኛው ዓመት የቤተ መቅደሱን ሥራ ሲጀምሩ (ዕዝ. 2፥8) ስለዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ናፍቆት የነበረው ዳንኤል (ዳን. 9፥1-9) እስከ ፋርሳዊ ቂሮስ 3ኛ ዓመት ድረስ ወደ አገሩ ሳይመለስ እዚያው እከለዳውያን

ምድር መቆየቱ (ዳን. 10፥1) በእርጅናው ምክንያት ለመጓዝ ባለመቻሉ እንደሆነ ይገመታል።

ምናልባት የተረፈ ዳንኤል ደራሲ ነቢዩ ዳንኤል ባይሆንስ? እንደዚህ ከሆነ ለትንቢተ ዳንኤል 13ኛ ምዕራፍ በመሆን ተለጣፊ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ ነበር። ስለዚህ እንደተባለው የትንቢተ ዳንኤል ተረፍ ነው ወደሚል ግምት እንኳን ቢገባ በጥንቃቄ ሁለቱን የሚያነብ ሰው ከታሪኩ ዘመንና ዕድሜ መፋለስ ሌላ በቃላት አጠቃቀም፥ በሐረግ አስተሳሰር፥ በዐረፍተ ነገር አቀነባበር በሃሳብ አቆጣጨት ... ሊያስተውል ሁለቱ ጨርሶ እንደማይገናኙ ሊገነዘብ ይችላል።

በተጨማሪም በተረፈ ዳንኤል 12፥27-42 ዳንኤል የባቢሎን ሰዎች ያመልኩት የነበረውን ዘንዶ በመግደሉ ምክንያት የጣዖት ካህናትና ሕዝቡ «ዘንዶው ከሞተ ንጉሡ መንግሥቱን ተቀማ!» እያሉ ወደ ንጉሡ በመሄድ ዳንኤል ይሰጠን ይህ ካልሆነ እንገድልሃለን፥ ገንዘብህንም እንዘርፋለን፥ ቤትህንም በእሳት እናቃጥለዋለን በማለት ንጉሡን ስላስጨነቁት ንጉሡ ዳንኤልን አሳልፎ ሰጣቸውና ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት። በዚያም ሰባት ቀን ተቀመጠ። በሰባተኛው ቀን ዕንባቆም የወሰደለትን የምስር ንፍሮ እና እንጀራ በልቶ ሲነሳ ንጉሡም እያለቀሰ ሲመለከተው በአንበሶቹ መካከል ተቀምጦ ነበር። ንጉሡም ዳንኤልን ከአንበሶቹ ጉድጓድ አወጣው። ከሳሾቹን ግን በአንበሳ ጉድጓድ እንዲጣሉ አድርጉ አንበሶቹ በፊቱ በሉአቸው ብሎ ይተርካል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ዳንኤል ምዕ. 6፥7-23 ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ የተጣለው ንጉሥ ዳርዮስ ባወጣውና ከንጉሡ በቀር ማንም እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ልመና ከአምላኩ ወይም ከሰው ቢለምን በአንበሶች ጉድጓድ ይጣላል ተብሎ በተላለፈው ትዕዛዝ መሠረት ሲሆን ራሱ ዳንኤል አዋጁንና ጽሕፈቱን እንደተጻፈ በሰማ ጊዜ በቤቱ መስኮቶቹን ከፍቶ ዘወትር እንደሚያደርገው በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ ይፀልይ ስለነበረ ነው። በአንበሶች ጉድጓድ በተጣለ በሰባተኛው ቀን ሳይሆን ንጉሡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ የሄደው ሌሊቱን እንቅልፍ አጥቶ ምግብም እንኳን አስጠልቶት አድሮ ዳንኤል በተጣል በማግሥቱ ሄዶ «የህያው አምላክ ባሪያ ዳንኤል ሆይ ...» ብሎ እንዳነጋገረው የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል (ዳን. 6፥18-23)። ነገር ግን ተረፈ ዳንኤል ዋናውን መልዕክት የሚቃረንና ያልተጨበጠ ሃሳብ ይዞ እውነት መስሎ ለመቅረብ የሚሞክር ነው። ስለሆነም ቃሉን ከእውነት ጋር ላገናዘበ ሰው ገና ንባቡን ሲጀምር ውሸት መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታየዋል። እውነቱን ለማወቅ የፈለገ ሰው ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ስድስትንና ተረፈ

ዳንኤልን ቢያነብብ መልካም ይሆናል። በምዕራፉ መጀመሪያ ይህ የተፈጸመው ንጉሥ ዳርዮስ ከሞተ በኋላ በንጉሥ ቂሮስ ዘመን እንደሆነ ተረፈ ዳንኤል ሲገልጽ በትንቢተ ዳንኤል ግን አዋጁን ያወጣውና ዳንኤልን በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ያስጣለው በኋላም ያወጣው ቂሮስ ሳይሆን ዳርዮስ እንደሆነ ተብራርቷል። ለምን ያምታታል? ይህ ተረፍ ብዙ የዋሆችን ከእውነት እንዲርቁ የሚያደርግና ራሱም ከእውነት የራቀ የፈጠራ ድርሰት ነው።

16.1.4 መጽሐፈ ባሮክ

ባሮክ ነቢዩ ኤርምያስ የሚናገረውን የትንቢት ቃል እየመዘገበ በጸሐፊነት እግዚአብሔርን ያገለገለ ሰው ነው። (ኤር. 36፥1-8፤ 27፥32)

በኤርምያስ አፍ እንደተነገረው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የይሁዳን ምድር በመውረር የኢየሩሳሌምን ከተማ ከነቅጥሯ አፍርሶ የቤተ መቅደሱን መገልገያ ዕቃዎች ከወሰደና ቤተ መቅደሱን ካቃጠለ በኋላ የሕዝብ አለቆችንና ባለሙያዎችን ወደ ባቢሎን አፈለሰ። ስለደረሰው ጥፋት ቀደም ብሎ በሴዴቅያስ ዘመን ትንቢት በመናገሩ በግዞት ለነበረው ለነቢዩ ኤርምያስ በፈለገው ቦታ የመኖር መብት ተሰጠው። (ኤር. 38፥17-18፤ 39፥11-14፤ 40፥1-6)

ነገር ግን ለባቢሎናውያን መገዛትን ባልተቀበለና እስማኤል ተብሎ በሚጠራ ሰው የተመራ ቡድን የከለዳውያን ተሿሚ የነበረውን ጎዶልያስንና ተከታዮቹን ከገደለ በኋላ ኤርምያስንና ጸሐፊውን ባሮክን በማስገደድ ወደ ግብፅ ይዞ ኮበለለ። (ኤር. 40፥7-16፤ 41፤ 42፤ 43፥1-7)

ነቢዩ ኤርምያስ በምድረ ግብፅ በነበረበት ጊዜ በግብፅና በመንግሥቷ በሕዝቧም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ተነበየ። ወደ ግብፅ ተወስደው በመጡት ወገኖቹ ላይም የፈሩት ረሃብ በሽታ ጦርነትና ችግር እንደሚደርስ እንዲያውም ናቡከደነፆር ወረራውን በመቀጠል ወደ ግብፅ እንደሚደርስ በግልጽ ተናገረ። ከዚህም በቀር ስደተኞች ወገኖቹ «ንግሥተ ሰማይ» እያሉ በሴት መንፈስ ስም ጠበልና ፀዲቅ የሚዘክሩትን ምስለ ጣዖት ማምለክን እንዲተውና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ እያስተማረ በግብፅ ቆይቶ ነበር። (ኤር. 43፥8-13፤ 44፥1-30) እንግዲህ ባሮክ የተባለው የኤርምያስ ፀሐፊ ከሆነ እውነተኛው ታሪክ በእግዚአብሔር ቃል አኳያ ይህን ሲመስል በመጽሐፈ ባሮክ የተተረከው ግን ከእውነት ውጪ የሆነ የፈጠራ ታሪክ ነው።

በ1980 ዓ.ም በታተመውና በ66ቱ መጻሕፍት ላይ 18 መጻሕፍት በተጨመሩበት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቀኖና መጻሕፍት አንዱ ሆኖ የቀረበው ይህ መጽሐፈ ባሮክ ከግዕዙና ከእንግሊዝኛ ትርጉሞች የተለየ እንደሆነ በጮራ መጽሔት ቁጥር 7 በዝርዝር ተገልጾአል። ለአማርኛው መጽሐፈ ባሮክ በምንጭነት ያገለገለው በየትኛው ቋንቋና በምን ዘመን የታተመው መጽሐፍ እንደሆነ ስላልተጠቀሰ ስህተቱ ከአማርኛው ትርጉም ወይም ከምንጩ እንደሆነ ለማረጋገጥ አልተቻለም። ይኸውም፤

1ኛ) በአማርኛው መጽሐፈ ባሮክ እንደተገለጸው ትረካ ደብዳቤው ተጻፈ የሚለው ወደ ባቢሎን ስለሆነ ጸሐፊው ባሮክ በወቅቱ በኢየሩሳሌም ነበረ ለማለት ታስቦ ነው። በምዕ. 1፥1 እንዲሁም ወደ ባቢሎን ተማርኮ የነበረው የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአቄም ልጅ ኢኮንያንና (ዩአኪን ሌሎች ምርኮኞች በኢየሩሳሌም ወዳሉ ካህናት የጻፉትን ይህን መጽሐፍ (ደብዳቤ) ባሮክ አነበበው ስለሚል ባሮክ በኢየሩሳሌም ነበረ የሚለውን ሃሳብ ያጠነክራል።

ይሁን እንጂ በዚሁ መጽሐፍ ከምዕ. 1፥3 እስከ መጨረሻ ያለው ምርኮኛው ኢኮንያን (ዩአኪን) በኢየሩሳሌም ወደነበሩት ካህናት ጻፈ የሚለው ብቻ ነው እንጂ ባሮክ ራሱ የጻፈው ነገር በመጽሐፉ ውስጥ ስፍራ አልተሰጠውምና ምናልባት የኢኮንያን ደብዳቤ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቶ መጽሐፉን በስሙ እንዲሰየምለት አደረገ ለማለት ካልተፈለገ በስተቀር በውስጡ ባሮክን የመጽሐፉ ባለቤት እንዲሆን የሚያደርገው ሃሳብም ሆነ ነጥብ የለም። ምናልባት በምዕ. 1፥1 እንደተነገረው ባሮክ ወደ ባቢሎን ለኢኮንያን ደብዳቤ ጽፎ ከቆየ በኋላ ለዚያ መልስ ከኢኮንያን የተጻፈለት ደብዳቤ በመጽሐፈ ባሮክ ስፍራ ሲሰጠው የባሮክ ደብዳቤ ግን ባለመገኘቱ ሊመዘገብለት ሳይችል ቀርቶ ይሆናል። መጽሐፉ መቼም በባሮክ ዘመን ቢጠረዝ ኖሮ የራሱ ደብዳቤ የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ ምናልባት ኢኮንያን የጻፈው የመልስ ደብዳቤ ደግሞ ተከታይ በሆነ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ በምዕ. 1፥5 ናቡከደነፆር ኢኮንያንንና የኢየሩሳሌምን ወገኖች ማርኮአቸው ወደ ባቢሎን ከወሰዳቸው በኋላ ሴዴቅያስ የብሩን ዕቃ አሠርቶ ከወርቁ ጋር ሰደደላቸው ተብሎአል።

ነገር ግን የይሁዳ ንጉሥ ዩአኪን (ኢኮንያን) ከተማረከ በኋላ ከለዳውያን በምትኩ ሴዴቅያስን አንግሠውት እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል። (2ነገ. 24፥8-17) ሴዴቅያስም ስላመጸ ከለዳውያን

እንደገና ወደ ይሁዳ ዘመቱ በ11ኛው ዓመት ንጉሥ ሴዴቅያስን ማረኩት፥ ዓይኖቹን አውጥተውና በሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት፤ እስከ ዕለተ ሞቱም በወህኒ ቆየ። (2ነገ. 25፥6-7፤ ኤር. 52፥8-11፤ ሕዝ. 12፥10-13) ይህን ሴዴቅያስ ነው ንዋየ ቅድሳትን ወደ ኢየሩሳሌም ላከ እያለ መጽሐፉ የሚተርከው።

ኢኮንያንም (ዮአኪን) ከባቢሎን ወህኒ ቤት የወጣውና የንጉሥ ባቢሎን ተቀላቢ የሆነው ለ37 ዓመታት ከታሰረ በኋላ ነበር። (2ነገ. 25፥27-30፤ ኤር. 52፥31-34) ይህ ሰው ከምርኮኞች ወገኖቹ ጋር እየተገናኘ ደብዳቤ የመጻፍ ዕድል አግኝቶ ይሆን?

በምዕራፍ 1 ቁጥር 8 ላይ እንደተጠቀሰው ይህችን መጽሐፍ በእግዚአብሔር ማደሪያ በቤተ መቅደስ አንብቡአት አለ ተብሎአል። ነገሩ የሚያስደንቀው የመጽሐፈ ባሮክ ደራሲ ጽሑፉን ሲያቀነባብር ቤተ መቅደስ ተቃጥሎ ስፍራው ወና እንደሆነ አለማስተዋሉና አለማጤኑ ነው።

2ኛ) በግዕዙና በእንግሊዝኛው መጽሐፈ ባሮክ የመጽሐፉ ደራሲ በባቢሎን የነበረ ሰው እንደሆነ ጠቅሶታል። ይህም ከፍ ብሎ ከተገለጸው ከአማርኛው ትርጉም ጋር የሚቃረን ነው። ምርኮኛው ንጉሥ ኢኮንያ (ዩአኪን) ሌሎቹ ምርኮኞች በባቢሎን ሶዲ (ሱድ) በተባለ ወንዝ አጠገብ ሲሰበሰቡ ባሮክ ያዘጋጀውን ይህን መጽሐፍ አነበበላቸው። የሰሙትም አለቀሱ ጸሙ ጸለዩ ገንዘብም አዋጡ ያዋጡትንም ገንዘብ እንዲሁም ቀደም ሲል ሴዴቅያስ ያሠራውንና ናቡከደነፆር ከቤተ መቅደስ የወሰደውን ንዋየ ቅድሳት በይሁዳ ወደሚገኙት ካህናት ከደብዳቤ ጋር ላከላቸው ይላል። በገንዘቡ ለመስዋዕትና ለቁርባን የሚሆነውን እየገዙ በተላከላቸው ንዋየ ቅድሳት እንዲገለገሉበት ስለ ንጉሥ ናቡከደነፆርና ስለ ልጁ ብልጣሶር ዕድሜና ስለ ምርኮኞቹ ኑሮ መቃናት ምሕላ (ፀሎት) እንዲደረግ ማሳሰቢያው እንደ መግቢያ ሆኖ በመጽሐፉ ቀርቦአል። መጽሐፉም በኢየሩሳሌም በቤተ እግዚአብሔር እንዲነበብ ያሳስባል። ምዕ. 1፥1-14

ሀ) ደብዳቤው (መጽሐፉ) የያዘው፤ 1) ምርኮኞች ስለ ራሳቸው ስለ ሕዝባቸው ኃጢአት ያደረጉትን ኑዛዜ 2) የእግዚአብሔር ይቅርታና ምህረት የጠየቁበትን ጸሎት 3) ስለ ጥበብ ታላቅነት 4) የእስራኤል ሕዝብ ስለሚመራበት መለኮታዊ ጥበቃ 5) ስለ ወደፊቱ ተስፋ ሲሆን ምናልባት ይህንን ደብዳቤ ከባቢሎን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረሰው ባሮክ ይሆን?

ለ) ኢየሩሳሌም በተደመሰሰች በ5ኛው ዓመት ግለትም በናቡከደነፆር ዘመነ መንግሥት የቤተ መቅደስ ዕቃዎች ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሳቸውና ካህናቱ ሥርዓተ ኣምልኮ ስለ መፈጸማቸው በመጽሐፈ ባሮክ የተጻፈው ትረካ በእጅጉ ከእውነት የራቀ ነው። ምክንያቱም፤

1ኛ) ኢየሩሳሌም ተደምስሳ ቤተ መቅደስ ሲቃጠል ታዋቂና ባለ ሙያ ሰዎች ወደ ባቢሎን እንዲማረኩ ሲደረግ ምድሪቱ ለ70 ዓመታት እንድታርፍ በእግዚአብሔር ተወስኖ ስለነበረ ፋርሳዊው ቂሮስ እስከ ነገሠ ድረስ የቤተ መቅደስ ዕቃ እንዳልተመለሰ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። (2ዜመ. 36÷17-23፤ ዕዝ. 1÷1-11)

2ኛ) በፋርሳዊው ቂሮስ አዋጅ መሠረት ኢያሱና ዘሩባቤል ከምርኮኞች ወገኖቻቸው መካከል የመጀመሪያውን ተጓዥ ቡድን እየመሩ በፈራረሰችው የኢየሩሳሌም ከተማ ሲደርሱ መሠዊያ አላጋጠማቸውም ይልቁንስ ይህን ለማድረግ መሠዊያ መሥራት ነበረባቸው (ዕዝ. 3÷1-3)

«መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ቅዱስ አይደለም!» እያሉ ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍና ቁጥር እየጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ የሆንነውን ክርስቲያኖች በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከሚዋጉን ሌላ አፈ ታሪክና ተረት የሚጨምሩ ወገኖች ትምህርታቸውን በቃሉ መሠረት ቢመረምሩ ራሳቸውንና የሚሰሟቸውን ያድናሉ። (2ጢሞ. 4÷3-5፤ መዝ. 12÷6፤ 18÷30፤ 19÷7፤ ምሳ. 30÷5)

በተጨማሪም የባሮክ መጽሐፍ በአማርኛው ትርጉም በአምስቱም ምዕራፎች ያሉት ቁጥሮች 83 ሲሆኑ በግዕዙና በእንግሊዝኛው በእያንዳንዳቸው 141 ቁጥሮች ይገኙበታል። በግዕዙና በእንግሊዝኛው ከተካተተው የመጽሐፈ ባሮክ በአማርኛው ላይ 141-83 = ከ58 ቁጥሮች ጋር ሃሳቡን ጐደሉ አድርጐታል። ዳሩ ግን መጽሐፉ የእግዚአብሔር ቃል ስላልሆነ ቢጐድልም ቢጨመርም ጉዳትም ሆነ ጥቅም የለውም።

16.1.5 መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

ምዕ. 1÷1 አገራችን ኢየሩሳሌም በጠፋች በሦሳ ዘመን ዕዝራ አባል የነበርኩ እኔ ሱቱኤል በባቢሎን ነበርኩ ይላል። ሆኖም መጽሐፉ ኢየሩሳሌም በጠፋች በሦሳኛው ዓመት የተጻፈ ሆኖ እንዳይታመን የሚያደርጉ አያሌ ጉዳዮች በመጽሐፉ ውስጥ አሉ። ለምሳሌ ያህል በምዕ. 3÷25 ከአገሮች ሁሉ አንድ አገር መረጥህ በአገር ሁሉ ከታነጹ

ምኩራባት አንድ ቤተ መቅደስን መረጥህ ይላል። በምዕ. 1÷4 ... ምድርን በፈጠርካት ጊዜ ... አዳምን በፈራሽ ሥጋ ታስገኘው ዘንድ ይህንን ብቻህን መሬትን ያዘዝካት አይደለምን ይላል። በዘፍጥረት ምዕ. 2÷7 እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ይላል። ነገር ግን የዕዝራ ሱቱኤል ድርሰት ከሌሎች እንስሳትና ዕፅዋት ባልተለየ ሁኔታ በቃሉ እንደ ፈጠራቸው እንደ ፀሐይ ጨረታና ከዋክብት ሁሉ ሰውንም እግዚአብሔር መሬትን በማዘዝ እንዳስገኘ ይተርካል። ይህ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነት ጋር አይጣጣምም። ይኸውም እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው (ዘፍ. 2÷7) የሚለውን ይቃረናልና።

በኢየሩሳሌም አንድ ቤተ መቅደስ እንዲኖር አስቀድሞ በእግዚአብሔር መመረጡና መታዘዙ በዚህም መሠረት መታነጹ በእግዚአብሔር ቃል ተገልጾአል። (ዘዳ. 7÷14፤ 22-25፤ 16÷1-17፤ መዝ. 132÷13-14፤ 2ዜመ. 3÷1፤ 6÷1-11። ሆኖም ከቤተ መቅደስ መታነጽ በፊት ምኩራባት መታነጻቸውና ለምርጫ መቅረባቸው በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ አይደለም። ቤተ መቅደስ ከተደመሰሰና ሕዝቡ በምርኮ ከተበታተኑ በኋላ ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ ባህላቸው ሊወያዩ የምኩራብ ማቋቋምን ሥርዓት እንደተለማመዱ ከታሪክ መረዳት ይቻላል።

የመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ደራሲ በ30ኛው የምርኮ ዓመት ሳይሆን ቤተ መቅደስ እንደ ገና ታንጻ ከምኩራባት ጋር አገልግሎት መሰጠት ከጀመረ በኋላ የጻፈው ቢሆን ነው እንዲህ ለማለት የበቃው ከሚሰኝባቸው ነጥቦች ቀጥሎ ያሉት ለአስረጅነት ተጠቅሰዋል።

ምዕ. 4÷5-6 የሚመጣው ዓለም የመንግሥተ ሰማይ ምስጢር ሳይታወቅ ሃይማኖትን የሚያፀኗት ሰዎች በልበ ሥላሴ ሳይቆጠሩ የዚያን ጊዜ ፍጡር ያይደለሁ እኔ ይህን ዓለም እንበኝ ዘንድ አስቤአለሁና ቀድሞ በነቢያት አድሬ ኋላ እኔ ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ አስተምራለሁ አለኝ፤ በማለት የመጽሐፉ ደራሲ ሥላሴ (አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ) የአማኞችን ቅድመ ሁኔታ ያላወቁበት ጊዜ እንደነበረና ዕውቀታቸው ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደመጣ አስመስሎ ጽፎአል። የእግዚአብሔር ቃል ግን ይህንን አባባል በፍጹም አይደግፈውም። ሮሜ 8÷29-30፤ ኤፌ. 1÷4፤ 1ጴጥ. 1÷20-21። እግዚአብሔር አልፋና ኦሜጋ ሲሆን በባህርዩም የነበረ ያለና የሚኖር ህላዌው ዕውቀቱ

ፍጹምነትና ሙሉነት ያለው ነው። (ኢሳ. 44÷6፤ 48÷12፤ ዘፀ. 3÷14፤ መዝ. 139÷6)

ምዕ. 6÷9-32 ጻድቃንም ሆኑ ኃጥአን ሲሞቱ ነፍሶቻቸው ወደ ሲዖል ወይም ወደ ገነት እንደማይወርዱ፥ ነገር ግን በሥጋ ሕይወት በነበሩበት ጊዜ ስለ ሠሩት መልካም ሥራ እየተወደሱ ወይም ስለ ፈጸሙት ክፉ ሥራ እየተወቀሱ የሚያሳልፏቸው ነፃ ሰባት ቀናት እንዳሉ ይናገራል። ይህ ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ፈጽሞ የማይስማማ ተረታዊ አባባል ነው። ገነትና ሲዖል እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ነፍሳት የሚቆይባቸው ቦታዎች ናቸው። ስለሆነም፤

1) ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ - ሉቃ. 23÷43

2) ድሃውም ሞተ መላዕክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ባለጠጋውም ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲዖልም በስቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ።(ሉቃ. 16÷23)ሲል ያስተምረናል።

16.1.6 መጽሐፈ ጦቢት

መጽሐፈ ጦቢት ከላይ እንደተገለጸው ከብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት ከሆኑት አንዱ ሲሆን በርዕሱ ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም የሆነው የጦቢት ልጅ ጦቢያ በሩርስ ንጉሥ በሰልምናሶር ዘመን መማረኩን ይናገራል። ነገር ግን ሰልምናሶር የአሦር ንጉሥ እንጂ የሩርስ ንጉሥ አልነበረም። ግዛቱንም በማስፋፋት የአሦርን ወሰነተኛ አገሮች ሩርስን ጨምሮ ማስገበሩን ለመግለጽ ይሆናል። አባባሉ ግን ከእውነት የራቀ ነው።

ምዕ. 1÷1 ወደ ነነዌና ወደ ሩርስ አገር ከእኔ ጋር ለመጡ ለወገኖቼ ብዙ ምፅዋት መጸወትሁ ይላል። የአሦር ንጉሥ ሰልምናሶር ምርኮኞቹን እስራኤላውያንን በሚገዛቸው አገሮች ሁሉ ደልድሎአቸው ይሆናል።

ምዕ. 1÷2 ሕፃን ሆኜ ... አባቴና የንፍታሌም ወገኖች ሁሉ ... በኢየሩሳሌም ከተሠራው ሕግ ወጥተው ካዱ ይላል።

ነገደ ንፍታሌም ከሌሎቹ ዘጠኝ የእስራኤል ነገዶች ጋር በማበር ከዳዊት ቤት ተገንጥለውና አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተው ሌላ መንግሥትና ልዩ ባዕድ አምልኮት ሲያቋቁሙ ጦቢት ሕፃን እንደ ነበረ ይገልፃል። በአማርኛው ትርጉም ግን በቁጥር 1 የተገለጸውን ሃሳብ በዚህ በቁጥር 2 በመድገም ሕፃን ሆኜ እመጸውት ነበር የሚል የሌለ ንባብ ታክሎበታል።

በዚህ ክፍል እንደተገለጸው አሥሩ ነገደ እስራኤል የራሳቸውን መንግሥት በለዩበት ጊዜ ጦቢት ሕፃን የነበረ ከሆነ የሰለሞን አገዛዝ ዘመን ከማክተሙ (930 ከክርስቶስ ልደት በፊት) አስቀድሞ ተወልዶ ነበር ማለት ነው የእስራኤል መንግሥት ከ241-261 ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ በአሦር መንግሥት ሲፈርስ ጦቢት ከተማረከው ሕዝብ ጋር ወደ ነነዌ ተወሰደ። ከዚያም አስራዶን እስከ ነገሠበት (680 ከክ.ል. በፊት) ጦቢት በነነዌ ነበር። ቁ. 48 ተጠቃሹ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ ባይታወቅም ከዚያ በኋላም ለብዙ ጊዜ በነነዌ እንደኖረ መጽሐፉ ይገልጻል። ከምዕ. 2 እስከ ምዕ. 14 ቁ. 11 ያለው ረዥም ታሪክ የሚገልጸው ሥራ የተሠራው አስራዶን ከነገሠ በኋላ መሆኑን ያስነብበናል። ታዲያ በዚህ ስሌት የጦቢት ዕድሜ ወደ 270 ዓመት ይጠጋል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ በዘመኑ ትውልድ የዕድሜ ርዝማኔ ግምት አራት ትውልድን ወይም የ22 ነገሥታት የግዛት ዘመንን አሳልፎአል ማለት ነው።

ምዕ. 1÷15 ስልምናሶር በሞተ ጊዜ ሥራው ክፉ የሆነ ሰናክሬም በእርሱ ፋንታ ነገሠ ይላል። ከስልምናሶር ቀጥሎ በአሦር የነገሠው ሰናክሬም ሳይሆን ሰርጎን ነበር። ከዚያም ቀጥሎ ሰናክሬም ነገሠ። የመጽሐፈ ጦቢት ደራሲ ሰርጎንን ለምን ዘለለው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለበት።

ምዕ. 5÷12-14 ጦቢት ልጁን ጦቢያን ወደ ሜዶን ሊልከው ወሰነና አብሮት የሚሄድ ተቀጣሪ እንዲፈልግ አዘዘው። ልጁ ጦቢያም አብሮት የሚሄድ ሰው በመፈለግ ላይ እያለ ሩፋኤል የተባለውን መልአክ በሰው አምሳል አገኘውና ተነጋግረው ተስማሙ። እርሱንም ወደ አባቱ ወደ ጦቢት አመጣው። ጦቢትም ስሙንና ነገዱን እንዲነግረው ሩፋኤልን በጠየቀው ጊዜ የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ልጅ አዛርያ ነኝ በማለት ዋሸቶ መለሰለት። እዚህ ላይ እንግዲህ ቅዱሳን መላዕክት የማይዋሹና ውሸትም በእነርሱ ላይ ሊገኝ የማይገባ ስለሆነ የውሸት አባት ሰይጣን ዲያብሎስ ብቻ ነውና በዮሐ. 8÷44-45 በተገለጸው መሠረት እውነት ከሆነ አዎ ውሸት ከሆነ አይደለም ነው። ከዚህ ያለፈ ከጠላት ነው። ማቴ. 5÷37፤ ዘፀ. 23። ስለዚህ ከላይ መልአክ ሩፋኤል ነው የተባለው ማን እንደሆነ ሊመረመር ይገባል። ምዕ. 13-15

ጦቢት በቅድሚያ በነገረው መሠረት ጦቢያ የነነዌን ጥፋት ሰማ ስልምናሶርና ናቡከደነፆርም የነነዌን ጥፋት ሰምተው ደስ አላቸው ይላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ስልምናሶርና ናቡከደነፆር ምን አገናኛቸው፤

ስልምናሶር (726-722 ከክ.ል. በፊት) በነነዌ የነገሠ የአሦር ንጉሥ ሲሆን ናቡከደነፆር ግን (605-562 ከክ.ል. በፊት) የባቢሎን ንጉሥ ነበር። ይህም ከሰልምናሶር የንግሥ ዘመን 117 (አንድ መቶ አሥራ ሰባት) ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው። ነነዌም የጠፋችው በናቡከደነፆር አባት በናቡፓላዘር የግዛት ዘመን ነበር። ስልምናሶርንና ናቡከደነፆርን ዘመን አገናኝቷቸው ባንድ ወቅት በየአገራቸው የነገሡ እንኳን ቢሆን ኖሮ የነነዌ ጥፋት ለናቡከደነፆር ብቻ ደስታ፥ ለስልምናሶር ግን አገሩ ነውና የልብ ስብራትና ሀዘን በሆነ ነበር። ስለዚህ ይህም መጽሐፈ ጦቢት ሲመረመር ከመጽሐፍ ቅዱስና ከእውነተኛው ታሪክ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

16.2 የአዋልድ መጻሕፍት አውራ የተባለውና ተከታዮቹ

16.2.1 ከዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ የተጻፈና «ተግሳፅና ምክር» የተሰኘ መጽሐፍ እውነትና ሐሰት በሚል ስለ አዋልድ መጻሕፍት ሲጠቅስ የአዋልድ አውራቸው መጽሐፈ ሄኖክ የሚባለው መላዕክት ወደ ምድር ወርደው ሴቶችን እየመረጡ አግብተው እርስ በርሳቸው የሚባልጉ ሶስት ሺህ ክንድ የሆነ ቁመታቸው ከነፋስ ጋር የሚሯሯጡ ግለትም ቁመታቸው (አንድ ሺህ አምስት መቶ ሜትር መሆኑ ነው) አንድ ዝሆን በአንድ እጃቸው አንስተው ከፀሐይ አቅርበው ጠብሰው የሚውጡ ወንዶች ልጆችን ወለዱ፤ የተወለዱትም እናት አባቶቻቸውን በሉ፥ እርስ በርሳቸውም ተባሉ፥ ስመ ነገዳቸው አዛኤልና አዛዝኤል ይባሉ ነበር ይላል። (ሄኖክ 2፥1-16) ሄኖክ ግን ከአዳም 7ኛው ትውልድ ሲሆን ሄኖክ ማቱሳላን፥ ማቱሳላ ላሜህን፥ ላሜህ ኖህን ወለደ። ከኖህ ዘመን በኋላ ከጥፋት ውሃ የዳኑት ኖህና ልጆቹ ስምንት ቤተሰብ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል። (ዘፍ. 6፥13-22፤ 7፥1-24፤ 8፥15-22)

የእነ አዛኤልና አዛዝኤል ዘር ግን በዓለም ላይ ስለሌለ የባልቴቶች ተረት የመሰለ ፍጹም ውሸትና የፈጠራ ጽሑፍ ሲሆን ለመጽሐፈ ሄኖክ ጓደኛውና ምስክሩ ቁርዓን ወይም ማህዱስ ከሚባለው ዋናው የመሐመዳውያን መጻሕፍት መላዕክት ወርደው ሚስቶችን አግብተው ሂሩትና ማሩት (አዛኤልና አዛዝኤል) የሚባሉ ረጃጅሞች ሰዎች ወለዱ ይላል። ስለዚህ የመጽሐፈ ሄኖክም ጽሑፍ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የፈጠራ ድርሰት ነው በማለት ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ተብራርቶአል።

ጦቢት 4፥15 «... ለመስከር ወይን አትጠጣ ከሰካሮች ጋር በጐዳና አትሂድ ይላል። ይህም ከምሳሌ 23፥18-35 ከተጠቀሰውና «ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት» ከሚለው ጋር ይስማማል። ነገር ግን አንዳንድ እኛም ክርስቲያኖች ነን የሚሉ የመጠጥ ሱሰኞች ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወይን ጠጅ ጠጣ ብሎ ፈቅዶለታል በማለት ኪሳቸውን ሲያራቁቱና ቤተሰባቸውን ሲያስርቡ በየመንገዱም ሲወላገዱ ይታያሉ። ጳውሎስ የተናገረው የወይንን መድሃኒትነት በመጥቀስ ጢሞቴዎስ ውሃ ብቻ ሲጠጣ ሆዱን የሚያመው በመሆኑ እንጂ አልኮል እንዲጠጣ መፍቀዱ አይደለም። «ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ ወደፊት ውሃ ብቻ አትጠጣ (1ጢሞ. 5፥23)

ጦቢት 6፥7 «... ጋኔን ያደረበት ወንድ ወይም ሴት ቢኖር የዓሣን ጉበትና ልብ ያጭሱላቸው ከዚያ በኋላ አይታመሙም» ይላል። ይህ አባባል ጨርሶ ባዕድ አምልኮን የሚያመለክትና ከዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር ፈጽሞ የሚቃረን ነው። ማር. 16፥16-21 «... ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ...» ይላል። እንጂ በዓሣ ጉበት በጅብ ቅንድብ ወዘተ. እና በጠበል ውሃ አጋንንት ይወጣል አልተባለም። እነዚህ ከባዕድ አምልኮ የተወረሱ ባህሎች ናቸው እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ በጭራሽ አልተጠቀሱም።

1ኛ መቃብያን 23፥1-2 ቃየል በየዋህነት የተከተለውን ወንድሙን በሴት ቀንቶ ገደለው ይላል። በእውነቱ ቃየል ወንድሙን አቤልን የገደለው በየትኛዋ ሴት ቀንቶ ነው? ዘፍጥረት ምዕ. 4፥3-8 ባለው ክፍል በግልጽ የተጻፈው አቤል ከበጐቹ መንጋ መጀመሪያ የተወለደውን መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር በማቅረቡ እግዚአብሔር ደስ ተሰኘ ተቀበለውም ነገር ግን ወደ ቃየልና ወደ መስዋዕቱ አልተመለከተም። ቃየል ወንድሙን የገደለው በዚህ በመስዋዕት ምክንያት ነው እንጂ በሴት አይደለም።

ሲራክ 5፥1 ገንዘብ በቃኝ አትበል ይላል። የሲራክ ደራሲ 1ጢሞ. 6፥6፤11 «ያለኝ ይበቃኛል» የሚለውንና «ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሥር ነው» የሚለውን ያላነበበ ይመስላል።

ሲራክ 3፥28 ሥላሴ ከሰው ይልቅ የገለጡልህ ምስጢር የለምና ገብተህ ባህሪየ ሥላሴን አትመርምር ይላል። አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ከሰው ይልቅ ምስጢርን መግለጥ ተሰኖታል ማለቱ ነው?

ሲራክ 20፥25 «ሀሰት ከመናገር መስረቅ ይሻላል ሀሰተኛ ሰው ይጐሰቁላል ፈጽሞም ያፍራል» ይላልና አንባቢ ይፍረድ። ዘፀ. 20፥4-17፤ ዘዳ. 5፥6-21 አሥርቱ ትዕዛዛት ተጠቅሰዋል። ከነዚህም 8ኛው ትዕዛዝ አትሰረቅ የሚል ነው። ኃጢአትን አንዱ ከሌላው ይሻላል ብሎ ማስተማር መጽሐፍ ቅዱስን መቃወም ነው። ኃጢአት ስሙንና መልኩን ሊቀይር ቢሞክርም ኃጢአት ነው። ስለዚህ ሀሰትና ሌብነት ሁለቱም ኃጢአት ናቸው እንጂ አንዱ ከአንዱ በሲራክ አባባል በምኑ ይሻላል?

ሲራክ 24፥3፤10 እኔ እግዚአብሔር አብ ተወለድኩ ... በእርሱ ፈቃድ በከበረ በማርያም ማኅፀን ሥጋን ተዋሐድኩ በምኩራብ አስተማርኩ ... ይላል። ለነገሩ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው ተብሎ ነው መጽሐፈ ሲራክ በብሉይ ውስጥ ደባል ሆኖ የገባው፥ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ስለ ማርያም ያወራል።

ሲራክ 35፥6 በወርቅ ዝርግፍ ያለ ዕንቁም ያማረ እንደሆነ መሰንቆና ዘፈንም እንደእርሱ በመጠጥ ቤት የተወደደ ነው። በማለት ዘፈንንና መሰንቆን ይፈቅዳል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ዘፋኝነት እና ስካር ኃጢአት እንደሆነ በገላትያ 5፥21 ሲገልጽ ዘፋኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ይላል።

የመጽሐፈ ኩፋሌ መግቢያ

በዚህ ዓለም በሚመላለሱት ዘመኖች ሁሉ ሰባት ተብለው የሚቆጠሩ የዘመናችን ሥራ ለማወቅ አምልኮቱና ሕጉን የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው። ሕጉ ትዕዛዙ የተጻፈባቸውን ሁለቱን የዕንቁ ጽላት ይቀበል ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ተራራ ራስ ውጣ እንዳለው በወጣ ጊዜ በደብረ ሲና ለሙሴ እንደተናገረው የዘመኑን አከፋፈል ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ይላል። ሙሴ የተቀበለው ጽላት የድንጋይ መሆኑ ቀርቶ የዕንቁ ነው ይለናል።

ኩፋሌ 4፥8-9 አዳም በመጀመሪያይቱ ሱባዔ ተፈጠረ፤ ሄዋን ደግሞ በ2ኛ ሱባዔ ተፈጠረች፤ አዳም በ40ኛው ቀን ወደ ገነት ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ አስገባነው ሚስቱንም በ80 ቀን አስገባናት ይላል። ይህ አባባል ዋናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ለመቃወም የተጻፈ የፈጠራ ድርሰት ነው።

ኩፋሌ 15፥16 መልዓከ ውቃቤ ለበጐ ነገር ይጠብቅሃልና ከሞትና ከክፉ ነገርም ያድንህ ዘንድ መማለጃና እጅ መንሻ አትቀበል ይላል። ስውን የሚጠብቅ ውቃቤ ነውን?

ሄኖክ 12፥7 ... በመላክ ውቃቤያቸው ቁጥር ሃይማኖታቸውን እርስ በርሳቸው ይጠብቃሉም ይላል።

ሄኖክ 12፥12፤ 14፥20-23 ስለ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተጽፎአል እንዲሁም በምዕ. 13፥4-6፤ 19-31 እና ምዕ. 14፥11 አስታራቂ ክርስቶስ ... ይላል ስለ መንፈስ ቅዱስም ተጠቅሶአል። ክርስቶስ ከሰው ተወልዶ ሰው ተባለ ስሙም ከስድስቱ ዕለታት ከምትበልጠው ከዕለተ እሑድ የቀደመ ተባለ ይላል። እንዲሁም ስሙ ብሉየ-መዋዕል ተባለ ይላል። ለመሆኑ ይህ ሁኔታ በአዲስም ሆነ በብሉይ ተጠቅሶአል?

ሄኖክ 17፥27፤ 34፥39፤47 ... የአዳምን ልጅ ክርስቶስን ተስፋ ያደርጉታል ... ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ለማርያም ሲያበስር የሚወለደውም ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት እንጂ የአዳም ልጅ ይባላል አላላትም። ሉቃስ 1፥35

ሄኖክ 17፥39 ክርስቶስን ተስፋ ያደርጉታል ይግልዱታልም ይላል። ሄኖክ 20፥1-2፤ 18፥22-24 የአዳም ልጅ ክርስቶስ የተሰወረ ስሙ የክስብኤል ሁለተኛው ቤቃ ነው ይልና ስሙን ቅዱስ ሚካኤል ስለ ገለጠላቸው እርሱን አክብሩ ይላል። ነገር ግን በኢሳይያስ 7፥14 እና ማቴ. 1፥23 አማኑኤል እንደሚባልና በሉቃስ 1፥31 መልዓኩ ገብርኤል ለማርያም ወንድ ልጅ ትወልጅያለሽ ካለ በኋላ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ነው ያለው።

ሄኖክ 33፥42-43 ከሐዋርያት ለይተው አንዱን ዮሐንስን ይዘው ገደሉት፤ ሐዋርያትንም ፈጽመው ገደሉአቸው።

ሄኖክ 33፥54 ሮማውያን እስራኤልን ለማጥፋትና የክርስቶስንም ሥልጣን ሊያጠፉ ተራዱ ።

ሄኖክ 33፥58-59 ለሐዋርያት ታላቅ ሥልጣን ተሰጥቶአቸው ዕውቀት የሌላቸውን አሕዛብን ሊያጠፉአቸው ወጡ። በከፍታ የሚኖሩ አሕዛብም ሁሉ ከፊታቸው ሸሹ።

ሄኖክ 34፥17-18 ከሰማይ በታች ያሉ አሕዛብ ሁሉ ለሐዋርያት ወድቀው ይሰግዳሉ ይለምኑአቸዋል ... ይላል። ጌታችን

ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሕይወትን ስለ ማዳን እንጂ ሕይወትን ስለ ማጥፋትና ስለ ጦረኝነት አላስተማራቸውም። ማቴ. 26፥52 ጌታ ኢየሱስ ሰይፍን የሚያነሱ በሰይፍ ይጠፋሉ አለ።

ሄኖክ በምዕ. 39፥13-15 አሪትን አፍርሶ ነቢያትና ካህናቱን አስወጥቶ ጥሎ ወንጌልን አምጥቶ አስቀድማ በፈረሰችው ቤት ቦታ አጸናው ይላል። ይህ አባባል ትክክል ነው መጽሐፍ ቅዱሳዊም ነው ግን ማን ተቀበለው?

ሄኖክ 42፥12-13 የከበረ ስሜን የወደዱትን ሰዎች በበራ ብርሃን ከገሃነም አወጣቸዋለሁ ይላል። ስሙን የወደዱማ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ስለሆኑ ወደ ገሃነም ቀድሞውኑ ለምን ተጣሉ? በመጨረሻው ሄኖክ 42፥1 ለልጁ ለማቱሳላ ከእሱም በኋላ ለሚመጡ ሰዎች በኋላ ዘመንም ሥርዓቱን ለሚጠብቁ ሰዎች ሄኖክ የጻፈው 2ኛ መጽሐፍ ይህ ነው ይላል፤ ለመሆኑ በሄኖክ ዘመን ሥነ ጽሑፍ ነበረ?(1ጢሞ. 1፥4) አንዳንድ ሰዎች ሃሰተኛ ትምህርት እንዳያስተምሩና ወደ ተረት መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ቆጠራ እንዳይመለሱ ... የሚለው መጤን አለበት ማለት ነው።

ዕዝራ ሱቱኤል 5፥28-29 ልጅ ክርስቶስ ከፃድቃን ጋር ተገልጦ በዕለተ ዓርብ የጀመረውን አገልግሎት ይፈጽማል ... ይላል። ስለዚህ እነዚህ መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ለመቆጠር ሚዛን የሚደፉ ሆነው ያልተገኙና ዋናውን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማፍረስ የሚጥሩ ስለሆኑ ማገናዘብ የሚችል አእምሮ ያለው ሰው በሞፍን ካልደገፋቸው በስተቀር ሊቀበላቸው አይችልም። (1ጢሞ. 6፥3-5)

16.3 የአንዳንድ መጻሕፍት ይዘት ከቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ አንጻር

በቅርብ ጊዜ ከታተሙትና የጸሎት መጻሕፍት ናቸው ከሚባሉት ውስጥ በተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ በ1976 ዓ.ም የታተመች «ሰይፈ ሥላሴ» በተባለች መጽሐፍ መግለጫ ላይ ጸሐፊው ይህችን መጽሐፍ በኪስ ለመያዝ በሚያመች ሁኔታ አዘጋጅቼ ስላቀረብኩላችሁ በጸሎቱ እንድትጠቀሙ አሳስባለሁ ብለዋል።

ከመቅድሙ ጀምሮ በገጽ 12፥ 14፥ 43፥ 46፥ 63፥ 64፥ 68 (ሁለት ጊዜ) 83፥ (ሁለት ጊዜ) 87፥ 116፥ 140 (ሁለት ጊዜ) 147፥ 162 (ሁለት ጊዜ) 169፥ 186፥ 195 በጠቅላላው ከሃያ ጊዜ በላይ በየክፍሉ ስለራሳቸው እንደሚከተሉ ጽፈው ያስነብባሉ።

- ጠላቶቼ ሁሉ በሲያል መከከል ባለ ጨለማ ውስጥ ይጣሉ፤ እኔ አገልጋያችሁ ተስፋ ገብረ ሥላሴ በእናንተ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ተማፅኖለሁና እስከ ዘለዓለሙ አሜን። (ገጽ 12)

- ይቅርታቸውና ሀብተ ረድኤታቸው ለአገልጋያቸው ለተስፋ ገብረ ሥላሴ ይደረግለትና የሥላሴ ተአምራታቸው ይህ ነው። ... (ገጽ 43)

- ልዩ ሦስት ሆይ፥ እኔን ባሪያችሁን ተስፋ ገብረ ሥላሴን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ጠብቁኝ አድኑኝ ለዘላለሙ በእውነት። ... (ገጽ 43)

- ይቅርታቸውና ሀብተ ረድኤታቸው በወዳጃቸው በተስፋ ገብረ ሥላሴ ላይ ይኑር ለዘላለሙ በእውነት ይሁን ይሁን። (ገጽ 195) ... በማለት የጸሎት መጽሐፍ ናት የተባለችውን ይህችን መጽሐፍ የሚጠቀም ሁሉ የእርሳቸውን ስም እየጠራ እንዲጸልይ ጽፈዋል።

ነገር ግን የዛሬን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በዛሬ ላይ ቆመን ነገን ማየት ብንችል እንዲህ ዓይነቱ ጽሑፍ ከቤተ ክርስቲያን ተልዕኮም ሆነ ከክርስትና መመሪያ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ምን ያህል ያስኬዳል? የሚመጣው ትውልድስ ምን ብሎ ሊፈርድ ይችላል ብሎ በመገመት አንባቢ የህሊና ዳኝነት ይስጥበት። ለነገሩ ሰውን የሚያጸድቀው ወይም የሚያስኮንነው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መኖር ወይም አለመኖር እንጂ ስም ስለተጠራ አይደለም። ገላ. 6፥7-8።

አምደ ሃይማኖት በሚል ርዕስ በተጻፈ መጽሐፍ ገጽ 35-37 ደግሞ ጸሐፊው 66ቱን መጻሕፍት በያዘ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በብሉይ ኪዳን 7 በአዲስ ኪዳን 8 በድምሩ 15 መጻሕፍት እንደተጨመሩ ሲጠቅሱ ከ66ቱ ጋር 81 ያደርጉታል። ይሁን እንጂ በተጠቀሱት ዝርዝር እርሳቸው ያልጠቀሱአቸው በሌሎች መጻሕፍት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ናቸው የተባሉት ከብሉይ ኪዳን ቀኖናዎች :- 1) ዕዝራ ሱቱኤል 2) ዕዝራ ካልዕ 3) 1ኛ መቃብያን 4) 2ኛ መቃብያን 5) 3ኛ መቃብያን 6) ፀሎተ ምናሴ 7) ተረፈ ኤርምያስ 8) ሶስና 9) ባሮክ 10) መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ 11) ተረፈ ዳንኤል ናቸው። እንግዲህ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚባሉት 81 ብቻ ሳይሆኑ 81 + 11 =92 ናቸው ማለት ነው።

በተጨማሪም ጸሐፊው ድርሳናትም ሆኑ ገድላት ስለ እግዚአብሔር አዳኝነትና ታላቅነት የሚገልጹ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ገደብ ሳይደረግ በቅዱሳን አባቶችም ሆነ በሌሎች ክርስቲያኖች የተጻፉትን መንፈሳዊ መጻሕፍት ሁሉ መቀበል እንደሚገባ ጽፈዋል። እነዚህ መጻሕፍት ሃሳባቸውና እምነታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ አንድ ዓይነት ሃሳብና እምነት የሚገልጹ እንጂ ባዕድ አምልኮን የሚሰብኩ አይደሉም ይላሉ።

በአጠቃላይ መልኩ እውነትን ለማወቅና እውነት ከሚመስል ውሸት ለማምለጥ መፍትሔው መጽሐፍ ቅዱስን በጥሞናና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማንበብ ነው። እርሳቸው የጠቀሱአቸውንም ተአምሮች፥ ገድሎችና ድርሳናች በጭፍኑ ያስፈልጋሉ ወይም አያስፈልጉም ከማለት ይልቅ ማየትና መመርመር በእርግጥም እነዚህ መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ጋር የሚጋጩ ናቸው ወይስ አይደሉም ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጠናል። «መንፈስን አታጥፉ ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ...» ተብሎ ተጽፎአልና። (1ተሰ. 5፥19-22) ስለዚህ የክርስትና መጻሕፍት ሲጻፉ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ከወንጌል ተልዕኮ አንጻር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እየተገናዘበ ለነፍሳት መዳን በሚረዳ መልኩ መሆን አለባቸው እንጂ ስለ ግለሰቦች የሕይወት ታሪክና የኑሮ ሁኔታ መጻፍ አይገባቸውም።

ተበዳይ፥ በዳይና አማላጅ (ጠበቃ)

አማላጅ ማለት ሁለት የተጣሉ ወገኖችን ለማስታረቅ ለተበዳይ የበዳይን ሰው አቤቱታ ይዞ ይቅርታ ጠያቂን ወክሎ የሚቀርብ ወገን ነው። በተጨማሪም አንድ ተራ ሰው ሥልጣን ያለውንና የከበረን ሰው ለማግኘትና የደረሰበትን ችግር ወይም ብሶት ተናግሮ መፍትሄ ለመሻት አቅምም ሆነ መንገድ ስለማይኖረው አገናኝ ወይም አማላጅ ይፈልጋል። ይህም አማላጅ ከከበረውና ተራው ሰው ሊያገኘው ከማይቻለው ሰው ጋር በሥልጣን እኩል መሆኑ ወይም የቅርብ ግንኙነትና እውቀት ያለው መሆኑ በመጀመሪያ ይረጋገጣል። ከዚያም አማላጁ የግለሰቡን ሀሳብና ጥያቄ ከተረዳ በኋላ ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብለትና ከችግሩ የሚላቀቅበትን መንገድ ሊያስተካክልለት ያነጋግረዋል፥ በጉዳዩም ጣልቃ በመግባትና መካከለኛ በመሆን ይፈጽማል ያስፈጽማልም።

ይህ ሁኔታ ወይም አቀራረብ በአንድ ሥልጣን ባለው የከበረ ሰው ፊት ብቻ ሳይሆን ሰዎች በእግዚአብሔርም ፊት በቀጥታ ለመቅረብና ችግራቸውን ለርሱ ለራሱ ነግረው መፍትሄ ለማግኘት ሀሊናቸው ስለማይፈቅድላቸው ስለ እነርሱ ሆኖ ልመናቸውንም ሆነ አቤቱታቸውን እንዲሁም ስዕለታቸውን የሚያቀርብላቸውን አማላጅ ይፈልጋሉ።

17.1 ብቃት ያለው አማላጅ (ጠበቃ)ና የዘላለም ካህን

የክርስትና እምነት መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አማላጅም ሆነ አማላጅነት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የሰውን ግምታዊ አስተያየት ሳይሆን እውነቱንና ሐቁን በትክክል ያስጨብጣል።

«አንድ አምላክ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው (አማላጅ) ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» 1ጢሞ. 2፥5 «... የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞም ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» ይላል። (ሮሜ 8፥34) «... እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው። ስለ

እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና። ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ. 7፥24-25)

<u>በሮሜ 3፥23</u> በተጠቀሰው መሠረት ደግሞ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከእግዚአብሔር ፍቅር በመለየቱ በኃጢአትና በሞት ግዞት ውስጥ ታስሮ ይገኛል። ከዚያ ጭንቀትና ሞት ለመውጣት የሚችለው በፍጡር ዋስትና ሳይሆን ኃጢአተኛ በሆነው ሰውና (አዳምና) ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ በመሆን ሁለተኛው አዳም የተባለውን አምላክ ሆኖ ሳለ እንደ እኛ ሥጋ ለብሶ ሰው በመሆን ከድንግል ማርያም የተወለደውን ጻድቅና ቅዱስ የሆነውን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኙና ጌታው አድርጐ በመቀበል ዳግም ሲወለድ ብቻ ነው።

በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ...» ዮሐ. 10፥9።

የአማላጅነትና የአስታራቂነት ብቃት ያለው ጠበቃና ዋስ ከእርሱ ሌላ ለዓለም ሁሉ ደሙን ያፈሰሰ ማንም የለም።

«የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው። ዕብ. 9፥15

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባው ቃል ኪዳን የአሪት ሕግ ሲሆን ማንኛውም ሰው ከሠራው ኃጢአት ሊነፃ የሚችለውም በሕጉ መሠረት በካህን በተለይም በሊቀ ካህኑ አማካይነት የማስተሰሪያ ደም ይዞ በመቅረብ ብቻ ነበር። ዕብ. 7፥17-22፤ 8፥2-13፤ 9፥11-14።

«ተግሳጽና ምክር» መጽሐፍ በዮሐ. 10፥1 ያለውን በመጥቀስ ብዙ ሰዎች እውነተኛውን አማላጅ ትተው የስርቆሽ መንገድ አማላጅነት፥ የጻድቅ ሰውና የመልዓክ ነው የሚል የሰይጣን አሠራር ለራሳቸው አብጅተዋል ይላል። ቀጥሎም ይህ መንገድ ግን የሚያዋጣ አይደለም ሌባው ሊሰርቅ ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለሌላ አይመጣም። ... በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል፤ እርሱም ስለራሱና ስለ ሕዝቡ ስህተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም ...» ዕብ. 9፥7፤ ዘሌ. 16፥6 እነርሱም ያለ መሃላ ካህናት ሆነዋልና እርሱ ግን ጌታ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ፤ አይፀፀትም ብሎ በተነገረለት ከመሃላ ጋር ካህን ሆኖአልና፥ ያለ መሃላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ (ጠበቃ ወይም አማላጅ) ሆኖአል። ... ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ

(በክርስቶስ ኢየሱስ) የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ. 7፥20-25) በማለት ይገልጻል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር አስገድዶት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፥ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ ሰውን ለማዳን እንደ መጣ የታወቀ ነው። አባታችን አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ የእምነት አባት ተብሎ የሚታወቀውና «አብርሃም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» ተብሎ የተነገረለት ሰው እንኳን ጽድቁ ከራሱ አልፎ ለሌላ ሰው አይተርፍም። (ዘፍ. 15፥6) ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ለአራት መቶ ሠላሳ ዓመታት ከነበሩበት ከግብፅ የባርነት ቀንበር ተላቅቀው ወደ ቃል ኪዳን አገራቸው ወደ ከነዓን እንዲሄዱ እግዚአብሔር በምድረ በዳ በእሳት የተገለጠለት፥ ብዙ ድንቅና ተዓምር በእጁ በመፈጸም ድልንና ኃይል እየተቀዳጁ እንዲጓዙ ያደረገና በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉትን የቃል ኪዳን ጽላቶች በሲና ተራራ የተቀበለ ሰው ከሞተ በኋላ ለማንም ሊያማልድ አልቻለም አይችልምም። (ዘፀ. 3፥2-10)

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። «... ፍርዴን አድርጉ፥ በእርስዋም ትሄዱ ዘንድ ሥርዓቴን ጠብቁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። የሚሰራቸው ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖራልና፥ ሥርዓቴንና ፍርዴን ጠብቁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» ይላል ዘሌ. 18፥1-5።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «መንገድ እውነትና ሕይወት እኔ ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ. 14፥6)። እያለ በእርሱ በኩል ሳይሆን በሌላ ሰው ሠራሽ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ልንገባ እንችላለን ማለት መጽሐፍ ቅዱስን መቃወም አይሆንምን? መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ ካልተቀበልንና ከሸራረፍነው ክርስትናችን ምኑ ላይ ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እኛ የማንፈልገውን ቃል ለቅመን የምናስወግድና ለሥጋዊ ጥቅማችን የምንፈልገውን ጽሑፍ ልንጨምርበት እንችላለን ብለን የምንሟገት ከሆነ «መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ቅዱስ አይደለም» እያሉ ለሚጽፉ ለአንዳንዶች የበለጠ በር ከመክፈቱም በላይ በእግዚአብሔር ዘንድ መቅሰፍትን የሚያስከትል ነው፤ ራዕ. 22፥18።

17.2 ምልጃ በ«መልክአ ሥላሴ»

በተስፋ ማተሚያ ቤት ከተጻፉት ከብዙ መጻሕፍት መካከል በ1985 ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ በታተመች የጸሎት መጽሐፍ በምትባልና

«መልክአ ሥላሴ» በመባል በምትታወቀው በገጽ 10፥ 11፥ 12፥ 13፥ 24፥ 25 ላይ እንደተገለጸው፤ ገብርኤልም ሆነ ሚካኤል እንዲሁም ጻድቃንና ሰማዕታት ጊዮርጊስና ተክለ ሃይማኖት ... ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅም ሆነ ማማለድ ሥራቸው እንዳልሆነ ተገልጸአል። እንዲሁም በሲና ለእስራኤል ልጆች የተሰጠች ሞገዚት የነበረች ሕግ ተሽራ ነፃ በሚያወጣው በአዲስ ኪዳን መለወጢና ስፍራ መልቀቋ ተብራርቷል። ይህም በትንቢተ ኤርምያስ ምዕ. 31፥31-33 «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፥ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና እኔም ቸል አልኳቸው ይላል እግዚአብሔር። ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል እግዚአብሔር ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፥ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል» ተብሎ ከተጻፈው ጋር ይስማማል። ይህም በነቢዩ የተነገረው የትንቢት ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱና በጦር ተወግቶ ደሙን በማፍሰሱ የብሉይ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀዶ (ተተርትሮ) ስፍራ ለቆ በምትኩ አዲስ ኪዳን (አዲስ ውል) እግዚአብሔር አምላክ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካይነት ከሕዝቡ ጋር መዋዋሉን ይገልጻል። መልክአ ሥላሴ መጽሐፍ ላይ ከተጻፈው ክፍል ለግንዛቤ እንዲሆን ሁለት ገጽ ፎቶ ኮፒ ከዚህ ቀጥሎ የተያያዘ ሲሆን ሌሎችም የዚህች መጽሐፍ ጓደኞች እውነትን መግለጥ ከዚህች መጽሐፍ ተምረው የእርስዋን አርአያ ቢከተሉ መልካም በሆነ ነበር።



መልክአ ፡ ሥላሴ ።

በ አ ማ ር ኛ ።

አ. አ. ፲፱፻፺፰ ፡ ዓ. ም.

በተስፋ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ዘወትር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማ
ይሰጥ ፡ ምስጋና ፡
ሰንፍ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ አያገኝም ፡ ጤና
ዘወትር ፡ እትስነፉ ፡ ለምትበርቱና
ተመልከቱ ፡ ጌታ ፡ ሁሉን ፡ ያያልና
ቸሩ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ለሕዝቡ ፡ አዛኝ
ነውና ።

የዕለት ምግብና ፡ ልብስ ፡ እንዲሰጠን
ሥራችንን ፡ እንዲባርክልን
አገራችንን ፡ በሰላም ፡ እንዲጠብቅልን
አንድነታችንን ፡ እንዲያጸናልን ፡
ከክፉ ፡ መከራ ፡ እንዲሰውረን ፡
ዘወትር ፡ እንለምነው ፡ መድኃኔ ፡ ዓለምን ፡
አገርን ፡ ውደዱ ፡ በሥራችሁ ፡ ትጉ ፡
የወገንን ፡ ፍቅር ፡ ፍጹም ፡ አትዘንጉ
አንዱ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ የፈጣሪ ፡ ሕጉ

አምልኩት ፤ በፍጹም ፡ ቸርነታችሁ ፡ በሚ
መጣው ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ እውነ
ው ፡ አምላክ ፡ አምልኮት ፡ አምልኩ
ቴን ፡ ለውጡልኝ ።

፲፫ ፡ ለአስናኒከሙ ።

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
ሥጋዊ ፡ አስናን ፡ ላይደሉ ፡ አስናናችሁ
ሰላምታ ፡ ይገባል ። ለተዋህዶ ፡ ሃይማኖት
ደመናም ፡ የአንድነቱ ፡ ዝናማት ፡ ናቸው ።
ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
በመንፈሳዊ ፡ ውስጣዊ ፡ ልቦና ፡ ውስጥ
ሕጋችሁን ፡ በሠራችሁ ፡ ጊዜ ፡ በጭለማ
የተከበበች ፡ የሰና ፡ ሕግ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ
ቷወገደች ። ለሕጋችሁም ፡ ቦታዋን ፡
ለቀቀች ።

፲፬ ፡ ለልሳነ ፡ ሥ ።

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከመነገሩ ፡ አስቀድሞ ፡
በመናገር ፡ ላይ ፡ ለነበረ ፡ አንደበታችሁ
ሰላምታ ፡ ይገባል ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
መለኮታዊ ፡ መንበረ ፡ መንግሥታችሁ ፤
ሥጋዊ ፡ መንበረ ፡ መንግሥትን ፡ የሚ
ያስደነግጥ ፡ ነው ። ሕጋችሁን ፡ በተላላ
ፈና ፡ ትእዛዛችሁንም ፡ በአፈረሰ ፡ ጊዜ ፡
የሚገባውን ፡ የጥፋት ፡ ገጽታ ፡ የቴዎ
ዳስ ፡ ዓይን ፡ አየ ። ገሊላዊው ፡ ይሁዳም
የሞት ፡ ጐዳናን ፡ ተጓዘ ።

፲፭ ፡ ለቃልከሙ ።

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
የእሳቱን ፡ ነበልባል ፡ ሠንሰለት ፡ ቆራጦ ፡
ሰጥ ፡ ለሚያደርግ ፡ ቃላችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ይገባል

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡
የታታሪ ፡ ነጋዴ ፡ ልዩ ፡ ገንዘቡ ፡ ናችሁና
ቅዱሳንን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሚወ
ልድ ፡ ትሮታችሁ ፡ በንስሐ ፡ በተወለዱ
ጊዜ ፤ ጴጥሮስ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይን ፡
መክፈቻ ፡ ተቀበለ ። ምዕመናንን ፡ ያሳ
ድድ ፡ የነበረ ፡ ጳውሎስም ፡ የወንጌል ፡
መምህር ፡ ሆነ ።

፲፮ ፡ ለአብርሃንፍሐሙ ፡

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

የሕያዋን ፡ ፍጥረታት ፡ ሁሉ ፡ ሕይወት ለሚሆን ፡ እስትንፋሳችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ይገባል ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

ሥርየተ ፡ ደማችሁ ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአት ነውና ። የነፍሴን ፡ ቤት ፡ መቃን ፡ በሥርየት ፡ ደማችሁ ፡ እርጩት ። የእንስሳት ፡ ደምና ፡ የጣያት ፡ አምልኮት ፡ እንደማይረባ ፡ አስቀድሜ ፡ ተመራምሬ ፡ ፈትኜዋለሁና ።

፲፯ ፡ ለጽርዓኩሙ ።

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ስለጥልቅ ፡ ንስሐ ፡ የተነሣሕያን ፡ ስቴ አንብዐ ፡ ደም ፡ አስፈላጊው ፡ ለሆነ ፡ ጕርዔያችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ይገባል ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

የቢለሚልነት ፡ ባለጸጋ ፡ ናችሁና ፡ ከቢለሚልነታችሁ ፡ አታውጡኝ ። ከባለሚልነት

አውጥታችሁ ፡ በቸልታ ፡ ከተመለከታችሁኝ ። ሚካኤል ፡ ገስግሶ ፡ ሥጋዬን ፡ ለማስገኘት ፡ ይሆንለታልን ፡? ወይስ ፡ ገብርኤል ፡ በከንፋፉከንፎ ፡ የነፍሴን ፡ ሕይወት ፡ ሊሰጠኝ ፡ ይቻለዋልን ።? ከሂሎት የናንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፰ ፡ ለክሣደነኩሙ ።

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ከሣደ ፡ አዳምን ፡ ለፈጠረ ፡ መለኮታዊ ፡ ከሣዳችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ይገባል ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

በቸርነታችሁ ፡ ከኃይላችሁ ፡ ኃይልን ፡ አሳትፋኝና ፡ በሥጋዬ ፡ ጠፈር ፡ ወይም ሰማይ ፡ ላይ የአርሳንዮስ ፡ ፀሐይ ፡ ገድል ትቆም ፡ ዘንድ ፡ እዘዙ ። ቀድሞ ፡ በታች በመሬት ፡ ያለ ፡ ኢያሱ ፡ በላይ ፡ በሰማይ ያለ ፡ ፀሐይን ፡ በቸርነታችሁ ፡ ኃይል ፡ ሊያቆም ፡ ችሏልና ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

ከከላውያዎን ፡ ይልቅ ፡ የካራንን ፡ ምድር የመረጠ ፡ አብርሃም ፡ የምስትንታችሁን ፡ ትክክለኛ ፡ ሥስትነት ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ከድንኳኑ ፡ በስተምሥራቅ ፡ ወይም ፡ ባሻገር ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ አየ ፡ ተመለከተ ። ከሦስቱ ፡ አንዱም ፡ ከልጅ ፡ ልጅህ ፡ ተወልጄ ፡ አድንሃለሁ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተቀበለ ።

፲፰ ሙስተ ፡ ፡ሕረትክሙ ፡

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ከውሳጣዊ ፡ ባሕርያችሁ ፡ የሚገኝ ፡ ቸርነታችሁን ፡ ሰላም ፡ እላለሁ ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

የትሩፋት ፡ አበጋዝ ፡ እንደመሆናችሁ ፡ የገድል ፡ ትሩፋትን ፡ አጐናጽፉኝ ። ከገድላቸው ፡ ገድል ፡ እሳተፍ ፡ ዘንድ ፡ በሄድኩ ፡ ጊዜ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከደሙ ፡ ጠብታ ሊሰጠኝ ፡ አልፈቀደም ። ተክለ ፡ ሃይማኖ

ትም ፡ ከሰባረ ፡ ዐፅሙ ፡ አንዲት ፡ ስንጥር ፡ እንኳ ፡ ክልክሉኛልና ።

፲፱ ፡ ለሐዲነኩሙ ፡

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ መታጠቂያው ፡ የቸርነት ፡ ሠቅ ፡ ለሆነው ወግባችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ይገባል ።

ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡

አምላክነታችሁ ፤ በለዓም ፡ እንደሚያመልከበት ፡ ጣያት ፡ ከንቱ ፡ ያይደለ ፤ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ነው ፡ እኮን ። አቤቱ ፡ የቸርነታችሁ ፡ ምልክት ፡ ወደ ፡ ዕውነተኛ ፡ ውሳኔያችሁ ፡ መርቶ ፡ ያደርሳልና ። በዓለ ፡ መሥዋዕቱ ፡ አብርሃምና ለመሥዋዕት ፡ የሚቀርበው ፡ ይስሐቅ ፡ ከመሠዊያው ፡ ቦታ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሥስት ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ ለማድረግ ፡ ተዘጋጁ ።

፳፩ ለአቅደደኩሙ ፡

አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ በዓይን ፡ ለማይታዩ ፤ ህልውናቸው ፡

ስለዚህ የብሉይ ሕግ በአዲስ መፈጸሙ የተጠቀሰው ከላይ ስሟ በተገለጸው መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የክርስትና ሕይወት መመሪያ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከዚህ በላይ በኤርምያስ ትንቢት የተጠቀሰው ክፍል በዕብራውያን መልዕክት ምዕ. 8÷3-13 ተብራርቶ በ13ኛው ቁጥር «አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል አሮጌውና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል» ይላል። ዕብ. 7÷19 ደግሞ «... የማትጠቅም ስለሆነች የቀደመችው ትዕዛዝ ተሽራለች ...» ይላልና።

በዘመናችን ብዙ ሰይጣንና የጥልቁ መናፍስት «መላዕክት ነን» እያሉ በማታለል የቅዱሳን መላዕክትን ስም እየጠሩ ገብርኤል ነኝ፥ ሚካኤል ነኝ ወዘተ. በማለት ሕዝብን በማሳሳት እንዲያመልካቸው እያደረጉ በክፋት ሥራቸው እየጠቀለሉት ይገኛሉ። አብዛኛው ሕዝብም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ ዕውቀት ስለሌለው ትክክለኛውን አምልኮት እንዳያመልክ እየገለበጡት ለእግዚአብሔር ሊሰጥ የሚገባውን አምልኮና ስግደትም ወደ ራሱ እያደረገ ሰይጣን በማታለል ላይ ነው። የቃሉ ዕውቀት ያለው ሰው ግን ለማንኛውም መንፈሳዊ ነገር መመዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይረዳል። በግልጽም ሆነ በስውር የሚሠሩትን የመናፍስት የክፋት ሥራ ለመለየት የሚጠቀመውም የግል ልምምዱን ወይም የባህልን ሥርዓት ሳይሆን ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ ስለታም የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች መላዕክት ጻድቃን ሰማዕታትና ቅዱሳን ያማልዳሉ ብለው ትምህርት ይሰጣሉ። ጥቂቶች በአዲስ ኪዳን ሳይሆን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ለሙሴ በሰጠውና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በተዋዋለው የድንጋይ ጽላት (ብሉይ ኪዳን) ውል እስከ ዛሬ ለሚያምኑት ከላይ የተጠቀሰችው መጽሐፍ ምክር ልትሰጥ ጥረት አድርጋለች። በተጨማሪም አንዳንዶች እንጨትና ድንጋይ ጠርበውና አለዝበው ቤት ሠርተው በማስቀመጥ ሲሰግዱ ሌሎች ደግሞ ለተቆረጠና ለሞተ ሳይሆን ለቆመ ለምለም ዛፍና ጥያቄ ለማይመልስ ቋጥኝ ድንጋይ የሚሰግዱ በዚህች ምድር ዛሬም አሉ። ይኸውም አድባር፥ አውጋር፥ ጨሌ፥ ቆሌ፥ ቦረንትቻ ... እያሉ የሚያመልኩት በዛፍ ሥርና በወንዝ አጠገብ ሲሆን አንዳንዶችም ከብት አርደው በግንባራቸውና በየዛፉ ላይ ደም የሚቀቡ «እኛም ክርስቲያን ነን» የሚሉ ናቸው። እንዲህ ዓይነቱን ባዕድ አምልኮ ምዕመናኖቼ ናቸው የምትላቸው ሰዎች ሲከተሉ ቤተ ክርስቲያን ልታወግዝ ይገባል እንጂ በቸልታ ልታይ አይገባትም። (ኤር. 46÷10)

17.3 ሰው ከሞተ በኋላ በሕይወተ ሥጋ ላለው ዋስ (ጠበቃ) ይሆናል ስለሚባለው

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነትና መልካም ሕይወት ለሌላው ትውልድ አርአያ ይሁን እንጂ ፍጡርን ከፈጣሪ ጋር የማስታረቅ ሥልጣን አልነበራቸውም። በእርግጥ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ስለሌላው ሰው ማማለድ (መጸለይ ወይም መለመን) ይችሉ ነበር እንጂ ከሞቱ በኋላ ግንንም ሰው ከገነት ወደ ሲያል ወይም ከሲያል ወደ ገነት የማዛወር ኃይልም ሆነ ሥልጣን እንደሌላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በዲድስቅልያ መጻሕፍት ሳይቀር ተጠቅሶአል። ለምሳሌ ዕዝራ ሱቱኤል 6፥33-37 «... መለስኩለት እንዲህ አልሁት አቤቱ ጌታዬ በፊትህ ባለሟልነትን ካገኘሁ ለእኔ ለባሪያህ ዳግመኛ ይህንን ንገረኝ ቍርጥ ፍርድ በሚደረግበት ቀን በልዑል ዘንድ ጻድቃን ለኃጥአን ማማለድ ይችላሉን? አባቶች ለልጆቻቸው ልጆች ለአባቶቻቸው ወንድሞች ለወንድሞቻቸው ዘመዶች ለዘመዶቻቸው ማማለድ ይችላሉን? ብዬ ጠየኩት መለሰልኝም እንዲህ አለኝ በፊቴ ባለሟልነትን አግኝተሃልና ይህን እነግርሃለሁ። ቍርጥ ፍርድ የሚደረግበት ቀንስ አንድ ጊዜ ናት በፍጹም ትዕዛዝ የእውነተኛ ማህተሙን አብሮ ያሳያቸዋል። ዛሬ አባት ልጁን ባሪያ ጌታውን ወዳጅ ወዳጁን ስለርሱ ይታመም ዘንድ እንደማይልከው ... እንደዚሁ አንዱ ለአንዱ መለመን ፈጽሞ የሚችል የለም። ሁሉም ዋጋውን ይቀበላል። ሥራውም የየራሱ ነውና» በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል።

ኤልያስ ለእግዚአብሔር እጅግ ከመቅናቱ የተነሣ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ዝናብ እንዳይዘንብ ጸልዮ ሆኖለታል። ከባዓል ነቢያት ጋር ተወራርዶ እሳት ከሰማይ ወርዶ መስዋዕቱን በመብላት እግዚአብሔር ከርሱ ጋር መሆኑን አረጋግጧል። ከዚያም አራት መቶ ሃምሳ የባዓል ነቢያት በሙሉ በቂሶን ወንዝ ከታረዱ በኋላ እንደገና በግንባሩ ተደፍቶ ጸልዮ ዝናብ ሊዘንብ ችሎአል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት እምነት ያለውና የእግዚአብሔር ታላቅ ተዓምር በእጁ የተከናወነለት ይህ ሰው ከሞተ በኋላ ለማንም ጠበቃ፥ ዋስና አማላጅ መሆን አልቻለም። 1ነገ. 17፤ 18፤ 19፤ ያዕ. 5፥17-18።

ከላይ በተጠቀሰው ዕዝራ ሱቱኤል ምዕ. 6፥38-46 ባለው ክፍል ደግሞ አብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ፥ ሙሴ ስለ በደሉት የእስራኤል ሕዝብ፥ ኢያሱ በአካን ዘመን ስለ እስራኤል፥ ሳሙኤል ሳዖል በንገሠበት ወራት፥ ዳዊትም ስለ ቸነፈር፥ ሰለሞንም ስለ ቤተ መቅደስ፥ ኤልያስም ስለ ዝናብ፤ ሕዝቅያስም በሰናክሬም ዘመን ስለ ሕዝቡ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የለመኑት ልመና እንጂ ከሞቱ በኋላ እንደማይቻላቸው በመግለጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ጋር ይስማማል።

እንግዲህ ከአዳም ጀምሮ ሥጋ የለበሰ ሰብዓዊ ፍጡር ለሌላው አማላጅ ዋስ ወይም ጠበቃ ሊሆን ስላልቻለ የሰው ልጅ በኃጢአት ሰንሰለት ታስሮ በሞት ፍርድ ውስጥ መሆኑን ቃሉ በግልጽ ያሳየናል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» ይላልና። ዮሐ. 5፥24 ሐዋርያው ጳውሎስ «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ ...» ይላል። ኤፌ. 2፥1 «፪ጋው በእምነት አድኖአችኋል ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ...» ይላል። ኤፌ. 2፥1-9።

ስለዚህ ሰው በልቡ ፈቃድ በእግዚአብሔርና በቃሉ በማመን መዳን ወይም ባለ ማመን መኰነን ከሚችል በስተቀር በሌላው ፍጡር ጽድቅ ወይም የአማላጅነት ዋስትና ከፍርድ ሊድን እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ሕዝ. 14፥13-20

17.4 ፍጡር የፍጡርን የኃጢአት ዕዳ ሊከፍል አለመቻሉ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የመረጣቸው ሐዋርያትም ሆኑ በኋላ በጌታ አምነው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ሕይወታቸውንም ለእርሱ በማስረከብ ለወንጌል አገልግሎት በሰማዕትነት ያለፉት ደቀ መዛሙርትና ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ለማንም ማማለድ አይችሉም። በራዕይ ምዕ. 6፥9-10 የተጠቀሰው «... ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ» ይላል። ይህም በግልጽ የሚያስረዳው ሥጋ የለበሱ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ሌላው እንዲድን ያቀረቡትን የምልጃ ጥያቄ ሳይሆን

ይልቅስ በራሳቸው ላይ ስለ ደረሰው ግፍና ዐመጽ የበቀል እርምጃ እንዲወሰድ የጠየቁት ጥያቄ መሆኑን ነው።

«... ንጹህ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው? እነሆ በቅዱሳኑ ስንኳ አይታመንም፥ ሰማያት በፊቱ ንጹሐን አይደሉም፥ ይልቁንስ አጸያፊና የረከሰ ኃጢአትንም እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ» ኢዮብ 15፥14-16።

ቸሩ አምላካችን ማናቸውም ፍጡር የአዳምን ዕዳ ከፍሎ ሰውን ከእርሱ ጋር ለማስታረቅና አማላጅ ሆኖ ፍጡር ለፈጣሪው ካሣ መክሰ እንደማይቻለው ዐውቆ በገዛ ራሱ ታራቂና አስታራቂ አማላጅም ሆኖ ዕዳችንን በመስቀል ላይ ከፈለው እንጂ የአድኅኖተ ሰብእን ነገር ፍጡራንን ልኮ እንዳልፈጸመው በሃይማኖተ አበውም ሆነ በቅዱስ ቃሉ በግያሻማ ሁኔታ ተገልጸአል። «... በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹን ከንዱ የሚያደርግ ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚመልስ ሰው ርጉም ነው ...»። ኤር. 17፥5-8

መጽሐፍ ቅዱስ የፍጡር አማላጅ ሰውን ከፍርድ ለማዳን እንደማይችል ሲያብራራ «... የሰው ልጅ ሆይ፥ ምድር በማመፅ በእኔ ላይ ኃጢአት ስትሰራ፥ እኔም እጀን ስዘረጋባት የእንጀራዋንም በትር ስሰብር ራብም ስሰድድባት፥ ሰውንና እንስሳውንም ከእርስዋ ሳጠፋ እነዚህ ሦስት ሰዎች ኖህና ዳንኤል ኢዮብም ቢኖሩባት በጽድቃቸው የገዛ ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ... እነርሱ ብቻቸውን ይድናሉ እንጂ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም ምድሪቱም ባድማ ትሆናለች ይላል ጌታ እግዚአብሔር ...» ሕዝ. 14፥13-20።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ክፍል ስንመለከት የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑት ጻድቃን እንኳንስ ሌላውን የማያውቁትን ቀርቶ ልጆቻቸውንም ሊያድኑና ከፍርድ ነፃ ሊያወጡ እንደማይችሉ ነው።

አንዳንድ ሰዎች የአማላጅነትን ነገር ከዓለማዊ ሥርዓት ጋር በማያያዝ በታላቁ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቶ በሰው ፊትም ቢሆን ለመቅረብ አማላጅ ያስፈልገናል ይላሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር እንደ አንድ ምድራዊ ንጉሥ ወይም ባለ ሥልጣን በመቍጠር ወደ ንጉሡ ወይም ወደ ባለ ሥልጣኑ ለመቅረብና ችግሬን ነግሬው መፍትሄ ለማግኘት ሰተት ብዬ መቅረብ ስለማይሆንልኝና ስለማልችልም አማላጅ (አገናኝ) ፈልጌ በእርሱ አማካይነት እቀርባለሁ እንጂ በቀጥታ እገባለሁ ማለትማ የድፍረት

ድፍረት ይሆንብኛል ይላሉ። ነገር ግን ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። (ዮሐ. 1፥12) ተብሎ እንደ ተጻፈ እንዲሁም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። (ሮሜ 8፥14) በቃሉ መሠረት ዕርቅ መፈጸሙን አምነን በመቀበል የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን ወራሾች ነን ብሎ ቃሉ ሥልጣን ስለሚሰጥ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የግል መድሃኒታቸው አድርገው የተቀበሉት ያለአንዳች ጥያቄ ወደ አባታቸው ሲገቡ ሌሎች ግን ልጆች ስላልሆኑ አይችሉም። ቃሉ የሚለውን ባለማወቃቸውና ይህንኑ እውነት ባለ መቀበላቸው አንዳንድ የቃሉ ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች የሚነግሩአቸውን የባልቴቶች ተረት ተቀብለው ፍጡራን እነ እገሌና እነ እገሊት ያማልዱልኛል በማለት በኃጢአትና በአመጽ ውስጥ የሚመላለሱ ያሉበትን ተረድተው በቃሉ መሠረት ወደ አምላካቸው በንስሐ ቢመለሱ እርሱ መሃሪና ይቅር ባይ ነውና ይቀበላቸዋል። በመንፈስ ከእግዚአብሔር ከተወለዱ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት እንደ ቃሉ ይጐናጸፉሉ። «በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን» 2ቆሮ. 3፥4።

ስለዚህ በእርግጥ ከምድራዊ ሥርዓትም ሁኔታ ስንመለከት ወደ ንጉሡ ወይም ወደ ትልቁ ባለ ሥልጣን ማንም ተራ ሰው ዘው ብሎ ሊገባ አይችልም። ስለዚህም ንጉሡን ወይም ባለ ሥልጣኑን የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል ቀጠሮም ይይዛል። ከተሳካለት ብቻ አግኝቶ ያነጋግረዋል። ይሁን እንጂ ወደ ንጉሡ ወይም ወደሚፈራው ባለ ሥልጣን ግቢ መግባት የሚፈልገው ሰው የራሱ የንጉሡ ወይም የባለ ሥልጣኑ ልጅ የሆነ እንደ ሆነ ወደ አባቱ ግቢ እንዳይገባ የሚከለክለው የለም። የቤተ መንግሥት ክቡር ዘበኞችም ሆኑ የትልቁ ሰው ግቢ ዘበኞች የንጉሡን ወይም የባለ ሥልጣኑ ታማኝ ልጅ ሰላምታ ሰጥተው በክብር ወደ አባቱ እንዲገባ ያደርጉታል እንጂ እነርሱን «እባካችሁ ከአባቴ ጋር ለመገናኘት ስለምፈልግ አማልዱኝ» ብሎ አይጠይቃቸውም። እነርሱም ቢሆኑ እኛ አማልደን ወደ አባትህ ልትገባ ትችላለህ አይሉም። ምክንያቱም ልጅ የሆነ ወራሽም ነውና።

ስለዚህ የሰማዩ ሥርዓት ሰዎች ካወጡት ከምድር ሥጋዊ ሥርዓት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በሰማያዊ መንግሥት ሥርዓት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚቻለው በዮሐ. 1፥12 «ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች

ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው» ተብሎ እንደተጠቀሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ዳግም በመወለድና በመንፈስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን ብቻ እንጂ እንደፈለገ በሥጋ በዓለምና በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ሲጨፍር ቆይቶ ሥጋ ለባሽ በሆኑ ሰዎች ወይም በመላዕክት አማላጅነት ወደ ጽድቅ (መንግሥተ ሰማያት) መግባት ይቻላል ብሎ ማመንና ለሌሎችም ይህንን ማስተማር፤ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ፤ ማቴ. 22÷29 ተብሎ በተጻፈው መሠረት የእግዚአብሔርን ቃልና ኃይል አለመረዳት እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ሰው እውነት በሚመስል ውሸት የገባና በስህተት ትምህርት ውስጥ የተዘፈቀ መናፍቅ ሆኖ ሌሎች ተከታዮቹንም በባሰ ስህተትና የዘላለም ፍርድ ውስጥ የሚዘፍቅ የወንጌል ዕንቅፋት ይሆናል።

ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ÷ በእነዚህ ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ። (1ጢሞ. 4÷16)

17.5 ማስታረቅና ማማለድ

ማስታረቅና ማማለድ በሁለት ተጣዮች መካከል ገብቶ በመገላገል በጥላቻ ፈንታ ፍቅርን÷ በመለያየት ፋንታ ኅብረትን ማደስ ስለሆነ ሁለቱም አንድ ናቸው። የሚለያዩት ግን በማስታረቅ ሦስቱም ሰዎች እኩል ሊሆኑ ይችላሉ። በማማለድ ግን አማልዱኝ ባዩ ያንሳል። ነገር ግን አማላጅና ተማላጅ እኩል ናቸው። ስለሆነም አማላጅና ተማላጅ አብና ወልድ እኩል ናቸው። የሚያንሰው አማላጅ ፈላጊ አዳም (ሰው) ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም በመወለዱ አምላክም ሰውም ነው። በመሆኑም በኃጢአተኛው በአዳምና በተበዳዩ በአብ መካከል መካከለኛ ሆኖ ለእርቅ ሊገባ ችሎአል። በመለኮቱ እኩያው ከሚሆን ከአባቱና ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስም ሕይወቱ አማልዶ÷ ለምኖ÷ ጸልዮ ራሱን ሰውቶ ሊያስታርቅ ችሎአል። ይህንንም የማማለድና የማስታረቅ ሥራ መፈጸሙ ከአባቱ በመለኮቱ ያንሳል ማለት አይደለም፤ ክብሩም አይቀንስም። አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር በሰው አእምሮ ለመገደብ ይሞክራሉ። እግዚአብሔር ፍቅሩ ከአእምሮ በላይ ነው። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዮሐ. 3÷16

አቶ ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ «ሁሉም ሁሉን ይወቅ» በሚል ርዕስ በ1987 ዓ.ም. በጻፉት መጽሐፋቸው ስለ ክርስቶስ አማላጅነት በዝርዝር ሲያብራሩ÷ ክርስቶስ ለደቂቀ አዳም አዳኝ÷ አስታራቂ÷ ጠበቃ÷ አማላጅ÷ ጸላይ÷ በለበሰው ሥጋ ደግሞ በአባቱና በአዳም መካከል ገብቶ (ሆኖ) ዘላለም ተከራካሪ÷ መሆኑን ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ይገልጻሉ።

ሀ) ከእግዚአብሔር አብ አባቱ ፦ እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ። ትዕዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድኩህ÷ ለምነኝ አህዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ። መዝ. 2÷6-8፤ 109÷4። እንዲሁም ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም። ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ ያለው እርሱ ነው። እንዲሁም በሌላ ስፍራ ደግሞ አንተ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ይላል። ከዚህ አያይዞ ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት ይላል። ዕብ. 5÷5

ለ) ራሱ ወልደ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ልጅ) ኢየሱስ ክርስቶስ፤

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ (አማላጅ) ይሰጣችኋል። ዮሐ. 14÷15-16። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ አማላጅነት÷ ጸላይነት÷ ከአብ ስለ መላኩ ራሱ የተናገረውን ለማስረዳት ዮሐ. 17 በሙሉ ደጋግሞ ማንበብ ሃሳቡን ለመረዳት ይጠቅማል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደካማ ያማልዳል÷ ይጸልያል÷ ጸልዮአልም÷ «ስምዖን ሆይ÷ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» አለ። ሉቃ. 22÷32

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ እንዲላክም ያማልዳል፤ ብትወድዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ እኔም አብን እለምነዋለሁ ከናንተ ጋር

ለዘላለም ይኖር ዘንድ ሌላ አጽናኝ (አማላጅ) ይሰጣችኋል። ዮሐ. 14፥15-16

ለቤተ ክርስቲያን ይጸልያል፥ ያማልዳል፥ እኔ ስለ እነዚህ አለምናለሁ፥ ስለ ዓለም አልለምንም፥ ስለ ሰጠኸኝ እንጂ ያንተ ናቸውና። ዮሐ. 17፥9

ከነፍሱ ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፥ ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል። ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይካፈላል ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ አመፀኞችም ማለደ። ኢሳ. 53፥11-12

ሐ) ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአማላጅነት ሥራ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከጠቀሰው፤

1) ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በልጁ ሞት እንድናለን፥ ይህም ብቻ አይደለም አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን። ሮሜ 5፥9-10

2) እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማነው የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ሮሜ 8፥34

ፍጡር ከሞተ በኋላ ያማልዳል የሚሉትን የባልቴቶች ተረት ይህ የቅዱስ ጳውሎስ አነጋገር ውድቅ ያደርገዋል። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ የሚጽፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ስለ እኛ የሚማልደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ ጌታ ኢየሱስ የዘላለም አማላጅ መሆኑን ገልጾ አስተምሮናል።

3) እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥና የማይሻር ክህነት አለው። ስለ እነርሱ ለማማለድ በሕይወት ይኖራል። ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሠሩች የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ

(ይከራከር፥ ያማልድ ዘንድ) ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ። ዕብ. 7፥25

ሠ) «ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ» በ1942 ዓ.ም በታተመው ተግሳጽና ምክር የተሰኘ መጽሐፍ ስለ አማላጅ ሲያብራሩ ከዚህ እንደሚከተለው ገልጸዋል ፦

የአማላጅነት ነገር የክርስቶስ ሥራና የብቻው ገንዘብ በመሆኑ ይህንኑ የሚያሳስት እውነተኛ የሕይወት መንገድና እርግጠኛ አማላጅ ትተህ ሌላ የስርቆሽ መንገድ የማይጠቅም ባዕድ የፍጡር አማላጅ ይዘህ ራስህ የፈጠርከው ጠማማና ወደ ሕይወት የማያሳልፍ መንገድ ስህተት ከህደት፥ ድንቁርና ልማድ ፍጻሜው (መድረሻው) የዘላለም ጥፋት ይባላል። ዮሐ. 10፥1፤ ኤር. 5፥7፤ 17፥13፤ 18፥15፤ ማቴ. 7፥13)

የኃጢአት ዕዳህን ሊከፍል በቀራኒዮ መስቀል ላይ እርቃኑን ተሰቅሎ የዋለውና አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው (ሉቃ. 23፥34) ያለው እውነተኛ አማላጅ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ጻድቁ መድሃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው። (ዮሐ. 3፥13-18)

ሰው ሰውን ለማዳን የሚችል ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ ከተጠራው ከአብርሃም የበለጠ ጻድቅ አልነበረም። ነገር ግን የእርሱ ጽድቅ ከራሱ አልፎ ለሌሎች ሊተርፍ አልቻለም። (ዘፍ. 15፥16፤ ዘፀ. 3፥2-10)

አንዳንድ ሰዎች ጻድቃን ስለ ኃጥአን ለምነው አማልደው ኃጥአንን ከሲዖል እጅ ያድናሉ፤ ስማቸውን አንስቶ ጠላ ስለተጠጣ ሁሉም ከገሃነም ይወጣሉ ጻድቁው ያጸድቃሉ። ከሞቱ በኋላም ልመናችንን ሊያስፈጽሙልን ይችላሉ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋልና የፈቀዱትን ይሠራሉ እያሉ ሥጋቸውን ለመጠገን አስመስለው ቢሰብኩህ እውነት መስሎህ እንዳትቀበል ተጠንቀቅ፤ ይልቁንስ ከእግዚአብሔር ቃልና ከክርስትና ሃይማኖት መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስህ ጋር የማይጣጣም ነውና አስብበት።

በሌላ አቅጣጫም ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው ተብሎ በነቢያት እንደተነገረ ፍሬ የሌለው ቅጠሉ የለመለመ ግን የተረገመ በለስ መስለህ የስም ክርስቲያን በተግባር ስትታይ ደግሞ አረመኔና አመፀኛ ሆነህ እንዳትገኝ ተጠንቀቅ። (ማቴ. 21፥18-20)

ስለ ጽድቅ ግን በእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች የለምና ሐ.ሥ 4፥12። አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና። በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከገዛ ሥጋው መበስበስን ያጭዳል ...። ገላ. 6፥7-8 በማለት በቃሉ መሠረት ለሰው ሁሉ አስታራቂ አማላጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው በማለት አስረድተዋል።

18.1 ቅድስት ድንግል ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎች መጻሕፍት

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም በሕይወት እያለች በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2፥1-11 ላይ እንደምናነበው በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሠርግ ነበረ፥ የኢየሱስ እናት በዚያ ነበረች ኢየሱስም ደግሞ ደቀመዛሙርቱም ወደ ሠርጉ ታደሙ። የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም» አለችው። ኢየሱስም «አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» አላት እናቱም ለአገልጋዮች የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው። አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፥ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር። ኢየሱስም ጋኖቹን ውሃ ሙሉ አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው። አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው (ለግብዣው ኃላፊ) ሰጡት አላቸው ሰጡትም አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር። ... ኢየሱስ ይህንን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀመዛሙርቱም በእርሱ አመኑ» ይላልና ማርያም የሚላችሁን አድርጉ በማለት ጠቃሚ የሆነ ምክር ያስተላለፈችውን ከእግዚአብሔር ቃል ቢማስተዋል ጌታ ኢየሱስ አድርጉ ያሉንን ማድረግና አታድርጉ ያሉንን ደግሞ መተው አለብን።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው «ወንጌላችን የተከደነ እንኳን ቢሆን የተከደነባቸው ለሚጠፉት ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዲያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» ተብሎ በ2ቆሮ. 4፥3-4 እንደተጻፈው ካልሆነ በቀር አባባሉና ቋንቋው ግልጽ ነው። ማርያምም ያለቻቸው «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ነው እንጂ እኔ ለዚህ ጉዳይ አማላጅ ነኝ አላለችም። እርሷስ ብፅዕት ቅድስትና ከሴቶች ሁሉ የተባረከች እንደሆነች የተመሰከረላት «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» ሉቃ. 1፥48 ያለች አይደለችምን?

ይህ ቃል የማርያምን ቅድስናና ብፅዕና የማይቀበል ማንም ቢኖር ትክክል እንዳልሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ትውልድ ሁሉ ሲል የኛንም ትውልድ ያጠቃልላል። እንግዲህ የማርያምን ብፅዕና ማወቅ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ማርያም የሚናገረውን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማገናዘብ ማስተዋል ይገባናል። «ቃሉ በሙላት ይኑርባችሁ» ይላልና። ቆላ. 3÷16

ማርያም የኢየሱስ እናት ብትሆንም እንዲህ ብላ ጸለየች፤ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድሃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች» ሉቃ. 1÷47 ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዋና መድሃኒቷ መሆኑን ማርያም ራሷ መስክራለች። ስለ ምርያም በተጻፉ አንዳንድ መጻሕፍት ላይ ግን ከላይ በእግዚአብሔር ቃል ከተጠቀሰውና እርሷም ከተናገረችው ውጪ ያላደረገችውን አደረገች፥ ያልሆነችውንም ሆነች በማለት ስሟን ሲያጠፉ ይስተዋላል።

በተጨማሪም ሰባ ስምንት ሰው የበላውን «በላዔ ሰብዕ» በመባል የሚታወቀው ሰው ጥርኝ (እፍኝ) ውሃ በማርያም ስም ለአንዱ ለማኝ በመስጠቱ የተሰጠው አንድ ጥርኝ ውሃና ሰባ ስምንቱ የተበሉ ሰዎች ነፍሳት በሚዛን ተመዝነው በማርያም ስም የተሰጠው ጥርኝ ውሃ ስለ መዘነ ሰው በላው ሰው በማርያም አማላጅነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ ቻለ ብሎ ይተርካል። (ተአምር 12 ቁጥር 91-125)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ (ማቴ. 11÷28) በማለት የኃጢአት የኑሮና የባህል ተፅዕኖ ሸክም የከበደው ሁሉ ለመፍትሄና ለዕረፍት ወደ እርሱ ብቻ እንዲሄድ ወደ እኔ ኑ ካለና ማርያም ደግሞ የሚላችሁን አድርጉ ካለች በቀጥታ መሄድ ያለብን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢናር ይድናል። (ዮሐ. 10÷9)

ስለ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ለግል ጥቅም ሲሉ ማዛባት ትልቅ ኃጢአት ነው። ተአምር 11 ገጽ 66 ቁጥር 20 ላይ የተአምሯን መጽሐፍ የጻፈውን የባሪያዋን የተስፋ ጊዮርጊስን ስም በውነት ለዘላለም በሕይወት መጽሐፍ ትጻፍለት ይላል። በተጨማሪም :- ከንጉሥ ልጅዋ ጉን በፈሰሰ ደሟ እኛን ንጹሐን አድርጋ እንደ ስሟ ትርጓሜ ወደ ልጅዋ ባሮች አባቶቻችን ፍጹምነት መርታ ... በኃጢአት ያደፈውን ከኃጢአት ታነጻዋለችና ወደ መንግሥተ ሰማያትም ታደርሰዋለች ይላል። (ተአምር 12 ገጽ 73 ቁጥር 54)

ከኃጢአት የሚያነጻው በመጽሐፍ ቅዱስ አውነተኛ ቃል መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ ደም መሆኑ ቀርቶ ወይም ተሠርዞ የማርያም ደም ነው የሚለውን መጽሐፍ ምን ይሉታል? «... የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።» 1ዮሐ. 1÷7 ይላል። ምናልባት በዚህ አንጻር የማርያም ደም ከኃጢአት ያነጻል የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደሆነ በዚህ አካያ የሚሟገቱ ሰዎች ቢገለጹ መልካም ነው።

18.2 ርግማንና ፍርድ በአጼ ዘርአ ያዕቆብ የሥርዓት መጽሐፍ

በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ተዘጋጀ በሚባለውና በ1924 ዓ.ም በታተመው ተአምረ ማርያም የዘወትር መቅድም ከቁጥር 33-36 ባለው ክፍል «እመቤታችን ማርያም በፍጥረት አንደበት ትመሰገናለችና የቤተ ክርስቲያን ልጆች አክብሯት፤ ለእናንተ ለኃጥአን መድሃኒታችሁ ስለሆነች፥ በጉ አገልግሎትም ለሚያገለግላት ዋጋውን ትሰጠዋለች ሳትጠራጠሩ በፍጹም ልቡናችሁ እመኑባት እርሷ መድሃኒታችሁ ናትና። በስዕሏም ፊት ስገዱ ለሥዕሏ ያልሰገደ ግን ከቆመበት ቦታ ይጥፋ ስም አጠራሩም አይታወቅ። በሰማይ ያሉት መላዕክትም ይደረግ! ይሁን! ይበሉ» ይላል። ስለ ስግደት በዘፀአት 20÷4-5 እና በዘዳግም 5÷8-10 ከተጻፈው ጋር እንዲያገናዝቡ ክፍሉ እነሆ :-

ነገሀ የዘወትር መቅድም።

ሰማይ፣ እግዝአትን፣ ማርያም፣ ውድስት፣ በልሳን፣ ሁሉ፣ ፍጥረት፣ አነቦርዋ፣ ውሉዶ፣ ቤቲ፣ ክርስቲያን፣ እስ ሙ፣ ይእቲ፣ ቤዛክሙ፣ ለኃጥአን።

ወወሃቢተ፣ ጸጋ፣ ይእቲ፣ ለዚ ሠናየ፣ መልእክተ፣ተአመ ሠ በሎ፣ልብክሙ፣እንዘ፣ ኢትና ፍቁ፣እስመ፣ይእቲ፣መድኃኒትክሙ።

ወቅድመ፣ ሥዕላ፣ ስግዱ፣ዘ ኢሰገደሰ፣ ላቲ፣ ይደምስስ፣ እምቅ ዋመ፣ ወኢይትዐወቅ፣ ዝክረ፣ስሙ።

ወይበሉ፣ መላእክተ፣ ሰማይ፣ ሁሉሙ፣ አሜን።

ወጽ፣ እመቤታችን፣ማርያም፣ በፍጥረት፣ አንደበት፣ ትመሰገናለችና፣ የቤተ፣ ክርስቲያን፣ ልጆች፣ አክብሯ ት፣ ለናንተ፣ ለኃጥአን፣ መድኃኒታች ሁ፣ ስለሆነች።

ወበጎ፣ አገልግሎትም፣ ለሚያገ ለግላት ዋጋውን፣ትሰጠዋለች፣ሳትጠ ራጠሩ፣ በፍጹም፣ ልቡናችሁ፣ እመኑ ባት፣ እሷ፣ መድኃኒታችሁ፣ ናትና።

ወበቅድመ፣ሥዕላ፣ ፊት፣ስገዱ፣ ለሥዕ ላ፣ ያልሰገደ፣ ግን፣ ከቆመበት፣ ቦታ፣ ይጥፋ፣ ስም፣ አጠራሩም፣ አይታወቅ።

ወበሰማይ፣ ያሉ፣ መላእክትም፣ ያጽረግ፣ ይሁን፣ ይበሉ።

የሰንበት መቅድም ከተራ ቁጥር 7-37 ባለው ክፍል ደግሞ ቈስጠንጢኖስ የተባለ ንጉሣችን ዘርአ ያዕቆብ በነገሠ በሰባት ዓመት የሥርዓታቸው መጽሐፍ እንዲህ ይላል ፦ በየሳምንቱ እሑድ እሑድ በእመቤታችንም ሠላሳ ሦስቱ በዓላት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን በፍጹም ክብር በብዙ ደስታ የእመቤታችንን ታምሯን ማንበብ አያስታጉሉ ... በዓላቱም እኒህ ናቸው፤

ነሐሴ 7 ቀን የተጸነሰችበት

ነሐሴ 16 ቀን ሥጋዋ የፈለሰበት ከአሥራ ስድስት ጀምረው እስከ ሃያ አንድ ቀን ድረስ እንደ ልጅዋ ትንሣዔ በዓል አድርገው ያከብሩ።

መስከረም 10 ቀን የእመቤታችን ሥዕል የመሪና ቦታ ወደምትሆን ጌዴንያ ወደምትባል አገር ገብታ የተቀመጠችበት ነው። ይህችም ሥዕል ሥጋን የለበሰች ትመስላለች ከፊቷም ወዝ ሲወጣ ይታይ ነበር በዚሁም በሃያ አንድ ቀን ትከበራለች።

ጥቅምት 21 ቀንም ትከበራለች

በጎንደር 6 ቀን ቁስቋም በምትባል አገር ገብታ የተቀመጠችበት ነው። በጎንደር 21 ቀንም ዘካርያስ የመቅደስ ፋና ሲያበራ ያየበት ነው።

በታህሣሥ 3 ቀንም ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት ነው በዚህ ወር በ21 ቀንም ትከበራለች፤ በ22 ቀንም ደቅስዮስ የሚባል ኤጲስ ቆጶስ በዓሏን ያከበረበት ቀን ነው። በዓሏን ባከበረላት በዚህ ቀን በሰው እጅ ያልተሠራ ሰማያዊ ልብስ፥ ሌላ መምህር የማይቀመጥ ቦታ ላይ ወንበር ሰጠችው።

በ28 ቀንም ጌታን የወለደችበት ነው፤ በ29 ቀንም መድሃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችበት ነው። ጥር 21 ቀን ያረፈችበት ነው። የካቲት 16 ቀን ተዝካሯን ላደረገ ስሟን ለጠራ የምህረት ቃል ኪዳን ልጅዋ የሰጠበት ቀን ነው በዚሁ ወር 21 ቀንም የምትከበርበት ነው።

መጋቢት 21 ቀን በዓሏ ነው። በዚህ ወር በ29 ቀንም መድሃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የፀነሰችበት ነው።

ሚያዝያ 21 ቀንም በዓሏ ነው።

ግንቦት 1 ቀን የተወለደችበት መስከረም 11 ቀን ልደቷ ነው የሚሉም አሉ። እኛ ግን በተረዳ ነገር አባቶቻችን ሊቃውንት እንዳስተማሩን ልደቷን ግንቦት 1 ቀን ነው እንላለን።

ግንቦት 21 ቀን በግብፅ አገር ደብረ ምጥማቅ በምትባል በተሠራች ቤተ ክርስቲያን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያሉ ሰዎች ይሰባሰባሉ ከያገሩም ሁሉ ይመጣሉ። ከግንቦት 21 ቀን እስከ ግንቦት 25 ቀን ድረስ ድንግል ሳታቋርጥ በነዚህ በአምስቱ ዕለታት ከመላዕክት ከፃድቃን ከሰማዕታት ጋራ ትገለጽላቸው ነበር። ክርስቲያንም እስላምም በገሃድ ተገልጻ ያዩአት ነበር። በፍጹም ክብር በፍጹም ደስታ በዓሏን ያከብሩ ነበር። በ21፥ በ22፥ በ23 ቀን ከሳቸው ጋራ። በ24 ቀንም ወደ ግብፅ አገር የገባችበት ታላቅ በዓል ነው።

በዚሁ ወር በ25 ቀን ልጅዋ የደረቁ በትሮችን ተክሎ ያለመለመበት ነው።

በሰኔ 8 ቀን ለሀሙግን ደህንነት ሊሆን ልጅዋ ውሃን ከዐለት ያፈለቀበት ነው።

ሰኔ 20 ቀንም ሐዋርያት የተሰበሰቡበት ልጅዋም ቤቷን ለመሥራት የወረደበት ነው። 21 ቀንም ቤቷን ያከበረበት ነው።

ሐምሌ 21 ቀንም ትከብራለች። አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በደንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችን በዓላቶችዋ ሁሉ ሠላሳ ሦስት ናቸው። እኒህን በዓላት እንደ እሁድ ሰንበት አድርገው ያከብሩአቸው። «እመቤታችን ማርያም ታምሯን የሚናገር መጽሐፍ ሲነበብ የሚሰሙትን ወንዶችንና ሴቶችንም ሁሉ ቢሆን ትባርካቸዋለችና»› ቁጥር 37 «ሥጋ ወደሙን መቀበል ያልቻለ «ተአምሯን ሰምቶ ወደ ቤቱ ይሂድ ሥጋውን ደሙን እንደተቀበለ ይሆንለታል» ቁጥር 45 «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላ የካቲት 16 ቀን ጀምሮ ከተሰቀለበት ቦታ (ጉልጐታ) እየሄደች በመቃብሩ ላይ መጸለይዋን አላቋረጠችም፤ ልጅዋም በየቀኑ ይጐበኛትና የምትሻውንም ይፈጽምላት ነበር» ይላል።

ይህ መጽሐፍ ማርያም ወደ መቃብር ሄዳ ፀለየች የሚለው ጌታ ሞትን ድል አድርጐ መቃብር ፈንቅሎ መነሳቱን አላወቀችም ለማለት ይሆን?

በዚሁ ከላይ በተጠቀሰው የአጼ ዘርአ ያዕቆብ የሥርዓታቸው መጽሐፍ በተባለው ላይ «... የማርያም ስም ሲጠራ ሰማይና ምድር እስከ ሲያል ድረስ ይናወጣሉ፥ የመላዕክትም ክንፋቸው ልርገፍ ልርገፍ ይላል። የሁሉ ሥልጣን በጁ የሆነ ልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን የበቀል ፍርድ ሊፈርድባቸው በፊቱ የቆሙትን ኃጥአን በቃል ኪዳን ቀለም የተጻፈ የድንግል ስም ሲጠራ የአደባባዩን ፍርድ ትቶ ይነሣል፤ በኃጥአን ላይም አይፈርድም። ስለዚህ እንደ እኔ ያላችሁ ኃጥአን ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእንግዲህስ ወዲያ 16ቱን ሕግጋት (አሥርቱን ቃላተ አሪትና ስድስቱን ቃላተ ወንጌል) ለመፈጸም የእግዚአብሔር ባሮች መሆንን እንሻ ይላል። (ገጽ 73 ተአምር 12 ቁጥር 49-52)

እንግዲህ ከላይ በርዕሱ እንደተጠቀሰው በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ተዘጋጁ ከሚባሉት ከበርካታ መጻሕፍት አንዱ በሆነው በዚህ መጽሐፍ እንደተገለጸው በአሪትና በአዲስ በተጻፈው መሠረት የእግዚአብሔር ባሮች ተብለን ልንጠራ አያስፈልግም። ምክንያቱም የማርያም ስም ሲጠራ ከዘላለም ፍርድ ነፃ መሆን ይቻላልና የሚል ነው።

ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ አባባልና ከክርስትና መሠረተ ሀሳብ ጋር የማይጣጣም ሰዎች ንስሐ ገብተው ከኃጢአትና ከበደላቸው ተጸጽተው በመመለስ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን እንዳይፈጽሙ የሚያደፋፍር ክፍል ስለሆነ ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶበት ቢጤን መልካም ነው።

መጽሐፉ የሃይማኖት (የእምነት) መመሪያ ሳይሆን የሥርዓት መጽሐፍ እንደሆነ በመቅድም ገጽ 3 ቁጥር 1 ላይ ተጠቅሶአል፤ በገጽ 4 ቁጥር 8 ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ የሥርዓት መጽሐፍ እንደሆነ ይገልጻል።

ምንጊዜም ሃይማኖት አይለወጥም አይሻሻልምም ሥርዓት ግን የማይጠቅምና ከእውነት የራቀ ከሆነ በሃይማኖቱ መሪዎች እየተጠና በየጊዜው ሊለወጥና ሊሻሻል ይችላል። የማይለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። መጽሐፉ የተጻፈው ከላይ ስሙ በተጠቀሰውና ቆስጠንጥኖስ በመባል በሚታወቀው በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1426-1460) መሆኑ ነው። ይህም ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ወደ 1100 ዓመታት ገደማ በኋላ ነው ማለት ነው። ከዚያ በፊት ግን ይህ የሥርዓት መጽሐፍ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ያልነበረ ነው።

ጻድቃን ሰማዕታት

19.1 የሞቱ ፃድቃንና ጽድቃቸው

በመጽሐፈ መክብብ 9፥4-6 እንዲህ ይላል :- «ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና ሰው ከሕያዋን ሁሉ ጋር በአንድነት ቢኖር ተስፋ አለው። ሕያዋን እንደሚሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸውም ተረስቶአልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም። ፍቅራቸውና ጥላቻቸው ቅንዓታቸውም በአንድነት ጠፍቶአል ከፀሐይ በታችም በሚሰራው ነገር ለዘላለም ዕድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም።»

የእምነት አባትና የእግዚአብሔር ወዳጅ በመባል የሚታወቀው አብርሃም በሕይወት እያለ ስለ ሰዶምና ገሞራ ሲማልድ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18 ላይ እናነባለን። ከሞተ በኋላ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትም ስፍራ ሲማልድ አናገኝም። ሰዎችም ስለሰሩት ኃጢአትና በደል ወይም መተላለፍ ይቅርታ ለመቀበል ወደ ሞቱት ጻድቃን ሰማዕታት አማልዱን ብለው አልጸለዩም። ጻድቃን የገዛ ነፍሳቸውን እንጂ ሌላውን የማዳንና ከፍርድ ነፃ የማውጣት ሥልጣን እንደሌላቸው በሕዝቅኤል 14፥12-20 በግልጽ ተብራርቶአል።

በሕይወት ያለ የእግዚአብሔር ሰው ለሌሎች መጸለይና ማማለድ እንደሚችልና ከሞተ በኋላ ግን ምንም ማድረግ እንደማይችል የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ያስረዳናል። ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሞቱ ፃድቃን እንደማያማልዱ ከፀሐይ በታች በሚሠራው ነገር ዕድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም እያለ ሰዎች ግን የሞቱ ፃድቃንና ሰማዕታት ያማልዱናል ብለው ባልሆነና በማያዋጣ መንገድ መንከራተታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ካለማወቅና ምናልባትም ለማወቅም ካለመፈለጋቸው የተነሳ ነው። አንዳንዶቹም ቃሉን እያወቁ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የግል ጥቅምን በመፈለግ ወይም ወግንና ሥርዓትን ለማክበር ብቻ ሲሉ የዐዋቂ አጥፊ የሆኑም አሉ። እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ተከታዮቻቸውንም ከእውነት መንገድ አስተው እውነትን በሚመስል ፍጹም ሐሰት በሆነ የጥፋት ጐዳና ይመሩአቸዋል።

ጌታ ኢየሱስ እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች «እናንተ ስለ ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ትተላለፋላችሁ» ይላቸዋል። ማቴ. 15፥3

ማንም ሰብዓዊ ፍጡር ለዓለም ኃጢአት ቤዛና መድሃኒት በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የነፍስ ደህንነት ካላገኘ ሌሎች በሥጋት የጽድቅ ሥራ እድናለሁ ብሎ ተስፋ ማድረግ ማለት የዋህነት ሳይሆን ሞኝነት ነው። የሰው ልጆች ከንቱ እንደሆኑና ሐሰተኞች በመሆን በሚዛን እንደሚበድሉ (በመዝ. 62፥9) ተጠቅሶአል።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርም እርዱኝ እረዳችኋለሁ ብሎአል በማለት እግዚአብሔርን ደካማና ደጋፊ ፈላጊ እንደሆነ አድርገው ያቀርባሉ። ከየት እንደሚጠቅሱ ግልጽ ባይሆንም ከዚህ የባሰ ደግሞ ሰዎች እውነትን አውቀው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይገቡ ግድግዳ ሆኖ የጋረደ የሰው ሥርዓትና ወግ ሰርተው «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተም አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ» (ማቴ. 23፥13) ተብሎ እንደተጻፈ ስተው ያስታሉ።

ምህረትንና ይቅርታን ጠይቆ ወደ እግዚአብሔር ለሚመለስ ሰው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። (ዮሐ. 3፥16) በተጨማሪም ከአዳምና ከሄዋን በደምና በሥጋ ከወረሰው ኃጢአትና በምድር ላይም በምኞት በድርጊትና በተግባር ከፈጸመው ከተገለጠና ከስውር ኃጢአት ሊያነፃው የሚችለው የክርስቶስ ክቡር ደም ብቻ ነው። ከአብ አባቱ ጋር ለማስታረቅ የመጣ እርሱ ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ የአማላጅነት ሥራም የእርሱ ብቻ ነው። (ማቴ. 11፥28፤ 28፥18፤ ዕብ. 2፥17-18፤ 4፥14-16፤ ራዕይ 1፥5-8፥ 5፥1-14) ሐዋርያው ዮሐንስም ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ (አማላጅ) አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይላል። (1ዮሐ. 5፥10)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ኦሰገድዶት የአዳምን ዕዳ ለመክፈል ወደ ዓለም እንደ መጣ ከላይ ተደጋግሞ ተገልጾአል።

እርሱም ኃጢአታችንን ተሸክሞ መከራን ታግሦ እጆቹ በምስማር፥ ጐኑ በጦር ተወግቶ ሞቶ ተቀብሮ ሞትን ድል አድርጐ ተነስቶ ከአባቱ ጋር አማልዶ ከጥፋት ያዳነን መድሃኔዓለም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

(ማቴ. 27፥22-50፤ ሮሜ 5፥5-11፤ ኤፌ. 2፥4-18፤ ቆላ. 1፥10-23፤ 1ዮሐ. 4፥14)

19.2 ፍጡራን ከሞቱ ወዲያ ሌሎችን ሊረዱ አይችሉም

ፍጡራን ከሞቱ በኋላ ስለ ሕያዋን ጥቅም ወይም ጉዳት ማሰብና መሥራት መገናኘትና መረዳዳት እንደማይችሉ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ከመወሰዱ በፊት ለኤልሳዕ የተናገረውን ብንመለከት ከአንተ ከተለየሁ በኋላ ልሰጥህ አልችልምና አሁን ሳንለያይ የሚያስፈልግህን ጠይቀኝ ማለቱ ሰዎች ካረፉና ካንቀላፉ በኋላ ምንም እንደማይሠሩ ያሳያል። (2ነገ. 2፥9-14፤ ኢዩ. 3፥11-18፤ 14፥1-22)

ስለዚህ ጽድቅና ደህንነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት ካልሆነ በቀር ከቶ በፍጡራን ስም አይገኝም። እውነትን በውሸት ለመሸፈን ካልተፈለገ በቀር የመዳንና የጽድቅ መንገድ አንድ ሲሆን እርሱም ነፍሱን ስለ ብዙዎች ቤዛ የሰጠ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ሙታንን ተስፋ አድርጐ በእነርሱ ስም እየበሉና እየጠጡ መኖር ምናልባት ለሥጋ ጠገን ለጥቂት ነገር ይጠቅም ይሆናል እንጂ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ባዶ ነው።

ተግሳፅና ምክር ገጽ 61 ላይ ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ሲጠቃለል ወንድሜ አንባዚ ሆይ፥ እንደ አገራችን ባህልና ልማድ እምነታችን ተስፋችንና መታመኛችንም ምንም ከማይሰሙ ሙታን ጻድቃን ሰማዕታት፥ ቅዱሳን እያልን ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ባወጡት ሥርዓትና የስህተት መንገድ ሄደን እንዳንታለል ጥንቃቄ እናድርግ። ማቴ. 7፥13-19፤ ቆላ. 2፥8 ይላል።

ሰው ሁሉ ኃጢአተኛና በደለኛ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። ሮሜ 3፥23-24

የኃጢአታችንን ይቅርታ ለማግኘት ከፈለግን ተደጋግሞ እንደተገለጸው ያለው አንድ መንገድ ነው። እርሱም እኛን ኃጢአተኞችን ለማዳን ክብሩን ትቶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋ ለብሶ በመጣው በጌታችንና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

በግመን ብቻ ነው። እርሱ ብቻውን መድሃኒትና ቤዛ ነው። መድሃኔዓለም ማለት የዓለም መድሃኒት ማለት እንደሆነ ብዙዎች በስም ብቻ ያውቁታል። እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው የሰው ልጅ ወደደም ጠላ በዘር ሐረግ በሥጋና በደም የውርስ ኃጢአት አለበት። በተጨማሪም በምድራዊ የሥጋ ሕይወቱ በሃሳብ፥ በምኞትም ሆነ በድርጊት ኃጢአተኛ ነው። ስለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ ...። (ኤፌ. 2፥1) የሚለው። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ሆነ። ሮሜ 10፥3-4 ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። ዮሐ. 1፥12

የዓለም በሽታዋ ኃጢአት ነው የኃጢአት ደመወዝ ደግሞ ሞት ነው። ሮሜ 6፥23 ከኃጢአት እንጽቶ ወደ ጽድቅ የሚያገባ ሌላ መድሃኒት ከፍጡር ሊገኝ ባለ መቻሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተቸንከረ፥ ሞተ፥ ተቀበረ፤ መቃብርን ፈንቅሎ ሞትን ድል አድርጉ ተነሣ ወደ ሰማይም አረገ፥ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይከፍል ዘንድ ዳግም ይመለሳል።

20.1 መላእክትና አገልግሎታቸው

መልአክ ማለት ትርጉሙ መልእክተኛ (ተላላኪ) ማለት ነው። ስለዚህ ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር ተላላኪዎች ናቸው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መላእክት ራሱን የቻለ ተግባር ሲፈጽሙ እንደሚገኙ እናነባለን።

ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉን ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ። (መዝ. 103፥20) በማለት የመላእክት ዋና ተግባር የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማትና የእርሱን ትዕዛዝ መፈጸም መሆኑን ይነግረናል። በጉልህ እንደተቀመጠው መላእክት የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ሰው ማምጣት ነው እንጂ የሰውን አቤቱታ መቀበል ወይም ወደ እግዚአብሔር ማድረስ አይደለም። ቃሉን የምትፈጽሙ ... ሲል የእግዚአብሔርን ቃል እንደሆነ እንጂ የሰውን ቃል እንደሆነ አይናገርም።

መላእክት የእግዚአብሔርን መልእክት ለአብርሃም፥ ለሕዝቅኤል፥ ለዳንኤል፥ ለዘካሪያስ፥ ለሶምሶን አባት ለማኑሄ፥ ለቅድስት ማርያም፥ ለሐዋርያው ዮሐንስ ወዘተ. እንዳስተላለፉና ስግደት ግን እንዳልተቀበሉ እናነባለን። ነገር ግን ከእነዚህ ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር መልእክትን ወይም ምልጃን ይዘው ሲሄዱ አልታዩም። ዘፍ. 18፥1-8፤ ዳን. 10፥10-21፤ ሉቃ. 1፥8-23፥26-38

የመላእክት ተግባር በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ሰዎች መጠበቅ ነው። በመንገድህም ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና እግርህም እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱሃል። (መዝ. 91፥11-12)

መላዕክት መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን? (ዕብ. 1፥14) የሚላኩ ሲል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው።

መላእክት ከዚህ አገልግሎታቸው ሌላ ለመቅሰፍም ይላካሉ። ሐሥ. 12፥20-23 ስንመለከት ንጉሡ ሄሮድስ በእግዚአብሔር ላይ ስላመጸና

ክብርም ስላልሰጠው የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ ይላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፥ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። ትህትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ፤ እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው (ወደ ኢየሱስ) አይጠጋም ... (ቆላ. 2፥16-19) ከዚህ ከፍል እንደምንመለከተው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ ለመኖርና የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ መንገድ እውነትና ሕይወት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ዮሐ 14፥6 ስለሆነም ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ሥልጣን ያለው ማንም ምንም ስለሌለ በቃሉ ላይ ፦

1. የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትም ሆኑ መላዕክት እንደማያማልዱ በግልጽ ይነገረናል (መክ. 9፥4-6፤ ሕዝ. 14፥12-20፤ ራእ. 22፥8-9፤ 12)
2. በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው አማላጃችንና አስታራቂያችን ስለ እኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ የሞተው የተቀበረውና ከሙታን በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ወደ ሰማይ ያረገው በታላቅ ክብርና ግርማ የሚመለሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሮም 8፥34፤ ዋስ - ዕብ. 7፥20-21፤ ጠበቃ - 1ዮሐ. 2፥1፤ አስታራቂ - 2ቆሮ. 5፥17-25፤ ኤፌ. 2፥13-22፤ 7፤25።

ጌታ ኢየሱስ ያማልድልናል ሲባል እርሱ ከአብ ያንሳል ወይም ማዳን አይችልም ማለት ሳይሆን የእኛን ሥጋ ለብሶ በባህሪያችን ያለውን ድካም የሚረዳ በመሆኑ በድካማችን ሊራራልን የሚችል ሊቀ ካህናችን (አስታራቂያችን) እርሱ ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳናል (ዕብ. 4፥15)።

ስለዚህ ሌላ ፍጡር አማላጅ ይሆናል ተብሎ አልተጻፈም አልተነገረም። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ሲናገር እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና አለ። ማቴ.

11፥28፤ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። ዮሐ. 7፥33

ከእነዚህና ከሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስንረዳ ወደ ኢየሱስ ለመቅረብ ልዩ የሆነ የቢሮክራሲ አሠራር ተበጅቶ መላዕክትንና ጻድቃንን አማላጅ በማድረግ ደጅ ካልጠናችሁ አትገቡም ተብሎ አልተጻፈም። የሰውን ሥጋዊ ሥርዓትና የእግዚአብሔር መንግሥት ዘላለማዊ የፍቅር ሥርዓት ማደባለቁ ወይም ለይቶ አለመረዳቱ ጉዳት ነው። «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና»። ሮም 8፥1-2

«የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል» 1ዮሐ. 1፥9 ተብሎ እንደ ተጻፈ ኃጢአታቸውን በንስሓ በደሙ ታጥበውና ነጽተው በእግዚአብሔር መንፈስ ፈቃድ የሚመሩ ናቸው እንጂ፤ «ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ ይላቸዋል። (ማቴ. 7፥22-23)

እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት የሚቆምና የራሱን የሥራና የአገልግሎት ዋጋ የሚቀበል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እየገለጸ ኃጢአተኛው ቶሎ ንስሓ እንዳይገባና እንዲቆይ ለማበረታታት የሚደረገው ከእግዚአብሔር ፈቃድና ቃል ውጪ የሆነ ማንኛውም ነገር በራሱ ተጨማሪ ወንጀል ነው።

ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ያለውን ኃጢአት የሰማይ መላዕክት ሊያስወግዱ ሊያማልዱና የኃጢአትን ዕዳ ሊከፍሉ እንዳይችሉ መላዕክት መናፍስት ስለሆኑ ደም የላቸውም። ያለ ደም ደግሞ ሥርየት የለም። «... ደምም ሳይፈስ ሥርየት የለም።» ዕብ. 9፥22

20.2 የመላዕክት ተልዕኮ

የመላዕክትን ተልዕኮ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት ፦

መላዕክት ቀንና ሌሊት ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣሉ፤ ያመሰግናሉ (ኢዩ. 6፥3-4፤ ራእ. 5፥11-12፤ 7፥11-12)

መላዕክት ለማዳንም ሆነ ለማጥፋት ከእግዚአብሔር የሚላኩ ናቸው። (ዘፍ. 19፥1-28፤ 2ሳሙ. 24፥15-16፤ ዳን. 6፥19-22)

መላዕክት ምዕመናንን ለመጠበቅ ይታዘዛሉ። (መዝ. 34፥7፤ 91፥10-12፤ ዕብ. 1፥14)

መላዕክት ከእግዚአብሔር የሚላኩ መልእክቶችን ለሰዎች ያደርሳሉ። (ዳን. 8፥15-19፤ 9፥22-23፤ ሉቃ. 1፥26-28፤ ራእ. 22፥16)

መላዕክት የሰዎች መልዕክተኞች ሆነው ወደ እግዚአብሔር የተላኩበት ጊዜ የለም። ከሰው ስግደትና አምልኮም ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም። (መሳ. 13፥15-20፤ ራእ. 19፥10፤ 22፥8-9)

በስም የታወቁት መላዕክት ሚካኤልና ገብርኤል ናቸው። (ዳን. 10፥10-15፤ 18፥16፤ 9፥21፤ ሉቃ. 10፥26፤ ይሁዳ 9) ነገር ግን ሱራፌል (ኢሳ. 6፥2-3) ኪሩቤል (ሕዝ. 1፥4-28፤ 10፥9-22) የተጠቀሱ መላዕክት ሲሆኑ ከእነዚህም ሌላ እጅግ ብዙ እልፍ አእላፋት ሠራዊተ መላዕክት እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የወደቁ መላዕክትም ገብርኤልና ሚካኤል ነን እያሉ አንዳንዶችን የሚያታልሉ ስላሉ መላዕክት የሚያመጡልንን መልዕክት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አመዛዝነንና መርምረን እንጂ መልዓክ ነኝ ያለንን ሁሉ እሺ ብለን ልንቀበል አልታዘዝንም። «ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደዚህ ዓለም ወጥተዋልና» 1ዮሐ. 4፥1።

አንዳንድ ጊዜ የተጣሉ መላዕክትም (ርኩሳን መናፍስት) «የእግዚአብሔር መላዕክት ነን» በማለት የሐሰት ሥራቸውን ሊያከናውኑ ስለሚችሉ ግንዛቤ በመውሰድ ጥንቃቄ ልናደርግና በሁኔታዎቻችን ሁሉ በመጸለይ ከቃሉ መንፈሳዊ መረዳትን ማግኘት አስፈላጊ ይሆናል። (ሕዝ. 28፥11-19፤ ይሁዳ 6፤ ራእ. 12፥7-9) እነዚህ መናፍስቶች የዚህ የጨለማው ዓለም ገዥ በመባል የሚታወቁ ሲሆን ዓለማዊውን ሥርዓት የመምራትና ያለ ክርስቶስ የሚኖሩትንም የዓለማቸው ተገዥ የማድረግ ውስን ሥልጣን አላቸው። (ሉቃ. 4፥5-6፤ ዮሐ. 12፥36፤ 16፥31፤ ኤፌ. 2፥2፤ 6፥12) ይሁን እንጂ የወደቁ መላዕክት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አማኞችን ሊጐዱ ፈጽሞ አይችሉም። (ኢዮ. 1፥6-12፤ 2፥1-9፤ ሉቃ. 22፥31-32)።

እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ለዘላለም በገሃነም እንዲኖሩ የተወሰነባቸው ሲሆኑ ሰዎችንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይገቡ በተለያየ

የሃይማኖት ስርዓትና የባህል ተጽዕኖ በመጫን በማታለልና በማባበል ወደ እነርሱ የጥፋት ዓላማ እየሳቡ ተከታዮች በማድረግ ላይ ይገኛሉ። (ማቴ. 25፥41፤ ዘዳ. 31፥17፤ 2ነገ. 21፥5፤ 2ዜና. 11፥13፤ መዝ. 106፥35፥38፤ ራእ. 9፥20-21።

የተለያዩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችም ሆኑ ግለሰቦች መላዕክትን በሚመለከት ረገድ ልዩ ልዩ አስተሳሰብና እምነት ሊኖራቸው ይችላል። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተገናዘበና ትክክለኛውን ፈር የተከተለ ሃሳብ ማቅረቡ ለሚፈጠረው አለ መግባባት ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል። ለዚህም ዓላማ መሳካት በስብዓዊ ምርምርና በፍልስፍና ወይም መጨበጫ በሌለው ተረት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ መደገፉ ግዴታ ይሆናል።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው መላዕክት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ የሰማይ ሠራዊት ሲሆኑ የማይጨበጡና የማይዳሰሱ ረቂቃን መናፍስት ናቸው። (ዕብ. 1፥14)። በክብር ከሰው ጥቂት ይበልጣሉ (መዝ. 8፥5)። የተፈጠሩት ቅዱሳን ሆነው ነው (ዘፍ. 1፥31)። ቁጥራቸው ... ብዙ ሺህ ... ወይም አእላፋት ... ነው (መዝ. 68፥17፤ ዕብ. 12፥23)። ሰዎች ያገባሉ ይጋባሉ። መላዕክት ግን አያገቡም አይጋቡምም (ሉቃ. 20፥34-36)። ተፈጥሮአቸውና ባህሪያቸው ከሰው የተለየ ነው። ሰው ሥጋ ለባሽ ሲሆን እነርሱ ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸው መናፍስት ወይም የማይዳሰሱና የማይጨበጡ ፍጡራን ናቸው። ይሁን እንጂ በሚያስፈልግበት ጊዜ እንደ ሰው ለመታየት የሚያስችል ኃይል አላቸው። ምግባቸው ከሰው ምግብ የተለየ ሰማያዊ እንጀራ እንደሆነ በመዝ. 78፥25 ተገልጸአል። በኢዮብ 1፥6 ላይ የአምላክ ልጆች የሚል ስያሜም ተሰጥቶአቸዋል።

20.3 የመላዕክት ባሕርይ

መላዕክት ክፉና መልካም ተብለው ይለያያሉ። አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው ወይም ኃጢአት በመሥራታቸው ወደ ገሃነም ተጥለው በጨለማ ጉድጓድ ፍርዳቸውን ይጠባበቃሉ። 2ጴጥ. 2፥4፤ ይሁዳ 6 የቀሩት ክፉዎች መላዕክት ደግሞ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ሥራ ይቃወማሉ፥ ፈቃዱንና ዕቅዱን ይጻረራሉ። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድል እንደሚሆኑና በአማኞች ላይ ሥልጣን እንደሌላቸው ተጽፎአል። መልካሞቹ መላዕክት ግን እግዚአብሔርን ያመልካሉ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይረዳሉ፥ ይጠብቃሉ (ዘፍ. 19፥11፤ መዝ. 91፥11)።

የመላዕክት ዓይነት የተለያየ ነው። ሱራፌል፥ ኪሩቤል፥ ሊቃነ መላዕክትና ጠባቂ መላዕክት የተባሉት ሚናቸዉ ይለያያል።

ሱራፌል ስድስት ክንፍ ያላቸው ሲሆን የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚናገሩ ናቸው (ኢሳ. 6፥1-8)።

ኪሩቤል፥ አራት ክንፍ ሲኖራቸው ሥራቸውም የእግዚአብሔርን ዙፋን መጠበቅ ነው። (ሕዝ. 1፥4-25፤ 10፥1-22፤ ራዕ. 4፥6-8)

ሚካኤል፥ ከሊቃነ መላዕክት ታላቁና አንዱ ነው። በታላቁ መከራ ጊዜ ለእስራኤል ልጆች በመቆም ተዋግቶላቸዋል። (ዳን. 12፥1-2) እንዲሁም በመጨረሻው ቀን ከዲያቢሎስ ጋር በሰማይ ታላቅ ውጊያ ያደርጋል (ራዕ. 12፥7-9)።

ሌላው ሊቀ መላዕክት ገብርኤል ነው። እርሱም የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ያከናውናል፥ ያበስራልም። በሚከተሉት ክፍሎች ስለ እርሱ ተጽፎአል፤ (ዳን. 8፥15-17፤ 9፥20-27፤ ሉቃ. 1፥11-20)።

የመጨረሻው የወደቀው ሊቀ መላዕክት የነበረው ሰይጣን ነው። እርሱም ዘንዶ፥ ዲያቢሎስ፥ የቀደመው እባብ፥ ክፉው፥ እሳች፥ የወንድሞች ክሳሽ፥ ብዔልዜቡል፥ ቤልሆር፥ አብዶንና አጵልዮን፥ ባላጋራ፥ ነፍሰገዳይ፥ የሃሰት አባት ወዘተ. ተብሎም ይጠራል። ዲያቢሎስና ተከታዮቹ የሆኑት ሌሎች መላዕክት ከሰማይ ወደ ምድር የተጣሉ በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው እንዲሁም አምልኮና ስግደትን ለራሳቸው በመፈለጋቸው ነው። ኢሳ. 14፥12-16

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ስለ መልካሞቹና ስለ ክፉዎቹም መላዕክት በሰፊው ተገልጾአል። ስለሆነም የክፉዎቹን መላዕክት የክፋትና የጥፋት ዓላማ በመገንዘብ እነርሱን መቃወምና ሥራቸውንም በክርስቶስ ስም ማፍረስ ይገባል። መልካሞቹ መላዕክት የእግዚአብሔር መልዕክተኞች ናቸው። መልዕክተኛ ቢባል ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ወይም ወደ ሌላ ቦታ የሚላክ በቃልም ሆነ በጽሑፍ አንድን መልዕክት የሚያደርስ አካል ማለት ነው። የመልዕክቱ ዓይነት ብዙውን ጊዜ ይለያያል። መልዓኩ የምስራችን፥ መርዶን፥ ምስጋናን፥ ወቀሳን፥ ምክርን፥ ተግሣጽንና ፍርድን የሚመለከት ነገር ሲናገርና ሲፈጽም በሁኔታው አያዝንም ወይም አይደሰትም። በዚሁ ዓይነት መላዕክት ከእግዚአብሔር የተላኩበትን ጉዳይ ለሰው ሲያደርሱ ስሜታቸውና አቀራረባቸው በመልዕክቱ አፈጻጸም ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

20.4 መላዕክት ለተለያዩ ሰዎች ያስተላለፉት መልዕክት

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መላዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ተለያዩ ሰዎች ተልከው መልዕክት እንዳደረሱ ተጠቅሷል። ይኸውም ፦

ግብፃዊቷ አጋር ከጌታዋ ከአብራም ባረገዘች ጊዜ እመቤትዋን ሦራን በዓይንዋ አቃለለች፤ በዚህም ምክንያት ሦራ አጋርን አሠቃየቻት አጋርም ስቃይ ስለበዛባት ኮበለለች።

የእግዚአብሔር መልዓክም በበረሃ በሚገኝ አንድ የውሃ ምንጭ አጠገብ አገኛት፤ ምንጩ የሚገኘው ወደ ሱር በሚወስደው መንገድ አጠገብ ነው። መልዓኩም የሦራ ባሪያ አጋር ሆይ ከወዴት መጣሽ? ወዴትስ ትሄጃለሽ? አላት። አጋርም እኔ ከእመቤቴ ከሦራ የኰበለልሁ ነኝ አለች። መልዓኩም ወደ እመቤትሽ ተመለሺ ከእጅዋም በታች ሁኚ ተገዥ ... እነሆ አንቺ ፀንሰሻል ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ እግዚአብሔር መቸገርሽን ሰምቶአልና። እርሱም የምድረ በዳ እህያን የሚመስል ሰው ይሆናል እጁ በሁሉ ላይ ይሆናል የሁሉም እጅ ደግሞ በእርሱ ላይ ይሆናል ... አላት፤ ዘፍ. 16፥7-12።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ለአጋር በጭንቀቷ ወቅት እግዚአብሔር መልዓኩን ልኮላት 1ኛ) ከኖረችበት ቤት ኩብልላ በመንከራተትና በሀዘን ላይ ለዝረች ለአጋር የማጽናኛ መልዕክት ነግሮአት ወደ ወጣችበት ወደ አብራምና ወደ ሦራ ቤት እንድትመለስ ነገራት፤ 2ኛ) የምሥራች ያዘለ የተስፋ ቃል ይኸውም የምትወልደው ወንድ ልጅ እንደሆነና እግዚአብሔርም መቸገሯን ማየቱን መልዓኩ ገልጾላት አጋር ወደ አብራምና ሦራ ቤት ተመልሳ በተነገራት መሠረት እስማኤልን ወለደች።

አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መስዋዕት አድርጐ ለእግዚአብሔር ሊሰዋ በሞሪያ ተራራ ላይ ቢለዋ ባነሣ ጊዜ የእግዚአብሔር መልዓክ ከሰማይ ጠራውና አብርሃም አብርሃም ... በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልከምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ። በዚህ ጊዜ አብርሃም አንድ በግ በዱር ውስጥ አግኝቶ በልጁ ፈንታ ሠዋው። የእግዚአብሔር መልዓክ ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው እንዲህም አለው እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ ይላል ይህን ነገር አድርገሃልና አንድ ልጅህንም አልከለከልከምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ። ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብት በባህር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፥ ዘርህም

የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ቃሌንም ሰምተሃልና (ዘፍ. 22፥11-18)።

አብርሃም በልቡ እግዚአብሔርን እንደሚፈራና ጽኑ እምነት እንዳለው የእግዚአብሔር መልዕክተኛ አረጋገጠለት። ቀጥሎም ስለዘሩ ያለውን የዘላለም ተስፋ ነገረው። ተስፋውም የማያወላውልና ውሸት የሌለበት ነበር።

20.5 መልዓክ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሲቆም

የሞዓብ ንጉሥ የነበረው የሴፎር ልጅ ባላቅ አገሩ በእስራኤላውያን መከበቡን አይቶ በመፍራቱ እስራኤልን እንዲረግምለት ወደ ነቢዩ ወደ በለዓም መልዕክተኞችን ላከ። መልዕክተኞቹም የምዋርቱን ዋጋ ይዘው ወደ በለዓም ከሄዱ በኋላ ከባላቅ የተላኩትን ቃል ነገሩት በለዓም ግን ከእግዚአብሔር ጋር ከተማከረ በኋላ አብሮአቸው ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጸላቸው። ምንም ከአሕዛብ ወገን ቢሆን ስለ እስራኤል አምላክ በጥቂቱ ሰምቶ ነበርና ባላቅ ከመጀመሪያዎቹ የሚበልጡ መልዕክተኞችን ልኮበት ሲነጋ አህያውን ጭኖ ከሰዎቹ ጋር ሄደ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ የእግዚአብሔርም መልዓክ ሊቋቋመው በመንገድ ላይ ቆመ። አህያይቱም የእግዚአብሔርን መልዓክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየች። ከመንገዱም ፈቀቅ ብላ ወደ እርሻ ውስጥ ገባች። በለዓምም ወደ መንገድ ይመልሳት ዘንድ አህያይቱን መታት። የእግዚአብሔርም መልዓክ ከወይን ቦታዎች መካከል በወዲያና በወዲህ ወገን ግንብ በነበረበት በጠባብ መንገድ ላይ ቆመ። አህያይቱም የእግዚአብሔርን መልዓክ አየች፤ ከበለዓምም በታች ተኛች በለዓምም እጅግ ተቆጣ አህያይቱንም በበትሩ ደበደባት። እግዚአብሔርም የአህያይቱን አፍ ከፈተ በለዓምንም ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌብህ ነው? አለችው። በለዓምም አህያይቱን ስላላገጥሽብኝ ነው በእጄስ ሰይፍ ቢኖር አሁን በገደልኩሽ ነበር አላት። አህያይቱም በለዓምን፤ ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን? በውኑ እንዲህ አደርግ ዘንድ ልማዴ ነበርን? አለችው፤ እርሱም እንዲህ አላደረግሽብኝም አላት።

እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርን መልዓክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ፥ ሰገደም በግንባሩም ወደቀ። የእግዚአብሔርም መልዓክ አህያህን ሦስት ጊዜ ለምን መታህ? እነሆ መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና እቋቋምህ ዘንድ መጥቻለሁና አህያይቱም አይታኝ ከፊቴ ሦስት ጊዜ ፈቀቅ አለች፤

ከፊቴስ ፈቀቅ ባትል በእውነት አንተን አሁን በገደልኩህ እርስዋንም ባዳንኳት ነበር አለው። በለዓምም የእግዚአብሔርን መልዓክ በድያለሁ አንተ በመንገድ ላይ እንደቆምክብኝ አላወቅሁም እንግዲህም አሁን አትወድድ እንደሆነ እመለሳለሁ አለው። የእግዚአብሔር መልዓክም በለዓምን ከሰዎቹ ጋር ሂድ ነገር ግን የምነግርህን ቃል ብቻ ትናገራለህ አለው በለዓምም ከባላቅ አለቆች ጋር ሄደ፤ ዘኍ. 22፥22-35።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የበለዓም ታሪክ እጅግ አስገራሚ ነው። የባላቅ ምኞት እስራኤላውያንን ወግቶ ለማሸነፍና ከአገሩ ለማባረር ስላልቻለና ስለፈራ በበለዓም ለማስረገም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ስለማይፈልግ መልዓኩን ልኮ አህያዋን በማናገር የበለዓምን ዓላማና ሀሳብ ለወጠው። የበለዓም ዓይኖች ተከፈቱ። እርግማኑ ወደ ምርቃትና በረከት ተለወጠ። እንዲያውም ስለ መሲሁ ስለ ክርስቶስ ሳይቀር ትንቢት ተናገረ። በለዓም በመልዓኩ ፊት የወደቀውና የሰገደው በድንጋጤ ከመዋጡ የተነሣ እንጂ ሊያመልከው እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

20.6 የመላዕክት መመሪያ ለእግዚአብሔር ሕዝብ

የእስራኤል ልጆች ለብዙ ዓመታት በግብፅ አገር በባርነት ከሚኖሩበት እግዚአብሔር በፀናች እጅ በበረታችም ክንድ አውጥቶአቸው ሳለ እነርሱ ግን የእግዚአብሔርን ስም አረከሱ አስታሮትንና በዓልንም አመለኩ። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር አዘነ በተለያዩ መንገዶችም ጥፋታቸውን ይነግራቸው ነበር። የእግዚአብሔርም መልዓክ ከጌልጌላ ወደ ቦኪም ወጥቶ ጥፋታቸውን ሁሉ በነገራቸው ጊዜ የእስራኤል ልጆች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ መሳ. 2፥1-5።

የእስራኤል ልጆች በክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው ለጠላቶቻቸው ለምድያማውያን አሳልፎ ሰጣቸው። እነርሱም ለሰባት ዓመታት በብዙ ዓይነት ጭቆናና ሥቃይ ገዙአቸው። በኋላም ጥፋታቸውን ተገንዝበው ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ እግዚአብሔር መልዓኩን ልኮ ጌዴዎንን «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው እግዚአብሔር ካንተ ጋር ነው» አለው ጌዴዎንም ጌታዬ ሆይ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን? ... እግዚአብሔር ትቶናል በምድያማውያንም እጅ አሳልፎ ሰጥቶናል አለው። እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ዞር ብሎ በዚህ በጉልበትህ ሂድ እስራኤልን ከምድያም እጅ አድን እነሆ ልኬሃለሁ አለው። ... ጌዴዎንም አቤቱ አምላክ ሆይ፥ ወዮልኝ

የእግዚአብሔርን መልዓክ ፊት ለፊት አይቻለሁና አለ። እግዚአብሔርም ሰላም ላንተ ይሁን አትፍራ፥ አትሞትም አለው። መሳ. 6፥11-24

በሌላ ጊዜ ደግሞ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ስለ ሠሩ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን እጅ አርባ ዓመት አሳልፎ ሰጣቸው።

ማኑሄ የሚባል ከዳን ወገን የሆነ አንድ የጾርዓ ሰው ለሚስቱ የእግዚአብሔር መልዓክ ተገልጦላት «እነሆ አንቺ መካን ነሽ ልጅም አልወለድሽም ተጠንቀቂ የወይን ጠጅን የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ ርኩስም ነገር አትብዪ። ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናል በራሱ ላይ ምላጭ አይደርስበትም እርሱም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል። ሴቲቱም ወደ ባልዋ መጥታ «አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ መልኩ እንደ እግዚአብሔር መልዓክ የሚያስደነግጥ ነበር ከወዴት እንደ መጣ አልጠየኩትም እርሱም ስሙን አልነገረኝም» በማለት መልዓኩ የነገራትን ሁሉ ነገረችው።

ማኑሄም ጌታ ሆይ፥ የላክኸው የእግዚአብሔር ሰው እባክህ እንደገና ወደ እኛ ይምጣ ለሚወለደውም ልጅ ምን እንድናደርግ ያስገንዝበን ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ። እግዚአብሔር የማኑሄን ድምፅ ሰማ፥ የእግዚአብሔርም መልዓክ እንደገና ለሴቲቱ በእርሻው ውስጥ ተቀምጣ ሳለች ተገለጠላት ባልዋ ማኑሄ ግን ከእርስዋ ጋር አልነበረም። ሴቲቱም ፈጥና ሮጠች ለባልዋም እነሆ በቀደም ዕለት ወደ እኔ የመጣው ሰው ደግሞ ተገለጠልኝ ብላ ነገረችው። ማኑሄም ተነስቶ ሚስቱን ተከተለ ወደ ሰውየውም መጥቶ ከዚህች ሴት ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህን? አለው። እርሱም እኔ ነኝ አለ። ማኑሄም ቃልህ በደረሰ ጊዜ የልጁ ሥርዓት ምንድነው? የምናደርግለትስ ምንድነው? አለው የእግዚአብሔርም መልዓክ ማኑሄን ሴቲቱ ከነገርኳት ሁሉ አትብላ ያዘዝኳትንም ሁሉ ትጠብቅ አለው። ማኑሄም የእግዚአብሔርን መልዓክ የፍየል ጠቦት እስክናዘጋጅልህ ድረስ እባክህን ቆይ አለው። የእግዚአብሔርም መልአክ ማኑሄን አንተ የግድ ብትለኝ መብልህን አልበላም፥ የሚቃጠለውንም መስዋዕት ግዘጋጀት ብትወድስ ለእግዚአብሔር አቅርበው አለው። ማኑሄም የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን አላወቀም ነበር፤ መሳ. 13፥3-23።

ከዚህ በኋላ የማኑሄ ሚስት ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሶምሶን ብላ ጠራችው። ሶምሶን ባደገ ጊዜ ከሰው ሁሉ የተለየ ኃይለኛና ብርቱ

ሆነ። የእግዚአብሔር ዕቅድ እስራኤላውያንን እንዲታደግና ነፃ እንዲያወጣቸው ነበር። ስለዚህ መንፈሱን ከሶምሶን ላይ በኃይል አወረደ። ሶምሶንም ፍልስጥኤማውያንን ያጠቃ ጀመር። በእነርሱና በንብረታቸው ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አደረሰ። የሚቋቋመው ሰው ጠፋ። ከዚህም የተነሳ በፍልስጥኤማዊት ጋለሞታ ፍቅር ተነደፈ የእግዚአብሔርንም ዓላማ ሳተ። ይህችኑ ደሊላ የምትባለውን ጋለሞታ አገባ። እርስዋም ሶምሶንን ለወገኖችዋ አሳልፋ ለመስጠት ፈልጋ ከብዙ ጊዜ ሙከራ በኋላ ራሱን ላጨችው። ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ተለየው። ሶምሶንም እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ሆነ፤ ጠላቶቹም ይዘው ዓይኖቹን ካወጡ በኋላ እስር ቤት አግብተው ወፍጮ አስፈጩት እንደፈለጋቸውም መዘባበቻ አደረጉት።

እግዚአብሔር መልዓኩን ልኮ መልዕክቱን የሚያስተላልፈውም ሆነ መንፈሱን ለሰዎች የሚሰጠው እንደሚገባ እንዲይዙትና እንዳያስመርሩት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ከኃጢአት ወይም ከጣዖት ጋር አብሮ በሰው ልብ ውስጥ ሊኖር አይፈቅድም። ሰዎች እግዚአብሔርን ሲበድሉና ሕይወታቸውን በዓለም ነገር ሲያረክሱ ያዝናል። መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ኃጢአት መሥራትን ቢቀጥሉና ንስሐ ባይገቡ ትቶአቸው ይሄዳል። ከዚህ በኋላ ያለው ሕይወታቸውና ኑሮአቸው በጣም የሚያስከፋ ይሆንባቸዋል።

20.7 "ገብርኤል" የምስራች ተናጋሪ መልዓክ

ሄሮድስ ይሁዳን ይገዛ በነበረበት ዘመን ዘካሪያስ የተባለ ካህን ነበር። ለእርሱም ኤልሳቤጥ የምትባል ሚስት ነበረችው። የሁለቱም ዕድሜ የገፋ ከመሆኑም በላይ ልጅ አልነበራቸውም።

አንድ ጊዜ ዘካርያስ የአገልግሎት ተራው ስለ ደረሰ ለማጠን ወደ ቤተ መቅደስ ገባ። በዕጣኑ ሥነ ሥርዓት ላይ ሕዝቡ በውጭ ቆመው ይፀልዩ ነበር። የጌታም መልዓክ በዕጣኑ መሰዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርሃትም ወደቀበት። መልዓኩም እንዲህ አለው ዘካርያስ ሆይ ፀሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፥ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል። እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትን ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና

ኃይል በፊቱ ይሄዳል። ዘካርያስም መልዓኩን እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? አለው። መልዓኩም መልሶ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ገብርኤል ነኝ። እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፥ እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ድዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው። (ሉቃ. 1፥8-20) ከዚህም የተነሣ መጥምቁ ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ አባቱ ዘካርያስ ዲዳ ሆኖ ቆየ።

ዘካርያስ የሰብዓዊ ተፈጥሮን ሁኔታ በማየት ማመን ቢያቅተውና ቢጠራጠርም እግዚአብሔር መልዓኩን ገብርኤልን ልኮ ያስተላለፈው የምሥራች ቃል እንደተፈጸመ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ክርስቲያን እግዚአብሔር የተናገረውን የሚፈጽም አምላክ መሆኑን በማመን መጠበቅ ይገባዋል።

ከዘካርያስና ከኤልሳቤጥ ታሪክ ጋር የተያያዘው ሌላው ጉዳይ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ የሚመለከት ነው። «በስድስተኛው ወር መልዓኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልዓኩም ወደ እርስዋ ገብቶ ደስ ይበልሽ ፀጋ የምላብሽ ሆይ፥ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። መልዓኩም ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። እርሱም ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፥ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። ማርያምም መልዓኩን ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልዓኩም መልሶ እንዲህ አላት :- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፥ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም፤ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልዓኩም ከእርስዋ ሄደ። (ሉቃ. 1፥26-38)

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ቃል መላዕክት በምድር ላይ ለሰዎች ከበሰሩአቸው መልዕክቶች ሁሉ የተለየና ብልጫም ያለው ነው።

ምክንያቱም ስለ ዓለም መድህን መወለድ የሚያበስር ነውና። የማርያም ለዚህ ከፍተኛ ጉዳይ መመረጥም ሌላው አስገራሚ ነገር ነው። እግዚአብሔር ልጁን በሌላ መንገድ ለመላክ ይችል ነበር። ነገር ግን የሰዎችን ኑሮና ችግር እንዲካፈል ብሎ ሰውን መረጠ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሄም በተወለደ ጊዜ ለሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ያበሠሩ መላዕክት ናቸው። በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ። እነሆም የጌታ መልዓክ ወደ እነርሱ ቀርቦ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ። መልዓኩም እንዲህ አላቸው። እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ። ዛሬ በዳዊት ከተማ መድሃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል፥ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ። ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልዓኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ አሉ።

መላዕክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ እረኞቹ እርስ በርሳቸው :- እንግዲህ እስከ ቤተልሄም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ። ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ። ... እረኞችም እንደተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ። (ሉቃ. 2፥8-20)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ታላቅ የምስራች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጐ መነሳት ነው። የእርሱ ትንሣዔ የተከታዮቹ ማለት የክርስቲያኖች ትንሳዔ ነው። ወደ መቃብር እንደ ወረደ ሞት ይዞ ቢያስቀረው ኖሮ የዘላለም ሕይወት ጉዳይ ተረት በሆነ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን ለመግለጽና ለማረጋገጥ ልጁን ከሞት አስነሳው። የትንሳዔውንም የምሥራች መጀመሪያ ያበሠረው የእግዚአብሔር መልዓክ ነው።

በሰንበትም መጨረሻ የመጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱም ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። እነሆም የጌታ መልዓክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልዓኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር። ጠባቆችም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልዓኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው :- እናንተስ

አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደ ተናገረ ተነስቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተነሣ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ እደቀመዛሙርት ንገሩአቸው። እነሆም ነገርኳችሁ። (ማቴ. 28፥1-7፤ ማር. 16፥5-7፤ ሉቃ. 24፥4-7፤ ዮሐ. 20፥11-13)

20.8 መልዓክ የደህንነትን መንገድ ሲገልጥ

በቂሣሪያ ኢጣሊቅ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበር። እርሱም ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ፥ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ ነበር። ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ያህል ቆርኔሌዎስ ሆይ፥ የሚለው የእግዚአብሔር መልዓክ ወደ እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልጽ አየው። እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ :- ጌታ ሆይ ምንድነው? አለ። መልዓኩም አለው :- ጸሎትህና ምፅዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ ዐረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ። እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቁርበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ በእንግድነት ተቀምጦአል፤ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል አለው። (ሐሥ. 10፥1-7)

እግዚአብሔር መልዓኩን ወደ ሰዎች የሚልከው ለሥጋዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለነፍሳቸው ደህንነትም ጭምር እንደሆነ የቆርኔሌዎስ ታሪክ ያስረዳል። ምክንያቱም ለቆርኔሌዎስ የሚያስፈልገው የመዳን ትምህርትና ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት መነገር ያለበት በሐዋርያው ጴጥሮስ በኩል እንደሆነ መልዓኩ አቅጣጫውን አሳየው። ቆርኔሌዎስም በቅንነት በመስማቱ ለራሱ ለቤተሰቡና ለጉረቤቶቹ ጭምር መዳን ምክንያት ሆነ።

አንድ ጊዜ አይሁድ ጳውሎስን ለምን ስለ ክርስቶስ ትናገራለህ? ለምንስ ስለ እርሱ ታስተምራለህ? ብለው በመክሰስ ከንጉሥ አግሪጳ ፊት እንዲቀርብ አደረጉ። ነገር ግን ጉዳዩ በቀላሉ ሊፈጸም ባለ መቻሉ ጳውሎስ ወደ ቄሣር ይግባኝ አለ። በዚሁ መሠረት ከሌሎች እስረኞች ጋር በመርከብ ተሳፍሮ ጉዞውን ወደ ኢጣሊያ ቀጠለ። በባህር ጉዞው ላይ እርሱና አብረውት የነበሩት ሁሉ ከባድ ሞንቶት አጋጠማቸው። ይሸውም ተሳፍረውበት የነበረውን መርከብ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ተነስቶ እየደጋገመ አናወጠው። መንገደኞቹ ሕይወታቸውን ለማዳን የተለያየ

አሳብ አቀረቡ። ከሞንቱም ወደ ባህር ጣሉ። ነገር ግን ለመዳን የነበራቸው ተስፋ ተሟጠጠ። ሳይበሉ ብዙ ቀን ከቆዩ በኋላ ያን ጊዜ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አለ :- እናንተ ሰዎች ሆይ፥ ሰምታችሁኝ በሆነ ኖሮ ከቀርጤስ እንዳትነሱ ይህንም ጥፋትና ጉዳት እንዳታገኙ ይገባችሁ ነበር። አሁንም አይዞአችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋምና። የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የእግዚአብሔር መልዓክ በዚህች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና። እርሱም ጳውሎስ ሆይ፥ አትፍራ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፥ እነሆም እግዚአብሔር ካንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል አለኝ። ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሆይ፥ አይዞአችሁ እንደተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁና። ነገር ግን ወደ አንዲት ደሴት እንድንወድቅ ያስፈልገናል። (ሐሥ. 27፥21-26)

ስለሆነም መላዕክት ከእግዚአብሔር ተልከው የእግዚአብሔርን ሰዎች በሚያስፈልጋቸው ቦታና ሁኔታ ሲያገለግሉአቸው በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን እንመለከታለን።

20.9 መላዕክት ለጥበቃ ሲታዘዙ (ጠባቂ መላዕክት)

የእስራኤል ልጆች ከግብፅ አገር ባርነት ወጥተው ወደ ተስፋይቱ አገር ለመግባት በምድረ በዳ ይጓዙ በነበሩበት ጊዜ ፈርዖንና ሠራዊቱ ሊያጠፉአቸው ያሳድዱአቸው ነበር። ወደ ኤርትራ ባህር እንደቀረቡ በፊታቸው ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልዓክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ። (ዘፀ. 14፥19)። መልዓኩ በመጀመሪያ የሚጓዙበትን መንገድ እንዳይስቱ ሲመራቸው ቆየና ከጠላቶቻቸው ሊያድናቸው ወደ ኋላቸው ዞረ። እግዚአብሔርም ሕዝቡን ለመጠበቅ የገባው ቃል ኪዳን «በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆኝ እኔ መልዓክን በፊትህ እሰድዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ፥ ቃሉን አድምጡ፥ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት። አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ ጠላቶችህን እጥላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋለሁ። መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና ወደ አሞራውያንም፥ ወደ ኬጢያዊያንም፥ ወደ ፌርዛውያንም፥ ወደ ከነዓናውያንም፥ ወደ ኤዊያውያንም፥ ወደ ኢያቡሳውያንም ያገባሃል እኔም አጠፋቸዋለሁ። (ዘፀ. 23፥20-23)

የእስራኤል ሰዎች ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ በጌልገላ ሠፍረው ነበር። መሪያቸው ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንስቶ ተመለከተ፥ እነሆም የተመዘዘ ሠይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር።

ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ? ብሎ ጠየቀው። እርሱም መልሶ፤ «አይደለሁም እኔ የእግዚአብሔር የሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ» አለ ... ኢያሱንም አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ። (ኢያሱ 5፥13-15)

ኤልያስ አራት መቶ ሃምሳ የባዓል ነቢያት በሰይፍ ማስገደሉን የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤል በሰማች ጊዜ ልትበቀለው ፈልጋ መልዕክተኛ ላከችበት። ኤልያስም ሕይወቱን ለማዳን ወደ ምድረ በዳ ሸሸ። ደክሞትም ከአንድ ክትክታ ዛፍ ሥር ተጋደመ እንቅልፍም አንቀላፋ። እነሆም የእግዚአብሔር መልዓክ ዳሰሰውና ተነስተህ ብላ አለው። ነቅቶም ሲመለከት በራሱ አጠገብ የተጋገረ እንጐቻና በማሰሮ ውሃ አገኘ። በላ ጠጣም፥ ተመልሶም ተኛ። የእግዚአብሔር መልዓክ ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰውና የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነሥተህ ብላ አለው። ተነሥቶም በላ ጠጣም፥ በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ። (1ነገ. 19፥5-8)

ዳዊት በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላዕክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል ይላል። (መዝ. 91፥11-12)

ናቡከደነፆር መልአኩን ልኮ ሲድራቅን ሚሳቅንና አብድናጐን ከእሳት ያዳናቸውን አምላክ አመሰገነ። (ዳን. 3፥28)

እንደዚሁም እግዚአብሔር በመልዓኩ አማካይነት በአናብስት ጉድጓድ ተጥሎ የነበረውን ዳንኤልን እንዳዳነ ተጽፎአል። (ዳን. 6፥22)

የእግዚአብሔር መልዓክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል። (መዝ. 34፥7)

አንድ ጊዜ የሶሪያ ንጉሥ ሠራዊቱን ሰብስቦ እስራኤልን ለመውጋት በሰዋራ ቦታ ሰፈረ። በዚያን ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ ወደ እስራኤል ንጉሥ እንዲጠነቀቅ ላከበት። የሶሪያ ንጉሥ ኤልሳዕ ያደረገውን ስለ ሰማ ሊያስይዘው ፈልጐ ያለበትን ቦታ አይተው እንዲመለሱ ሰዎችን ላከ። መልዕክተኞቹ ያለበትን ቦታ ከነገሩት በኋላ የሶርያ ንጉሥ ፈረሶችንና ሠረገሎችን እጅግም ብዙ ጭፍራ ሰደደ። በሌሊትም መጥተው ከተማይቱን ከበቡ። የእግዚአብሔር ሰው (የኤልሳዕ) ሎሌ ማለዳ ተነስቶ በወጣ ጊዜ እነሆ በከተማይቱ ዙሪያ ጭፍራና ፈረሶች ሠረገሎችም ነበሩ። እርሱም ጌታ ሆይ ወዮ ምን እናደርጋለን? አለው። ኤልሳዕ ግን ከእኛ ጋር

ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ አለው። ዓይኖቹንም እግዚአብሔር እንዲገልጥለት ኤልሳዕ ለመነ የብላቴናውም ዓይኖች ተገለጡ አየም እነሆ በኤልሳዕ ዙሪያ ያሉት የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች ተራራውን ሞልተውት ነበር። (2ነገ. 6፥15-17)

መላዕክት ከሰው ማስተዋል በላይ የሆኑ አንዳንድ ድንቅ ነገሮችን እንዲያደርጉ ወይም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለሰው እንዲገልጡ ወይም እንዲያስረዱ ከእግዚአብሔር ይላካሉ። ዘካ. 1፥9፤ 19፤ 21፤ 2፥4፤ 4፥5-6፤ 6፥4-5።

20.10 የመላዕክት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን

እስካሁን የተመለከትነው መላዕክት በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእግዚአብሔር ሰዎች ይሰጡ የነበረውን የአገልግሎት ዓይነት ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመንስ?

የእግዚአብሔር መልዓክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ አገር ሽሽ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። (ማቴ. 2፥13)

ሄሮድስ ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልዓክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ፦ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለው። (ማቴ. 2፥ 19-20)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጦመና በዲያብሎስ ከተፈተነ በኋላ መላዕክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር። (ማቴ. 4፥11)

ኢየሱስ ተይዞ ወደ መስቀል ሞት ከመሄዱ በፊት በጌቴሴማኒ በሚጸልይበት ጊዜ የሚያበረታው መልዓክ ከሰማይ መጥቶ ታየው። (ሉቃ. 22፥43)

በሐሥ. 5፥17-19 እንደምናነበው የአይሁድ ሃይማኖት ሊቀ ካህናትና ሰዱቃውያን ልባቸው በቅንዓት ስለ ተሞላ የኢየሱስ ክርስቶስን ተከታዮች (ሐዋርያትን) ወደ ወህኒ ጨመሩአቸው። የጌታ መልዓክ ግን በሌሊት የወህኒውን ደጅ ከፍቶ አወጣቸው።

ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ ክርስቶስ ያመጣው በጌታ መልዓክ አማካይነት ነው። በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ሂድ አለው። (ሐሥ. 8፥26) ንጉሥ ሄሮድስ ሐዋርያትን ሲያሳድድ አንዳንዶቹንም ሲያስገድል ጴጥሮስን

ወህኒ አገባው። ጴጥሮስ በወህኒ ይጠበቅ ነበር። ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሠንሰለት ታስሮ በሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር። ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወህኒውን ይጠብቁ ነበር። እነሆም የጌታ መልዓክ ቀረበ። በቤቱም ውስጥ ብርሃን በራ፥ ጴጥሮስንም ጐድኑን መትቶ አነቃውና ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። መልዓኩም ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው። እንዲሁም አደረገ። ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፥ ራዕይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልዓኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደሆነ አላወቀም። የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ። እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው። ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልዓኩ ከእርሱ ተለየ። ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ :- ጌታ መልዓኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ። (ሐሥ. 12፥6-11)

በዓለም ፍጻሜ መላዕክት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር እንደሚሰበሰቡ በምሳሌያዊ አነጋገር ተጽፎአል። በመግለጫውም መሠረት እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ እንክርዳዱን የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፥ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው። አጫጆቹ መላዕክት ናቸው። «... የሰው ልጅ መላዕክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፥ ... በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል። መላዕክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከፃድቃን መካከል ይለዩአቸዋል። ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፥ መላዕክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል ይሰበስባሉ ይላል። (ማቴ. 13፥39-41፤ 49፤ 24፥31)

ስለ መላዕክት በክርስትና ሃይማኖት መመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ በምናገኘው በማንኛውም ክፍል ግለትም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን አማላጅ ናቸው የሚል አልተጻፈም። በአንዳንድ የእምነት ክፍሎች ግን መላዕክት አማላጅ ናቸው በማለት (ማቴ. 18፥10፤ ራዕ. 8፥2፤ ሉቃ. 1፥19፤ ዘካ. 1፥12-26) ይጠቅሳሉ። ይሁን እንጂ በእነዚህም ክፍሎች በትክክል የተጠቀሰው መላዕክት ከእግዚአብሔር ተልከው ወደ ሰዎች እንደሚመጡ እንጂ ራሳቸው አማልክት ሆነው ሊሰገድላቸው እንደሚገባ አይደለም።

ሊመለክና ሊሰገድለት የሚገባው (አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) አንድ አምላክ ብቻ እንጂ ለሌሎች ፍጡራን መስገድም ሆነ ወደ እነርሱ

መጸለይ የእግዚአብሔርን ቃል (መጽሐፍ ቅዱስን) መጻረር ወይም መቃወም ነው። እግዚአብሔር በመላዕክት ወይም በሌሎች ፍጡራን በኩል ወደ እኔ ፀልዩ አላለም። እርሱ ያለውና በግልጽ በቃሉ ላይ የተጻፈው «ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ» (ኤር. 33፥3) የሚል ነው።

20.11 ለቅዱሳን መላዕክት ይሰገዳልን?

ቅዱሳን መላዕክት ስግደትን ለጌታ እንጂ ለራሳቸው አይቀበሉም፤ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ሲለምኑ ወደ እርሱ የልመና የምልጃም ሆነ የምስጋና ፀሎት ሲያደርጉ ወይም ሲያመልኩና ሲሰግዱ በቀጥታ መስመር ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙ ነበር እንጂ በተዘዋዋሪ ወይም በስግ በለው ሲያመልኩ ወይም ሲጸልዩ አናይም። ስለዚህ ግናችንም ብንሆን ለራሳችን ሃሳብ ይመቻል ብለን የእግዚአብሔርን ቃል በማጣመም የማይሆነውን ይሆናል በማለት ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ወደ ጥፋት ጉዳና ልንመራ አይገባም። ሐዋርያው ጳውሎስም (በሮሚ 8፥14-17) በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል ይላል። «እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፥ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።» መዝ. 145፥18 ስግደት፥ አምልኮ፥ ክብር፥ ምስጋና የሚገባው እርሱ ብቻ ነው። ሰዎች እውነተኛውን የእግዚአብሔርን መንገድ ትተው በሰው ሠራሽ ሰፊ ጉዳናና እውነት በሚመስል ውሸት እንዲመሩ ማድረግና የክርስቶስን ቤዛነት ተረድተው ወደ ነፍሳቸው አዳኝ እንዳይመለሱ በመንገድ ላይ ቆሞ መዝጋት ራሱ ትልቅ ስህተት ነው። «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ፤ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ» ማቴ. 23፥13።

«ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ፥ በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ላንተ አታድርግ፥ አትስገድላቸው አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

ለሚወዱኛ ትዕዛዜን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የሚደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» (ዘፀ. 20፥3-6፤ ዘዳ. 5፥7-10)።

እግዚአብሔር እኔ ቀናተኛ ነኝ ለሌሎች ፍጡራንም ሆነ ለእጅህ ሥራ አትስገድ እያለ በልዩ ልዩ መልክ የአምልኮትና የስግደት መመሪያ አውጥቶ ለፍጡራን መስገድ ይገባል ብሎ ማስተማር የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጋፋት አይደለምን? ይልቅስ ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር በመታረቅ ከስህተት በንስሓ መመለስ ከጥፋት መዳን ነው።

ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ በእነዚህም ፅና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና» (1ጢሞ. 4፥16)

ሰዎች እውነትን እያወቁና ቃሉንም እያነበቡ ሲያጣምሙ እግዚአብሔር ያዝንባቸዋል። «... ነገር ግን እኛ ብንሆን ከሰማይ መልዓክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላ. 1፥8-9)።

የእግዚአብሔርን መላዕክት ማምለክና በስማቸው ዝክር ማድረግ ወይም ስዕለት ማግባት የሰውን ነፍስ የሚያድንና የእግዚአብሔርን ውሳኔ የሚለውጥ ሳይሆን ሰው ሠራሽና ከእግዚአብሔር ያልሆነ ምድራዊ ሥርዓት ሰይጣናዊም ተግባር ነው። በአንዳንድ ስፍራ በመላዕክት ስም የሚገባው ስዕለት ዓይነት የሚደነቅና የሚያሳፍር ነው። ለምሳሌ፤ አይጥ፥ ቅማል፥ እንዲሁም ሌላ የሚያሳፍር ተግባር ... መፈጸም እንደ ልማድ እየተወሰደ ነው። እውነተኛው የእግዚአብሔር መልዓክ ስግደትን ለራሱ በመውሰድ ፈንታ ሊሰግድለት በእግሩ ፊት የወደቀውን ዮሐንስን እንኳን «ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልዓኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ካንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ» (ራዕ. 22፥8-9) ብሎ መሰከረ። ይህም አምልኮትና ስግደት የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ያሳየናል። ነገር ግን በተቃራኒው አምልኮትና ስግደት ፈላጊ ከነሠራዊቱ ወደ መሬት የወደቀው የጨለማው መልዓክ ክፉው (ሰይጣን) ነው። እርሱም ሆነ ተከታዮቹ ሕዝብ እንዲሰግድላቸው እያደረጉ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ እውነተኛ መልዓክ መስለው በብዙ ሕዝብ እየተመለኩ ናቸው።

ተግባራቸውና የማሳሳቻ መንገዳቸውም ጥሩ ሥነ ምግባር በማስመሰል እንዲሁም የመላዕክትን ስምና የሃይማኖት መልክ በማስያዝ ስለሆነ እውነት ፈላጊ የሆነ ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራው እየተማፀነ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናትና በቃሉም መሠረት መመራት ከጥፋት ያድነዋል። (2ዮሐ. 2፥1)

«ተዐቀቡኪ እምሐሳውያን ነቢያት» በሚል መጽሐፍ ገጽ 34 ላይ ለመላዕክት ስለሚገባው ስግደት በሚል ርዕስ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ለፈጣሪና ለፍጡር የሚቀርበው ስግደት እንዳለ በመግለጽ ለፈጣሪ የሚቀርበው የአምልኮት ስግደት እንደሆነና ለፍጡር ደግሞ የሚቀርበው የጸጋና የአክብሮት ስግደት ነው ይላል። በአስረጅነትም የተጠቀሰው ዘፍ. 22፥31፤ ዳን. 8፥15-18 ነው።

በለዓም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ መልዓክ አይቶ ደንግጦ በፊቱ መውደቁንና መስገዱን እንዲሁም ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ የሠራዊት አለቃ (የመላዕክት አለቃ) ባየ ጊዜ በግንባሩ ተደፍቶ የሰገደ መሆኑን ይገልጻል። (ኢያሱ 5፥13-15)

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት በለዓምም ሆነ ኢያሱ በሁኔታው ደንግጠው መውደቃቸው ስግደት ነው አያሰኝም። ስግደት ማለት ትርጉሙ ሰው በአምላኩ ፊት አክብሮትን ለመግለጽ ከውስጥ ልቡ በሙሉ ፈቃደኝነት ሲጐነበስ (ራስን ማዘንበል፥ አጽኖን) ኢሳ. 46፥2)፤ በጉልበቱ ሲንበረከክ (አስተበርኮ) 2ዜና 6፥13 ወይም በግንባሩ በመሬት ላይ ሲወድቅ ስግደት ይባላል። (ዳን. 2፥46) እንደ ሙሴ ሕግ ዐሥርቱ ቃላት አሪት ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጥ አክብሮት ሲሆን የአምልኮት መግለጫ ነው። (ዘፀ. 20፥4-6)

መርዶክዮስ ለሐማ አልሰገደም (አስ. 3፥2-4) ሌሎች ዘበኞች ግን ለሐማ ሲገባም ሆነ ሲወጣ ይሰግዱለት ነበር። ጳውሎስና በርናባስም ስግደትን አልተቀበሉም ሐሥ. 14፥13-18። የእግዚአብሔር መልዓክ በራዕይ 19፥10 እና 22፥8-9 «... እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ...» ብሎ ለዮሐንስ እንደ ተናገረው እንዲሁ ጴጥሮስም የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ከእግሩ በታች ወድቆ ሲሰግድለት «ተነሣ! እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ» ብሎ አስነሣው። (ሐሥ. 10፥25-26) ክርስቶስ ግን አምላክ ስለሆነ የሰዎችን ስግደት ተቀብሎአል። (ማቴ. 28፥9) የሚሰግድለት እና አምልኮት የሚገባው እግዚአብሔር ሲሆን ስግደትም በመንፈስና በእውነት እንጂ ለሥርዓትና ለወግ ብቻ እንዳልሆነ በዮሐ. 4፥24 ተጠቅሶአል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንዳንድ ቦታ ለሰዎችና ለመላዕክት ስግደት እንደ ተደረገ ብናገኝም በወቅቱ በተፈጠረው ድንገተኛ ክስተት በድንጋጤ ወይም በፍርሃት እንጂ ለማምለክ አስበውበትና አቅደው ያደረጉት እንዳልሆነ ልናስተውል ይገባል (ኢያሱ 5፥14፤ ዳን. 2፥46፤ 2ነገ. 4፥37 ሐሥ. 10፥26፤ 16፥29)። ምክንያቱም ሰውን ሊያስደነግጥና ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ ሁኔታ በመሬት ላይ እንዲደፋ የሚያደርግ ክስተት ለምሳሌ እንደ ነጐድጓድ፥ ኃይለኛ ፍንዳታ ወይም ጩኸት ... ሰምቶ በድንገት የወደቀ እንደሆነ ለዚያ ነገር ነው የሰገደው ብንል ትልቅ ስህተት ነው።

ቅዱሳን መላዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚላኩ ስለሆንና ተልዕኮአቸውም ለእርዳታ ግለትም የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማገዝ፥ ከታሰሩበት ለማውጣት ወይም በመከራ ጊዜ ለማበረታታት ሲሆን በሌላ አንጻር ደግሞ በእግዚአብሔር የፍርድ ውሳኔ መሠረት ለማጥፋት፥ ለመግደልና ለመደምሰስም ነው።

መላዕክት እግዚአብሔር አድርጉ ያላቸውን ብቻ የሚፈጽሙ የእግዚአብሔር ታዛዥ አገልጋዮች ናቸው። «... ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» ዕብ. 1፥14። መላዕክት ያለ ማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። (ራዕይ 4፥8፤ ኢሳ. 6፥2-3፤ ራዕ. 5፥11-12)

ከላይ እንደተገለጸው እውነተኞቹ ቅዱሳን መላዕክት አምልኮንና ስግደትን ለራሳቸው አይቀበሉም። ምክንያቱም የጨለማው መላዕክት አለቃ ዲያብሎስ ከእግዚአብሔር በላይ ለመሆን በመሞከሩና ስግደትንና አምልኮን ለራሱ በመፈለጉ ከክብር ስፍራው ወደ ምድር ተወርውሮ እንደ ተዋረደ ያውቃሉና። ዛሬም እግዚአብሔር ከክብር ስፍራው የጣለው ሰይጣን (ዲያቢሎስ) ስሙን በመቀየርና የብርሃን መልአክም በመምሰል ራሱን እየለዋወጠ በማሰገድ ላይ ስለሆነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይጣላ መጠንቀቅ ይኖርበታል።

20.12 «ጂን» እንደ መልአክና «ጃንሆይ» እንደ ማዕረግ ስም

የኢትዮጵያ ነገሥታት የሰይጣንን ስም እንደ ትልቅ ማዕረግ በመውሰድ «ጃን» ተብለው ይጠሩ ነበር። ይህም ጃንሆይ የተባለ ስም በዐረብ ቋንቋ አጋንንት የሚጠሩበት ስም ነው። ዐረቦች ጋኔን ሲሉ «ጂን» ይላሉ። ስለዚህ ሰማያዊ ንጉሥ ሰውንና መላዕክትን አጋንንትንም ጨምሮ እንደሚገዛ ምድራዊ የኢትዮጵያ ንጉሥም ሰውንና አጋንንትን ቀጥቅጦና

አንቀጥቅጦ በግርማ መንግሥቱ ይገዛል በማለት ነገሥታት ጃንሆይ በሚል ስመ መንግሥት መጠራት ጀመሩ። በዚህም መሠረት ድግና ጂን፥ ግዳ ጂን፥ ጃን ሥዩም፥ ጃን አሰግድ የተባሉ ነገሥታት በዚህ ስመ ግርማ ይጠሩበት ነበር። እንደዚሁም አውሮፓውያን በመካከለኛው ዘመን ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ ሲጽፉ በኢትዮጵያ ላይ የነገሠ ንጉሥ ዣን (ጃን) ተብሎ ይጠራል ብለዋል። (የኢትዮጵያ ታሪክ ከአባ ጋስፓሪኒ)።

ለመሆኑ ሕዝቡ ነገሥታቱን ጃንሆይ ብሎ የሚጠራቸውና እነርሱም ጃንሆይ ተብለው መጠራቱን የመረጡት የስሙን ትርጉም አውቀው ነበር? ወይስ ሳያውቁና ሳያስተውሉ ዝም ብለው?

ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ስለገባው የተስፋ ቃል ኪዳን ስንመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእስራኤል ቀጥሎ ለብዙ ጊዜያት የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ስም እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጾአል። ከተጠቀሱትም ከእነዚህ ተስፋዎች አንዱ «በመዝ. 68÷31» ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚል ቃል ይገኝበታል። ይህም የሚገልጸው ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ ፈጣሪዋ እንደምታነሳ ነው። እጅ ማንሣት ወይም እጅን ወደ ላይ መዘርጋት መማረክንና መሸነፍን የሚያመለክት ሁኔታ ነው። ስለሆነም ይህ ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ ለመገዛትና ለመታዘዝ እጅ የምትሰጥበት ዘመን እንደሚመጣ የሚያሳይ ክፍል ነው።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ዘመን የነበረው ንጉሥ ኢዛና የክርስትናን እምነት ከተቀበለ በኋላ ባሠራቸው ገንዘቦች ላይ ቀድሞ አሕዛብ ሳለ ባሠራቸው ላይ የነበረውን የጣዖት ምስል አስወግዶ በምትኩ የመስቀል ምልክት በአርማነት ተጠቅሞአል። በድንጋይ ሐውልትና በተለያዩ ጽሑፎቹ እግዚአብሔር ብርታትና ኃይል እንደሰጠው ገልጾ በማስቀረጽ ለትውልድ አስተላልፎአል።

ከኢዛና በኋላ የነገሡት ሌሎች ክርስቲያን ነገሥታትም በዘመነ መንግሥታቸው ባሠሩአቸው ገንዘቦች ላይ የተለያየ የመስቀል ምልክት አስቀርጸዋል። ከዚህም ጋር በገንዘቦቹ ላይ ያሠፈሩት ጽሑፍ ለእግዚአብሔር ያላቸውን አክብሮትና ለሕዝቡም የሚመኙለትና በጐ ነገር የሚገልጽ ለመሆኑ ከዚህ በላይ በክፍል ሦስት በዝርዝር ተገልጾአል።

21.1 ኢትዮጵያ የማንንም አጋዥነት አትሻም (ዳግማዊ ምኒልክ)

አጼ ምኒልክ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ተብለው የነገሡት ከ (1881-1908) ዓ.ም ባለው ጊዜ ነበር። ይህም የሆነው ለሰባ ዓመታት ገደማ አንድነቷ ፈራርሶ የተበታተነችውን ኢትዮጵያን አጼ ቴዎድሮስ

አንድ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት ዳር ሳይደርስ ሞተው ከርሳቸውም በኋላ የነገሡት አጼ ዮሐንስም አንድነቷን ሊያናጉ ከተነሱባት ጠላቶች ጋር ሲፋለሙ ሕይወታቸው ካለፈ በኋላ ነው።

ከአንድ ሺህ ዓመታት ገደማ በፊት የራሷን ገንዘብ አሠርታ ትገበያይ የነበረች አገር ኢትዮጵያ በትልቅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ውድቀት ውስጥ ተዘፍቃ ሥልጣኔው ተንኮታኩቶ ወድቆ ብዙ ቆይቶ ለመጀመሪያ ጊዜ የመገበያያ ገንዘብ ያሠሩ ንጉሥ አጼ ምኒልክ ናቸው። እርሳቸውም በጽሑፍና በንግግር ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚል ቃል ይጠቀሙ እንደነበረ በአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ጉባዔ ላይ ካደረጉት ንግግር እንረዳለን። ንጉሠ ነገሥቱ ከጣሊያን መንግሥት ጋር የተፈራረሙት የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 በኢጣሊያ ቋንቋና በአማርኛ ትርጉሙ የተለያየ ነበረ። ይኸውም የአማርኛው ትርጉም «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ በጣሊያን መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል።» ሲል በጣሊያንኛ ደግሞ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለሚፈልጉት ጉዳይ የጣሊያን መንግሥት መልካም ፈቃድ ከሆነ መላላክ ይቻላቸዋል» ይላል።

ከላይ እንደተጠቀሰው አጼ ምኒልክ በመንግሥታቱ ጉባዔ ላይ «ኢትዮጵያ የእግዚአብሔርን እንጂ የማንንም አጋዥነት አትሻም «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» በማለት ተናግረዋል።

ንጉሡ ባሠሩአቸው ገንዘቦችና በማህተም ላይ አስቀርጸው የተገለገሉበት አርማ አንድ አንበሳ ባለ መስቀል ዘውድ በራሱ ላይ ያጠለቀ፥ ሰንደቅ ዓላማ ያለበትን ባለ መስቀል ዘንግ በቀኝ የፊት እግሩ ከፍ አድርጐ በትከሻው ላይ የተሸከመ አንገቱን ቀና አድርጐ የቆመ ይታያል። ይህ ምልክትና አርማ በዘመኑ በተሠሩት ልዩ ልዩ የመጠቀሚያ ዕቃዎችም ላይ ተመልክቶአል ወይም ተቀርጾአል። በማህተሙም ዙሪያ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» የሚል ተጽፎበታል።

ሚያዝያ 14 ቀን 1883 ዓ.ም አጼ ምኒልክ «ለንግሥት ቪክቶሪያ የብሪታንያና የአይርላንድ ንግሥት የሃይማኖት ረዳት የሕንድ ነገሥታት ንግሥት» በሚል አድራሻ በጻፉት ደብዳቤ ቀደም ሲል መስከረም 25 ቀን 1883 ዓ.ም ተመሳሳይ ደብዳቤ መጻፋቸውን ጠቅሰው በድጋሚ ለአውሮፓ ነገሥታት በዚያ የችግር ወቅት የኢትዮጵያ ድንበር ነው የሚሉትን ክልል በዝርዝር ለንግሥቲቱ ገልጸውላቸዋል። በዚህም

ደብዳቤአቸው በ2ኛው ገጽ ላይ ይህንን ዛሬ የያዝኩትን ድንበር ስለ ጻፍኩ እግዚአብሔር ዕድሜና ጉልበት ከሰጠኝ የጥንቱን የኢትዮጵያ ግዛት ለማቅናት እፈልጋለሁ። ለ1400 ዓመታት ሙሉ ኢትዮጵያ እንደ ክርስቲያን ደሴት በአረመኔ ባህር ተከባ ስትኖር ከሩቅ አገር የመጣ መንግሥት አፍሪቃን እንካፈላለን ሲል ዝም ብዬ ማድመጥ አላስብም። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እስከ ዛሬ እንደ ጠበቃት ከእንግዲህም ወዲህ ይጠብቃታል ያሰፋታል ... እንጂ ለሌላ መንግሥት አከፋፍሎ ይሰጣታል ብዬ አልጠራጠርም ...። በማለት በጠላት የተነጠቁት ሰሜናዊው የኢትዮጵያ ግዛት አንድ ቀን እንደሚመለስ በማመን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ተስፋ የገለጹበት ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።



ሞዒ፡አግበሰ፡ዘአምነገሢ፡ይሁሂ፡፡ያግማዊ፡ምኔልክ፡ሠዒመ፡እግዚአ
ብሔር፡ኀጉሠነገሥት፡ዘኢትዮዽያ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡
ይዒደ፡ከወይጀጉ፣ከገግሥት፡ብክሮ፡ይ፡ሃታሳቲት፡ብሪታግይ፡ሃቢ
ርሳሄዮመ፣ግሥት፡ዒሃዒሳናት፡ረዒት፡ዒህግዩ፡ነገሠታ፡ት፣ግሥት፡
ክላመ፡ሰርሰዋ፡ይሀ፡ግ፡፡ ዒክበረት፡ዒጤናዎግ፡ዒህግነት፡በጣም፡እሃ
ወይታዕሃ፡፡በመሠከረም ።በ፲ ፫ ፲፣ ባ፲ ፫ ፲ ፫ ፲ ፫ ፲ ዒመተ፡ምሕረት፡ዒተ
ጸረ፡ዒብይቤ፡ልኪ፡ነበር፡መዒረሰ፣ት፡አለወቅሀ፡ም፡፡ ታሳቱ፡ዒእግሃሪ
ዝ፡መነግሥት፡አሰከ፡ዘረ፡ዒረሰ፡ለአ፣ት፡ዒ፡ይ፡መነግሥት፡ወጂ፫፡ሰለ
ሀነ፡በመልካም፡ነገር፡ሀ፡ሉ፡ማሰ፡ሀ፣ት፡እሃወቅ፣ት፡እናመሠግናለን።
አሀ፣ም፡ዒመግሥታች፣ት፡ዒአ፣ት፡ዒ፡ይ፡ዒም፡በር፡ለወይጂቾች፣ት፡ዕ
ዒው፡ሮ፫፡ነግሥታ፣ት፡ማሰ፡ወ፣ት፡ብለወይዒ፣ት፡ጽፈግሳችኋልና፡እናገኙ
ም፡በመልክም፡ፈቡ፡ናችሀ።ትመዕከ፣ልናሳችሁ።ብፅሃ፣ት፡ሰ፡ፈ፡እናዒር
ጋለን።ዒአ፣ት፡ዒ፡ይ፡ዒም፡በር፡ሃ፡ህ፡ነው።ከአጠልያ፡ዒ፡ም፡በር፡ብ

ሕር፡ዒር፡ከሰው።ከፈ፡ፈ፡ሉ፡አግሰት፡ወዒ፡ም፡ዕራ፡ባ፡ከሻ፡ግራ፡ጫያ፡ዒዘ፡
ጣሒዒ፡ሐዕይ፡ዒ፣ከሰ፣ግ፡ን፡ራ፡አዒ፣ባ፡ር፡ዒ፡ሃ፡ር፡ሰፈ።ኑ ካዒ፣ባ፡ር፡እግሰት
ዒመ፣ረ፣ብ፡ወግዝና፡ያራ፡ተ፡ብ፡ወግዝ፡ለሀግና፡ር፡ዒ፡ረሰ።ከ፣መ፣ረ፣ባና፡ከ፣ዒ፡
ተ፡ብ፡ወግዝ፡መንና፡ኛ፡አግሰት፡ወዒ፡ይ፡ቡ፡ብ፡ያ፡ተ፣ባ፣ራ፡ወግዝ፡ከ፣ባ፣ሕ፡ር፡ሰ፣ዝ
ነ፡፡ወግዝ፡መንና፡ኛ፡ቅ፡መ፡ት፡ዒ፣ዒ፡ባ፡ል፡ከ፡ተ፣ማ፡ከ፣ለ፣በ፡ት፡ይ፡ዒ፡ር፡ሰ፣ል።ኑ
ከ፡ቀ፣ማ፡ት፡አግሰት፡ዒ፡ከ፣ዒ፣ሬ፡ፍ፣ግ፡ግ፣ዝ፡ት፡ዘ፡አ፣ባ፡ይ፡ያ፡ሰ፡ከ፡ተ፣ማ፡ከ፣ር፡ክ፣
ይ፡ዒ፡ር፡ሰ፣ል።ከ፣ከ፡ር፡ጕ፣ግ፡አግሰት፡ኑ፡ጭ፡ አ፣ባ፡ይ፡ና፡ዒ፣ሰ፣ባ፡ት፡ወግዝ፡ለመንና፡ኛ
ይ፡ይ፡ር፡ሰ፣ል።ከ፣ከ፡ጭ፡አ፣ባ፡ይ፡ና፡ከ፣ሰ፣ባ፡ት፡ወገዝ፡መንና፡ኛ፡አግሰት፡ዒ፣ሰ፣ባ፡ት
ግ፡ወግዝ፡ይዘ፡አ፡ር፡ቦ፡ረ፡ጋ፣ሰ፣ግ፡ጭ፡ም፡ሮ፡ሰ፡ም፡ባ፡ራ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡ሰ፡ወዒ
ም፡ሥ፡ፈ፡ት፡ቦ፡ራ፡ኑ፡ጋ፣ሰ፣ግ፡ይዘ፡አ፡ራ፡ሲ፣ግ፡ው፡ሉ፡ይዘ፡አ፡ስ፡ስ፡ማ፡ሊ፡ዒ፡ም፡ዐ፡ር፡ዒ፡ር
ሰ፡ዐ፡ጋ፡ዒ፣ግ፣ጭ፡ም፡ሮ፡ወዒ፡ሰ፡ዒ፣ግ፣ት፡መ፡ል፡ሰ፡ነ፡ዐ፡ራ፡ው፡ል፣ግ፣ገ፣ዒ፣ር፡ሲ፣ኘ፡ኢ፡ሳ፡
ይ፡ሜ፣ሲ፣ግ፡ይ፡ዘ፡ህ፡ም፡ጣ፡ሰ፡ዒ፡ይ፡ር፡ሰ፣ል።ከ፡ህ፡ም፡ዐ፡ሰ፡ኑ፡አግሰ፡ት፡ያ፡ሰ፣ል፣ግ፡ባ፡ሕ፡ር፡ጭ፡ም
ር፡ዒ፣ግ፣ት፡ዒ፡ዝ፣ጋ፡ት፡ዒ፣ዒ፡ም፡ዒ፡መ፡ሕ፡መ፡ው፡ሉ፡ግ፣ዒ፡ረ፡ገ፣ግ፣ዝ፣ት፡ው፡ሉ ፡ይ፡ዘ፡ብ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡
ይ፡ር፡አ፣ዒ፣ዒ፡ክ፡ረ፡ፋ፡ሊ፡ይ፡ዒ፡ር፡ሰ፣ል።ይ፡ህ፣ነ፣ዝ፡ረ፡ዒ፣ይ፡ዝ፡ኩ፡ት፣ግ፡ው፡ም፡በ፡ር፡ሰ፡ል፡ጥ
ኩ፡እ፣ግ፡ዚ፡እ፣ብ፡ሔ፡ር፡እ፡ው፡ጫ፡ና፡ን፡ረ፡ዐ፡ት፡ከ፡ሰ፡ጠ፣ኘ፡ዒ፣ኘ፣ት፣ግ፡ዒ፡ኢ፡ት፡ዮ፡ጵ፡ያ፣ግ፣ግ፣ዝ
ት፡እ፡ሰ፡ከ፡ር፡ተ፣ም።እ፡ሰ፡ከ፡ኢ፣ያ፣ኘ፡ሰ፡ባ፡ሕ፡ር፡ጋ፡ዐ፡ዒ፣ኑ፡ባ፡ሰ፡ው፡ሉ፡ሰ፡ጣ፣ት፡ና፡ኑ፡ ከ፡ረ፡ጃ፣ጋ
ከ፡ሠ።ከ፣ዒ፣ኘ፡ዒ፡ጣ፡መ፡ት፡ው፡ሉ፡ኢ፡ት፡ዮ፡ጵ፡ያ፣ግ፣ዒ፡ክ፡ር፡ስ፡ተ፡ያ፣ግ፡ዒ፡ል፡ቱ፡ወ፡ዕ፡ረ
መ፡ዐ፡ሕ፡ር፡ተ፡ክ፡ቦ፡ሲ፣ኘ፡ር፡ከ፡ሂ፡ት፡እ፣ግ፡ር፡ዒ፡ዘ፡መ፣ጣ፡መ፣ነ፣ግ፡ሥ፡ት፡አ፣ና፡ፈ፡ቃ፣ግ፡እ፣ግ፡ካ፡ረ
ሰ፡ስ፣ግ፡ሲ፡ል፡ዝ፡ም፡ብ፡ዒ፡ጣ፡መ፣ነ፣ግ፡ሥ፡ት፡አ፡ሴ፡ሰ፡ብ፡ዒ፣ኘ፣ ።እ፣ግ፡ዚ፡አ፡ብ፡ሔ፡ር፡አ፡ት፡ዮ፡ጵ፡ያ፣ግ፡አ
ሰ፡ከ፡ዘ፡ረ፡እ፣ግ፡ዚ፡አ፡መ፡ዐ፡ፋ፡ት፡አ፣ና፣ግ፡ሚ፣ሂ፣ም፡ወ፡ዒ፡ህ፡ይ፡ዒ፡መ፡ዝ፡ግ፡ብ፡ታ፡ታ፡ል፡ያ፡ሰ፡ሩ፡ታ፡ል፡ብ፡ዒ፡ተ፡ሰ
ሩ፡አ፡ዒ፡ር፡ጋ፡ሰ፡ዒ፡ው፡እ፣ግ፡ዚ፡ብ፡ሔ፡ር፡መ፣ግ፡ሥ፡ት፡አ፡ስ፡ቱ፡ፍ፡ሉ፡ዒ፡ሰ፣ጣ፡ታ፡ል፡ነ፡ዒ፡ተ፡ለ፡መ፡ጠ፡ር
ም፡ት፡ዒ፡ጣ፡መ፡ር፡ጋ፡ዒ፡ዒ፡ት፡ኢ፡ት፡ዮ፡ጵ፡ያ፣ግ፣ዒ፡ክ፡ር፡ስ፡ተ፡ያ፣ግ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡ነ፡በ፡ር፡ዒ፡ት፡አ፡ት፡ዮ፡ጵ፡ያ፣ግ፡ጉ፡ዳ
ት፡ዒ፣ያ፣ሰ፡ዒ፣ዒ፡ር፡ሲ፣ኘ፡ክ፡ር፡ስ፡ተ፡ያ፣ግ፡ብ፡ና፡ጣ፡የ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ም፡በ፡ራ፡ች፣ግ፡ከ፡ሕ፡ሰ፡ላ፡ም፡ች
እ፡ግ፡ገ፡ው።ኑ፡ሰ፡ው፣ግ፡ም፡ዒ፣ግ፡ሰ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡ዮ፡ም፡በ፡ራ፡ች፣ግ፡ገ፡ው፡በ፣ግ፡ሊ፡በ፡ታ፡ች፣ግ፡እ፡ና፣ግ፡ና፡ለ፣ግ፡ኑ
ገ፡ል፡ም።ኑ፡ዒ፡ክ፡ር፡ሰ፡ተ፡ያ፣ግ፡ነ፣ግ፡ሥ፡ታ፣ት፡ክ፡ር፡ሰ፡ተ፡ሶ፡ስ፡ከ፡መ፡ል፡ክ፡ዒ፡ለ፡ች፡ው።ዒ፣ግ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡ዮ
ም፡በ፡ራ፡ች፣ግ፡ገ፡ው፡ተ፡መ፡ል፡ሰ፡ል፡ና፡ኖ፡ች፡ሁ።ኑ፡በ፡ይ፡ሆ፣ግ፡ም፡ከ፡ባ፡ሕ፡ር፡ይ፡ር፡ይ፡ዒ፡ዕ፡ታ፡ተ፡ሰ፡ሙ፣ና
ከ፣ሜ፣ዒ፡ዘ፡ል፡ዐ፣ግ፡ቱ፡ሰ፡ኑ፡ እ፣ና፡ዒ፡ር፡ጋ፡ለ፣ግ፡ኑ።ኑ፡በ፡ጢ፡ያ፣ዝ፡ያ፡ባ፡ይ፡ዒ፡ኑ፣ግ፡ባ፡ዒ፡ሰ፡ አ፡በ፣ግ፡ከ
ዮ፣ና፡ኑ፡ጓ፡ዴ።ኑ ፡ኑ ፡ኑ ፡

21.2 «እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ» (ቀ.ኃ.ሥ)

ሐምሌ 16/1884 ዓ.ም. የተወለዱት ቀ.ኃ.ሥ (ተፈሪ መኮንን) በባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት መስከረም 17/1909 ዓ.ም፥ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተብለው መስከረም 27/1921 ዓ.ም፥ እንዲሁም አጼ ተብለው ዘውድ የጫኑበት መጋቢት 24/1922 ዓ.ም የዘውድ በዓል ያከበሩበት ጥቅምት 23/1923 ዓ.ም ሲሆን በጦር ኃይሎች በፖሊስ ሠራዊትና በብሔራዊ ጦር «ደርግ» ከሥልጣን እስከ ወረዱበት እስከ መስከረም 2/1967 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን ለ59 ዓመታት ያስተዳደሩ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ።

ከኢትዮጵያ ነገሥታት የመጨረሻው ባለ ዘውድ ቀ.ኃ.ሥ ዘውድ ጭነው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሔር የነገሥታት ንጉሥ የራሶች ራስ በሚል ስያሜ ከነገሡ ከአምስት ዓመታት ገደማ በኋላ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ተወረረች። የአገሪቱ አርበኞች የመጣባቸውን በዘመናዊ የጦር መሣሪያ የተደራጀ የጠላት ወራሪ ጦር ለመመከት አቅም ስላልነበራቸው ወደ ዱር ገደሉ ተሰደዱ።

ቀ.ኃ.ሥ ቤተ መንግሥታቸውን በጊዜያዊነት ወደ ጐሬ በማዛወር ሚያዝያ 23/1928 ዓ.ም ወደ ድሬዳዋ ተሳፍረው በጅቡቲ በኩል በኢየሩሳሌም አድርገው እንግሊዝ አገር በመሄድ ለአምስት ዓመታት በስደት ቆይተዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀው ፋሺስት የጣሊያን ጦር በማይጨው ላይ የኢትዮጵያን ሠራዊት በብዙ ስለ ፈጀና የሰው ኃይልም እያለቀ ስለሄደ የወሰዱት የመጨረሻው እርምጃ ነው። በስደቱም ወቅት ለጀኔቭ የመንግሥታት ማህበር ጉባዔ ግንቦት 11/1928 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ሆነው በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን የጣሊያንን የግፍ ጦርነት እንዲገታ እንዲደረግ መልዕክት አስተላለፉ። ከኢየሩሳሌምም ተነስተው ወደ ሎንደን በመሄድ ጥቂት ቆይተው ሰኔ 23/1928 ዓ.ም የማህበሩ አባል ስላልነበረች ዩናይትድ ስቴትስ ብቻ ስትቀር ሌሎች የሰለጠኑ 52 የመንግሥታት እንደራሴዎች በተገኙበት በጀኔቩ የመንግሥታት ማህበር (ሊግ አፍ ኔሽንስ) የጣሊያን መንግሥት በግፍ ተነስቶ ዘር ለማጥፋት ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ መክፈቱን ገለጹ። በመግለጫቸውም ጣሊያን በ1908 ዓ.ም የተደረገውን የወዳጅነት ውል አፍርሶ ለአሥራ አራት ዓመታት ለጦርነት ሲዘጋጅ

ቆይቶ የከፈተው ወረራ መሆኑን አመለከቱ። በ1915 ዓ.ም ኢትዮጵያ በመንግሥታቱ ማህበር ከገባች በኋላ ጦርነት ከሕግ የወጣ ነገር ለመሆኑ በፓሪስ ላይ በ1920 ዓ.ም የተፈረመውን ውል ጥሶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ የሚገዛ መንግሥት አሥራ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ ያለውን አገር የወረረ ስለሆነ በስምምነቱ መሠረት ለተጠቂው መንግሥት ተፈርዶ ሳለ የተደረገልን እርዳታ ግን የለም። በማለት ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ «ከእግዚአብሔር መንግሥት በቀር የፍጡር መንግሥት አንዱን ከአንዱ የሚያበላልጥ ሥራ የለውም ... እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ። ... ለሕዝቤስ ምን ምላሽ ልውሰድለት?» በማለት ተናግረዋል።

ከላይ የተገለጸውን ንግግር ካደረጉ ከዘጠኝ ወራት በኋላ የካቲት 12/1919 ዓ.ም በቀድሞ ቤተ መንግሥት አሁን (አ.አ. ዩኒቨርስቲ) ግራዚያኒ ንግግር በማድረግ ላይ እያለ ሁለት ኢትዮጵያውያን (የኤርትራ ተወላጆች) አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በወረወሩት የእጅ ቦምብ ተናጋሪውን ግራዚያኒን አቁስለውት ስለ ወደቀና ሦስት የጣሊያን ወታደሮችም ስለ ሞቱ እንዲሁም በርካታ ሰዎች ስለ ቆሰሉ በአዲስ አበባ ከተማ ከሰላሳ ሺህ ሕዝብ በላይ ተጨፈጨፈ። ይህንንም የግፍ ጭፍጨፋ ንጉሡ በድጋሚ ለመንግሥታቱ ማኅበር ዋና ፀሐፊ ለሙሴ ዦሴፍ አቫኖስ መጋቢት 6/1929 ዓ.ም አቀረቡ።

ይህ በዚህ እንዳለ ፈረንሳዊው ፕሮፌሰር ጋስቶን ዣዝ በፖለቲካው ረገድ ሁኔታዎችን በመተንተን ንጉሡ ለመንግሥታቱ ማኅበር ስለ ወረራው እንዴት ቢያመለክቱ እንደሚያዋጣቸው በመምከር እገዛ እንዳደረጉና ዶር. ፍራንክ ጉድማን የተባሉት እንግሊዛዊ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል በምክርና በማጽናናት ይቀርቡአቸውና ይረዱአቸው እንደነበረ ይነገራል።

በዚያን ወቅትም ንጉሠ ነገሥቱ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና እንደ እግዚአብሔር ቃል መጸለይ እንደሚገባቸው ተመስክሮላቸው በመንፈሳዊ ሕይወት አኳያ ለውጥ አሳይተዋል። በዚህም ምክንያት ሃይማኖታቸውን ለውጠዋል የሚል ወሬ በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በአርበኞች ጆሮ ገባ። ይህንን ለመሸፈን በበኩላቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የአዋጅ ጽሑፍ አስተላለፉ :-

ኢትዮጵያ፡ እኛን፡ ወዳ፡እግዚአብሔር፡ትዘረጋለች፡

ቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡

ሥዩመ፡እግዚአብሔር፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ፡

አ ዋ ጅ፡

ለጉዳም፡ ሕዝብ፡

ታላላሥ፡ ቴ ቀኒ፡ በጐ፡ፈም፡ሳይ፡የተጣለው፡እዋጅ፡በስሕተት፡የተጸፈን፡ነው። ጠላት፡የሚናገረውን፡ነገር፡ሁሉ፡እትመኑ።

እኛ፡ ድል፡አማጽፈግ፡የሚናስፈልገንን፡ኔናዘጋጃለን።ነገር፡ግን፡እግሊፋና፡ጀርመን፡እኔድነት፡ሁነው፡በናናሰበት፡ስለሚወጉ፡ድሉ፡በቶሎ፡

አይጨም፡ እንጉስም።

የ ፈ ኒ ንሣዊ፡መውደት፡ ሉኖ፡ ብር ቱ፡ጉዳት፡ሁሮብናል።ነገር፡ግን፡ሞነም፡ኢጣሊፋና፡ጀርመን፡ ኃይሳችውን፡ሁሎ፡ስኔድነት፡እድ

ርገው፡ ሲቃወመዉን፡ኢኖ፡ ድል፡አማጽፈግ፡እኔፀምገችል፡ ስለመረው፡ ጦርነቱ፡ የለማቋረጥ፡ ኔንቀጥሳለን።

ፅድሳችን፡ ከእንግሊዝ፡ ፅደል፡ ጋራ፡የተያያዘ፡ ስለሆነ፡ የእኒግሊዝ፡ ጠባቂነት፡ አኢትዮጵድ፡ የዘሳሳለሙ፡ጸኖች፡ሙሰት፡ነው።እኒግሊዝ፡

በሥልጣኒና፡በመልካም፡አናናር፡ጐዳና፡ቀመሪናለች። የመ ጀመሪያው፡ ር ዳት፡ተልኮልናል። ስለዚህ፡ እኒግሊዞች፡ጉደት፡ናፂር

ኑብናል፡ ብሳችሁ፡ መስጋት፡አይገባችሁም። በሉሳን፡ወታደሮችና፡ በጸ ጂዝማች፡መገገሸ፡ስዎች፡ መማከል፡የተጸፈገውም፡ግሮ

ች፡ በጣ ም፡ ቀሳል፡ነው። እኒ ጂሁም፡ ወዳ ፌች፡ ይህን፡ የመሳሰሉ፡ ሌኳኑ ጉዳት፡ሲኖገኙችሁ፡ ግሣችሁን፡እኒያ ምንገኙ ፡ እኔ፡

አ ኒ ጋግጥሳች ኋለሁ ። በ እሁኑ፡ጊዜ፡ያሰደርጡሽ፡ወ ታደሮች፡ር ዳት፡ ምንም፡ሊመሥራት፡አይችለኝም።ነገር፡ግን፡ በዚህ፡ም

ከንኖች፡እኔን፡ሳይ ማሞቱኔ፡ ሉ ውጊል፡ብሎ፡ ማሰብ፡ እለማስተዋል፡ ይሆናል።እኒግሊዞች፡ብዙ፡ገንዘቡ፡ሰሞተውናል።

ስለዚህ፡ ወዳ ፌች፡በኖ፡ ምክንያት፡ ጉዳት፡ለሚኔኖው፡ሁሉ፡ ግሣውን፡እኒስጠዋለን።

ደ ግሞ፡ ወ ዱ፡እኒግሊዝ፡ግዛት፡ ቀ ገቡትን፡የኢ ትዮ ቁኒ፡ ሰዎች፡ሁሉ፡እኒግሊዞች፡መሣሪ፡እየሰጡ፡ሰግድ፡

ኖዋ ቀዋ ቆዋል፡ ተብሎ፡የተወራው፡ወሬ፡ ውሸት፡ነውና፡እኑስመ።ዝህ፡በ ኬት፡ሞቂት፡ሰዎች፡መዋጋታችው፡እርግሞ፡

ነው።ለወዳ ፌት፡ግን፡እስኬባር፡ግልሆነ፡በቀር፡ወዳ፡እኒግሊዝ፡የገቡት፡የኢትዮ ቁኒ፡ሰዎች፡ ከጦርነቱ፡እደገቡም።

የ ኛ፡ አኤሮፕላኖ ች ን፡ የ ጄ ርመን፡ አኤሮፕላኖች፡ የኡገደኝ፡ ነ ተ ማ፡ በ ጭራሽ፡ አሞ ፍ ተው ታል፡ እኖሉ፡

ኢጣሊያኖች፡ የሚፃወጊሳችሁን፡ወሬ፡ አትሰጠመ። እ ርማ ሞ፡ነውኔ አስገሙን፡ ድ ሊስ፡ የ ገኘ ኝ፡ ጉዳት፡ብዙ፡ነው። ይሁን

እንጂ፡ ይህ፡ የ ገኘ ኝ፡ጉዳት፡ ጦርነቱን፡ ለመቀጠል፡የሚ ከለከለን፡አይ ዪለም።

እውነተኛነ ታ ችን፡ ታሌም፡ የማይታበል፡ መሆኑን፡ ታውቃ ታችሁ። በሊግሊ

ያ ኖች፡ ሳይ፡ ዮ ምትነሡበት፡ ጊዜ፡ ደ ር ሷል።

ይኸው፡ እ ን ግዲህ፡ ታሳቂ ቱ፡እንግሊዝ፡እ ር ዳታዋ ን፡ ል ታደ ርግልን፡ነው። ስለ

ዚህ፡ በ ት ዕግሥት፡ ጠ ብቋ። ኃይሳችንንም፡ ከ ሚመጣው፡ ከ ፤ም ት፡በ ጌ ት፡ ታ ዩ ታሳችሁ።

እ ስካሁን፡ ጽ ኒ ስ፡በ ጽ ግነት፡ ሊ መራችሁ፡ የ ቆየውን፡ ጽ ኧዝማች፡ መ ንገሻ፡ ኧ ምበሬን፡እሁ

ን፡ለ ጊዚው ራ ስ፡ ብለን፡ ሱ መነዋል። ኢ ጣሊ ያኖቹም፡ድ ል፡ ካ ደ ረግን፡ በ ኋ ላ፡ ዘ ው ድ፡

ሰ ጥ ታ ን፡ በ ሙ ሉ፡ ጐ ጀም፡ ሳይ፡ እ ና ነ ግ ሠ ዎ ለ ን ።

ኢ ት ዮ ጵ ያ፡ ቢ ነ ኛ ት፡ ለ ዘ ለ ዓ ለ ም፡ ት ኑ ር ።

ታ ሳ ቂ ት፡ ብ ሪ ታ ኒ ያ፡ ለ ዘ ለ ዓ ለ ም፡ ት ኑ ር ።

ኅ ደ ር፡ ፱ ቀ ን፡ ፲፱፻፴፫፡ ዓ መ ተ ምሕረት።



ቀ ኃይለ ለሚካኤል ሃ/ኒ.



ኢትዮጵያ፡ እጆቻዋን፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ትዘረጋለች።

ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡

ሥዩመ፡እግዚአብሔር፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ።

አ ዋ ጅ፡

ለ ኢ ት ዮ ጵ ያ፡ሕዝብ፡ ከ ማ ሞ ግ ስ ና፡ እ ር ስ ዕ ኛ ች ።

ባ ጽ አ ሌ ሙ ፡ እ ኖ ሮ ት ፡ ኑ ሮ ች ፡ ው ስ ጥ ፡ በ ቻ ሻ ግ ነ ቱ ፡ ቀ ስ ፍ ፡ ባ ስ መ ው ሩ ት ፡ ፡ ለ ው ት ር ፡ ኃ ይ ሌ ች ሁ ፡ ሰ ይ በ ር ር ፡ ከ ጠ ሮ ው ፡ ሠ ማ ያ ች ን ፡ ፡ ባ ሌ ፡ እ ን ደ ፡ ጠ ላ ት ፡ ኑ ሮ ች ፡ ፡ ከ ሰ ው ፡ ፡ ሰ ው ፡ ፡ ሰ ይ ሆ ን ፡ ፡ ከ ፈ ጣ ሪ ው ፡ ፡ ሰ ይ ሆ ን ፡ ፡

በሌላ በኩል ደግሞ የጣሊያን መንግሥት የንጉሡን ፊርማና ማህተም አስመስሎ በአይሮፕላን የበተነው አዋጅ ነው የተባለው ጽሑፍ ቀጥሎ ያለው ነው





ኢትዮጵያ፡እጅጌን፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ትዘረጋለች።

ቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ

ሠዶመ፡እግዚአብሔር፡ገንዘ፡ነንሡ፡ነንሥት፡ዘኢትዮጵያ።

ሰ ዋ ጅ ፡

ለሸዋ፡ሕዝብ።

በኢጣሊያኖች፡ላይ፡የመትሠጠበት፡ጊዜ፡ደርሷል። እኛ፡ግሌአች፡እንደዓላለን፡ብለው፡ተስፈ፡ለዋተውጮል። አንዲ ምታዩትም፡ወረቀቲን፡የሚየደርሱሳችሁ፡የእንግሊዝ፡አሌርቲሳዮት ናቶው። ምናልባት፡እናንተ፡ደህነ፡እነግሌአች፡እንደ ፍንደሰለ ፡ብለው፡የሰጡንን፡ቃል፡እታመኑትም፡ይሆናል። አሁን፡ግን፡በወነ፡እነዚሊዩ፡እርግጥ፡ነው።

እንግሊዝ፡ከኢጣሊያኖች፡ጋራ፡የምታደርገው፡ጦርነት፡ስጀዚው፡የጠነከረ፡መሆኑ፡እውነት፡ነው። እኛሊኖችም ባጺሊት፡ ዱል፡ይመገሉ። ነገር፡ግን፡በቀን፡ብዛት፡ ድሉ፡የእንግሊዝ፡መሆኑ፡የታወቀ፡ነው።

እስከ፡ጥቂት፡ወራት፡ ድረስ፡ ሊዘገይም፡ከሚመጣው፡ከረምት፡ በኋኒ፡የእንግሊዝ፡መንግሥት፡የሚየደርግልን፡እርዳ ታ፡ሲጀምም፡ታያንችሁ። ስለዚህ፡ጥርጥር፡ ሳታንጡ፡በትዕግሥት፡ጠብቁ።

ከእንግሊዞች፡ጋራ፡በመሆነ፡ በሃያማኖቲያ፡ፅሊ፡ማርያም፡የሆነው፡እይመሰሳችሁ።ቦኒ፡ሃይማኖቲ፡ ቦታየሂደሳጣቦት፡ ነው። ለለኢትዮጵያ፡ ጥቅም፡ነው፡እያሉ፡ለባዕድ፡ለሚደነሰግሉት፡ ለሁለ፡ኃይሉ፡ ጎጌችሁ፡ለሁለ፡ሠዶም፡ለሁለ፡ጎታችው፡ለሁለ፡ከበደ፡ ለሁለ፡ገብረ፡ ሕይወት፡ ለደጓዝማች፡ አባ፡ውቃው፡ ብሌ፡ ለደጓዝማች፡አመዱ፡ አሊ፡ ለደጓዝማች፡ አያሌው፡ ብሌ፡ ለደጓዝማች፡ ሀጣት፡ሚካኤል፡ ለደጓዝማች፡ አምባቸው፡ገሠሠ፡ ለደጓዝማች፡ መሰቦንና፡ እነሱንም፡ለመለሰት፡ ከጠጓዎች፡ ሁሉ፡ ያለ፡አገኝ፡ ርግሌጌ፡ ቦተንባቹውን፡ ቅጣት፡እንለማንቾዋለን።

ለኢኢትዮጵያ፡ ጥቅም፡ነው፡የሚሉትስ፡ ነጉሠዋን፡ ንጣት፡ ሰኔነ፡ኢትዮጵያ ምነ፡ጥቅም፡ለማግኘት፡ልትችል፡ነው። በጌነገሣዊ፡ ዱል፡መሆነ፡ ተስፈጀሁነ፡እት ቁረጡ። ፌነገሣዊ፡ ምገጀዚም፡ ሲሆነ፡ ጠላታችን፡ መሆኔን፡ ሁሌጀሁም፡ታውቃላችሁ። እኛ፡ አለነ፡ብለን፡ በሙሉ፡የምነታማመንበት፡እነግሊዝ፡ነው።ሌሉ፡ ንጣና፡ ፌታውሬሪ፡ብሌ፡ደህነ፡እሁን፡ከኢጣሊያኖች፡ጋራ፡የምናደርገው፡ ጦርነት፡ፌታጸችው፡ሁሮ፡አልተቀበልኑትም፡ ተብሎ፡የተወራው፡ ውሸት፡ነው። እንዲሁም ለኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ሌገሉ፡ በምሥጢር፡የመሰጠ፡ቃሳችውን፡አቅርበዋል፡የተባለው፡ ውሸት፡ነው።

ራስ፡ሠዶምና፡ ራስ፡ጌታቸው፡ ኢሎችም፡እገዳት፡ መኳንንቶች፡ የለጠፍዋችውን፡ ሽፉ፡ምክር፡ትከተለው፡ንጉርግጥ ነው፡ለ መግባት፡ አለበው፡ነበር። ነገር፡ግን፡ ደህነ፡ጠሳቦች፡ውን፡ አልፌአሙትም።

ኢትዮጵያ፡ ሰነሻነት፡ ለዘለዓለም፡ትኑር።

ታኅሣሥ፡ ኅሪ፡ ታኒየ፡ለዘለዓለም፡ ትኑር።

ሀ.ሥላሴ ፈላጭ ቆርጮ ንጉሥ

ከዚህ በላይ በተመለከቱት አዋጆች ላይ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚል ተጽፎባቸዋል።

ይሁን እንጂ ከላይ የተጻፈውን ዓረፍተ ነገር በቃል ወይም በጽሑፍ ብቻ ማስቀመጡ ለውጥ የሚያመጣ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ መሪዎች እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ካላከበሩና አሁንም በተሰፋ ቃሉ መሠረት እጃቸውን ወደ እግዚአብሔር ፈጥነው ካልዘረጉ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ በረከት መዘግየቱ አይቀሬ ነው።

21.3 የሮማ ብርሃን (ታህሣሥ 1932 ዓ.ም)

ቀ.ኃ.ሥ ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ወረራና አልቂት ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ በማመልከትና በስደት በእንግሊዝ አገር እያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ወርሮ በመያዝ ለአምስት ዓመታት ገዝቶአል። በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ይታተሙ ከነበሩት መጽሔቶች «የሮማ ብርሃን» በሚል ስያሜ የሚታወቀው አንዱ ነው። በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም በወጣው በዚሁ የሮማ ብርሃን መጽሔት ላይ የኢጣሊያን መንግሥት በማሞገስ በዳግማዊ ምኒልክም ሆነ በቀ.ኃ.ሥ. ዘመን ሕዝቡ በተለያዩ ሁኔታዎች በችግር ውስጥ እንደ ነበረ ያብራራና አሁን ግን በደጉ ጣሊያን መንግሥት ህብረተሰቡ ነፃ ወጥቶአል ይላል።

በተለይም አፈ ቁሳር አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ዘብሔረ ዘጌ «የትላንትናና የዛሬ ገበሬ» በሚል ርዕስ የጻፉት ነው ተብሎ በዚሁ መጽሔት ላይ የቀረበው ጽሑፍ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል።

«ድሮ በኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረበት ጭንቅ ምን ያህል ከባድ እንደ ነበረ ሲታይ ለቤተ መንግሥቱ አዛዦችና ለሻለቆች ሕዝቡ የደረቀ ጌሾ ቅጠልና የበርበሬ ዛላ እንዲወስድላቸው ምስለኔዎች ያዝዙታል። ሲቀበሉም በቁና ስፍር ስለነበር የጌሾው ቅጠልና የበርበሬው ዛላ በጋማ ከብት ሲጫን በመጫኛ ሲታሰር ተከስክሶ ቅቡጭ ሲል መጠኑ ስለሚያንስ የጐደለውን ሙላ ካልሆነ ታሰር ይሉታል። ነጭ ኑግ ጥቁር ወተት አምጣ ይሉታል። የለኝም ካለ አያምኑትም ያለውን ቢሰጥ አይጠግቡም ስለሆነም ጥጋብ አይሰለች ለፈጣሪ አይመች እንኳን ለሰው ለዲያብሎስም ሲያሰለች ይኖር ነበር» በማለት ያለፈውን የምኒልክና የቀ.ኃ.ሥ. መንግሥት ሲያማርር የኢትዮጵያ ገባርና አራሽ ነፃ ወጣ በሚል ርዕስ ደግሞ እንደሚከተለው ያስነብባል።

«የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ከያዘ ወዲህ ለደሃው ስላዘነለት ምንም ግብር ሳያስከፍል ሙሉ ምህረት አደረገለት። ቀድሞ የነበረበትን ግብር ፋቀለት። ከቶም ዘር ላጣ ዘር፥ በሬ ላጣ በሬ እየሰጠ ደሃው ደስ እንዲለው አደረገ። ዓለም ሆነ፥ ደስታ ሆነ ሁሉን ደስ አሰኘው ሁሉን አከበረ።

በአጤ ምኒልክ ጊዜ አራሽ ከሚያመርተው እህል ተአሥር አንድ ይከፈል የሚል ደንብ ወጣ። ሕዝቡ ተጨንቆ ሳለ በመሐሪው፥ በወለላው፥ በቸሩ፥ የጣሊያን መንግሥት እንደ ቀድሞ ታሥር አንድ እህል መስጠት ግር መቅዳት እህል መፍጨት፥ ዱቄት መጫን፥ አጥር ማጠር፥ ድንኳን መጫን ታንዱ አገር ወዳንዱ አገር ሠራዊት እየተከተሉ በፀሐይና በውርጭ መዝመት፥ ያዳፋኝ መቀጫ መክፈል፥ ምጣድና ረጀት ተሸክሞ ተሠራዊት ጋር መንከራተት መጨነቅ መዋረድ ዛሬ ቀረ። አሁን ግን በአሥራት ፋንታ ገንዘብ ይለገሰዋል። ይኸውም ለሕዝቡ ጥቅም ለመንገድ ለድልድይ ለማናቸውም አገርና ሕዝብ ለሚከብርበት ሁሉ መሥሪያ መግኛ ያደርገዋል። ዋናው የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ከኢጣሊያ የሚመጣ ነው። ደሃ እህል ታገኘና እህል ከተቆጠበለት ሀብታም ይሆናል። ስለዚህ ገንዘብ አያጣም። ታሥር አንድ እህል ከመስጠት ገንዘብ መስጠት በጣም ቀላል ነገር ነው።» በማለት ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ጸሐፊ ገልጸዋል ይላል መጽሔቱ።

በቤተ ሃይማኖት በኩል ደግሞ የእስላሞች አረፋ በዓል በወሎ ዋና ከተማ በደሴ በተከበረበት ዕለት በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰቡት ሰዎች ንግግር ያደረጉት የደሴ የእስላሞች ቃዲ ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ «... በሙሉ ታማኝነትና ከልብ ሆናችሁ ታላቁንና ደጉን የኢጣሊያን መንግሥት ማገልገል የሚገባ ነውና ... የኢጣሊያ መንግሥት ሃይማኖትን በየወገኑ ስለሚያከብር ሁሉም ደስ ብሎት እያመሰገነው ውለታውን በታማኝነት ሲገልጥ ይኖራል» ብለዋል ይላል ጽሑፉ።

በጅማ ከተማ በወቅቱ ስለ ተሠራው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ህንፃ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተጠሪ ሲናገሩ «... ዳዊት ሊሠራ ያልቻለውን ቤተ መቅደስ ሰለሞን አሳምሮና አስጊጦ እንደ ሠራው ሁሉ በኢትዮጵያም ከአብርሃ አጽብሐ ጀምሮ የነገሡ ነገሥታት ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ሲመኙ ኖሩ እንጂ አልሠሩም። ደጉ የጣሊያን መንግሥት ግን ይህንን ቤተ ክርስቲያን ሠርቶልናል» በማለት መናገራቸው በመጽሔቱ ላይ ሰፍሮአል። በኢየሩሳሌምም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳም ንጉሣችን ቋሚር እንጂ ኃ.ሥላሴ አይደለም

በማለት አንዳንድ የገዳሙ መሪዎች ለኢጣሊያ መንግሥት ታማኝነታቸውን ገልጸዋል።

ከዚህ የምንመለከተው በየዘመኑ የነበሩ አንዳንድ ጽሐፊዎችና የሃይማኖት መሪዎች ለመጣው መንግሥት ሁሉ ያለ አግባብ መጐብደዳቸውንና ለጥቅሙ ማስከበሪያ ዘብ መቆማቸውን ነው። ይህም ሲባል በእግዚአብሔር ቃል 1ጢሞ. 2፥1-2 «... ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ»። የሚለው እንደ ተጠበቀ ሆኖ አግባብ በሌለው መንገድ ውሸትን እውነት ነው ብለው ሕዝቡን ግታለልና ራሳቸውንም ለጊዜያዊ ሥልጣንና ሥጋዊ ጥቅም መሸጥ እንደሌለባቸው ለማሳየት ነው።

ቀ.ኃ.ሥ. በድል አድራጊነት ወደ መንበረ መንግሥታቸው ከተመለሱ በኋላ ደግሞ ነገሩ ተገልብጦ በተለያዩ የጸሎት መጻሕፍትና በድርሳኖች ላይ ስማቸው ተጽፎአል። እርሳቸውን የተቃወመውን በእጁ ጭብጥ! በእግሩ ርግጥ! አድርጉ መልአኩ እንዲይዝላቸው ከበርካታ ድርሳኖች በአንዱ ላይ ተጽፎላቸዋል። መልከአ ኃይለ ሥላሴ የሚል ድርሳንም ተጽፎላቸዋል ተብሎ ይወራል። ከዚህም ሌላ በተአምረ ማርያም ገጽ 9ሀ ላይ «ይህንን መጽሐፍ ከግዕዝ ወደ አማርኛ አስተርጉሞ ያሳተመ ንጉሣችን ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በ2ኛው ዓመት ... በማለት በግዕዝ የሌላውን ዘር ልንጨምርበት ይገባናል ብለው አስፍረዋል። ከላይ እንደ ተጠቀሰው ጸሐፊዎቹ ወይም ተርጓሚዎቹ ለመኖር ሲሉ የሚያደርጉት አድርባይነት እንደሆነ የማይታበል ነው። የዚህ ዓይነቱ ተግባር በደርግ ዘመንም አልጠፋም። ምክንያቱም ቀድሞ እግዚአብሔርን አመልካለሁ ሲል ከነበረው ሕዝብ አብዛኛው በዘመኑ ፖለቲካ ውስጥ ካልገባ የማይሾምና የማይሸለም በመሆኑ አውቆም ሆነ ሳያውቅ የደርግ አገልጋይ ሊሆን ችሎአል።

ዛሬም አንዳንድ ሰው ከጉስቁልና ለመሸሽና ኑሮውን ለማሸነፍ ሲል የግል መጠሪያ ስሙን እንኳን እየቀየረ ወደ ተለያዩ አገሮች ለዕለት እንጀራ ፍለጋ መፍለሱ መፍትሔ መሰለው እንጂ የሚያዋጣው አይደለም። ይልቅስ ከተንኮል ከምቀኝነት ከእርስ በርስ ክፋትና ከተለያየ ኃጢአት ንስሐ ገብቶ ወደ ሁሉን ቻዩ ጌታ ቢመለስ መፍትሔው ከፈጣሪ ዘንድ እንደሚመጣ አምኖ መቀበል ይገባዋል።

ቀ.ኃ.ሥ. በዘመነ መንግሥታቸው ቀደም ሲል በደብዳቤ አርማነት ይጠቀሙበት የነበረው በመዝ. 68፥31 የተጻፈውና ከላይ ተደጋግሞ

የተጠቀሰው ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚል የተሰፋ ቃል ነበር። ባሰሩአቸው ዝርዝር ሳንቲሞችና የወረቀት ብሮች እንዲሁም በማኅተም አርማነት ዳግማዊ ምኒልክ እንዳስቀረጹት ዓይነት ባለ መስቀል ዘውድ በራሱ ላይ ያጠለቀ፥ በጫፉ ላይ መስቀልና ሰንደቅ ዓላማ ያለበት ዘንግ በፊት እግሩ ከፍ አድርጐ በትከሻው የተሸከመና አንገቱን ቀና አድርጐ የቆመ አንድ አንበሳ ይታያል። በክብ ማህተሙ ዙሪያ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» የሚል ተጽፎበት ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያንና የውጪ ዜጐችም ሳይቀሩ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር አንስታ የምትባረክበትንና ለሌሎችም የምትተርፍበትን ጊዜ ለማየት በጉጉት ላይ ናቸው። አሁንም ቢሆን ሕዝቡም ሆነ መሪዎች ይህንን ከፈጣሪ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ትተው በራሳቸው ግትር ሃሳብና የግል ጥቅም ፍለጋ እንደፈቀዳቸው እየሄዱ በቸልታ የሚያልፉት ከሆነ አገሪቱ እንደ ልማዷ የጉስቁልና ዘመን መቀጠሏ የማይቀር ነው። እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ግን ብታምጹም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና። (ኢሳ. 1፥19-20)

በየዘመናቱ የተነሱት የኢትዮጵያ ነገሥታትና መሪዎች ለአገር ልማትና ለሕዝብ ዕድገት የራሳቸው የሆነውን የተለያየ ሙከራ አድርገዋል። ከእነርሱ በፊት በሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት ያቆመውን ሥርዓት በማፍረስና አዲስ ጅምር በመመሥረት ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማድረጋቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው። ነገር ግን የመፍትሔ ቁልፉ በእግዚአብሔር እጅ ሆነና የሰው ጥረት አገሪቱን ካለችበት ፈቀቅ ሊያደርጋት አልቻለም። የአገር መሪዎች ብልህ አመራርም ሆነ ለልማት ትኩረት መስጠት ተፈላጊና አንገብጋቢ መሆኑ ቢታመንም ወደ ምህረትና ወደ ሰላም ጌታ ወደ እግዚአብሔር መመለሱ ግን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሰንደቅ ዓላማ መስቀያ ጫፍ ላይ የመስቀል ምልክት ያለበት ሲሆን «አምላክ ነሰ አምላክ አድኅኖ» «አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው» የሚል ጽሑፍ የሚነበብበት ነበር። በኋላ ቆይቶ ግን የመስቀያው ጫፍ ጦር መሳይ ሹል ሆነና ጽሑፉም ተቀይሮ «ቅንት ሠይፍከ ኃይል ውስተ ሐቆኤከ» «ጦበዝ ሠይፍህን በወገብህ ታጠቅ» በሚል ተለወጠ።

ቀ.ኃ.ሥ. ከእንግሊዝ አገር ከስደት ከተመለሱና ወደ ቤተ መንግሥታቸው ገብተው ከተረጋጉ በኋላ በደብዳቤ ላይ ቀድሞ እንደሚያደርጉት ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለውን ቃል መጠቀም አላዘወተሩም። ለምሳሌ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥታቸውን ለዩኒቬርሲቲ በሰጡበት ወቅት በጻፉት ደብዳቤ ፊርማቸው ብቻ እንጂ የተሰፋ ቃሉ አልተጠቀሰበትም። ደብዳቤውም እነሆ :-



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።
ተወዳጁ ሕዝባችን በሥልጣኔ ከኖ እንዲለና አገራችንም
እንድትበለጽግ እስካሁን ከደረግነው ጋር አብን ደግሞ የሌሎች አገሮች ወጣቶች ከደረሱበት የዕውቀት ደረጃ የኢትዮጵያም ወጣቶች ደርሰው እገራቸውን በበለጠ እንዲያገለግሉ በማሰብ በሌቃደኛ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርሲቲ እንዲመሠረት ከአባቶቻችን ከልዑል ራስ መኮንን የወረስነውን የሳል ርስታችን የሆነውን ገነተ ልዑልን ከቦታው ጋር ርስት አድርገን ስጥተናል ... ማኅተማችን ይህ ነው ዘመኑ ዓ.ም ዓ.ም
ዳሚተ ምሕረት።

21.4 የቀ.ኃ.ሥ. ጅማሬና ፍጻሜ

በዲፕሎማሲ በአርቅና በሌሎች ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ትልቅ ቦታ የነበራቸው ቀ.ኃ.ሥ. የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም እንዲቋቋም አስተዋፅኦ ካደረጉት መሪዎች ግንባር ቀደም ናቸው። እኚህ ንጉሠ ነገሥት መጋቢት 22/1922 ዓ.ም የንግሥ በዓል ሲያከብሩ በልዩ ጌጥና ክብር የተንቆጠቆጠ ባለ መስቀል ዘውድ በራሳቸው ላይ በማድረግ ነበር።

የይሁዳ አንበሳ ?

የተፈሪ መኮንን የንግሥና ስያሜ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ሞኅ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሔር፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ የራሶች ራስ የሚል ነው።



ንጉሠ ነገሥቱ በደርግ ተገድለው በምኒልክ ቤተ መንግሥት ውስጥ በሰውር ምስት ሜትር ጥልቀት ባለው ጉድጓድ ከተቀበሩበት አጽማቸው የወጣው የደርግ መንግሥት ግንቦት 20/83 ዓ.ም ከወደቀ በኋላ በኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ በየካቲት ወር 1984 ዓ.ም ነበር። በተጨማሪም በራዕይ 5፥5 ላይ «... ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሰር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማህተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሰቶአል ...።» ተብሎ የተጻፈው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራና አገልግሎት ያለ ቦታው ለአንዳንድ የኢትዮጵያ ነገሥታት ተሰጥቶ እነርሱም ይህንኑ አሜን ብለው ተቀብለው «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ (ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ) ንጉሥ እገሌ እየተባሉ መጠራታቸው የሚታወስ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጅግራአቸው ከላይ እንደተገለጸው በታላቅ ግርግና ክብር ነበር። ነገር ግን ፍጻሜያቸው በውርደት ሆነ እንጂ። ይኸውም መስከረም 2/1967 ዓ.ም ለረዥም ዘመናት ከቆዩበት ቤተ መንግሥት በአንዲት አሮጌ ቮልስ ዋገን መኪና ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ተወስደው እዚያው በአሰቃቂ ሁኔታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ በተጠቀሰው እስር ቤት ውስጥ ሲግትቱ የነበሩበትን ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶግራፍ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ባለ ሥልጣንም ሆነ ማንኛውም ተራው ሰው እግዚአብሔርን በመፍራት የሰውን ጅግራና ፍጻሜን በሚያውቅ በእርሱ ፊት በቅንነትና በእውነት ለታሉ መታዘዝና ህብረተሰቡን ማገልገል እንዳለበት መረዳት ይኖርበታል። በተጨማሪም ከጅግራዩ ይልቅ ፍጻሜዩን አሳምርልኝ በማለት በንስሓ የሕይወት መታደስ ማግኘት ይገባዋል።



የይሁዳ አንበሳ ?

የተፈሪ መኮንን የንግሥና ስያሜ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ሞኣ አንበሣ ዘእምነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሔር፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ የራሶች ራስ የሚል ነው።



ንጉሠ ነገሥቱ በደርግ ተገድለው በምኒልክ ቤተ መንግሥት ውስጥ በስውር ሦስት ሜትር ጥልቀት ባለው ጉድጓድ ከተቀበሩበት አጽማቸው የወጣው የደርግ መንግሥት ግንቦት 20/83 ዓ.ም ከወደቀ በኋላ በኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ በየካቲት ወር 1984 ዓ.ም ነበር። በተጨማሪም በራዕይ 5፥5 ላይ «... ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ስር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማህተም ይፈታ ዘንድ ድል ነስቶአል ...።» ተብሎ የተጻፈው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራና አገልግሎት ያለ ቦታው ለአንዳንድ የኢትዮጵያ ነገሥታት ተሰጥቶ እነርሱም ይህንኑ አሜን ብለው ተቀብለው «ሞኣ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ (ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ) ንጉሥ እገሌ እየተባሉ መጠራታቸው የሚታወስ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጅግራአቸው ከላይ እንደተገለጸው በታላቅ ግርማና ክብር ነበር። ነገር ግን ፍጻሜያቸው በውርደት ሆነ እንጂ። ይኸውም መስከረም 2/1967 ዓ.ም ለረዥም ዘመናት ከቆዩበት ቤተ መንግሥት በአንዲት አሮጌ ቮልስ ዋገን መኪና ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ተወስደው እዚያው በአሰቃቂ ሁኔታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ በተጠቀሰው እስር ቤት ውስጥ ሲማቅቁ የነበሩበትን ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶግራፍ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ባለ ሥልጣንም ሆነ ማንኛውም ተራው ሰው እግዚአብሔርን በመፍራት የሰውን ጅግራና ፍጻሜን በሚያውቅ በእርሱ ፊት በቅንነትና በእውነት ለታሉ መታዘዝና ህብረተሰቡን ማገልገል እንዳለበት መረዳት ይኖርበታል። በተጨማሪም ከጅግራዩ ይልቅ ፍጻሜዩን አሳምርልኝ በማለት በንስሓ የሕይወት መታደስ ማግኘት ይገባዋል።



21.5 ከሁሉም በላይ አብዮቱ (ደርግ- ኢሠፓአኮ)

የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር ደርግ ቀ.ኃ. ሥላሴን መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ከሥልጣን ካስወገደ በኋላ ቀደም ብሎ የቻይናን ቀጥሎም የራሺያን ኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም በመቀበሉ «እግዚአብሔር የለም» የሚል ትምህርት መስጠት ተጀመረ። በዓለም ላይ ያለው ኢምንትና ግዙፍ ፍጡር እንዲሁም ዓለም ራሷ ከቁስ አካል የተገኙ እንጂ ፈጣሪ የላቸውም ተብሎም ነበር። በደርግ ዘመነ መንግሥት እንኳንስ «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚል ቃልና አርማ ይቅርና «እግዚአብሔር ይመስገን» ለማለትም ራሱ እግዚአብሔር የሚባል የለም በሚል ጠማማ ትምህርት የተካኑ መሪዎች ይሾሙ ነበር። የወቅቱ መፈክሮችም «ኢትዮጵያ ትቅደም» «ፈውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝም ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ይውደም!» «አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት!» ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር! «ከአብዮታዊ መሪያችን አመራር ጋር ወደፊት!» «እናሸንፋለን!» አንጠራጠርም! ሳይንሳዊ ሐቅ ነው ወደፊት!» «የሃይማኖት እምነት ለአብዮቱ ጠንቅ ነው!» የሚሉና ሌሎች በርካታ የቃላት ጋጋታዎች ነበሩ። እነዚህንም መፈክሮች ሕዝቡን በየቀበሌው እየተሰበሰበ እንዲያስተጋባ ያስገድዱት ስለነበረ ይህንን ለማለት ፈቃደኛ ያልሆኑና ርግማን ኃጢአት ነው ያሉ ጥቂት ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት በእስር ቤት ማቅቀዋል።

«ዓመተ ምህረት» የሚለው ሐረግ በተለያዩ ጽሑፎችና በመሥሪያ ቤት ደብዳቤዎች እንዳይጻፍ በውስጥ መመሪያ ታገደ። ይህም ከ1974 ዓ.ም እስከ 1984 ዓ.ም ከአሥር ዓመታት በላይ በጋዜጦች በመጽሔቶችና በደብዳቤዎች ላይ ሳይጻፍ ቆይቶ ኢሕአዴግ ግንቦት 20 ቀን 83 ዓ.ም የአዲስ አበባን ከተማ በመቆጣጠር የደርግን መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በ1984 ዓ.ም በአንዳንድ ወገኖች ጥቆማ እንደገና በአዲስ ዘመንና በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣዎች መጻፍ ተጀመረ። የእግዚአብሔርን ስምና የምህረቱን ተስፋ ያልፈለገ መንግሥት ብዙ ችግር ሳይፈጠርና ጊዜም ሳይፈጅ ተንኮታኩቶ ወደቀ።

ስለዚህ ማንኛውም ባለ ሥልጣን የሚሾመው በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን የሚወድቀውም ጽዋው ሲሞላና ራሱ ፈጣሪ «በቃህ!» ሲለው መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል። ካልሆነ ግን ጉልበቱና ብርታቱ ወይም በዙሪያዬ ያለው ሠራዊቴ ይህንን ሥልጣን ሰጠኝ በማለት

የእግዚአብሔርን ሥልጣን ሲጋፋና በትዕቢት ልቡ ሲወጠር በሰው ዕቅድ ሳይሆን በራሱ ፈቃድ ባልተገመተ ሁኔታ ጌታ ራሱ ያወርደዋል። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው በቁጥር ከሰባት መቶ ሺህ በላይ መደበኛና ሚሊሺያ ሠራዊት የነበረው በአየርና በምድር ጦር በብቃት የተሟላ መሣሪያ የነበረው የደርግ መንግሥት ውድቀት ነው። ደርግ ከሁሉም በላይ የሆነውን እግዚአብሔርን ክዶ ሌሎችንም በማስካድ «ከሁሉም በላይ አብዮቱ!» አሰኘ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ መሆኑን በተጨባጭ አሳየ።

ስለ ኢትዮጵያ በተለያዩ ነቢያት የተተነበየ የተስፋ ቃል ኪዳን

«ኢትዮጵያ» የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንደተጠቀሰ በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ተመዝግቦ እንደሚገኝ ተደጋግሞ የተገለጸ ጉዳይ ነው። ከነዚህም ከፍሎች አንዱ በትንቢተ አሞፅ ምዕራፍ ዘጠኝ ከቁጥር ሰባት እስከ ስምንት ያለው ይገኝበታል።

ክፍሉም «የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር። ... እነሆ የጌታ የእግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው፥ ከምድርም ፊት አጠፋታለሁ።» የሚል ነው።

ነቢዩ አሞጽ የነበረበት ዘመን ከ783-743 ዓመት ክክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን በዘመኑ በእስራኤል ላይ ነግሦ የነበረው ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነበር። የአሞጽ ዕድገት እንደ ማንኛቸውም የነቢያት ልጆች ሳይሆን እግዚአብሔር ለነቢይነት ሳይጠራው በፊት ላም ጠባቂ (እረኛ) እና የወርካ ፍሬ ለቃሚ እንደነበረ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል። የተወለደበት ከቤተልሔም አሥር ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኝና ቴቁሔ በምትባል የገጠር መንደር ነው።

በነቢዩ በኩል ስለ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የተናገረውን ከማየታችን በፊት ራሱ ነቢዩ በሚኖርበት አካባቢ ያሉት እስራኤላውያንም ሆኑ አሕዛብ የሠራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሰው በግድየለሽነትና በጉልበታቸው ትምክህት የሚመላለሱበትን ሁኔታ መገሰጹን እንመለከታለን።

የሰማርያ ሰዎችም ግፍንና ጣዖት ማምለክን ትተው ጽድቅን እንዲሹና ወደ እግዚአብሔር በቅን ልብ እንዲመለሱ አስጠንቅቆአቸዋል። ወደ ፍጻሜ ዘመን ግን ለእስራኤልም ለአሕዛብም የደህንነትና የሰላም ጊዜ እንደሚመጣ በመጽሐፉ መጨረሻ የተነገረ ሲሆን የነቢዩ ትንቢት በአብዛኛው የፍርድ ቃል ነው። ይኸውም ፦

1ኛ) ፍርድ በእስራኤል ጐረቤት አገሮች (1፥1-5)

2ኛ) ፍርድ በእስራኤል (2፥6-16)

3ኛ) ፍርድ በእስራኤል ኃጢአት ምክንያት (3፥1-6፥ 14)

4ኛ) ፍርድ በአምስት ዓይነት መንገድ (7፥1-10)

5ኛ) በፍጻሜ ዘመን ስላለው ተስፋ (9፥11-15) ተናግሮአል።

ነቢዩ አሞጽ በትውልድ ሐረግ የነቢያት ወገን ባይሆንም እግዚአብሔር ለዓላማውና ለሀሳቡ ሊጠቀምበት ፈለገ። በመሆኑም ይህን ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ አስነስቶ በዘመኑ እግዚአብሔርን ከመስማት የተመለሱትንና ልባቸውን ያደነደኑትን ሕዝቦች ሊገስጻቸውና ሊመልሳቸው ወደደ። እግዚአብሔር በኃያል ክንዱ ቀብቶ ያስነሳው ስለሆነ ይህ ሰው ከነቢያት ወገን አይደለምና እግዚአብሔር በእኛ በኩል እንጂ በእርሱ በኩል አይናገርም የሚሉ ተቀናቃኞች ዛሬም እንዳሉ ሁሉ በዚያን ዘመንም ቢኖሩ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሊገታ የሚችል ማንም እንዳልነበረ ዛሬም የለም። በእግዚአብሔር ቃል እንደተጠቀሰው ... የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችን ማስተዋል እጥላለሁ ...። (1ቆሮ. 1፥19) ባለው መሠረት እግዚአብሔር ለሥራው ካልታሰበና ካልተገመተ ቦታ አስነስቶ መጠቀም ይቻለዋልና አደረገው።

ስለሆነም ከላይ እንደተመለከተው በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢትዮጵያ ለበርካታ ጊዜያት የተጠቀሰው እውነተኛ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ኪዳን አገሪቱ በእግዚአብሔር ምህረት የተጠበቀች የወደፊት ተስፋዋና መሰረትዋ በእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

ነቢዩ አሞጽ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእስራኤል ሕዝብ የተላለፈውን መልዕክትና የፍጻሜ ዘመን ተስፋ ሲገልጽ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች እንደ ኢትዮጵያ ልጆች እንደሚወዳቸው በመገንዘብ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲመለሱ ከኃጢአት ከአመጽና ካለ መታዘዝ እንዲታቀቡ አስጠንቅቋል። (አሞጽ 9፥7-8) ከዚህ የምንረዳው በእግዚአብሔር ዘንድ የቀለምና የዘር ልዩነት የሌለ መሆኑንና ሁሉንም በእኩል እንደሚወድድ የሚገልጽ ሲሆን ሁሉም የሰው ዘር ደግሞ አምላኩን እግዚአብሔርን ሊወድ ሊያመልከና ሊገዛለት እንደሚገባ ነው። በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጠቅላላው ለ41 ጊዜያት ስለ ኢትዮጵያ ተጠቅሶአል። ስለሆነም የአገርና የሃይማኖት መሪዎች እግዚአብሔርን ከሚያሳዝንና ሕዝብን ከሚበድል ሀሳብና ከሥጋዊ ትምክህት ተለይተው በቅንነትና በበጐነት ቢያስተምሩ ቢመሩና ቢያስተዳድሩ እንዲሁም ልባቸውን ወደ ፈጣሪ ቢመልሱ ሕዝቡም ባንድነት ለእግዚአብሔር ቢገዛ «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ተብሎ በመዝሙረኛው ዳዊት አማካይነት ስለ ኢትዮጵያ የተነገረው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል (መዝ.

68፥31) ይፈጸማል ማለት ነው። እጅ መዘርጋትም የሚገልጸው መማረክን መገዛትንና መሸነፍን እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር በመዘርጋት ለእርሱ ብቻ ለመገዛት መማረክና መሸነፍ ይኖርባታል። ለአገሪቱ ልማት ዕድገትና ሰላም መፍትሔው ይህ መንገድ ብቻ እንደሆነ እንድናውቅና ለእግዚአብሔር ክብርና ለዜጐች ጥቅም የሚሆን ሥራ እንድናከናውን ፈጣሪ ይርዳን አሜን።

ዋቢ መጻሕፍትና መጽሔቶች

1. ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና - ከተከለ ጻድቅ መኩሪያ
2. የዓለም ታሪክ - ከዮሐንስ ወልደማርያም
3. ሁሉም ሁሉን ይወቅ - ከዓለማየሁ ሞገስ
4. ተግሣፅና ምክር - ከመንፈስ ቅዱስ አብርሃ
5. የኢትዮጵያ ሥልጣኔ - ከበላይ ግደይ
6. ፍትሐ ነገሥት - በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1961 ዓ.ም
7. የታሪክ ማስታወሻ - ከደጃ. ከበደ ተሰማ
8. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ - በቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት
9. ዜና ኢትዮጵያ - በኮከበ ፅባሕ ማተሚያ ቤት (አሥመራ) 1952
10. የአክሱም ጥንታውያን ገንዘቦችና ያሠሩአቸው ነገሥታት - ከአዝማች ክንፉ ኪዳኔ ዘሀገረ አክሱም በ1960 ዓ.ም
11. አዎ ኢየሱስ ፈጣሪ ነው - ከመምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን
12. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ ምን ይላል? - ከአህመድ ዲዳት
13. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን? (Is the Bible God's word?) - ከአህመድ ዲዳት
14. ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም - በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
15. ተዐቀቡኪ አምሐሳውያን ነቢያት - በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
16. የኢትዮጵያ የገባር ሥርዐትና ጅምር ካፒታሊዝም - ከዶር. ላጲሶ ጌያሌዎ
17. ባሃኡላህና አዲሱ ዘመን

18. ከሰማኒያ አሐዱ (የዲድስቅልያ መጻሕፍት)
19. ንጉሠ ነገሥቱ - ከጌታቸው መኮንን ሐሰን በ1984
20. ነጭ ጥለት በጥቁር ላይ -
21. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከአባ ጋስፓሪ ገብረ ማርያም
22. እስልምና እና ታላቁ ነቢይ የመሐመድ ታሪክ - ከሐጂ መሐመድ ሰኒ ሐቢብ
23. ሃይማኖት አይለያየንም - በመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት
24. አምደ ሃይማኖት - ከብርሃኑ ጉበና
25. የተለያዩ ድርሳናችና ገድሎች - ከተስፋ ገብረ ሥላሴ
26. ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት - ከማህበረ በኩር
27. መብሩክ ጋዜጣ
28. ነጸብራቅ መጽሔት
29. ቃለ ሕይወት መጽሔት
30. ኢትዮጲስ - ከግርማ ዘውዴ

ስለመጽሐፉ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካለዎት
በፖስታ ሳጥን ቁጥር 26718
አዲስ አበባ ብለው ይጻፉልን::